የነቢያት ታሪክ

قصص الأنبياء

በዶ/ር አሚር ኻሊድ

ትርጉም፡-ሐሰን ታጁ

ማውጫ

ርእስ **ገፅ**

መግቢያ_____10
የነብያት ታሪክ ለምን?_____12
ይህ በቂ ምክንያት አይደለምን?_____12
ከሁሉም በላይ አስፈላጊው_____13
እነሆ የአላህ ቃል_____14
ቲዎሪ ይብቃ ተግባር ይንገስ_____15
ልቦናችን ለምን አይጸና?_____16
እምነትና ጽናት_____17
የሱፍ እንዲህ ጸንተዋል_____18
ወሰን የለሽ መቋቋም_____18
ሁለተኛ አላማ ትምህርት መቅሰም_____19
ሦስተኛ ዓላማ አርአያነታቸውን መከተል_____19
እነሆ ያንተ አርአያ_____20
ኢብራሂም ለወላጆቹ_____20
ግልጽ መልእክት_____21
በአዲስ ቅኝት_____21
አራተኛ ዓላማ ከተራራ የጸና እምነት_____22
የኢብን ዑመር ድንቅ ምላሽ_____22
ጥብቅ ግንኙነት_____22
አምስተኛ ዓላማ፤ወደ አላህ እንዴት ጥሪ ማድረግ እንዳለብን እንማራለን_____24
ስድስተኛ ዓላማ፣ቁርአንን መረዳት_____24
ከኪስህ የተቀመጠ ቁርአን ከልቦናህ የተኖረ ሐብት_____25

ማውጫ

ርእስ **ገፅ**

ሰባተኛ ዓላማ ቤታችንን እናስተካክል_____25

ታሪክ ራሱን ይደግማል_____26

አስተውሎት_____26

ሦስቱ ምሰሶዎች_____27

አንደኛ- ትምህርትና ተግሳጽ_____27

ሁለተኛ ፍሪያማ እውቀት_____28

ሦስተኛ- ከእስራኤላውያን አፈታሪኮች መራቅ_____28

ከመጀመራችን በፊት_____30

የነብያት ታሪክ ትርጉም_____31

ሁለተኛ፡- የተቀጠፈ ወሬ አይደለም_____32

ሦስተኛ፡- ለምን ይደጋገማል?_____33

ዛፏ ዛሬም አለች_____33

አራተኛ፡- የነቢይና የመልእክተኛ ልዩነት_____34

ተቀባይነት አለውን?_____35

እጅግ የከበደ ሐላፊነት_____35

አምስተኛ፡- የነብያትና የመልእክተኞች ቁጥር ምንያህል_____36

የማይሞት መልእክት_____37

ስድስተኛ፡- ያልተተረኩልን ነብያት_____38

ፋይዳ ስለሌለው_____39

ሰባተኛ፡- ማበላለጥ ይፈቀዳልን?_____39

የአላህ መልእክተኛ ስለራሳቸው ሲናገሩ_____41

የነቢዩ ሙሐመድ ቦታ_____42

ማውጫ

ርእስ **ገፅ**

ስምንተኛ፡- የጽናት ባለቤቶች እነማን ናቸው?_____42

ዘጠነኛ- ነብያት ከሐጢአት የተጠበቁ ናቸውን?_____44

መንታ ምልከታዎች_____44

ወዳጆቹንም_____45

እልህ ላንተ ያደረገው ጥበቃ_____45

ስጦታዬን ተቀበሉኝ_____46

የፍጥረታት ጅማሬ _____47

አላህ ብቻውን ነበር_____47

አምላካችን የት ነበር?_____48

ጅማሬ_____49

በልቦና ውስጥ ሊኖር የሚገባው እውነታ_____50

ሚንበሩ ተርገፈገፈ_____51

ጅማሬና ፍፃሜ _____52

ከዝንጋታ የሚያላቅቅ ጥያቄ_____53

አእምሮዎች የት ደረሱ?_____56

ከሁሉም ወንጀሎች መገላገል_____57

የሚገርም አገላለጽ_____58

ለዚህስ አልተፈጠርንም_____58

አልጀይላኒ በሩን ያመላክቱሐል_____59

ልእልናን ለሚያልሙ ነፍሶች_____60

የአላህን ማንነት በትክክል አላወቁም_____61

የፍጥረታት እውቀቱን ጻፍ_____61

ማውጫ

ርእስ **ገፅ**

የተለመደ ጥያቄ 62

ሰሪው የበለጠ ያውቃል 63

ዓላማችን 64

እንቅልፍ ማጣት ይብቃ 65

መመካት በተግባር ሲገለጽ 66

ይህን ተጠንቀቁ 67

አንዳች ሐሳብ አወከኝ 68

በእውነት ላይ ነህ 69

የጤንነት ምልክት 69

መድሐኒትህ በእጅህ 70

አሪፍ ሐሳብ 70

ማድረግ ይችላል 71

አስተውል! 72

አላህን ተዳፈሩ 72

ትከጅ ያለሽን? 73

በሩ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? 74

እድሉን ተጠቀም 75

እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የተቀደሰች 77

ለኪሣራ የሆነ ሰው ብቻ ነው 77

ዘልዓለማዊ መልእክት 77

ማውጫ

ርእስ	ገፅ
ግንኙነትህን ፈትሽ	78
መተናነስ ያሻናል	79
ኢባዳቸው ከኛ ኢባዳ አንጻር	80
የአዳም አፈጣጠር	81
መሰረታዊ አላማ	82
የአደም አፈጣጠር እርከኖች	82
ከርሷ ፈጠርናችሁ	82
የባህሪ መመሳሰል	83
አፈር ወደ ወርቅነት ተቀየረ	84
አስገራሚ ነገር	85
የስያሜው ምክንያት	86
የንጽህና ተምሳሌት	87
የእስልምና ጸጋ	88
የሚያጣብቅ ጭቃ	89
ከአምላክህ ዘንድ ያለህ ዋጋ	90
አላህ ሆይ! ወሰን ቶበትኩ	90
የሚያማልል ጭቃ	91
በእርግጥም ደካማ ነህ	91
ደካማ ጎኑን አውቆታል	92
ቀልብህን ሰብስብ	93,94
ከዚህ በላይ ክብር የለም	እ.ኢ.አ
ከኔ ሌላ አምላክ የአለህን?	94
ከኔ ለሸሹት ያለኝ ጉጉት	95
ምን ነካህ?	95
ራሱን እንጅ ሌላን አይውቀስ	96
እጅግ ጠቃሚ ምክር	97
ጋላቢው ማን ነው?	98
ለልጆቻችሁ አስተምሩ	99
የቀናት ሁሉ አውራ	99
ሊታወስ የሚገባው	101

ማውጫ

ርእስ **ገፅ**

ከራሳችን ይበልጥ ያውቀናል_____101

ላእምሮን ለመታደግ_____101

የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ስሪት_____102

አደምና ሐዋእ_____104

ኢብሊስ ከመላኢኮች ነበር_____104

ለምን ታዘዘ?_____105

ኢብሊስ ወይስ ሰይጣን _____106

ልዩነታቸው ምንድን ነው?_____107

ሦስት አደገኛ ፊደላት_____107

አደገኛ በሽታ_____108

የዚህ በሽታ አምስት ገጽታዎች_____110

አንደኛ፡- ሰዎችን መበደልና መናቅ_____110

ሁለተኛ- በአረማመድ መኮፈስ_____110

ሦስተኛ፡- ሐቅን አለመቀበል _____111

አራተኛ፡- ሰዎች እንዲተናነሱልህ መፈለግ_____112

አምስተኛ፡- ሶላትንና ዱዓን መተው_____112

የኩራት ውጤት_____113

ሁነኛ መረጃ_____114

የተሳሳተ እይታ_____114

ጥልቅ ግንዛቤ_____116

አስፈላጊ አዋጅ_____118

የትእቢተኛ ቅጣት_____119

ወሰን የለሽ ጥላቻ_____119

የተስፋ ድልብ_____120

ኢብን አባስ እውነት ብለዋል_____121

ጥንቃቄ_____123

ግልጽ ኪሣራ_____124

ተሳካለትን?_____126

ምክንያቱ አንተ ነህ_____128

የሐዋእ አፈጣጠር_____130

ማውጫ

ርእስ	ገፅ
ከመብት በፊት ግዴታ	132
የአካልህ ክፋይ	133
ማስታወሻ	134
አስደሳች መልእክት.	134
አሻፈረኝ አለች	136
ጀነት ውስጥ ነን	136
ከዛፏ ላይ ችክ ማለት ለምን?	138
በምልክት ብቻ	140
ወደ ምድር መውረድ	140
የሰይጣን የጠላትነት ቃል ኪዳን	144
ይህን ጠላት ለመመለስ የሚያስችሉ ስልቶች	145
አስታውስ	148
ተጠያቂው ማን ነው?	149
ይህችን ስህተት አርም	151
ከከንቱ ስሜት የገጠመ ግንዛቤ	152
ወሳኝ ስለሆነች ከርሷ ላይ አተኮረ	152
ከስድስቱ አምስቱ	153
ኋላ ከመቆጨት.	154
በእርግጥም የምታስከፋ	156
በእርግጥ ተሳክቶለታል፣ ግን...	156
የአደም ኃጢአት ውጤት	157
አቃልለህ አትመልከት	158
ሐጢአተኛ ሁሉ ይጠንቀቅ.	159
ሐጢአትን መከላከል	161
ለተውበት ያበቃቸው ሁኔታ	161
ወደ ተግባር	163
ጣፋጭ መልእክት	164
አንድ ወንጀል ብቻ ነበር	165
ወደ አላህ ተመለስ	165

ማውጫ

ርእስ	ገፅ
ልዩነታቸው	167
ቀጣዩን መልእክት ተረዳ	168
ወደ ምድር ወረደ. የቃሏ ይዘት	169
አቅሏ መጀመሪያና መጨረሻ	169
ከአባትህ ተማር	170
የጀነት ናፍቆት	171
በጎጆዎች ውስጥ ፍቅር ያነሰው ለዚህ ነው	172
በየትኛው ጎናቸው ነህ.	172
አላሁ አክበር !..	173
የአደም ልጆች ታሪክ.	174
በዱንያ አትሸንገል	175
ታሪኩ	176
በሐሳብህ እስማማለሁ ግን?.	177
ትኩረት የተቸሩ ሁለት ነጥቦች	178
የእንስት ፈተና መገለጫዎች.	179
መፍትሄ ልስጣችሁ	183
አንተም እንደዚሁ ሁን	187
ተጠያቂው ማን ነው?	189
ግንኙነቱ ምንድን ነው?.	190
እጅግ ጠቃሚ መልእክት	191
የምቀኝነት ውጤት	191
ምንዳን ይበላል	192
ሕክምናው	193,194
ተቀባይነት ከርሷ ጋር የተሳሰረ ነው	እ.ኢ.አ
እጇን ወዳንተ አልዘረጋም	196
ሁለቱ ሐጢአቶች	196
ተፈጥሯዊ ባህሪ	197
ኢብንል ቀይም ጅማሬውን ሲያስተዋውቁ	197
ጠንካራ ትስስር	198

ማውጫ

ርእሰ	ገፅ
እጅግ ጠቃሚ መልእክት	198
የቁርአን አወቃቀር መጣጣም	199
‹‹ሰውአህ	200
ስላቃተው ተጸጸተ	200

መግቢያ

ነቢያት የአላህ አምባሳደሮች፣ ቅኑን መንገድ መሪዎች፣ የሐቅ አስተማሪዎች፣ የደግነት ተምሳሌቶች በመሆናቸው ቁርአን ለታሪካቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት አብዝቶ ሲተርክልን እናስተውላለን። በየዘመናቱ የተነሱ ሙስሊም አሊሞችም የአጅንዳውን ክብደት በመረዳትስለ ነብያት ሲጽፉ፣ ከታሪካቸው የሚገኙ ትምህርቶችን እየመዘዙ ሲተነትኑ፣ ሲናገሩና ሲያስተምሩ ኖረዋል።

ስለዘ.ህም ከዘመናችን ወጣት የዳእዋ ከዋክብት መካከል አንዱ የሆኑት ዶ/አሚር ኻሊድ አጅንዳውን ትኩረት ችረው መዳሰሳቸው የሚጠበቅ ነው። ግና ቅኝታቸው ከሌሎች አሊሞች ቅኝቶች ለየት ይላል። በዋነኛነት እያንዳንዱን የታሪክ ክፍል ከተጨባጭ የየእለት ሕይወታችን ጋር ግሩም በሆነ መልኩ ያስተሳስሩታል። ታሪኮችን ያዋቀሩበት ስልትም ለኔ በጣም ማርኮኛል። ስሜቴን ገዝቶት፣ ቀልቤን ተቆጣጥሮ ልክ እንደ ልቦለድ ቀጣዩን ሐሳብ፣ ቀጣዩን ትምህርት ለማንበብ ከገጽ ገጽ እየጓጓሁ እንድጓዝ አስገድዶኛል።

ኡስታዝ አሚር ኻሊድ ከሌሎች ዳዒዎች በተለየ ሁኔታ ከአእምሮ ይልቅ ለቀልብ ቀረብ ያሉ በመሆናቸው በየመሐሉ ጣል የሚያደርጓቸው ስሜትን የሚንጡ፣ ቀልብን የሚያርገፈግፉ ምክሮችና ሐሳቦች ደረቅ ልቦናን ያለዝባሉ። ማልቀስ ያልለመዱባቸው አይኖች እንኳ በግድ እንዲያነሱ ያደርጋሉ።

መጽሐፉን ስሰራው በአድናቆት መደመሜን አልደብቃችሁም። በመሐል መጻፌን እያቆምኩ ለኡስታዙ ከልብ አጨብጭቤያለሁ። ምክራቸው ውስጤን ነክቶት ስለራሴ እያሰብኩ፣ ወንጀልን እያስታወስኩ ለረዥም ጊዜ ቆዝሜያለሁ። ይህን ስሜቴን ከአጠገቤ ሆና የምትተይብልኝ ባለቤቴ ተጋርታኛለች። እርሷም ልክ እንደኔው በኡስታዙ ጽሑፉን አቀራረብ ተመስጣለች። የሐሳባቸው ጥልቀት አስደሰቷት ፈንድቃለች። ምክራቸው ሰርጿት አንብታለች።

አሚር ኻሊድን የማውቃቸው ሚሊዮኖችን ባስለቀሱበት፣ ወደ አላህ መንገድ በመለሱበት ርቱእ አንደበታቸው ሲሆን፣ የንግግር ብቻ ሳይሆን የብእርም ጀግና መሆናቸውን በዚህ ስራቸው አስመስክረዋል። ስራቸውን በጣም ወድጀዋለሁና ውደዱልኝ። በጥሞና አንብቤዋለሁና አንብቡልኝ። አድንቄዋለሁና አድንቁልኝ።

በመጨረሻም ኡስታዝ አሚር ገና ወጣት ናቸውና ሌሎች ስራዎችን ያስነብቡን ዘንድ እድሜያቸውን እንዲያስረዝምላቸው አላህን እለምናለሁ። በምክራቸው ተጠቃሚዎች ያደርገን ዘንድም እማጸነዋለሁ።

ሐሰን ታጁ

ሕዳር 2003

የነብያት ታሪክ ለምን? __

በአንዳንድ ሰዎች አእምሮ ውስጥ የሚከተለው ጥያቄ ሊመላለስ ይችላል። የነብያት ታሪክ ለምን? ስለ ጥንት ዘመን የሚያወጋ እንደመሆኑ እርሱን ማንሳት ምን ይጠቅመናል? አሁን ስለምንኖረው _ ሕይወት ይበልጥ ማሰብና መጨነቅ አያሻንምን? መፍትሄ የሚሹ በርካታ ችግሮች፣ መድሐኒት የሚሹ በሽታዎች ከፊት ለፊታችን ተከምረው እያለ እነርሱን ችላ ብለን ለመቶዎች አመታት ወደኋላ በመመለስ ስላለፈ ዘመን ማሰብ ምን ይፈይደናል?

ይህ እይታ በጣም ያስደስተኛል። የደረስንበትን ብስለት የሚያመለክት ነው። የየሐገሮቻችንን ተጨባጭ ሁኔታ ለማስተካከል ካለን ጽኑ ፍላጎት የመነጨ በመሆኑ ወድጀዋለሁ። እኔም ከዚህ እይታ ውጭ አልሆንኩም። የነብያትን ታሪክ በአዲስ ንጻሬ መመልከት፣ የከጀልኩትም ለዚሁ ዓላማ ነው። ይህውም ከነብያት ጋር በታሪካቸው አማካይነት አብረን እንኖራለን። የእያንዳንዱን ነብይ የሕይወት ተሞክሮና አጋጣሚ አሁን ካለንበት ተጨባጭ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ትምህርት እንቀስማለን። ይህን ትምህርት ለሕብረተሰባችን ለሚጠቅምና አላህን ለሚያስደስት በጎ ስራ እንገለገልበታለን።

ይህ በቂ ምክንያት አይደለምን?

የነብያት ታሪክ እጅግ አስፈላጊ የሆነው በዚህ አዲስ ንጻሬ ስለምንመለከተው ብቻ አይደለም። እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ዘልዓለማዊ ተአምር የሆነው ቁርአን ከይዘቱ ሲሶው ያህሉ በነብያት ታሪክ የተሞላ ነው። ይህ እውነታ የአጀንዳውን አስፈላጊነት እና አያመለክትምን? የሰው ልጅ ከፍተኛ እድገትና እመርታ እንደሚያሳይ ክብደት አላህ ያውቃል። ይህም ሆኖ ግን ቁርአኑን በነብያት ታሪክ ሞልቶታል። እንዲህ ሲልም እውነትን ተናግሯል፡-

لَقَدْ كَانَ فِي قَصَصِهِمْ عِبْرَةٌ لِأُولِي الأَلْبَ (يوسف)

ታሪካቸው በእርግጥ ለአስተዋዮች ተግሳጽ እና ትምህርት ሰጭ) ነው›› (ዩሱፍ ፲፩)

አጀንዳውን እንቃኝ ዘንድ ይህ በቂ ምክንያት አይደለምን? አላህ ሆይ! ከአስተውሎት ባለቤቶች አድርገን።

መስፈርት

የነብያት ታሪክ እጅግ ጠቃሚ ነው። በሰው ልጅ ስነ ልቦና ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። የነርሱን ሕይወት በማወቅ፣ ከነርሱ ጋር በመኖር ባህሪያችን ይቀየራል። ሕይወታችን ይቀየራል። ግና ይህ ይሆን ዘንድ አንድ መስፈርት መሟላት አለበት። እርሱም ከአላህ ጋር እውነተኛ መሆን ነው። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ለአላህ እውነተኛ ከሆንክ ሐሳብህን ያሳካልሐል።›› (ነሣኢ)

ወንድሜ ሆይ፣ ብዙ አንብበናል። ግና በሕይወታችን ላይ የሚፈለገው ለውጥ አልመጣም። ለምን? ነውሩ ያለው ከመጽሐፍቱ ነው ወይስ ከኛ ከአንባቢያን? በእርግጥ መጽሐፍቱን በድለናቸዋል።

ወንድሜ ሆይ፣ ከእንግዲህ መርሃችሁ እንዲህ ቢሆን ድንቅ ነው። ‹‹ማንበብ ብቻ ይብቃ። ንባብ ከተግባር ይዋሃድ። እውቀት ከስራ ይዛመድ።››

ከላይ የሰማኸውን ሐዲስም አትዘንጋ፡- ‹‹ለአላህ እውነተኛ ከሆንክ ያሰብከውን ያሳካልሐል።›› ከሁሉም በላይ አስፈላጊው ኢብንል ቀይም የነብያትን ታሪክ አስፈላጊነት እንዲህ ሲሉ ያብራሩልናል፡-

‹‹መንፈስ ለአካል ወይም ብርሃን ለአይን ከሚያስፈልገው በላይ ነብያት ለሰው ልጅ ያስፈልጋሉ። ምክንያቱም አላህ የሚታወቀው በነርሱ

አማካይነት ነውና። አላህ ካልታወቀ መንፈስም፣ ብርሃንም፣ አይንም የለም። አላህ ደግሞ በነብያት በኩል እንጅ አይታወቅም።»

ነብያት በምድር ላይ ያላቸው ደረጃ ይህን ያህል ነው። ያለነርሱ አላህን አናውቅም። አላህን ማወቅ ደግሞ የሕልውና ሚስጥር ነው። አላህን ያላወቀ ከሕያውያን መሐል የሚኖር ሙት እንጅ ሌላ አይደለም።

ለአንድ ነገር ያለን አስፈልጎት ባደገ ቁጥር፣ ያን ነገር ለማግኘት የሚረዳን ሰበብም የዚያኑ ያህል አስፈላጊ ይሆናል። አላህን ማወቅ ከምንም በላይ የሚያስፈልገን ነገር ነው። ስለዚህም ነብያት _ አላህን ለማወቅ ምክንያት ስለሚሆኑ የዚያኑ ያህል ያስፈልጉናል። የነብያትን ታሪክ አስፈላጊነት አሁን ተረዳህን?

<u>እነሆ የአላህ ቃል</u>

የነብያትን ታሪክ አስፈላጊነት ለማብራራት ኢብንል ቀይም ያቀረቡት ማነጻጸሪያ በተከታዩ የአላህ ቃል በጉልህ ተመልክቷል፡-

وَكَذَلِكَ أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ رُوحًا من أمرينا ما كنتات تدري ما الكتب ولا الإشاءين : نُورًا نَهْدِى مَن نَشَاءُ مِنْ عِبَادِنَا وَإِنَّكَ لَتَهْدِي إِلَى صِرَاطٍ مُسْتَقِيم:: بِهِ

«እንደዚሁ (ከአንተ በፊት ለነበሩት መልዕክተኞች ራዕይን እንደገለጽን) ለአንተም በትእዛዛችን ራዕይን ገለጽን (ይህን ከማድረጋችን በፊት መጽሐፉ ምን እንደሆነ፣ እምነትም ምን እንደሆነ የምታውቅ አልነበርክም። ግና (ያወረድንልህን መልዕክት) ከባሮቻችን የምንሻውን የምናቀናበት ብርሃን አደረግነው። አንተ በእርግጥም ወደ ቅኑ ጐዳና ትመራለህ» (አል ሹራ 52)

እዚህ ላይ «መንፈስ» (ሩህ) የተባለው አላህን እናውቅበት ዘንድ ነብያት የተሸከሙት መልእክት ነው። የኢብነል ቀይምን ቃል ካላመንክ እነሆ የአላህ ቃል ተጠቅሶልሐል። እርሱንስ አታምነውምን?

ቲዎሪ ይብቃ፣ ተግባር ይንገስ

አሁን ንያችንን የምንፈትሸበት ጊዜ ደርሷል። ኒያ የሚለው ቃል ለምን ግራ አጋባህ? ይህን መጽሐፍ ለማንበብ ስትፈልግ ኒያ አልነበረህምን? ወንድሜ ሆይ፣ «ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው።» (ሙስሊም)

አሁንም ከፊት ለፊትህ እድል አለና ተጠቀምበት። ኒያህን አድስ። ይህን ታደርግ ዘንድ ሰባት ዓላማዎችን ወይም ኒያዎችን በመዘርዘር እገዛ አደርግልሐለሁ። እያንዳንዱ ዓላማ ወይም ኒያ፡- የሙእሚን ኒያው ከስራው ይበልጣል›' በማለት በከፍተኛ ድምጽ ይጣራል።

የነብያትን ሕይወት በአዲስ እይታ ለመቃኘት ተዘጋጅተናል። ለዚህም አላህ እንዲረዳን እንሻለን። ታሪክን ማወቅ ብቻውን በቂ አይደለም። ከተጨባጭ ሕይወት ጋር ማስተሳሰርና ለችግሮቻችን መፍትሄነት መጠቀም የግድ ነው። ጅምራችን ይህ ይሁን። ‹ቲየሪ ይብቃ፣ ተግባር ይንገስ።›

የመጀመሪያው ዓላማ- ልብህን ልናጸና

የነብያትን ታሪክ የምንዘክርበት የመጀመሪያ ዓላማ የሙእሚኖችን ቀልብ ለማጽናት ነው። አላህ በቁርአኑ ውስጥ የተረከልን ለዚሁ አላማ መሆኑን ጠቅሷል። እንዲህ ብሏል፡-

وَكُلًّا نَقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنْبَاءِ الرُّسُلِ مَا نَثَبِّتُ بِهِ فُؤَادَكَ وَجَاءَكَ فِي هَا

((وَمَوْعِظَةٌ وَذِكْرَى لِلْمُؤْمِنِينَ ،،ይህን ሁሉ (የቀደምት) መልዕክተኞች ታሪክ በርሱ ልብህን ልናፀና ተረክንልህ። በዚህች (ምዕራፍ) ውስጥ እውነትም ለአማኞችም ተግሳጽና ማስታወሻ የሆነ መልዕክት መጥቶልሃል።›› (ሁድ 120)

ይህ ዓላማ የሙእሚኖች የዘወትር ዜማ ነው። የአላህ መልእክተኛ ተከታዩን ዱዓ አስተምረዋል፡

2.ጦበራኒ

‹‹ቀልቦችን እና አይኖችን አገላባጭ የሆንከው አላህ ሆይ ቀልቤን በሐይማኖትህ ላይ አጽናልኝ››? ጽናት ምሉእ በሆነ ትርጉሙ::

<u>ልቦናችን ለምን አይጸና?</u>

የቁርአን ታሪኮች የሙእሚንን ልብ በመከራ ጊዜ ያጸናሉ:: ለአዩብ የተከሰተባቸውንና ውጤቱን ቁርአን እንዲህ ይተርካል፡-

لَهُ وَأَيُّوبَ إِذْ نَادَى رَبَّهُ أَنِّي مَسَّنِيَ الضُّرُّ وَأَنتَ أَرْحَمُ الرَّاحِمِينَ فَاسْتَجَبْنَا فَاسْتَجَبْنَا لَهُ وَآتَيْنَاهُ أَهْلَهُ وَمِثْلَهُم مَّعَهُمْ رَحْمَةً مِّنْ عِندِنَا وَذِكْرَى

አዩብንም ጌታውን “እኔ መከራ አግኝቶኛል:: አንተ የአዛኞች ሁሉ አዛኝ ነህ (እና ጭንቄን አስወግድልኝ” በማለት በተጣራ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ ጥሪውን ተቀበልነው:: የነበረበትን መከራም አስወገደ ንለት:: ቤተሰቦቹንም ሰጠነው:: ቁጥራቸውንም እጥፍ አደረግንለት ከኛ ዘንድ በሆነ ችሮታና ለአገልጋዮቻችን ትምህርት ሰጭ ይሆን ዘንድ (ይህን ሁሉ አደረግንለት)::›› (አል አንቢያእ 83-84)

አዩብ ከየትኛውም ሰው በበለጠ ሁኔታ በበሽታ ተንገላቱ:: ግና አላህ ከስቃይ ታደጋቸው:: በሽታቸውን ፈወሰላቸው:: የአዩብን ታሪክ በማወቃችን መከራን እንታገሳለን:: አላህ ክፉን ነገርና በፈታኝ እንደሚያስወግድልን እርግጠኞች ነንና:: አላህ ዱዓችንን እንደሚቀበለን እርግጠኛ በሆንበት ሁኔታ ልቦናችን ለምን አይጸና? ያለፉ ነብያት ታሪኮች በወደፊት ሕይወታችን ላይ ለሚደርሱ አጋጣሚዎች መፍትሄ አመላካች ይሆኑናል:: ለአዩብ ያጋጠማቸው የዱዓ ተቀባይነት እድል አንተንም ያጋጥምሐል:: የሙእሚን እይታ ይህ ነው::

2 ተርሚዚ

ወላጆችን ከሚያጋጥሙ መከራዎች ሁሉ ትልቁ በልጅ በኩል የሚመጣ መከራ ነው። ባለንበት ዘመን ብዙ ወጣቶች በለጋ እድሚያቸው ይሞታሉ። ሞታቸው ለወላጆቻቸው ብርቱ ሐዘን፣ አቻ የለሽ ሰቀቀን ነው። በአላህ መልእክተኛ ሕይወት ውስጥ ይህ አጋጣሚ ተከስቷል። እንዲህ ሲሉ ጥልቅ ሐዘናቸውን ገልጸዋል፡-

«አይኖች ያነባሉ። ልቦናም ያዝናል። ኢብራሃም ሆይ፣ ስለተለየህን አዝነናል። ግና አምላካችንን የሚያስደስት ነገር እንጅ አንናገርም። እኛ የአላህ ነን። ወደርሱም ተመላሾች ነን።»3

የአላህ መልእክተኛ እንኳ በልጃቸው ሞት ሳቢያ የደረሰባቸውን ብርቱ ሐዘን አስተውል።

በሰይዲና የእቁብ የደረሰውን መከራ ስናይ እንጽናናለን። እርሳቸው እንዲህ ሲሉ ታግሰዋል፡-

فَصَبْرٌ جَمِيلٌ عَلَى اللَّهُ أَن يَأْتِيَنِي بِهِمْ جَمِيعاً

ከመልካም ትዕግስት (ሌላ አማራጭ የለኝም)። አላህ ሁሉንም ያመጣልኝ ይሆናል።" አለ (ዩሱፍ 83)

ልጅህ ቢጠፋና እንደማታገኘው እርግጠኛ ብትሆን ነቢይ የእቁብን አስታውስ። አርአያነታቸውን ተከተል። የርሳቸውን እምነት እና ጽናት ተጋራ። የዩሱፍን ታሪክ በዝርዝር እናውቃቸዋለን። በጣምም እንወደዋለን። ግና ስንቶቻችን ይህን ዓላማ አስታውሰናል። ስንቶቻችን ከታሪኩ ጽናትን ተምረናል? ጽናት- የቁርአን ታሪኮች ሊያስተምሩን ካለማቸው አበይት ዓላማዎች መካከል አንዱ ነው።

3.ቡኻሪና ሙስሊም

<u>ዩሱፍ እንዲህ ጸንተዋል</u>

የዩሱፍ ታሪክ በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ያጸናሐል። በተለይም የእንስትን ፈተና በትእግስት እንድታልፈው ይረዳሐል። ዩሱፍ ቆንጆ፣ ወጣት ለመዘሞት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሁሉ የተመቻቹለት፣ ውበቷ የሚያማልል፣ ከዚህም በላይ አሳዳሪው የሆነች እንስት በሯን ዘግታ ጋብዛዋለች። እርሱ ግን እንዲህ ሲል ጸንቷል።

(قَالَ مَعَاذَ اللَّهِ إِنَّهُ رَبِّ أَحْسَنَ مَثْوَى إِنَّهُ لَا يُفْلِحُ الظَّلِمُونَ

በአላህ እጠበቃለሁ፡ በእውነቱ (ባለ ቤትሽ አሳዳሪዬ ነው፡

መኖሪያየንም መልካም አድርጐልኛል፤ (ሚስቱን ደፍሬ ልበድለው አልሻም እነሆ በዳዮች አይድኑምና።" አለ። (ዩሱፍ 23)

የዩሱፍን ታሪክ ከሰማህ፣ ‹በአላህ እጠበቃለሁ› ሲል ካደመጥከው፣ እርሷ ከጅላው ፈተናዋን እና ማባበያዋን ሁሉ መቋቋሙን ካወቅክ በኋላ በፈተና ትሸነፋለህን? ወንድሜ ሆይ፣ ጽናትን በተግባር እንሻለን። እይታህን ተቆጣጠር። ብልትህን ጠብቅ። ከዩሱፍ ታሪክ ተማር።

<u>ወሰን የለሽ መቋቋም</u>

ቁርአን የነብያት ታሪኮችን የመተረኩ አይነተኛ ዓላማ ሙእሚኖችን ማጽናት መሆኑን ቃኝተናል።

مَا نُثَبِّتُ بِهِ فُؤَادَكَ

‹ብርሱ ልብህን ልናፀና፡ ተረክንልህ።› (ሁድ 120) እጅግ ጠቃሚ ምክር እለግሳችኋለሁ። ይህውም ከፊት ለፊታችሁ ወንጀል ወይም ሽህዋ በማጋረጥ ጊዜ ጽናት ታገኙ ዘንድ ወደ አላህ መጽሐፍ ፈጥናችሁ በመሄድ የነብያትን ታሪክ አንብቡ። ይህ ሲሆን ሽህዋ ሊቆጣጠራችሁ፣ ስጋዊ ስሜት ሊያጠቃችሁና ሊጥላችሁ አቅም አይኖረውም።

በፈተና ጊዜ ትጸና ዘንድ ዩሱፍን አሰታውስ። በመከራ ጊዜ ትጸና ዘንድም አዩብን አስታውስ። የአላህን ትእዛዝ በመፈጸም ሃደት ጽናት ይኖርህ ዘንድም ኢብራሃምንና ኢስማኤልን አትርሳ። ኢብራሂም የአላህን ትእዛዝ በጸጋ ተቀበሉ። ልጃቸውን ለማረድም ቢላዋ አነሱ። ልጁም አልተቃወመም። ለትእዛዙ እጅ ሰጠ። ሁሉም የአላህን ፈቃድ ሳያመነቱ ፈጸሙ። ልጅን ማረድ ቀላል ፈተና አይደለም። ሕይወትን ለቢላዋ መስጠትም እንዲሁ። ግና እነዚህ ነብያት በአስደናቂ አኳኋን ተገበሩት።

የነብያት ታሪክ ለሙእሚኖች ጽናት ይሰጣል። መከራን፤ ወንጀልን፣ ሽህዋን የመቋቋም ወሰን የለሽ ክህሎትን ያጎናጽፋቸዋል። እስከ ሞት ድረስ መጽናትን መሪ መርሁ ያደረገ ጥንካሬ።

<u>ሁለተኛ ዓላማ፣ ትምህርት መቅሰም</u>

የነብያትን ታሪክ የማወቃችን ሁለተኛው ዓላማ ከእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ለሕይወታችን የተለያዩ ክፍሎች ትምህርት መቅሰም ነው። ተከታዩን የአላህ ቃል በጥሞና ማስተዋል ይኖርብናል፦

وَلَكِنَ الْيَتَبِينَ هِ وَتَفْصِيلَ لَقَدْ كَانَ فِي قَصَهِمْ عِبْرَةٌ لِأُولِي الْأَلْبَبِ مَا كَانَ حَدِيثًا يُفْتَرَ كُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً لِقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ)

«ታሪካቸው በእርግጥ ለአስተዋዮች ተግሳጽ እና ትምህርት ሰጭ ነው። (ቁርአን) የተቀጠፈ ወሬ አይደለም ግና ከርሱ በፊት የነበሩ (መለኮታዊ መልዕክቶችን አጽዳቂና ሁሉንም ነገር ገላጭ ለአማኞችም መመሪያና እዝነት ነው› (ዩሱፍ 111) አእምሮ፦ ‹ተግባርህ መረዳት ነው››፣ ለአካልም፦ ‹ያንተ ሚና መከተል ነው› የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ ትልቅ ዓላማ ነው።

<u>ሦስተኛ ዓላማ-አርአያነታቸውን መከተል</u>

የዚህ ትምህርት ሦስተኛው ዓላማ ክብደት ካለፉት ከሁለቱ የሚተናነስ አይደለም። እንዲያውም ይበልጣል። በተለይም ለወጣቶች። ምክንያቱም ተምሳሌት (Role Model) የማግኘት ጉዳይ ነውና።

ነብያት አርአያዎች (Role Model) ተደርገውልናል። በተለይም ባለንበት ዘመን ይህ ነጥብ እጅግ አስፈላጊ ነው። በወጣቶቻችን ዘንድ የአርአያ (ተምሳሌት) ጽንሰ ሐሳብ ተቀይሯል። የችግሮች ሁሉ አውራም ሆኗል። በተለይም ወጣቶች አርአያ አድርገው የያዟቸውን ስብእናዎች ስናይ ከባድ ችግር መሆኑን እንገነዘባለን።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱን ነብይ እንድታውቀውና እንድትወደው ለማድረግ ብርቱ ጥረት አድርጊያለሁ። ልፋቴ ፍሬ ይይዝ ዘንድ አላህን እለምናለሁ። ሐሳቤን እንደሚያሳካልኝም ተስፋ አደርጋለሁ፡

እነሆ ያንተ አርአያ

አንድ ወጣት የዩሱፍን ታሪክ አውቆ በጣም ቢወደው፣ ቀልቡና ስሜቱም በርሱ ቢሞላ፣ የሕይወቱ አርአያ አድርጎም ቢይዘው ደስታዬ ወሰን የለውም። በእርግጥም በዩሱፍ ታሪክ ውስጥ የንጽህናን፣ የጥብቅነትንና የተቅዋን ተምሳሌት ያገኛል። አንዲት ወጣት በድንግላዊት መርየም ስብእና ተማርካ በሁሉም የሕይወት ገጽታዎች የርሷን አርአያነት ብትከተል ደስታዬ ወሰን የለውም።

ኢብራሂም- ለወላጆች

ስለ ልጆቻቸው የወደፊት እድል እየተጨነቁ እንቅልፍ በአይናቸው ሳይዞር የሚያነጉ ወላጆች ያሳዝነኛል። ለነርሱ ዋስትና በትጋት ይሰራሉ። ሕይወታቸውን ደስተኛ ለማድረግ ያለመታከት ይለፋሉ። ይህም ሆኖ ግን ጭንቀት እና ሐሳብ አይለቃቸውም። ወላጆች ሆይ፣ እነሆ የኢብራሃምን አርአያነት የመከተል መልካም እድል ከፊታችሁ ተዘርግቷል። በአላህ የመመካትን ጥበብ ያስተምራችኋል። ወደ እሳት በተጣሉ ጊዜ የነበራቸውን መረጋጋትና በአላህ መመካት አስተውሉ። «አላህ በቂዬ ነው። በርሱ መመካት ምን ያምር፡» ማለታቸውን አልሰማችሁ ይሆን? ሰበቡን አድርሱ። የሰበቦችን ጌታም አትርሱ።

ግልጽ መልእክት

የተከበራችሁ ወዳጆቼ፣ የአላህ ነብያት አርአያዎቻችን ናቸው። ተከታዩ የአላህ ቃል ይህንኑ በግልጽ ይናገራል፡-

أَوْلَٰئِكَ الَّذِينَ هَدَى اللَّهُ فَبِهُدَاهُمُ اقْتَدِهْ قُل لَّا أَسْئَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِنْ هُوَ

«እነዚህ አላህ ቅኑን ጐዳና የመራቸው (ነቢያት) ናቸው። ٩٠ الانعام (ذِكْرَى لِلْعَالَمِينَ የነርሱን ቅን መመሪያ ተከተል (ለወገኖችህም) ለዚህ (የጥሪ ተግባሬ) ክፍያ አልጠይቃችሁም ይህ ለዓለማት የተላከ መልዕክት ነው በላቸው (አል አንዓም 90)

ከዚህች አንቀጽ በፊት የሰፈሩ አናቅጽን ቁርአን ከፍታችሁ ብትመለከቱ የነ8 ነብያትን ስም ዝርዝር ታገኛላችሁ። የአላህ ትእዛዝ ይህ ነው፡- «አርአያነታቸውን ተከተሉ።

በአዲስ ቅኝት

ትን ያሰርጻል። ቀ የድል ስሜት ሐሴትን ያሰርጻል። ቀልቦቻችንና አእምሮዎቻችንን ሊሸፍን የቀረበን ዝንጉነት የማሸነፍ ስሜት። የእያንዳንዱን ነቢይ ታሪክ ስናነብ የፈተና ቁልል እንመለከታለን። ያሸንፈዋል ብለን የማንገምተው ፈተና። ግና ሰባብሮት ሲያልፍ በአድናቆት እንዋጣለን። በድል አድራጊነት ስሜት እንደመማለን። ይህ ስሜት ወኔን ይወልዳል። ዓላማችንን የማሳካት፣ ካሰብነው የመድረስ፣ ያለምነውን የመፈጸም ወኔ። ውድ ዋጋ ያለው፣ የቀልብ ክቡር እንግዳ። አንዳንዶቻችን ይህ እንግዳ ከልቦናችን መስፈሩን እንገነዘባለን። ሁላችንም በተለያየ ደረጃ ስሜቱ ይሰርጻናል።

የነብያት ታሪክ ለስነ ምግባር፣ ለኢባዳና ቀልባችንን ለማስተካከል ትልቅ ግብአት ነው፡ ፡ ይህን ጽንሰ ሐሳብ በነብያት ታሪክ አማካይነት በአዲስ ቅኝት እናብራራዋለን።

ወንድሜ ሆይ፣ መታወክን አቁም። የቀልብህ ውድና ክቡር እንግዳ ኢማን መሆኑንም እወቅ።

<u>አራተኛ ዓላማ- ከተራራ የጸና እምነት</u>

የነብያትን ሕይወት የመተረካችን አራተኛ ዓላማ በቀልቦች ውስጥ ዓቂዳን ማጽናት ነው። ዓቂዳ ማለት በቀልብ ውስጥ እምነት ዘወትር ጽናት ማግኘቱ ነው። አንዳንዶቻችን ዓቂዳ የሚለውን ቃል ስንሰማ እንበረግጋለን። ሌሎቻችን ደግሞ ዓቂዳ ማለት ፊትን ማኮሳተር፣ አለመሳቅ፣ የስሜት መደነዝ፣ ከሰዎች ጋር ግንኙነትን ማቆርፈድ እንደሆነ እናስባለን።

ይህ እይታ ከእውነታው በጣም የራቀ ነው። በተጨባጭም መሠረት የሌለው ከንቱ ቅዠት ነው። እነሆ፣ ኢስላማዊ ቃላትን እና ጽንሰ ሐሳቦችን በትክክልና በወጉ ልንረዳቸው የሚገባበት ጊዜ አሁን ነው።

ወንድሜ ሆይ፣ ኒያን አስታውስ። ዓላማዎች በባህሪያቸው ኒያዎች እንጅ ሌላ አለመሆናቸውን ማረጋገጥን እንደማትዘነጋ አምናለሁ።

<u>የኢብን ዑመር ድንቅ ምላሽ</u>

የአላህ መልእክተኛ ሶሐቦች ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ሁላችንም ስለ ሶሐቦች፣ ስለ አነጋገራቸው፣ ስለ አካላዊ ገጽታቸው፣ ስለ እንቅስቃሴያቸው ወዘተ በአእምሯችን ውስጥ የየራሳችን ስዕል አለ። አብደላህ ቢን ዑመር ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሶሐቦች ይስቁ ነበርን?›› የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው።

ወንድሜ ሆይ፣ ለዚህ ጥያቄ መልስ አለህን? የኢብን ዑመርን ምላሽ እነሆ፣ ‹‹አዎ፣ ይስቁ፣ በጣም ይስቁ ነበር። ግና ኢማናቸው በልቦቻቸው ውስጥ ከተራራ የጸና ነበር።››

ያ አላህ! ሳቅን ማን ሐራም አደረገው? ፊታችንን ለምን እናጨፈግጋለን? መልእክተኛው ገጽታቸው ብሩህ ነበር። ፊታቸው በፈገግታ ብርሃን የተሞላ ነበር። ኢስላም በሁሉም ጉዳዮቻችን ሚዛናዊነትን ይሻል፡

<u>ጥብቅ ግንኙነት</u>

በአንዳንዶቻችን አእምሮ ውስጥ፡- ‹አቂዳን ማጽናት ከነብያት ታሪክ ጋር ምን አገናኘው? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ግኙነታቸው እንደ ረፋድ ጸሐይ ግልጽ ነው። የእያንዳንዱን ነቢይ ታሪክ ማወቅ፣ በሕይወት ውስጥ ላጋጠሟቸው ፈተናዎች ከወሰዷቸው እርምጃዎች ጋር ልቦናችን የሚፈጥረው መስተጋብር በእርግጥም እምነትን ያጸናል። ዩኑስ በአሳ ሆድ ውስጥ ሆነው ያሰሙትን ነ ብዜ እስኪ አስተውል፡ الأنبياء: ٨٧

(أَن لَّا إِلَهَ إِلَّا أَنتَ سُبْحَنَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ الظَّلِمِينَ

“ከአንተ ሌላ አምላክ የለም ክብር ላንተ ይሁን እኔ በእርግጥም ከበዳዮች ሆኛለሁ::" ሲል ተጣራ። (አል አንቢያእ 87)

እንዲህ የሚል ምላሽም ከሰማይ ወረደላቸው-

الشاء 88 أ> غشذي المؤمنين الؤنن فاستجبببببنا لهه الغغ الغغ الغغ

ኢብራሂም ወደ እሳት ሲወረወሩ ከአላህ ተከታዩ ብስራት መጣ፡-

(قُلْنَا يَنَارُ كُوني بَرْدًا وَسَلَامًا عَلَى إِبْرَاهِيمَ الأنبياء: ٦٩

“እሳት ሆይ! ለኢብራሂም ቀዝቃዛና ምቹ ሁኚለት።” አልን፡ (አል አንቢያእ 69)

እነዚህ ታሪኮች ልቦናን አያጸኑምን? ኢማንን አያጠነክሩምን? ከአላህ ዘንድ ባለው ጸጋ፣ በአብሮነቱና በእገዛው እንድንተማመን እንደሚያደርጉን ጥርጥር የለውም። በነብያት ታሪክ አማካይነት ካልሆነ በሌላ በምን መንገድ ይህን ማየት ይቻለናል?

አምስተኛ : ዓላማ- ወደ : አላህ እንዴት ጥሪ | ማድረግ እንዳለብን እንማራለን

ብዙዎቻችን የነብያትን አርአያነት በመከተል ሰዎችን በጥበብና በመልካም ግሳጼ ወደ አላህ መጥራት እንሻለን። የነብያትን ታሪክ የማጥናታችን አምስተኛ አላማ ይህ ነው። በነብያት ድንቅ ሕይወት ውስጥ የዳእዋ _ ስብእና በጉልህ ይገለጻል። በየትኛውም ቦታና ዘመን የአላህን መልእክት የሚያደረስ ሰው ማንነት ይጎላል። _ ይሆናሉ ብለን በማናስባቸው አጋጣሚዎች ሳይቀር ነብያት ዳእዋን በጥበብ ሲያከናውኑ ታሪካቸው ያሳየናል። ዩሱፍን እንመልከት። ለእስር ቤት ጓደኞቹ ዳእዋ ሲያደርግ። የልቡ ምት ሳይቀር በዳእዋ የተቃኘ ይመስላል። ተከታዩን የአላህ ቃል እንመልከት፡-

يُصَحِيَ اليَجْنِ أَرْبَابٌ تُتعرفون عبر أمر الله الواحد القهار است

የእስር ጓደኞቼ ሆይ፣ የተለያዩ ጌቶች ይሻላሉን ወይንስ አንድና ኃያል የሆነው አላህም (ዩሱፍ 39)

እዝነቱን ተመልከት። ጥበባዊ ስልቱን አስተውል፡

የእስር ጓደኞቼ ሆይ፣ ከፍቅር እና ከእዝነት የመነጨ ጥሪ። የነብያት ታሪክ እንዲህ የሚል መልእክት ያስተላልፉልናል፡-

የሰዎችን እጆች ይዛችሁ ወደ አላህ ምሩ። የነብያት መልእክተኞች ሁኑ።

እንደ ሐኪም ሁኑና ሕክምናውን ጀምሩ።››

ስድስተኛ ዓላማ- ቁርአንን መረዳት

የነብያት ታሪክ ስድስተኛ ዓላማ የአላህን መጽሐፍ መረዳት ነው። ከአሁን ቀደም እንደገለጽነው የቁርአን ሲሶ የነብያት ታሪክ ነው። የአላህን ኪታብ ሊረዱት የማይቻል እንቆቅልሽ፤ ሊፈቱት የማይቻል ቅኔ አድርገው የሚመለከቱ ወጣቶች ያሳዝኑኛል። ብዙ ወጣቶች በነርሱና በቁርአን መካከል ለቁጥር የታከቱ ግርዶዎች እንዳሉ ራሳቸውን

አሳምነዋል። ከቁርአን አንድ ገጽ አንብበው ከአንድ ወይም ከሁለት ቃላት በስተቀር አይገነዘቡም። ይህ በእርግጥ ያሳዝናል።

የነብያትን ታሪክ የማጥናታችን ሌላው ዓላማ ወይም ኒያ የአላህን ኪታብ መረዳት፣ ከርሱ ጋር ሊኖረን የሚገባውን መስተጋብር መገንዘብ፣ በርሱና በኛ መካከል ያሉ ግርዶዎችን ሁሉ ማስወገድ ነው። የነብያትን ታሪክ መከታተል፣ ሚስጥራቸውን መፈተሽ ለዚህ ግብ ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ከኪስህ የተቀመጠ ቁርአን፣ ከልቦናህ የተኖረ ሐብት

የነብያትን ታሪክ ለማወቅ አመላካቻችን ቁርአን መሆኑ እሙን ነው። የዚህ ታሪክ ዓይነተኛ ዋቢ እርሱ ነው። ስለዚህም ለምን ዘወትር ካንተ ጋር አይኖርም? አዎ፣ በሁሉም ቦታዎች ቁርአን ካንተ ጋር ሊኖር ይገባል። «መጸዳጃ ቤት ሲቀር፡» በማለት ፈጥነህ እንደምታርመኝ እገምታለሁ። በእርግጥ ትክክል ነህ። ግና የዋህ ምላሽ ነው። እውን በሌላ ቦታ ቁርአን ትይዛለህ? የኪስ ቁርአን ከሌለህ የቁርአንን አብሮነት እንዴት ታገኛለህ? ስለዚህም ቁርአን ከእጅህ አይለይህ። ከኪስህ እንዳይጠፋ አደራ። ነገ ሳይሆን ዛሬውኑ። ዘወትርም _ አንብበው። ያነበብከውን አስተንትን። በውስጡ የተካተተውን የነብያት ታሪክ ደጋግመህ ስታነብ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ከቀልብህ ውስጥ ይጸናል። የማይነጥፍ የልቦና ሐብትም ይኖርሐል።

ሰባተኛ ዓላማ- ቤታችንን እናስተካክል

የነብያትን ታሪክ የምናጠናበት ሰባተኛውና የመጨረሻው ቤቶቻችንን ማስተካከል ነው። _ በነብያት ድንቅ ሕይወት ቤቶቻችንን የምናስተካክልበትን ጥበብ እናገኛለን። ዓላማ ውስጥ

እነሆ ኢብራሃም ለልጃቸው ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። በመልካም ባህሪ ያንጹታል። በጥሩ ስብእና ይቀርጹታል። እርሱም ሲያድግ የነብይነትን ሐላፊነት የሚሸከም ድንቅ ሰው ሆነ። ዳውድ የኢብራሂምን አርአያነት ተከተሉ። ልጆቻቸውን ኮተኮቱ። ልጃቸው ሱለይማንም ሲያድግ ነብይ ሆነ። ይህ ድንቅ ነገር አይደል?

وَكَانَ أَبُوهُمَا صَلِحًا

" አባታቸው መልካም ሰው ነበር...›› (አል ከህፍ 82) ጎጆዎቻችን በአያሌ ችግሮች ይንገላታሉ። ተጋቢዎች አንዱ ስለሌላው ስሞታ ሲያሰሙ፣ ሚስት ባሏን፣ ባል ሚስቱን ሲከሱና ሲያማርሩ እንሰማለን። ወላጆች በልጆቻቸው አፈንጋጭነት ሲያማርሩ፣ ልጆችም አባቶቻችን እኛን አይረዱንም በማለት ሲናገሩ እንሰማለን። በሁሉም ወገኖች ዘንድ የውይይት ቋንቋ ጠፍቷል። ያለንበት ዘመን ለዚህ አባባል ጥሩ ምስክር ነው።

ታሪክ ራሱን ይደግማል

የነብያት ታሪክ በሕይወታችን ውስጥ በየቀኑ የሚደጋገም እውነታ ነው። ተመሳሳይ ተውኔት ነው። የሚለያዩት ተዋናዮች ብቻ ናቸው። ከሺዎች አመታት በፊት የተኖረውን የራሳችንን ሕይወት በነብያት ታሪክ አማካኝነት እንቃኛለን። የዩሱፍና ለፊተና የዳረገችው እንስት ታሪክ በሁሉም ቦታዎችና ዘመናት በየእለቱ ይደገማል። ሌሎች ክስተቶችም እንደዚሁ። ታሪክ ራሱን ይደግማል። ታሪክን በአግባቡ አንብበው፣ በወጉ አጢነው፣ ከጥንቶቹ ተምረው፣ ለወደፊት ሕይወታቸው ጥበብ የሚዘግኑ ብልሆች የት አሉ?

አስተውሎት

ሁላችንም ቆም ብለን ስለ ራሳችን እናስብ። የማስታወስ ክሕሎታችንን እንፈትሽ፡ : የነብያትን ሕይወት ማጥናት ያስፈለገበትን ሰባት ዓላማዎች ዘርዝረናል። እስኪ ለማስታወስ ሞክር፡-

1) ሙእሚኖችን ማጽናት
2) ትምህርት መቅሰም
3) መልካም አርአያነታቸውን መከተል
4) እምነትን ማጽናት

5) ወደ አላህ እንዴት ጥሪ እንደምናደርግ መማር

6) ቁርአንን መረዳት

7) ቤቶቻችንን ማስተካከል ወዳጆቼ ሆይ፤ የነብያትን ታሪክ በመቃኘት ለምናደርገው ጉዞ እነዚህ ዓላማዎች የግድ አስፈላጊ ናቸው። አሁን ስሜታችን ተነሳስቷል። ፍላጎታችን ጠንክሯል። አእምሯችን በሰባት ግሩም ዓላማዎች ተሞልቷል፡ ፡ ስለዚህም ወዳሰብነው አቅጣጫ መጓዝ እንችላለን። እነሆ ለመጓዝ ተዘጋጅተናል። ለመብረር አኮብኩበናል።

ሦስቱ ምሰሶዎች

የነብያት ታሪክ የተሰኘው ይህ ግዙፍ ሕንጻ የቆመባቸው ዋናዋና ምሰሶዎች ሦስት ናቸው። አዲሱ ቅኝታችን የሚፈለገውን ፍሬ ያስገኝልን ዘንድ እነዚህን ምሰሶዎች ማወቁ ተገቢ ነው።

አንደኛ- ትምህርትና ተግሳጽ

. የዚህ ትምህርታችን ዓላማ ታሪክ መተረክ ብቻ እንደሆነ ያሰበ ተሳስቷል፡ ፣ ልብ አንጠልጣይ ታሪክን ለማንበብ ብቻ ያለመ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሰበውን ላያገኝ ይችላል። በእርግጥ የእያንዳንዱ ነብይ ታሪክ ልብ ሰቃይ ነው። እኛም በዚህ ስራችን ይህን አልዘነጋንም። ግና ከላይ እንዳብራራነው ዓይነተኛው ዓላማችን ይህ ሳይሆን ከታሪኮቹ ትምህርት መቅሰምና ለተጨባጭ ሕይወታችን መጠቀም ነው። ታሪካችን ከፋፍለን እያንዳንዱን ክፋይ በጥልቀት የመተንተን ስልት እንደምንከተል ማሳወቅ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ማለት ሙሉ ታሪኩን በአንድ ጊዜ ላንተርከው እንችላለን ማለት ነው። ምክንያቱም የትረካችን ዓላማ አላህ እንዲህ ሲል የገለጸው ነውና፡

نا قصص القصَصَ لَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ) الأعراف

ያስተነትኑ ዘንድ ታሪኩን ተርክላቸው›› (አል አዕራፍ 176)
ከታሪኮች የምንሻው ዓይነተኛ ዓላማ ይህ ነው። አእምሮ የማያስብበትና ይህ ባህሪውም በአካል ላይ የተንጸባረቀበት የአሉታዊነት ዘመን አክትሟል። በእንዲህ ዓይነቱ ዘመን ለሰው ልጅ ከሕይወት ይልቅ መሞት ይሻለዋል። አሁን ግን ዘመኑ ተቀይሯል። ሁኔታዎች ተቀይረዋል። የጊዜያችን መንፈስም፦ ‹‹እምቢ ለአሉታዊነት፣ እምቢ ላለማሰብ፣ እምቢ ለአእምሮ ድንዘት›› የሚል ሆኗል።

ሁለተኛ ፍሪያማ እውቀት

ይህ ሕንጻ የቆመበት ሁለተኛው መሠረት ተከታዩ የሸሪዓ መርህ ነው፦

كل مسألة لا يبني عليها عمل فهى من التكلف الذي نهينا عنه

‹‹ከርሱ ላይ ስራ የማይታነጽበት የትኛውም አጀንዳ በሸሪዓው የተከለከልነው ጸጉር ስንጠቃ ነው።››
ስለዚህም ጥቅም ወደሌላቸው ነገሮች ውስጥ አንዘፈቅም። ለሕይወት ፋይዳ የሌላቸውን አጀንዳዎች እያነሳን አንፈተፍትም።ለምሳሌ፦ ‹አዘር የኢብራሂም _ አባት ነው ወይስ አጎት የሚለው ጥያቄ ለኛ አይጠቅመንም። አባቱ ይሁን አጎቱ ማወቅ አይፈይደንም። ስለዚህም ለምን ወደርሱ እንገፋፋለን?
ሱለይማንን ያናገረችው ጉንዳን ሴት ወይም ወንድ መሆኗን ለማወቅ ጓጉቶ የጠየቀ ድርጊቱ ከንቱ ነው።
ወደዚህ አይነት አንዳች ፋይዳ የሌላቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዘፈቅም። ምእራቡ ዓለም ይህን አሳምሮ ሰርቶበታል። በሚገባ ተጠቅሞበታል። ከዚህ የተነሳ ስለምእራባዊያን _ ስናወጋ፦ የተግባር ሰዎች ናቸው። በማለት እንመሰክርላቸዋለን።

ሦስተኛ- ከእስራኤላውያን አፈታሪኮች መራቅ

ይህ ግዙፍ ሕንጻ የቆመበት ሦስተኛው እና የመጨረሻው ምሰሶ ከእስራኤላውያን አፈታሪክ መራቅ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

رَحْمَةٌ سَبْعَةٌ وَثَامِنُهُمْ كَلْبُهُمْ قُل سَيَقُولُونَ ثَلَٰثَةٌ رَّابِعُهُمْ كَلْبُهُمْ وَيَقُولُونَ خَمْسَةٌ سَادِسُهُمْ كَلْبُهُمْ
ا مَاءً ظَهِرًا وَلَا تَسْتَفْتِ فِيهِم مِّنْهُمْ أَحَدًا (الكهف. رَّبِّ أَعْلَمُ بِعِدَّتِهِم مَّا يَعْلَمُهُمْ إِلَّا قَلْفِيلًا

‹‹(ከፊሎቹ ሦስት ናቸው፤ አራተኛው ውሻቸው ነው። ይላሉ። (ከፊሎቹም አምስት ናቸው፡ ስድስተኛው ውሻቸው ነው ይላሉ ሁሉም) በግምት (ይህን ይናጋራሉ) (ሌሎች ደግሞ)- ሰባት ናቸው ስምንተኛው ውሻቸው ነው ይላሉ። ጌታዬ ቁጥራቸውን ይበልጥ ዐዋቂ ነው። ጥቂቶች እንጂ አያውቋቸውም። በል። ስለነርሱ ጉዳይ ግልጽ (እውቀትን መሠረት ያደረገና ጠቃሚ ክርክርን እንጂ አትሟገት። ስለነርሱም ከመካከላቸው ማንንም አትጠይቅ›› (አል ከህፍ 22)

እንቀጹ አይሁዶችን የሚመለከት ነው። ቀደምት ነብያትን በተመለከተ ከነርሱ የሚነገረው የትኛውም ታሪክ አይታመንም። ከዚህ የተነሳ በየመጽሐፍቱ የተሰገሰጉ የእስራኤላውያን አፈታሪኮችን ሙሉ በሙሉ መራቅን መርጠናል።

አላህ ቁርአንን ከስህተት ጠብቆታል። ከመጨመርና ከመቀነስ፣ ከመበረዝና ከመከለስ ታድጎታል። ክብር ለርሱ ይሁን። ጥሩ፣ የተባረከና የበዛ ምስጋናም ይድረሰው።

በዚህ የነብያት ታሪክ ስራዬ ለጊዜ ቅደም ተከተል ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጊያለሁ። ሳላወሳው ያለፍኩት ወይም ቀዳሚ ሆኖ ከሌላው ያዘገየሁት ነብይ የለም። ነብያት የተነሱበትን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ታሪካቸው ቀርቧል። ይህ ደግሞ በኔ እይታ እጅግ ጠቃሚ ይመስለኛል።

ተወዳጁ ወንድሜ ሆይ፣ እነሆ በነብያት ጎዳና ላይ የመጀመሪያውን እርምጃ ተራምደሐል፡ ፡ አዎ፣ እጅግ የተላቀ የጉዞ መስመር ይዘሐል። እጅግ ወደተከበረ ስፍራ ዘልቀሐል። ስለዚህም ራስህን ወደዚህ የላቀ ደረጃ ከፍ አድርግና ጉዞህን ቀጥል። ኒያህን አትዘንጋ። ዓላማህንም አስታውስ።

ከመጀመራችን በፊት

የነብያትን ታሪክ በዝርዝር ከመቃኘታችን በፊት ዘጠኝ ነጥቦችን ማንሳት ማብራሪያዎች የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ተሰምቶናል። ወደታሪኩ ለመግባት መደላድል የሚፈጥሩልን፣ የታሪክ ቅኝታችንን የሚያገሩልን እንደሆኑም እናምናለን። ነጥቦቹን እነሆ፡-

አንደኛ ነጥብ፡- ታሪክ የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

ሁለተኛ ነጥብ፡- የነብያት ታሪክ በተጨባጭ የነበረ እውነታ ነው ወይስ ተጨባጭነት የሌለው ምናባዊ?

ሦስተኛ ነጥብ፡- በቁርአን ውስጥ የነብያት ታሪክ ለምን ተደጋግሞ ይነሳል?

አራተኛ ነጥብ፡- በነብይና በመልእክተኛ (ረሱል) መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

አምስተኛ ነጥብ፡- የነቢያት ቁጥር ምን ያህል ነው?

ስድስተኛ ነጥብ፡- አላህ የከፊል ነብያትን ታሪክ በቁርአን ውስጥ ተርኮ የሌሎችን የተወው ለምንድን ነው?

ሰባተኛ ነጥብ፡- አንድን ነብይ ከሌላው ማበላለጥ ይፈቀዳልን?

ስምንተኛ ነጥብ፡- ከመልእክተኞች መካከል የጽናት ባለቤቶች (ኡሉል ዓዝም) የተባሉት እነማን ናቸው? ለምንስ በዚህ የማእረግ ስም ተጠሩ?

ዘጠነኛ ነጥብ፡- ነብያት ነብይ ከመሆናቸው በፊትና በኋላ ከሐጢአት . የተጠበቁ ናቸውን?

ከላይ የተዘረዘሩ ጥያቄዎችን መልስ ብዙዎቻችን እናውቃቸዋለን። ግና አእምሮን ለማነቃቃትና ከአጀንዳው ጋር የበለጠ መስተጋብር ለመፍጠር ስንል ልናብራራቸው ወደናል።

ተወዳጁ ወንድሜ ሆይ፣ እባክህን ቀልብህን አውሰኝ። ስሜት እና አእምሮህን ከኔ ጋር አድርግ።

<u>የነብያት ታሪክ ትርጉም</u>

ቀሶስ የሚለው የዓረብኛ ቃል መሠረት እቅተሰል አስር የሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም እስከደረሰበት ድረ፡ ዱካውን ተከተለ ማለት ነው። በወንጀለኛ ላይ የሚወሰድ የቅጣት እርምጃ ቂሷስ የተባለውም ወንጀለኛን ተከታትሎ ለጥፋቱ ተገቢውን ቅጣት መቅጣት በመሆኑ ነው። ተከታዩን የአላህ ቃል እንመልከት፡-

(وَلَكُمْ فِي الْقِصَاصِ حَيَوةُ يَتأُولِي الأَلْبَابِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

አስተዋዮች ሆይ ቂሷስ ለናንተ ሕይወት ነው አላህን ትፈሩ ዘንድ (ይህ ድንጋጌ ሰፍሮላችኋል» (አል በቀራህ 179)

ጸጉርን እያንዳንዱን ዘለላዋን ተከታትሎ ማሳጠርም ቀሱ ሽእር› ይባላል፡ ስለዚህም : ቀሶስ አንድን ነገር ፍጻሜውን እስክታውቅ ድረስ መከታተል ነው። የሙሳ እናት እንዲህ ማለቷ በቁርአን ተተርኳል፡

(وَقَالَتْ لِأُخْتِهِ، فَضِيهِ فَبَصُرَتْ بِهِ- عَن جُنُبِ وَهُمْ لَا يَشْعُرُونَ «ለእህቱም ምን እንደሚያደርጉን) ተከተለ። አለበት: (ለእህቱም) እነርሱን ሳያውቁ ከርቀት አየችው። (አል ቀሶስ 11)

የእናት ፍላጎት የሙሳ እሳት ወሬ ተከታትሎ እንድታውቅ ሲሆን፣ ለዚህ ፍላጎቷ የተጠቀመችው ቃል ቀሲሂ የሚል ነው። «ወሬውን ተከታተይና የሚገኝበትን የመጨረሻ ሁኔታ ግለጭልኝ» ማለቷ ነው። እህትም የተባለችውን አደረገች። የልጁን ዱዓ ተከተለ። የሚገኝበትን ስራ አወቃቀር።ቀሶስ የሚለው ቃል በቁርአን ውስጥ 30 ጊዜ ያህል ጠቅሷል።

ያን ይህ ሁሉ ከነብያት ታሪክ ጋር ምን አገናኘው? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይችላል። እጅግ የተጠበቁ ግንኙነት አለ። ምክንያቱም የእያንዳንዱን ነ ነቢይ ታሪክ በመከተል ከይዘቱ ትምህርት እንቀስማለን። የቀሰምነውን ትምህርትም ወደተጨባጭ ሕይወታችን

እናመጣዋለን:: የሚጠበቅብንን ግዴታም እናብራራለን:: ይህን ቃላችንን በአላህ ፈቃድ አንዘነጋም:: ዓላማችንም ይህው ነው:: የመጽሐፉ ግብ የነብያትን ታሪክ በአዲስ እይታ መቃኘት መሆኑን አስታውስ::

<u>ሁለተኛ:- የተቀጠፈ ወሬ አይደለም</u>

የነብያት ታሪክ በተጨባጭ የሆነና የተፈጸመ ነውን? ወይስ የልብ ወለድና የቲአትር ጸሐፊዎች ለድራማዊ ትረካ ወይም ለሌላ ዓላማ እንደሚያደርጉት በጥቂት እውነታዎች ላይ የተገነባ፣ ተጨባጭነትም የሌለው፣ ምናብ የወለደው ነው:: መልሱን ሁላችንም እናውቀዋለን:: አላህ እንዲህ ብሏል:-

لَقَدْ كَانَ فِي قَصَصِهِمْ عِبْرَةٌ لِأُولِي الأَلْبَابِ مَا كَانَ حَدِيثًا يُفْتَرَى وَلَكِن تَصْدِيقَ الَّذِي بَيْنَ يَدَيْهِ وَتَفْصِيلَ كُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً لِقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ)

يوسف

ታሪካቸው በእርግጥ ለአስተዋዮች ተግሳጽ እና ትምህርት ሰጭ) ነው። (ቁርኣን) የተቀጠፈ ወሬ አይደለም።

ግና ከርሱ በፊት የነበሩ (መለኮታዊ መልዕክቶችን አጽዳቂና ሁሉንም ነገር ገላጭ ለአማኞችም መመሪያና እዝነት ነው›› (ዩሱፍ 111)

(نَحْنُ نَقُصُّ عَلَيْكَ نَبَأَهُم بِالْحَقِّ إِنَّهُمْ فِتْيَةٌ وَامَنُوا بِرَبِّهِمْ وَزِدْنَهُمْ هُدًى

ታሪካቸውን በእውነት እንተርክልሃለን በጌታቸው ያመኑ ወጣቶች ናቸው።

እኛም መቀናትን አከልንላቸው ›› (አል ከህፍ 13) አዎ፣ የተተረከልን በእውነት ነው:: እያንዳንዱ ክፍሉ ፈጠራ የሌለበት ሐቅ ነው። እኛ ይህን እናምናለን:: ዩኑስ በአሳ ሆድ ውስጥ ነበር። ኢብራሂም ወደ እሳት ተጥለዋል:: «ፈጠራ ወሬ አይደለም::» የነብያት ታሪክና እርሱን ማመናችን ለኛ ለሙስሊሞች የዓቂዳችን ዋነኛ አካል ነው:: ቁርአን ከአላህ የመጣ መልእክት ነው ብሎ የሚያምን ማንም ሰው ከውስጡ የሰፈረው ታሪክ ሁሉ እውነት መሆኑን እንደሚያምን ጥርጥር የለውም::

وَمَنْ أَصْدَقُ مِنَ اللَّهِ قِيلًا) النساء:

«ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማን ነው?» (አል ኒሣእ 122)

<u>ሦስተኛ፡- ለምን ይደጋገማል</u>?

የሚገርመው በቁርአን ውስጥ አንዱ ታሪክ ለበርካታ ጊዜ ይደጋገማል። ይህ ጉዳይ ለብዙዎች ስህተት መነሻ ሆኗል። ቁርአን አንድን ታሪክ ደጋግሞ ማንሳቱ ምን ፋይዳ አለው? በማለት ያልበሰለ አስተያየት እንዲሰጡ ዳርጓቸዋል።

በእርግጥ ይህ እይታ ብስለት ይጎድለዋል። ይህን ባዮቹ ከቁርአን ጋር አብረው የመኖር እድል እንዳላገኙም ያመለክታል። አላህ ታሪኮችን የሚደጋግመው መልእክቱ በልቦናህ ውስጥ እንዲጸና፣ በአካልህም በተግባር እንዲገለጽ ለማድረግ ነው። ለምሳሌ ኢብራሂም ልጃቸውን ያርዱ ዘንድ የመታዘዛቸው ታሪክ ተደጋግሞ ተወስቷል። ይህም የሆነው ለአላህ ያለ ተቃውሞ መታዘዝን ትማር ዘንድ እና ይህ ጥልቅ መልእክት በልቦናህ ውስጥ በሚፈለገው አኳኋን ይሰርጽ ዘንድ ለማስቻል ነው።

የኑህ ታሪክ እና ሕዝባቸውን ለ950 ዓመታት ሳይሰለቹና ሳይታክቱ የመጥራታቸው እውነታም ትእግስትን ትማርበት ዘንድ ተደጋግሞ ይተረካል።

ውድ ወንድሜ ሆይ፤ ታሪኩ ይሰርጽህ ዘንድ መደጋገሙ ግሩም ነገር ነው። ትምህርቱን ደግሞ ደጋግሞ የሚያጠና ተማሪ ከአንድ ጊዜ በላይ ካላየው የበለጠ ለመልስ ራሱን ዝግጁ ማድረጉ አይታይህምን?

<u>ዛፏ ዛሬም አለች</u>

አንዳንድ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ቁም ነገር እንማር ዘንድ ታሪኮች ይደጋገማሉ። ይህውም በቁርአን ውስጥ የሚደጋገመው ታሪክ በሕይወታችንም ውስጥ በጣም እንደሚደጋገም እናውቅ ዘንድ ነው። ለምሳሌ የአደምና የኢብሊስ ታሪክ በቁርአን ውስጥ ተደጋግሞ ይነሳል። በሕይወት ውስጥም እንደዚሁ። ኢብሊስ አደምን እና ሐዋእን

እንዳሳሳታቸው አንተንም ያሳስትሐል። እነርሱን በጠላትነት እንደያዘው ባንተም ላይ ጠላት ሆኖ ተሰይሞብሐል። አደም የተከለከችውን ዛፍ እንዲመገቡ አድርጓቸዋል። አንተም ይህችን ዛፍ ትመገባት ዘንድ ይጎተጉትሐል። ዛፏ ዛሬም አለች። ጥቂት የቅርጽ ለውጥ ብቻ አደረገች እንጅ። አዎ፣ ዛሬ ዛፏ ቅርጻን ቀይራ መጥታለች። ቁርአንን መራቅ፣ ሶላትን መተው፣ ሐራሞችን መዳፈር ሆና ተከስታለች።

አደም ዛፏን በመብላታቸው አምላካቸውን አስቀየሙ። በተውባ ከተመለሱ በኋላም ወደ ምድር እንዲወርዱ ተደረጉ። አንተ ግን ዛፏን ከተመገብክ እጣ ፈንታህ ምን ሊሆን እንደሚችል ታውቃለህን?

<u>አራተኛ፡- የነቢይና የመልእክተኛ ልዩነት</u>

በነብይና በረሱል (መልእክተኛ) መካከል ልዩነት አለ? ወይስ ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው በእርግጥ ልዩነት አለ። ለዚህም ተከታዩ የአላህ ቃል ጥሩ ዋቢ ይሆናል።

وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولِ وَلَا نَبِي إِلَّا إِذَا تَمَنَّى أَلْقَى الشَّيْطَانُ فِي أُمْنِيَّتِهِ. فَيَنسَخُ اللَّهُ مَا يُلْقِي الشَّيْطَنُ ثُمَّ يُحْكِمُ الله انيهِ، وَالله عَليه حَكِيمُ

ከአንተ በፊት አንድም ነቢይ ወይም መልዕክተኛ አልላክንም፡ እንዳች ነገር በተመኘ ጊዜ ሰይጣን በምኞቱ ላይ (ከንቱ ነገር) የጣለበት ቢሆን እንጅ ግና አላህ ሰይጣን የጣለውን ከንቱ ነገር ያስወግዳል ከዚያም መልዕክቱን (ይበልጥ) ያፀናል። አላህ ዐዋቂም ጥበበኛም ነውና (አል ሐጅ 52)

ስለዚህም በረሱልና በነብይ መካከል ልዩነት አለ። አላህ በአንቀጹ እንደተናገረው። ግና ልዩነታቸው ምንድን ነው? በዑለሞች ዘንድ በስፋት የሚታወቀው ትርጉም መልእክተኛ ማለት ወህይ የወረደለትና ለሰዎችም እንዲያደርሰው የታዘዘ ሲሆን፤ ነቢይ ማለት ግን ወህይ የወረደለት፣ ግና የማድረስ ግዴታ ያልተጣለበት ነው።

እዚህ ላይ አንዳንድ ጽንሰ ሐሳቦች ይምታታሉ። ብዥታዎች ይፈጠራሉ። ስለዚህም ጥቂት ማብራሪያ መስጠት ግድ ይለናል።

ተቀባይነት አለውን?

ከላይ የተቀመጠውን ትርጉም ሲያነብ ግራ የሚጋባ ሰው መኖሩ አይደንቅም። አላህ ለነብይ መልእክት አውርዶ ለሰዎች እንዲያደርሰው ሳያዘው መቅረቱ ለምን? ሲል መጠየቁም ተገቢ ነው። ነብይ ለምን የማድረስ ኃላፊነት አልተጣለበትም? እርሱ ይቅርና ዑለሞችና ዳኢዎች እንኳ ያወቁትን እንዲያደርሱ፣ በመልካም እንዲያዙ፣ ከመጥፎ እንዲከለክሉ ግዴታ ተጥሎባቸው የለምን? ስለዚህም የነብይ ትርጉም ይህ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። ተከታዩ የአላህ መልእክተኛ ሐዲስ የኛን እይታ ይደግፋል። እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የሚከሰቱ ሕዝቦች ተገለጹልኝ። ጥቂት ተከታዮችን ብቻ ያፈራ፣ አንድ ሁለት ብቻ ሰዎች የተከተሉት ነብይ አለ።»4

1991 ይህም ማለት ያ ነብይ መልእክቱን ለሌሎች አድርሶ የተወሰኑ ተከታዮችን አፍርቷል ማለት ነው።

የሁለቱ ቃላት ትክክለኛ ትርጉም እንዲህ ነው፡- መልእክተኛ (ረሱል) ማለት አላህ አዲስ ሸሪዓ በወህይ አውርዶለት መልእክቱን እንዲያደርስ ያዘዘው ሲሆን፣ ነብይ ማለት ግን ከርሱ በፊት የነበረው መልእክተኛ ሸሪዓ በወህይ የተገለጸለት እና እርሱኑ እንዲያስተምር የታዘዘ ነው።

አሁን ትርጉሙ ገባን ወይስ የተወሰነ የብዥታ ቅሬት አለ? ሙሉ በሙሉ ግልጽ እንዲሆንልን አላህን እለምናለሁ። ሁለንተናዊ ግንዛቤ ይሰጠን ዘንድም እማጸነዋለሁ።

እጅግ የከበደ ሐላፊነት

እንደተለመደው ሁሉ እዚህ ላይ ተግባር ተኮር እንሆናለን። ስለዚህም በነብይና በመልእክተኛ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ምን ይፈይደናል?

4*አህመድ እንደዘገቡት

የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ግድ ይለናል። ሁላችንም እንደምናውቀው የመጨረሻው ነብይም፣ የመጨረሻው መልእክተኛም ነቢዩ ሙሐመድ ናቸው። የዚህን እውነታ ጥልቅ መልእክት ተረዳህን? የመጨረሻው ነብይና የመጨረሻው መልእክተኛ ኡምማህ ነን። ለምን እርሳቸውን አርአያ አድርገን አንይዝ? ለምን አንከተላቸው ሱናቸውን ለምን አንጠብቅ?

እናንተ የመጨረሻው መልእክተኛና ነብይ ተከታዮች ሆይ፣ በጀርባችሁ ላይ ትልቅ ሐላፊነት ወድቋል። የነብያችሁን አርአያነት ተከተሉ። ሱንናቸውን ተግብሩ። እርሳቸው በተጓዙበት ፍኖት ተጓዙ። ይህ የናንተ ብቻ ሐላፊነት ነው። ከናንተ ውጭ ሌሎች ሊወጡት አይችሉም።

<u>አምስተኛ፡- የነብያትና የመልእክተኞች ቁጥር ምን ያህል</u>

አቡ ዘር አልጊፋሪ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡ የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ የመልእክኞች ቁጥር ስንት ነው? በማለት ጠየቅኳቸው፡

‹‹ከሦስት መቶ አስር በላይ›› ሲሉ መለሱ።
በታሪክ ውስጥ የአላህ መልእክተኞች ቁጥር ይህ ነው።

የነብያት ቁጥርስ ስንት ነው?› ስልም ጠየቅኳቸው። ‹‹120 ሺህ ናቸው፡ : ከነርሱ መሐል 365ቱ መልእክተኞች ናቸው።›› ሲሉ መለሱልኝ።

ከዚህ የነቢዩ ሐዲስ እጅግ ጠቃሚ የሆነ አንድ ትምህርት እናገኛለን። ይህ ትምህርት በተከታዩ የቁርአን አንቀጽ ውስጥ ተመልክቷል፡

إِنَّا أَرْسَلْنَاكَ بِالْحَقِّ بَشِيرًا وَنَذِيرًا وَإِن مِنْ أُمَّةٍ إِلَّا خَلَا فِيهَا نَذِيرٌ) فاطر: ٢٤

እኛ አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርገን በእውነት ላክንህ: አስጠንቃቂ (መልዕክተኛ ያልተላከለት አንድም ማኅበረሰብ የለም።›› (ፋጢር 24)

5*ኢማም አህመድ እንደዘገቡት

አዎ፣ ሁሉም ሕዝቦች አምላካዊው መልእክት ደርሷቸዋል። የተከታዩ አንቀጽም ምላሽ ተገኝቷል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

(وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّى نَبْعَثَ رَسُولًا)

«መልዕክተኛን ሳንልክ የምንቀጣ አይደለንም..» (አል ኢስራእ 15)

<u>የማይሞት መልእክት</u>

ብዙ ሰዎች አእምሯቸውን በተከታዩ ጥያቄ ያባክናሉ። መልእክቱ ያልደረሳቸውን ሰዎች አላህ ይቀጣልን?› እነዚህ ወገኖች ጥቂት ማስተንተን ቢችሉ አላህ ማንንም እንደማይበድል ይገነዘቡ ነበር። እንዲህ ብሏል፡-

(وما كنا مُعَذِّبِينَ حَتَّى نَعَت رَسُولاً)

“መልዕክተኛን ሳንልክ የምንቀጣ አይደለንም›› (አል ኢስራእ 15) ነገሩ ቁርጥ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው። አላህ ማንንም ቅንጣት ታክል አይበድልም። ስለዚህ እኛን ሊያሳስበን አይገባም። ይልቅስ ልንጨነቅለት የሚገባ ሌላ ነገር አለ። እርሱም የሚከተለው ነው።

የመጨረሻው ነብይ ተከታዮች መሆናችንን እናውቃለን። ከነቢዩ ሙሐመድ በኋላ ሌላ ነብይ አይላክም። እርሳቸው ደግሞ ሞተዋል። መልእክታቸው ለሰዎች ሳይደርስ ይከስማል ማለት ነውን? በፍጹም። በአላህ እምላለሁ ይህ አይሆንም። የነቢዩን መልእክት ለዓለም እናደርስ ዘንድ ሁላችንም ታዘናል። አላህ እንዲህ ብሏል፡

قُلْ هَذِهِ سَبِيلِي أَدْعُوا إِلَى اللَّهِ عَلَى بَصِيرَةٍ أَنَا وَمَنِ اتَّبَعَنِي وَسُبْحَانَ اللَّهِ وَمَا أَنَا مِنَ

المشركين و

ይህ ጐዳናዬ ነው ወደ እላህ ጥሪ አደርጋለሁ እኔም እኔን የተከተሉ ሁሉም ግልጽ መረጃዎችን ይዘናል። ክብር ለአላህ ይሁን። እኔ ከአጋሪዎች አይደለሁም። በል። (ዩሱፍ 108)

አዎ፣ እውነታው ይህ ነው። ሐላፊነታችንም ይህ ነው። እኔና የተከተለኝ ሁሉ ወደ አላህ በጥበብ እንጠራለን።›

ነቢዩ ሙሐመድ በመሞታቸው የአላህ መልእክት አልሞተም፤ ወደፊትም አይሞትም። ቁጥራቸው አንድ ቢሊዮን ከሩብ የደረሰ ተከታዮቻቸው እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ይህን መልእክት ለዓለማት ያደርሱ ዘንድ ታዘዋልና።

<u>ስድስተኛ፡- ያልተተረኩልን ነብያት</u>

አንዳንድ ሰዎች አላህ የከፊሎችን ነብያት ታሪክ ብቻ ያወሳልን ለምንድን ነው? በማለት ይጠይቃሉ። በእርግጥም ጥሩ ጥያቄ ነው። የአላህ መልእክተኛ በሐዲስ እንደነገሩን የመልእክተኞች ቁጥር 315 ሲሆን በቁርአን የተተረኩልን ግን 45 ብቻ ናቸው። በአል አንዓም ምእራፍ ውስጥ አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَتِلْكَ حُجَّتُنَا أَتَيْنَاهَا إِبْرَاهِيمَ عَلَى قَوْمِهِ تَرْفَعُ دَرَجَاتٍ مِّن نَّشَاءُ إِنَّ رَبَّكَ حَكِيمٌ عَلِيمٌ وَوَهَبْنَا لَهُ إِسْحَقَ وَيَعْقُوبَ كُلًّا هَدَيْنَا وَنُوحًا هَدَيْنَا مِن قَبْلُ وَمِن ذُرِّيَّتِهِ ، دَاوُدَ وَسُلَيْمَنَ وَأَيُّوبَ وَيُوسُفَ وَمُوسَى وَهَرُونَ وَكَذَلِكَ نَجْزِى الْمُحْسِنِينَ وَإِسْمَعِيلَ وَالْيَسَعَ وَزَكَرِيَّا وَيَحْيَى وَعِيسَى وَإِلْيَاسُ كُلٌّ مِنَ الصَّلِحِينَ وَيُونُسَ وَلُوطًا وَكُلًّا فَضَّلْنَا عَلَى الْعَالَمِينَ {

እነዚያ ያመኑትና እምነታቸውን በበደል ያልበከለት ሰላም የነርሱ ብቻ ነው : ቅኑን ጐዳና የተመሩትም እነርሱ ብቻ ናቸው አላቸውም ለኢብራሂም ሕዝቦችን ያስተምርበት ዘንድ) የሰጠነው መረጃ ይህ ነበር የምንሻውን ሰው በደረጃ ከፍ እናደርጋለን። ጌታህ ጥበበኛ ዐዋቂ ነው። ለርሱ ኢስሐቅንና የዕቁብን ሰጠነው ሁሉንም ቅኑን ጐዳና መራናቸው ከርሱ በፊትም ኑሕን መራነው፡ ከዝርያዎቹም ዳውድን፣ ሱለይማንን፣ አዩብን፣ ዩሱፍን፤ ሙሳንና ሃሩንንም (መራናቸው መልካም ሠሪዎችን በዚህ አካሳን እንመነዳለን። ዘከሪያንም የሕያንም፡ ዒሳንም ኢልያስንም እንዲሁ መራናቸው ሁሉም ቅን የአላህ አገልጋዮች ነበሩ። ኢስማዒልም የሰዖንም ዩኑስንም : ሎጥንም (መራናቸው) ሁሉንም ከዓለማት አበለጥናቸው›› (አል አንዓም 83- 86)

እነዚህ አናቅጽ የ18 መልእክተኞችን ስም ይዘዋል። ከላይ ለቀረበው ጥያቄ በተከታዩ አንቀጽ ውስጥ የሰፈረው ምላሽ ይበቃናል።

عَلَيْكَ وَكَلَّمَ اللهُ) وَرُسُلًا قَدْ قَصَصْنَاهُمْ عَلَيْكَ مِن قَبْلُ وَرُسُلًا لَّمْ السناء ُوسَى تَكْلِيمًام

አሁን ቀደም ታሪካቸውን በእርግጥ የዘከርንልህንም ያልዘከርንልህንም (በርካታ) መልዕክተኞች (ልከናል) አላህም ሙሳን

(በቀጥታ) አነጋግሮታል።›› (አል ኒሣእ 164)
‹ያልተረከንልህ› የሚለውን የአላህ ቃል መልእክት ተረዳህን?

<u>ፋይዳ ስለሌለው</u>

ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት ጉዳዩን እናሳጥረው። አላህ የነብያትን ታሪክ የሚተርክልን ከታሪኩ ሊቀሰሙ የሚገባቸው ትምህርቶች ሲኖሩ ብቻ መሆኑን ማወቅ ይገባል። ይህም በመሆኑ ያልተረከልን ነብያት ሕይወት ለኛ ፋይዳ ስለሌለው ወይም ፋይዳው ለነበሩበት ዘመን ብቻ በመሆኑ አላህ ታሪካቸውን አልተረከልንም።

ለአንዳንዶቻችን ይህ መልስ ላያረካን ይችላል። የሌሎችን ነብያት ስም ዝርዝርና የሕይወት ውሎም ካላወቅን ረፍት ላናገኝ እንችላለን። ከውድ ወንድሜ፣ እምነታችንን የሚጨምርልንን ወይም ለዱንያዊ ሕይወታችን የሚጠቅመንን እውቀት አላህ እንደማይነፍገን ተረዳ።

<u>ሰባተኛ፡- ማበላለጥ ይፈቀዳልን?</u>

አንዱን ነብይ ከሌላው ማስበለጥ ይቻላልን? ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ በተሳሳተ መልኩ የሚገነዘቡ ግለሰቦች አሉ፡-

في دَامَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ كُلٌّ مَا مَنَ بِاللَّهِ وَمَكتيكيه، وكيه. وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ، وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ

المصير) البقرة: ١٩٨٥

“መልዕክተኛው (ሙሐመድ ሶ.ዐ.ወ) ከአላህ ወደርሱ በተወረደለት መልዕክት አመነ አማኞችም (እንዲሁ አመነ) ሁሉም በአላህ በመላእክት በመጻሕፍትና በመልዕክተኞች በመካከላቸው ምንም ልዩነት እናደርግም ከፊሎቹን አምነን በከፊሎቹ አናስተባብልም ያሉ ሲሆን፥ አመነ። ጥሪህን ተቀብለናል፤ ለትዕዛዝህ አድረናል። ምሕረትህን እንሻለን። ጌታችን ሆይ! መመለሻም ወደ አንተ ነው አሉ።›› (አል በቀራህ 285)

እናም፦ ‹‹በመልእክተኞች መካከል ልዩነት አናደርግም።›› የሚለውን ቃል እንዲህ ይረዱታል፦
“መልእክተኞችን አንዱን ከሌላው ማበላለጥ አይፈቀድም።››

በእርግጥ ግንዛቢያቸው ስህተት ነው። የአንቀጹ ትርጉም በከፊል ነብያት አምኖ በሌሎች መካድ ከልክል ነው የሚል ነው። አይሁዶች ምን እንዳደረጉ ተመልከት፦

إِنَّ الَّذِينَ يَكْفُرُونَ بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ، وَيُرِيدُونَ أَن يُفَرِّقُوا بَيْنَ اللَّهِ وَرُسُلِهِ وَيَقُولُونَ نُؤْمِنُ بِبَعْضٍ وَنَكْفُرُ بِبَعْضٍ وَيُرِيدُونَ أَن يَتَّخِذُوا بَيْنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا

‹‹እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞቹ የሚክዱ በአላህና በመልዕክተኞቹ መካከልም ልዩነትን ሊያደርጉ የሚሹ በከፊሎች (መልዕክተኞች እናምናለን ከፊሎቹን ግን እናስተባብላለን።” የሚሉ በዚህ (በእምነትና በክህደት) መካከልም (አዲስ) መንገድን ሊያበጁ የሚሹ (አል ኒሣእ 150)

ይህ ማለት ግን ነብያት በደረጃ እኩል ናቸው ማለት አይደለም። አላህ ከፊሉን ከከፊሉ አብልጧል። እንዲህ ሲል እውነት ተናግሯል፦

تِلْكَ الرُّسُلُ فَضَّلْنَا بَعْضَهُمْ عَلَى بَعْضٍ مِنْهُم مَّن كَلَّمَ اللَّهُ وَرَفَعَ بَعْضَهُمْ دَرَجَاتٍ وَءَاتَيْنَا عِيسَى ابْنَ مَرْيَمَ الْبَيِّنَتِ وَأَيَّدَنَهُ بِرُوحِ الْقُدُسِ ›› البقرة: ٢٥٣

ሙሐመድ ሆይ! እነኝህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን ከከፊሉ አስበለጥን። ከመካከላቸው አላህ ያናገረው አለ ከፊሎቹንም በደረጃ ከሌሎች አላቅን።

ለመርየም ልጅ ዒሳ ግልጽ ተአምራትን ሰጠነው፡ በቅዱስ መንፈስም አጠናከርነው›› (አል በቀራህ 253)እንዲህም ብሏል፡

الإسراء: ٥٥

(وَلَقَدْ فَضَّلْنَا بَعضَ النَّبِيِّينَ عَلَى بَعْضٍ وَآتَيْنَا دَاوُدَ زَبُورًا

‹‹ጌታህ በሰማያትም በምድርም ውስጥ ስላሉ ሁሉ) ጠንቅቆ ያውቃል። ከነቢያት ከፊሉን ከከፊሉ አበለጥን ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው› (አል ኢስራእ 55)

በሁሉም ነብያትና መልእክተኞች እናምናለን። በአንዱ አምነን በሌሎች አንክድም። ይህ የእምነታችን አካል ነው። ወዳጃችን ነቢዩ ሙሐመድ የሰው ልጆች ሁሉ አይነታ መሆናቸውንም እናምናለን። ስማቸው ከአላህ ስም ጋር እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የተቆራኘ ሰው እርሳቸው ብቻ ናቸው፡

<u>የአላህ መልእክተኛ ስለራሳቸው ሲናገሩ</u>

በነብያት መካከል የደረጃ ልዩነት መኖሩ እርግጥ ነው። ይህ ከሆነ ከነብያትና ከመልእክተኞች ሁሉ በላጩ ማን ነው? ወዳጃችን ሙሐመድ መሆናቸው ጥርጥር የለውም። እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- ‹‹እኔ የሰው ልጆች ዓይነታ ነኝ። ይህን መግለጼ ለጉራ አይደለም። የምስጋና አርማ በእጄ ነው። ይህን ማለቴም ጉራ አይደለም። በዚያን ቀን አደምና ሌሎች ነብያት በሙሉ በኔ አርማ ስር ይሰለፋሉ። ይህም ጉራ አይደለም። የመጀመሪያው አማላጅና ምልጃውም ቀድሞ ተቀባይነት የሚያገኘው ሰው እኔ ነኝ። የጀነትን በር ከተዘጋበት መጀመሪያ የማንቀሳቅሰው እኔ ነኝ። ከጌታዬ ዘንድ ከመጀመሪያዎቹም ከኋለኞችም የሰው ልጆች ሁሉ በላጩ እኔ ነኝ። ይህን መግለጼም ለጉራ አይደለም።››

የአላህ መልእክተኛ ስለራሳቸው እውነታውን ለማስቀመጥ ከላይ ይህን ተናገሩ። _ ለጉራ ሳይሆን የሰፈረውን ዘከሩ። ሙስሊሙ

6* ቲርሚዚ እንደዘገቡት

ሕብረተሰብ ሆይ፣ የነብያትና መልእክተኞች መቋጫ የሆኑት ነብይ ተከታይ በመሆንህ ደስ ይበልህ።

<u>የነቢዩ ሙሐመድ ቦታ</u>

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَإِذْ أَخَذَ اللَّهُ مِيثَاقَ النَّبِيِّينَ لَمَا آتَيْتُكُم مِن كِتَابٍ وَحِكْمَةٍ ثُمَّ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مُصَدِّقٌ لِمَا مَعَكُمْ لَتُؤْمِنُنَّ بِهِ، وَلَتَنصُرُنَّهُ، قَالَ وَأَقْرَرْتُمْ وَأَخَذْتُمْ عَلَى ذَلِكُمْ إِصْرِى قَالُوا عمران أَقْرَرْنَا قَالَ فَاشْهَدُوا وَأَنَا مَعَكُم مِّنَ الشَّاهِدِينَ))

(የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! አላህ - መጽሐፍንና ጥበብን እሰጣችኋለሁ ከዚያም ከናንተ ጋር ያለውን (መልዕክት የሚያረጋግጥ መልዕክተኛ ይመጣላችኋል እንድታምነብት እንድትረዱትም" በማለት የነቢያትን ቃል ኪዳን በያዘ ጊዜ የሆነውን አስታውስ) ይህንን ቃልኪዳን አፀደቃች ሁን ኪዳኔንም ያዛችሁን? አላቸው አጽድቀናል አለ "እንግዲያውስ መስክሩ እኔም ከናንተው ጋር ከመስካሪዎች ነኝ" አላቸው (አል ዒምራን 81)

ይህም ማለት እያንዳንዱ ነብይ ነብዩ ሙሐመድን ካገኘ እንዲከተላቸው በአላህ ታዟል። እንዲረዳቸው ግዴታ ተጥሎበታል ማለት ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ከአላህ ዘንድ ያላቸው ቦታ ይህን ያህል የተላቀ ነው። ነቢዩ ከአላህ ዘንድ ያላቸው ቦታ ይህ ከሆነ ካንተ ዘንድ ያላቸው ቦታስ? ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሆይ፤ የነብይህን ደረጃና ልቅና አለማወቅህ ትልቅ ነውር ነው።

<u>ስምንተኛ፡- የጽናት ባለቤቶች እነማን ናቸው?</u>

ከመልእክተኞች መካከል የጽናት ባለቤቶች (ዑሉል አዝም) የሚል የማእረግ ስም የተሰጣቸው ነብያት አምስት ሲሆኑ እነርሱም ኑህ፤ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ኢሳና ሙሐመድ ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَإِذْ أَخَذْنَا مِنَ النَّبِيِّنَ مِيثَقَهُمْ وَمِنكَ وَمِن نُوحٍ وَإِبْرَاهِيمَ وَمُوسَى وَعِيسَى أَبْنِ مريم وأَخَذْنَا مِنْهُم مِيثَقًا غَلِيظًا) الأحزاب: ٧

«ከነቢያት ቃል ኪዳንን መያዛችንን (አስታውስ) -ከአንተም፡ ከነሕም፡ ከኢብራሂምም፡ ከሙሳም ከመርየም ልጅ ዒሳም : ከነርሱ የጠበቀ ቃል ኪዳንን ያዝን፡» (አል አህዛብ 7)

በዚህ ስያሜ የተጠሩት ከሌሎች እጅግ የበረታ ትግል እና ጥረት ስላሳዩ ነው። ሙስሊሞች ሆይ፣ የነብያችሁን ውርስ ያዙ። እርሳቸው ከጽናት ባለቤት ነብያት መካከል የመጨረሻው ናቸው። የናንተስ ጽናት ምን ያህል ነው? ጽናት ጀነትን ከምታልም ነፍስ የማይልፈሰፈስ ፍላጎት የሚመነጭ ድንቅ ባህሪ ነው። ስለዚህ ሁለት ረከዓዎችን በሌሊት ለመስገድ፣ ንጋት ላይ አላህን ምህረት ለመለመን፣ እይታህን ለመቆጣጠር አሁኑ ውሳኔ አድርግ። እውነተኛና ዘልዓለማዊ ተውባ ለማድረግም አሁኑኑ ቁረጥ። በውሳኔህ ላይም ጽና።

ስንፍናን እንጅ እንቢ ካልክ፣ መልፈስፈስን እንጅ ካልወደድክ፣ ደካማነትን እንጅ ካልፈቀድክ በዚህ ባህሪህ ምን ትጠቀማለህ? የጽናት ባለቤቶች የሚለው የማእረግ ስም ወኔውን አልቀሰቀሰውምን? ከአላህ ውጭ ለማንም የማያጎበድዱ የግዙፍ ዓላማ ባለቤቶችን ስሜት የሚያቀጣጥል፣ ወኔያቸውን የሚቀሰቅሱ ማእረግ ነው- የጽናት ባለቤቶች (ኡሉል አዝም)። ይህን ሁሉ አሻፈረኝ ካልክ ተከታዩን የአንድ ዓሊም ቃል ላሰማህ፡-

ወኔህ የተልፈሰፈሰ ሆይ፣ የዚህ ሐይማኖት ጎዳና ኑህ ያለቀሱበት፣ ኢብራሂም ወደ እሳት የተወረወሩበት፣ የህያ የታረዱበት፣ ዘከርያ በመጋዝ የተቆረጡበት፣ ሙሐመድ የተንገላቱበት ጎዳና ነው፡ ፡»

አንተ ግን በሌሊት ሁለት ረከዓ መስገድ ይታክትሐል። ወኔህ የት ሚሸሸ? በል ተነስ። የስንፍናን አቧራ አራግፍና መልፈስፈስን ከራስህ አስወግድ። ምክንያቱም እኛ የብርቱ ወኔና ጽናት ባለቤቶች የሆኑ ነብያት ተከታዮች ነንና።።

አዎ፣ የነርሱ ጎዳና የኛም ጎዳና፣ ወኔያቸው ወኒያችን፣ ጽናታቸውም ጽናታችን ነው። አይዞህ፣ በርታ፣

ዘጠነኛ- ነብያት ከሐጢአት የተጠበቁ ናቸውን? ከሐጢአት መጠበቅ ማለት ወንጀል እንዳይሰሩ፣ ከሐጢአት ላይ እንዳይወድቁ የአላህ ጥበቃ ይታደጋቸዋል ማለት ነው። ነብያት ትልቅም ትንሽም ወንጀሎችን አይሰሩም። አላህ ከሐጢአት ሙሉ በሙሉ ጠብቋቸዋል።

እምነታችን ይህ ነው። ነብያት የአላህ ምርጥ ፍጡራን ናቸው። በምድር ላይ እንደነርሱ የጠራና የከበረ ፍጡር የለም። ይህ ከሆነ እንዴት አይጠብቃቸው? ነብያት የኛ አርአያዎች፣ የቅን ጎዳና መሪዎች ናቸው። እናም ከጥፋት እንዴት አይታደጋቸው?

<u>መንታ ምልከታዎች</u>

በአይሁዶች መጽሐፍ ውስጥ ስለነብያት የተጻፉ ነገሮችን ስናነብ በግርምት እንዋጣለን። ሉጥ አስካሪ መጠጥ ጠጥተው በሁለት ሴት ልጆቻቸው ላይ ዝሙት ፈጽመዋል ይላሉ። ዳውድ የጦር አበጋዙን ሚስት አባልጓል ይላሉ። ሱለይማን ጣኦት እያመለከ የሕይወቱ ፍጻሜ ሆኗል ይላሉ። የወይፈን ጣኦት ለእስራኤላውያን የሰራው ሐሩን ነው ይላሉ።

እነዚህን በነብያት ስብእና ላይ የተለጠፉ ቅጥፈቶች ስናነብ እስልምናን የሰጠንን አምላክ እናመሰግናለን። ይህ ዲን ወደር የማይገኝለት ጸጋ መሆኑን እንረዳለን። ቁርአናችን እንዲህ ሲል ያዘናል፡-

أَوْلَئِكَ الَّذِينَ هَدَى اللَّهُ فَبِهُدَاهُمُ اقْتَدِهْ (الأنعام: ٩٠

“እነዚህ አላህ ቅኑን ጐዳና የመራቸው (ነቢያት) ናቸው የነርሱን ቅን መመሪያ ተከተል (አል አንዓም 90)

አይሁዶች የንጹሐን ነብያትን ስም በዚህ መልኩ በማጉደፋቸው አንገረምም። ምክንያቱም የአይሁዶችን ማንነት ጠንቅቀን እናዉቃለንና።

ወዳጆቹንም ከወንጀል የተጠበቁት ነብያት ብቻ ናቸው ወይስ ይህ ጥበቃ ሌሎች ሰዎችንም ይጨምራል? ከወንጀል መጠበቃቸው የተገለጸው ነብያት ብቻ ናቸው። ግና አላህ አንዳንድ ወዳጆቹን ከትልልቅ ወንጀሎች ይጠብቃል። እነሆ አቡበክር ኢማናቸው የኡመቱን ሁሉ ኢማን እንደሚመዝን ተመስክሮላቸዋል። የአላህ መልእክተኛ ዑመርን በተመለከተም እንዲህ ብለዋል፡-

«ዑመር ሆይ፣ በአላህ እምላለሁ፣ አንተ በአንድ መንገድ ብትጓዝ ሰይጣን መንገድ ቀይሮ ይጓዛል።»

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(أَلا إِنَّ أَوْلِيَاءَ اللَّهِ لَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ الَّذِينَ ءَامَنُوا وَكَانُوا يَتَّقُونَ

አዋጅ የአላህ ወዳጆች ፍርሃትም ሐዘንም የለባቸውም። (እነርሱም እነዚያ ያመኑትና (ዘወትርም) ፆጢአትን የሚጠነቀቁት ናቸው» (ዩኑስ63-63)

የአላህ ወዳጆች በአላህ ጥበቃ ስር ያሉ ናቸው። በርሱ ጥበቃ ስር የሆኑትን ደግሞ አላህ ይጠብቃል።

<u>አላህ ላንተ ያደረገው ጥበቃ</u>

ለአንዳንዶቻችን እንደ አየርና እንደ ውሃ የየእለት ቀለባችን ከሆነብን ወንጀሎች አላህ ይጠብቀን ዘንድ የርሱን ወዳጅነት ለማትረፍ እንትጋ፡ ሁላችንም ይህን ደረጃ ለማግኘት እንጓጓ። አላህ ይቅር ይበለን። እርሱን በመታዘዝ ላይም ያጽናን።

7*ቡኻሪና ሙስሊም

የአላህን ጥበቃ በበርካታ ክስተቶች ታየዋለህ፡-

➢ ከታላላቅ ወንጀሎች ሲያድንህ ታየዋለህ።

➢ ከዝሙት ሲያድንህ ታየዋለህ።

➢ አስካሪ መጠጥ ከመጠጣት ሲያድንህ ታየዋለህ። ልባች

➢ የወላጆችህን መብት ከመጣስ ሲታደግህ ታየዋለህ።

➢ ሶላትን ከመተው ሲጠብቅህ ታየዋለህ። ስብሰ

ትልቁ ጥበቃው ግን ቀልብን ከከንቱ ስሜት መጠበቁ ነው። ሰውየው ከአላህ ጋር ግንኙነቱ ሳይቋረጥ፣ እርሱን ብቻ እያየ፣ ንግግሩን ብቻ እየሰማ፣ እርሱ የሚወደውን ብቻ እየሰራ ሕይወቱን መምራቱ ነው።

<u>ስጦታዬን ተቀበሉኝ</u>

ያለ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ወይም ፈቃድ ልቤን ሰንጥቆ የገባ አንድ ዱዓ አለ። በዓረፋ ቀን አንድ ሰው እንዲህ በማለት አላህን ሲማጸን ሰማሁት፡-

«አላህ ሆይ፣ ይህችን ሐጅ የታላላቅ ወንጀሎቹ ፍጻሜ አድርግልኝ።»

ይህን እያለ እንባው የዓይኖቹን ግድብ ጥሶ በጉንጮቹ ላይ ይንቆረቆራል። ሰውየውን አላውቀውም። ዱዓው ግን ልቤን ነካኝ። እናም ይህችን መልእክት ለናንተ በስጦታ መልክ አበረከትኩላችሁ። እባካችሁን ስጦታዬን ተቀበሉኝ። ከታላላቅ ወንጀሎች ይጠብቀን ዘንድ አላህን አብረን እንለምነው፡-

«አላህ ሆይ፣ ከታላላቅ ወንጀሎች ጠብቀን። አላህ ሆይ፣ በትንንሽ ወንጀሎች ላይ ከመዘውተርም ጠብቀን።»

ከመዘውተር ጋር ትንሽ ወንጀል፣ ምህረት ከመለመን ጋር ትልቅ ወንጀል እንደሌለው እወቁ።

<u>የፍጥረታት ጅማሬ</u>

ከአደም በፊት የነበረው የፍጥረታት ጅማሬ ልቦናን ያርገፈግፋል። ይህን አጀንዳ ለመቃኘት አቅም እንዲሰጠን፣ ከችሮታው እንዲለግሰን አላህን እለምናለሁ። እናንተም በንጹህ ልቦና ትቀበሉኝ ዘንድ እንዲያስችላችሁ እማጸነዋለሁ።

የፍጥረታት ጅማሬ ታሪክ የደረቀ ቀልብን ያለዝባል። የጠጠረውን ያለሰልሳል። ቀልቦች በአላህ ፈቃድ በጎ ምላሽ ይሰጡታል። ግና አንድ መስፈርት መሟላቱ የግድ ነው። እርሱም ታሪኩን በአግባቡ መቀበልና ማስተናገድ መቻል ነው።

ኑ፣ ከፍጡራን መገኘት በፊት፣ ከነብያት፣ ከአደም በፊት፣ ከሰማያትና ከምድር በፊት የነበረውን እውነታ አብረን እንቃኝ።

<u>አላህ ብቻውን ነበር</u>

ከአደም፣ ከመላእክት ፣ ከጅን፣ ከነብያት፣ ከሰማያትና ከምድር፣ ከዳመናዎች፣ ከአሸዋው፣ ከባህሮች፣ ከሁሉ ነገር በፊት ምን ነበር? አንደበቶች በአንድ ድምጽ እንዲህ በማለት ምላሽ ይሰጣሉ፡-
አላህ ብቻውን ነበር።።»

ሁሉም ልቦች ሊያውቁት የሚገባ እውነታ፣ ሊሰርጻቸው የሚገባ መልእክት፣ ይህ ግንዛቤ እምነትን ያጸናል። ከአላህ ታላቅነትና ልእልና ጋር ያስተዋውቃል። ደካማ ማንነታችንን ከዚህ ልእልና ጋር ስናነጻጽረው እጅግ አንሶ ይታየናል። በእርግጥም _ ኢምንት _ ብልሐትም ሐይልም እንደሌለን ይሰማናል። በእርግጥም የአላህን ማንነት በወጉ አላወቅንም። ልእልናውን አልተረዳንም። እንዲህ ሲል እውነትን ተናግሯል፡-

وما قدروا اللهَ حَنَّ قدرِيه (الأنعام:

ባሎ ጊዜ ለአላህ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም። (አል አንዓም 91) እንዲህም ብሏል፡-

هُوَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَوتِ وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ اسْتَوَى عَلَى الْعَرْشِ يَعْلَمُ مَا يَلِجُ فِي الْأَرْضِ وَمَا يَخْرُجُ مِنْهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ السَّمَاءِ وَمَا يَعْرُجُ فِيهَا وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ وَاللَّهُ بِمَا

تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ) الجديد: ٥٧٢٤

«እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት የፈጠረ፣ ከዚያም ከዙፋኑ ላይ የተደላደለ አምላክ ነው ወደ ምድር የሚገባውን፣ ከርሷ የሚወጣውንም ከሰማይ የሚወርደውን፣ ወደርሷ የሚዘልቀውንም (ጠንቅቆ) ያውቃል። እርሱ የትም ብትሆኑ ከናንተው ጋር ነው አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው» (አል ሐዲድ 4)

ይህን አንቀጽ በጥሞና አንብበህው፣ መልእክቱን ተረድተህው ከሆነ አንዳች ስሜት ውስጥህን ይቆጣጠረዋል። ጥልቅ ትንፋሽም ትተነፍሳለህ። «ከአላህ ሌላ አምላክ የለም። _ በማለትም ከልብህ ትመሰክራለህ። በእርግጥ ሁሉም ሰው ይህ ላይሰማው ይችላል። ምክንያቱም ከአላህ ቃል ጋር ያለን ግንኙነት ተመሳሳይ አይደለምና።

ርእሰ ጉዳያችን የፍጥረታት ጅማሬ መሆኑን አልዘነጋንም። «ያኔ አላህ ብቻውን ነበር።» በሚለው ሐረግ ሊጠቃለል ይችላል። ይህ ሐረግ ያዘለው ጥልቅ መልእክት ልቦናን በአላህ ታላቅነት ይሞላል።

ይህን ጥልቅ መልእክት ለማስተንተን ራስህን አዘጋጅ። በዙሪያህ የምታየው ነገር ሁሉ፣ እንስሳት፣ እጽዋት፣ ሰዎች፣ ጨረቃ፣ ጸሐይ፣ አስደናቂ የቴክኖሎጂ ግኝቶች፣ እነዚህ ሁሉ ያኔ አልነበራቸውም። አላህ ብቻውን ነበር። ሕልውና

<u>አምላካችን የት ነበር?</u>

ኢማም አህመድና ቢን ማጃህ እንደዘገቡት አንድ ሶሐባ ለነቢዩ አምላካችን ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የት ነበር?» በማለት ጠየቃቸው። «አእምሮ ሊረዳው በሚችለው ሁኔታ ውስጥ ነበር። ምንም ነገር አብሮት አልነበረም።» በማለት መለሱ።

ይህ ትልቅ እውነታ ነው። እኛ ለዚህ ዩኒቨርስ አዲሶች ነን። የጥንት አድርጎ የሚቆጥረን ተሳስቷል። በፍጹም፣ ሁላችንም እንደምናውቀው የዚህች ምድር መጤዎች እንጅ ባለቤቶች አይደለንም።

ስለዚህም የፍጡራን ሁሉ ባለቤት የሆነውን አላህን እንሻለን። ‹ዓማእ› የሚለው የሐዲስ ቃል አእምሮ ሊረዳው የማይችለው፣ ሊያስበው የሚቸግረው ነገር ነው። አላህ ብቻውን ነበር።

በእርግጥ አእምሮ ይህን እውነታ የመረዳት አቅም የለውም። ክሕሎት ያንሰዋል። አንድ ብርጭቆ የባህርን ውሃ በውስጡ ማካተት ይቻለዋልን?

ጅማሬ ዑምራን ቢን ሁሰይን እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

ከየመን አንድ ልዑክ ወደ አላህ መልእክተኛ ዘንድ መጣና፡- የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ሐይማኖታችንን ለማወቅ መጥተናል። የዚህን ጉዳይ መጀመሪያ ንገረን› አሏቸው። እርሳቸውም እንዲህ ሲሉ መለሱ፡-

‹መጀመሪያ አላህ ብቻ ነበር። ከርሱ ጋር ሌላ ነገር አልነበረም። ከርሱ በፊትም ምንም ነገር አልነበረም።

ወንድሜ ሆይ፣ ይህን ሐዲስ አስተውል። ‹‹አላህ ብቻውን ነበር።›› የሚለውን መልእክት አስተንትን። ወደኋላ ብዙ ዘመናት ተመለስ እና ያኔ የነበረውን ሁኔታ ለመረዳት ሞክር። ከዚያም ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ አንብብ።

هَلْ أتى على الإنسَانِ حِينٌ مِنَ الدَّهْرِ لَمْ يَكُن شَيْئًا مذكورًا) الإنسان : ١ የሰው ልጅ የሚታወስ ሳይሆን (ሕልውና ሳይኖረው ረዥም ዘመን ተቆጥሯል። (አልኢንሳን ፣)

አስተንትን ስልህ ማለት የፈለግኩትን ተረዳህልኝን? እኛ ያልነበርንበትን ቀን አስታውስህ ታውቃለህ? በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል ሞክር። ከዚያ በኋላ አላህ አስገኘን። የመኖርን ጸጋም ለገሰን። ታዲያ የሕልውናችን

ምንጭ በሆነው አላህ ላይ እንዴት እንኮራለን? ባስገኘህ አምላክ ሩኩእና ሱጁድ አለማድረግህ ኩራት እንደሆነ አይሰማህምን?

በልቦና ውስጥ ሊኖር የሚገባው እውነታ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَمَا قَدَرُوا اللهَ حَقَّ قَدْرِهِ، وَالْأَرْضُ جَمِيعًا قَبَضَتُهُ، يَوْمَ الْقِيّمَةِ وَالسَّمَوَاتُ

مَطْوِيَت بِيَمِينِهِ، سُبْحَنَهُ وَتَعَالَى عَمَّا يُشْرِكُونَ) ››(
አጋሪዎች) ለአላህ በዕለተ ትንሳኤ መሬት ባጠቃላይ በጭብጡ (አንድ ጭብጥ) ሰማያትም በኃይሉ የሚጠቀለሉ ሆነው እያለ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም እርሱ ከሚያጋሩት ሁሉ የላቀ ነው›› (አል ዙመር 67)

يَوْمَ نَطْوِي السَّمَاءَ كَطَيّ السّجل للكتب كَمَا بَدَأْنَا أَوَّلَ خَلْقٍ نُعِيدُهُ وَعْدًا عَلَيْنَا إِنَّا كُنَّا فَعِلِينَ) الأنبياء: ›› ١٠٤
ሰማይን እንደመጽሐፍ ገጾች በምንጠቀልል ቀን (የሚሆነውን አስታውስ)። መጀመሪያ እንደፈጠርነው (ዳግም) እንመልሰዋለን። (ይህ) የገባነው ቃል ኪዳን ነው፡ እኛ (ይህን ቃልኪዳን) በእርግጥም ፈጻሚዎች ነን።›› (አል አንቢያእ 104)

እውነተኛ አንበሳ አምጥተን ነፍስ ካላወቀ አንድ ሕጻን አጠገብ ብናስቀምጠው ሕጻነ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ታውቃለህ? ምን አልባትም ከአንበሳው ጋር ይጫወታል። እጆቹንም ወደ አፉ ሊከት ይችላል። አይፈራውም። ምክንያቱም ትክክለኛ ማንነቱን አያውቅምና።

وَمَا قَدَرُوا اللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِ

“ተገቢውን ክብር አልሰጡትም› (አል ዙመር 67)

ጤነኛ አእምሮ ያለው ትልቅ ሰው ግን የአንበሳን ምንነት ስለሚያውቅ ይፈራል። እኛም አላህን ስለማናውቀው አንፈራውም። ትክክለኛውን እውቀት እርሱው ይለግሰን።

ውድ ወንድሜ ሆይ፣ አውነታዎች በምላስ የተነጋገም ብቻ በቀይና ላይ : አይጸም። ከቀልብ ውስጥ የሚያገናቸው በር ማመንና ወደተግባር መለወጥ ብቻ ነው።

<u>ሚንበሩ ተርገፈገፈ</u>

አብደላህ ቢን ዑመር እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡- አንድ ቀን ወይ ሚንበር ላይ ወጥተው በከፍተኛ ይዝ እንዲህ በማለት ሲናገሩ አየኋቸው፡-

وَمَا رُوا الله رب وَالْأَرْضُ جَمِيعًا فَصَنُّهُ يَوْمَ الْقِيَمَةِ وَالسَّمَوَاتُ

‹‹አጋሪዎች ለአላህ በዕለተ ትንሳኤ መሬት ባጠቃላይ በጭብ አንድ ጭብጥ, ሰማያትም በኃይሉ የሚጠቀለሉ ሆነው እያለ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም እርሱ ከሚያጋሩት ሁሉ የላቀ ነው (አል ዙመር 67)

ከዚያም ድምጻቸው ይበልጥ ተጠሙ። በጃቸው እየመከሩም እንዲህ አሉ፡-

“አላህ ራሱን ያሞግሳል። ንስ እኔ ብቻ ነኝ። ኩሩ እኔ ብቻ ነ ሐያል እኔ ብቻ ነኝ። አሸናፊው እኔ ብቻ ነኝ። አስተናባሪ እኔ ብቻ ነ የመጀመሪያው እኔ ነኝ። የመጨረሻውም እኔ ነኝ ይላል።

መልእክተኛው የአላህን መልካም ስሞችና ባህሪያት መንጋቸውን ቀጠሉ። የቆመበት ሚንበርም ሲርገፈገፍ አየሁት።

እንጨቱ በአላህ ልእልና ተናጠ። ለክብሩ ተንቀጠቀጠ። እርሱን በመፍራት ራ። የአንዳንድ የሰው ልጆች ልቦናዎች ግን ይህን መልእክት እያነበቡ ከአለት በጠጠረ ባህሪያቸው ቀጥለዋል። ግዑዙ ስሜቱ ሲነካ እነርሱ ግን እንደየፊቱ ቀርተዋል።

8*ቡኻሪና ሙስሊም

የሙስሊሞችን ቀልቦች ምን አገኛቸው? ይህ እውነተኛ ስሜት እንዳይደርሳቸው እንቅፋት የሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው? ለዚህ የስ መደነዝስ ምክንያቱ ማን ነው?

አላህን በማውሳት ከዓይኖች በፊት ያለቅሱ የነበሩ ቀልቦች አሁን አሁን አስገራሚ የጭካኔ ተግባር ሲፈጽሙ፣ የወላጆችን መብት ሲጥሉ ሂጃብን አሻፈረን ሲሉ፣ ሶላትን ሲያዘገዩ ማየት በእጅጉ ያሳስባል። ግሉዙ ሚንበር እንኳ ስሜቱ ተነክቶ በፍርሃት ሲርገፈገፍ እነርሱ የደነዘዙበት ሰበብ ምንድን ነው? ምን ችግር አገኛቸው? ምን እንከን ገጠማቸውን የሙስሊሞች ቀልቦች ሆይ፣ ሚንበሩ ተርገፍግፏል። የናንተ ተራስ አልደረሰምን?

<u>ጅማሬና ፍጻሜ</u>

ጅማሬው እንደዚህ ነበር። አላህ ብቻውን ነበር። ከርሱ ጋር ምንም ነገር አልነበረም። ፍጻሜውስ በእንዴት እንደሚሆን አስበህ ታውቃለህን? ከዚያ በፊት ምድርን በእንቅስቃሴ፣ በእውቀትና በስራ የሞላትን የሰው ልጅ ሁኔታ እንመለከታለን። አንዳንዶቻችን ምድርን እንደ ትንሽ መንደር እንቆጥራታለን። በእርግጥም ወደዚያ የተቀየረች ትመስላለች። የሰው ልጅ ፍጥረተ ዓለሙን የተቆጣጠረ ያህል ይሰማዋል። እዚህ ላይ የፍጻሜው ትእይንት ይመጣል። የዩኒቨርሱ እውነተኛ ባለቤት ከሆነው አምላክ የተላለፈ ቁርጥ ውሳኔ ነው። እንዲህ ሲል አውጇል።

وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِي السَّمَوَاتِ وَمَن فِي الْأَرْضِ إِلَّا مَن شَاءَ اللَّهُ ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ الْقرى فَإِذَا هُم قِيَام يَنظُرُونَ))

በቀንዱ ይነፋል። በሰማያትና በምድር ውስጥ ያሉ ሁሉም በድንጋጤ ይሞታሉ አላህ (ከሕልፊት ይጠበቁ ዘንድ) የፊቀደላቸው ሲቀሩ ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ ይነፋል፡ ወዲያውኑም እነርሱ (ሙታን ከየመቃብሮቻቸው) የቆሙና (የሚታዘዙትን) የሚጠባበቁ ይሆናሉ (አል ዙመር 68)

የሰው ልጅ፣ ደካማ ፍጡር፣ ሁሉም ነገር በእጁ ያለ ይመስለዋል። ግና የምንም ነገር ባለቤት አይደለም። ይህን ዘነጋህን? ጊዜያዊ ነዋሪ መሆንህን አታስታውስም? እንግዲያውስ ከእንቅልፍህ ንቃ። የነገሮች ባለቤት አንተ አይደለህም። እውነተኛ ባለቤታቸው አላህ ነው። በምድር ላይ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለብህ የሚወስነው እርሱ ብቻ ነው።

ክብር ለአላህ ይሁን። ይህ ዩኒቨርስ ወደ አደም አካል በተነፋ መንፈስ ተጀመረ። በቀንዱ መነፋትም ይጠናቀቃል። ይህች ዓለም በመነፋት ተወጥና በመነፋት ፍጻሜ ታገኛለች። የትንኝ ክንፍ ያህል እንኳ የጋና ክብደት የሌላት ደካማ ነገር ናት።

ከሁሉ ነገር በፊት ምን ነበር? የነገሮች ሁሉ ባለቤት ማን ነው? ሕያው አድራጊና ገዳይ ማን ነው? መጀመሪያ ያስገኘና ዳግም የሚመልስ ማን ነው? ይህን አስታውስ። የራስህን ማንንትም አስታውስ።

<u>ከዝንጋታ የሚያላቅቅ ጥያቄ</u>

በመጨረሻ መነፋት ጊዜ በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉት ሁሉ ራሳቸውን ስተው ይወድቃሉ። ይህ አወዳደቅ እንዴት እንደሆነ አስብ። ሁሉም ይወድቃሉ። እንስሳዎች፣ በራሪዎች፤ ሰዎች፣ አጋንንቶች፣ መላኢኮች፣ ሁሉም ነገር ይጠፋል። ሁሉም ነገር ይንኮታኮታል።

ከዚያም አላህ ለሞት መላእክ፡- ብሕይወት የቀረ ማን አለ?›› ሲል ይጠይቀዋል። የሞት መላክም፡ - ሚካኤል፣ ጅብሪል፣ ሱራፌልና ባሪያህ የሞት መላእክ ብቻ ቀርተዋል።› ሲል ይመልሳል። «የሱራፊልን ነፍስ አውጣ ይለዋል። ያወጣል። ‹ሌላ የቀረ አለን» ሲልም ይጠይቀዋል። «ሚካኤል፣ ጅብሪል እና እኔ ብቻ ቀርተናል› ሲል ይመልሳል። «እንግዲያውስ የሚካኤልን ነፍስ አውጣ ይለዋል። ያወጣል።

አንተ ሙስሊም ሆይ፤ ወንጀልህን አስታውስ። ዝንጋቱህን አስታውስ። ግዴለሽነትህን አስታውስ፣ ዝርክርክነትህን እና ሐጢአትህን አስታውስ።

አላህ ጥያቄውን በመቀጠል፡- የሞት መላእክ ሆይ፣ ማን ቀረ? ሲሉ ይጠይቀዋል። ‹‹ጅብሪልና እኔ አገልጋይህ ሲል ይመልሳል። አላህም የጅብሪልን ነፍስ አውጣ ይለዋል። ያወጣል። ‹‹አሁንስ ማን ቀረ ሲል ይጠይቀዋል። ‹አገልጋይህ የሞት መላእክ ብቻ ቀርቷል›› በማለት ይመልሳል። የራስህን ነፍስ አውጣ ሲል ያዘዋል። የሞት መላእክ የራሱን ነፍስ ለማውጣት ትግል ይጀምራል። ተሳክቶለትም ያወጣታል። ከዚያም የአላህ አዋጅ ይሰማል።

ሁላችንም ይህን አዋጅ እንስማ። ዝንጉዎች፣ ወንጀለኞች፣ ግዴለሾች≥ ሁሉ ነቅተን እናድምጥ። ቀልቦቻችን | ለዓመታት ከተቆጣጠሯች ሽህዋዎች ራሳቸውን ነጻ አድርገው በጥሞና ያድምጡ። አላህ እንዲህ ሲል ይጣራል፡-

‹‹ዛሬ ንግስና የማን ነው› (አል ጋፊር 16

እንዲህ ሲል ይመልሳል፡-

-አንድና አሸናፊ ለሆነው አላህ ብቻ ነው።›› (አል ጋፊር 6 ንጉሳን የት አሉ? አምባገነኖች የታሉ? ሹማምንት የታሉ?

ነቢዩ ሙሐመድ እንዲህ ብለዋል፡-

“አላህ ዛሬ ንግስና አሸናፊና ብቸኛ ለሆነው አላህ ብቻ ነው፣ እያለ ለአርባ ይቆያል። አርባ ምን? አርባ ቀን አርባ ወር? አርባ አመታት . አልተገለጸም። ምክንያቱም ያኔ ዘመን ትርጉም ያጣል። ከስሌት ውጭ ይሆናል።

‹ዛሬ ንግስና የማን ነው›› ይህን ጥያቄ መስማት ልቦናን ያርገፈፋል። ቀልብን በፍርሃት ያርዳል። ውስጥን ያንቀጠቅጣል። የዝንጉነትን ሰራዊት የሚያፈርስ በጎ ተጽእኖ እንደሚኖረው እንገምታለን።

<u>ማንነትህ</u>

ጅማሬው እንዴት እንደነበር፣ ፍጻሜውም እንዴት እንደሚሆን አይተናል። በመጀመሪያም በመጨረሻም አላህ ብቻውን እንደሚሆን

አውቀናል። አል አወሉ (የመጀመሪያውና አል አኺሩ (የመጨረሻው) የሚሉት የአላህ ስሞች ትርጉም ይህ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

سَبَّحَ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ (لَهُ مُلْكُ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ بحي.

(وَمِن وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرُ ‹በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉ ሁሉ የአላህን ክብርና ልዕልና መሰከሩ። እርሱ ኃያልና ጥበበኛ ነው። የሰማያትም የምድርም ንግስና የርሱ ብቻ ነው ሕይወትን ይለግሳል ይነፍጋልም። እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነው።›› (አል ሐዲድ 1-2)

(الجديد هُوَ الْأَوَّلُ وَالْآخِرُ وَالظَّهِرُ وَالْبَاطِنُ وَهُوَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمُ ‹‹እርሱ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም፡ ግልጽም ስውርም ነው። ሁሉንም ነገር ዐዋቂም ነው›› (አል ሐዲድ 3)

ነቢዩም እንዲህ ሲሉ ዱዓ አድርገዋል፡-

‹የሰማያትና የምድር ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ፣ የሁሉም ነገር ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ፣ የመጀመሪያው አንተ ነህ። ካንተ በፊት ምንም ነገር የለም። የመጨረሻውም አንተ ነህ። ካንተ በኋላ ምንም ነገር የለም፡ ፡ ግልጽ ነህ። ካንተ በላይ ምንም ነገር የለም። ስውር ነህ። ካንተ ባሻገር ምንም ነገር የለም።››9

ከላይ የሰፈረው መልእክት እምነትን ያጸናል። መልካም ፍሬ የሚያፈራ የኢማን ችግኝ ከልቦና ላይ ይተክላል። አዎ፣ ከዚህ ቀደም እንዳብራራነው የኢማን ታሪኮችን የመተረክ ዓላማ ኢማንን በልቦና ውስጥ ማስረጽና ማጽናት ነው። አላህ የመጀመሪያው እና ከርሱ በፊት ምንም ነገር የሌለ፣ የመጨረሻውና ከርሱ በኋላ ምንም ነገር የሌለ፣ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ፣ ሁሉንም ነገር የሚችል፣ መጀመሪያ ያስገኘ፣ በኋላም የሚመልስ መሆኑን ማወቅህ በእርግጥም አንዳች

9*ሙስሊምና ቲርሚዚ

የኢማን ስሜት ወደ ውስጥ ማስረጹ አይቀሬ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል።

وَهُوَ الَّذِي يَبْدُوا الخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ، وهو أهون عليه الروم

እርሱ ፍጡራንን ከምንም የሚያስገኝ ከዚያም የሚመልሳችሁ

(አምላክ) ነው ይህ ሰር እጅግ ቀላል ተግባር ነው ›› (አል ሩም 27

أولَمْ يَرَوْا كَيْفَ يُبْدِى اللَّهُ الخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ إِنَّ ذَلِكَ عَلَى اللهِ بَسِير الم

“አላህ መፍጠርን እንዴት እንደሚጀምር፣ ከዚያም (እንዴት እንደሚመ ልሳቸው አላዩምን? ይህ ለአላህ እጅግ በጣም ቀላል ነው›› (አል አንከቡት 19)

አእምሮ ስለ ሰው ልጅ በጥሞና ሲያስብ የሰው ልጅ በራሱ አንዳች የማድረግ አቅም የሌለው፣ ሌላ አካል ባሰመረው መስመር የሚጓዝ ደካማና ሚስኪን ሆኖ ያገኘዋል። ይህም ሆኖ ግን በዚህች አለም ውስጥ ያሻውን መርጦ እንዲሰራ አላህ አእምሮንና ነጻ ፈቃድን ለገሰው። ሊሳሳት እንደሚችል እያወቀ ይህን አደረገ። በሶ በግ

<u>አእምሮዎች የት ደረሱ?</u>

አላህ እንዲህ ይላል፡-

أَمْ خُلِقُوا مِنْ غَيْرِ شَيْءٍ أَمْ هُمُ الْخَالِقُونَ (3) أَمْ خَلَقُوا السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضَ بَل لَّا يُوقِنُونَ) أَمْ عِندَهُمْ خَزَائِنُ رَبِّكَ أَمْ هُمُ الْمُسَيْطِرُونَ))

"ከምንም ነው የተፈጠሩት? ወይስ እነርሱ ራሳቸውን ፈጣሪዎች ናቸው? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጥረዋል? አይደለም፡ በእውነቱ እነርሱ ጽኑ እምነት የላቸውም የጌታህ ግምጃ ቤቶች ከነርሱ ዘንድ ናቸው? ወይስ በነርሱ ላይ የተቆጣጣሪነት ሥልጣን አላቸው? (አፈጡር 35-37)

እነዚህ አናቅጽ ለመጀመሪያ ጊዜ ስናነባቸው ቀልብን ይቆጣጠራሉ። ቀልብ አንደበት ቢኖራትና ብትናገር ኖሮ፡- አእምሮህ የት ደረሰ?

አምላከ እንዴት ዘነጋህ? ቀልቦች ለምን ደረቁ?» በማለት ትጠይቅ ነበር።

ወይስ ፈጣሪዎች እነርሱ ናቸውን ወይስ ተቆጣጣሪዎች እነርሱ ናቸው? የሚሉትን የአላህ ቃላት አስተውል። ከላይ የተሰጠው መግቢያ የስው ፍጥም ሐያል ከሆነው አምላክ አንጻር ደካማነትህ፣ ክቡር ከሆነው አምላክ ፊት ወረዳነት ከባለጸጋው አምላክ ፊት ድህነትህ ሃሪማ ከንን የማደረግ ው። አላህ ብቻውን ነበር።።» የሚለውን መልእክት ትጥበብ ዘንደ ነው።

ከሁሉም ወንጀሎች መገላገል

ስሜቶችን ለመሥማት፤ ቀልቦችን ለማለስለስና ከታላቁ አምላክ አንጻር መጠን ምንነት እንደትረዳ ለማድረግ ከላይ ያስቀመጥነውን መንገርጋሪያ አፍረናል። ከዚህ በተለየ አኳኋን ልናናግራቸው የሚገባ የዎች ግን አለ።

ተቃራኒ ጌታ ከማካሄድ፣ አስካሪ መጠጥ ከመጠጣትና አደንዛዥ እጽ ከመጠቀም ባሻገር በ ጎላማ የሌላቸው ብዙ ወጣቶች አሁንም በነበሩበት ሁኔታ ይጥ ናቸው። በነርሱ የሕይወታቸውን አቅጣጫ የሚቀይር መደሰት ለን። ሄሞግን ከፍ አድርጌ እንዲህ እመክራቸዋለሁ፡-

ወዳጆች ሆይ፣ ከዚህ ሁሉ ወንጀሎች መገላገል ትችላላችሁ» እላቸዋለህ። ኢብንል ቀይም እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

ወደ አላህ የምትገባበት ትልቁ በር : አላህን የመከጀልና ሰርሱ የመዳና በር ነው። ሰዎቹ ወደ አላህ የምትገባበት ትልቅ በርና ብለው ሰይዳ አላህን መከጀልና ለርሱ መተናነስ ነው።። ነቢዩ ያደረጉትን ተከታየን ዱዓ አስተውል።

አላህ ሆይ፤ ባሪያ ሆና የባሪያህ ልጅ ነኝ፡እናቴ በእጅህ ነው። ፍርድህ በላይ ተማሪ ነው፤ብ ላይ የምታስተላልፈው ውሳኔ ፍትሃዊ ነዉ፡

በአላህ ፍቅር የተሞላ ቀልብ ይህን ዱዓ ሊያመነጭ ይችላልን? በአላህ ለም፤ ይህ በአላህ ፍቅር ሲሞላ ራስህን ትረሳለህ። እውነተኛ

አምልኮ' ፍጹም መንፈሳዊነት እና በአላህ የመመካት ስሜት ከውስጥ። ይነግሳል።

<u>የሚገርም አገላለጽ</u>

የኢስራእና የሚእራጅ ቀን ጅብሪል የነበረበትን ሁኔታ የአላህ መልእክተኛ እንዴት እንደገለጹት አስተውል፡

‹የሚእራጅ ቀን ጅብሪልን ከአላህ ፍርሃት የተነሳ እንደነተበ ጨርቅ ሆኖ አየሁት። ጅብሪል በአላህ ፍርሃት እንዲህ ተናንሶ አይተውታል። ጅብሪል መላኢካ መሆኑን እንዳንዘነጋ። ለዚያውም የመላኢኮች ሁሉ አውራ።

ታማኙ መንፈስ የጅብሪል ሁኔታና ድርጊት አላህ ከርሱ ዘንድ ያለውን ቦታ ያመለክታል። ለአላህ ክብርና ደረጃ መስጠትን ከጅብሪል ተማር። ይህ የፍርሃት ስሜት ከአካሉ ላይ እንዴት እንደተንጸባረቀ አስተውል። ከታላቁ ጌታው ፊት ፍጹም ተነሰ።

<u>ለዚህስ አልተፈጠርንም</u>

አላህ የፈጠረን በብቸኝነት እናመልከው ዘንድ ብቻ፡-

م وَمَا خَلَقْتُ الجن والإنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ) .
‹አጋንንትንም ሰዎችንም ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።› (አል ዛሪያት 56)

እናውቀው ዘንድም ፈጠረን። አላህን ማወቅ የሕልውና መሠረት ነው።

እንረዳው ዘንድም ፈጠረን። ስለዚህም አላህ የፈጠረን እንድንበላ፤ እንድንጠጣ፤ እንድናገባ፣ እንድንወልድና በመጨረሻም እንድንሞት እንደሆነ አድርጎ ያሰበ ተሳስቷል።

አላህ የሰውንልጅ አእምሮ በመስጠት አልቆታል። ከዚህ ልቅና በኋላ ውርደትን ይሻልን? ይህ ከሆነ በርሱና በእንስሳት መካከል ያለው ልዩነት

ምንድን ነው? እንስሳትም እኮ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ ይጋባሉ፣ ይወልዳሉ፣ በመጨረሻም ይሞታሉ፣ ከዚህም አልፈው የአላህን ክብር ይገልጻሉ፡-

نسبحُ لَهُ السَّمَوَتُ السَّبْعُ وَالْأَرْضُ وَمَن فِيهِنَّ وَإِن مِن شَيْءٍ إِلَّا يُسَبِّحُ بِحَمْدِهِ، وَلَكِن لَّا نَفْقَهُونَ تَسْبِيحَهُمْ إِنَّهُ كَانَ حَلِيمًا غَفُورًا)

‹ሰባቱ ሰማያትና ምድር እንዲሁ ከውስጣቸው ያሉ (ፍጡራን) ሁሉ ያወድሱታል። እርሱን የማያወድስና የማያመሰግን አንድም ነገር የለም: ይሁንና ውዳሴያቸውን አትረዱም። እርሱ ቻይና መሓሪ ነው›› (አል ኢስራእ 44)

<u>አልጀይላኒ በሩን ያመላክቱሐል</u>

አብዱል ቃድር ጀይላኒ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- ‹‹ወደ አላህ የሚያደርሱ በሮችን ሁሉ ቃኘሁ። እያንዳንዱ በርም በሰዎች ተሞልቶ አገኘሁት። ወደ ሶላት በር ስሄድ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገቡበት አየሁ። ወደ ጾም በር ስሄድም ሺዎች ሲገቡበት አየሁ። ወደ መተናነስ በር ስሄድ ግን ባዶ ሆኖ አገኘሁት። በርሱ በኩል ገባሁ። ሌሎችንም ሰዎች ወደርሱ ጠራኋቸው።››

ጀይላኒ ሁሉንም በሮች አንኳኩ። ሁሉም በሰዎች ተሞልተው አገኟቸው፣ ፡ የመተናነስ በር ግን ባዶ ነበር። በርሱ በኩል ገቡ። እኛስ ያንኳኳነው በር የትኛው ነው?

አምላኬ ሆይ፣ የድሆችን ልመና እለምንሐለሁ። የደካሞችን መማጸን እማጸንሐለሁ። የወንጀለኞችን ለቅሶ አለቅስብሐለሁ። ወንጀሉ በዝቶ፣ ብልሐቱ አንሶና መከራው በርክቶ አንተን የሚማጸንህን ሰው ተማጽኖ አቀርብልሐለሁ። አምላኬ ሆይ፣ ጠንካራው አንተ ነህ። እኔ ግን ደካማ ነኝ። ባለጸጋው አንተ ነህ። እኔ ግን ድሀ ነኝ። ታላቅ አንተ ነህ። እኔ ግን ላንተ የተዋረድኩ ነኝ። አምላኬ ሆይ አንተ ከኔ ውጭ ብዙ ባሮች ሲኖሩህ እኔ ግን ካንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለኝም።

ልእልናን ለሚያልሙ ነፍሶች

መጀመሪያ የተፈጠረው ፍጡር በአላህ ፈቃድ በጀነት ውስጥ የምናየው የአላህ ዓርሽ ነው። አንድ ልዑክ ከአላህ መልእክተኛ ዘንድ በመምጣት፣ «የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የመጀመሪያው ማን ነው?>> በማለት በጠየቃቸው ጊዜ፡- «አላህ ብቻውን ነበር። ምንም ነገር _ አብሮት አልነበረም። የአላህም ዓርሽ ከውሃ ላይ ነበር።» በማለት መለሱ።"10

ብዙዎቻችን የአላህን ዓርሽ ለማየት ናፍቀናል። ግሩም መሽቀዳደም ነው፡ ፡ የዑካሻን ታሪክ እናስታውስ። ብዙ ሶሐቦች በተገኙበት ከአላህ መልእክተኛ ጋር ነበር። «ጀነት ያለ ምርመራ የሚገቡ ሰዎች አሉ፡ በማለት ሲናገሩ ሰማቸውና «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እኔ ከነርሱ ውስጥ አንዱ እንድሆን ዱዓ አድርጉልኝ አላቸው። ‹ዑካሻህ ሆይ፣ አንተ ከነርሱ ውስጥ ነህ።» አሉት። ሌላ ሶሓባም፡-«ለኔም ዱዓ ያድርጉልኝ ሲላቸው በዐካሻህ ተቀድመሐል» ሲሉ መለሱለት።"11

መሽቀዳደም የሚገባው ለዚህ ዓይነቱ ትልቅ _ እድል ነው። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህን ጀነት ስትለምኑ ፊርደውስን ለምኑት። እርሱ የጀነት ማእከላዊና ከፍተኛ ክፍል ነውና። የጀነት ምንጮች ከርሱ ይመነጫሉ። ጣሪያውም የአላህ ዓርሽ ነው፡>>12

የራእያዊ ነፍስ ባህሪ ይህ ነው። ሁሌም ከፍተኛውን ደረጃ ታልማለች። አንድ ገጣሚ እንዲህ ሲል እውነት ብሏል፡

‹ተራራን መውጣት ያልፈለገ

ሁሌም ጉድጓድ ውስጥ ይኖራል።

በምግብ፣ በመጠጥና በሻህዋ የተገደቡ ነፍሶች በጀነት ውስጥ የነቢዩን ጉርብትና ከሚያልሙ ታላላቅ ነፍሶች መሐል ቦታ የላቸውም።።

10"አልሐኪም
11"ቡኻሪና ሙስሊም
12 "አህመድ

<u>የአላህን ማንነት በትክክል አላወቁም</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

አንደኛው ሰማይ ከሁለተኛው አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። ሁለተኛው ሰማይ ከሦስተኛው አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። ሦስተኛው ሰማይ ከአራተኛው አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። አራተኛው ሰማይ ከአምስተኛው አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። አምስተኛው ሰማይ ከስድስተኛው አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። ስድስተኛው ሰማይ ከሰባተኛው አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። ሰባተኛው ሰማይ ከኩርስይ አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። ኩርስይ ከዓርሽ አንጻር ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ማለት ነው። ዓርሽ ከአምላክ መዳፍ ውስጥ ከሜዳ ላይ የተጣለ ቅንጣት ይመስላል።»

በእርግጥ አምላክን ከፍጡራን ጋር አናመሳስልም። ለርሱ አካላዊ ቅርጽ አንሰጠውም። እንዲህ በማለት እንወሰናለን፡

لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ (الصور
«እርሱን የሚመስል አንዳችም ነገር የለም እርሱ ሰሚው ተመልካቹ ነው» (አል ሹራ ፲፩)

ወንድሜ ሆይ፣ ይህን ሐዲስ በወጉ አስተንትን። የአላህንም ታላቅነት አስተውል። ከርሱ ፊት ለፍርድ የምትቀርብበትን ችሎትም አስታውስ።

<u>የፍጥረታት እውቀቴን ጻፍ</u>

በነዚህ አናቅጽና ሐዲሶች አማካይነት ለዘመናት በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ የነበሩ ቀልቦችን ለመቀስቀስ አልማለሁ። እነዚህ ቀልቦች ከድንዘት ይነቁ ዘንድ በሐይል ወዝውዞ የሚቀሰቅሳቸውን አካል ይሻሉ። የአላህ ሐይል እንዲሰማቸው ከማድረግና ከውስጣቸው ከመትከል ይበልጥ ይህን ሚና የሚጫወት ሌላ ነገር አላገኘሁም።

ከአላህ ዓርሽ ቀጥሎ የተፈጠረው ሁለተኛው ነገር ብእር መሆኑን ነቢዩ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡
-

‹‹አላህ የፍጡራኑን አኳኋን ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ ከአምሳ ሺ ዓመታት በፊት ጽፏል። ያኔ ዓርሽ ከውሃው ላይ ነበር።››13

እናም መጀመሪያ የተፈጠረው የአላህ አርሽ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ብእር
ተፈጠረ።
ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ) ብእርን ፈጠረና ጻፍ አለው። እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የሚከናወነ ነገሮችን ጻፈ።››14

ይህው ሐዲስ በሚከተለው መልኩ ተዘግቧል፡-

‹‹አላህ ለብእር፡- እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የፍጥረታት እውቀቴን ጻፍ፤ አለው።*15

አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ሐዲስ በሰሙ ቁጥር አንዳች ጥያቄ ከአእምሯቸው ውስጥ ይመላለሳል። ጭንቅላታቸው በርሱ ይሞላል። መልስ ለማግኘትም በየትኛውም ቦታ ያሉ ዓለ.ሞችን በር ያንኳኳሉ። በሚሰጣቸው መልስም አይረኩም። ማለት የፈለግኩትን ይበልጥ ለማስረዳት ጥቂት ማብራሪያዎችን መስጠት እፈልጋለሁ።

<u>የተለመደ ጥያቄ</u>

እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ያሉ ነገሮች በብዕር ተጽፈዋል የሚለው ሐሳብ በተነሳ ቁጥር አንድ የተለመደ ጥያቄ አብሮ ይነሳል። ጥያቄው የጥንትም የአሁንም ነው። ይህውም፡- ሁሉም ነገር አስቀድሞ የተጻፈ ከሆነ የሰው ልጅ መርጦ የመስራት ነጻነት አለው ወይስ የለውም?›› የምንሰራው ስራ ሁሉ በብእር ከተጻፈ የኛ ልፋት ምን ፋይዳ አለው? ለምን እንደከማለን? ስራችንን ሁሉ ቀድሞ የጻፈብን አላህ ሆኖ እያለ በእለተ ቂያማ ለምን ይመረምረናል?›› የሚል ጥያቄ ይነሳል።

*13ሙስሊምና ቲርሚዚ
*14ቲርሚዚ፣ አቡ ዳውድና አህመድ
*15ቲርሚዚ

በእርግጥ የጥርጣሬ መነሻ ጥያቂ ነው። ሰይጣን በዚህ ጥያቄ የነቃቃል። ጉልበተንም ያሳይበታል። ከውይይትና ክርክር ውጭ ምንም ር እንዳትሰራ የሃርማራል። ይህም የኖ ከአንዳች ውጤት ላይ ብትነርስ፣ አንዳች ፋይዳ ብታገኝ መልካም ነበር። ግና ይህ አይሆንም። ይህን ጥያቄ በተመለከቱ ሦስት ነገሮችን አስተውያለሁ።

አንደኛ፡- የሚገርመው ነገር ይህን ጥያቄ የሚጠየቁት ወገኖች ሐጢአተኞች እንጂ በጎ ሰዎች አይደሉም። አላህን የሚታብዙ ሰዎች ይህን ጥያቄ ሲያነሱ አይተን እናውቃለን፡ በፍገም፣ ቀልቦቻቸው በአላህ ፍቅር የተሞላና እርሱን የሚታዘቡ ወገኖች በእንዲህ ዓይነት ፍልስፍናዊ ጥያቂዎች ጊዜያቸውን ለማን አይፈቅዱም።

ጥያቂው ለወንጀለኞች ትልቅ እንቅፋት የሚሆን ነው። ሱሰኞቹን እስረኛ እንደሚያደርገው አይንና እግ ማለት ነው። አላህን የማሰቡ የመልካም ልቦና ባለቤቶች ግን በንግግርና በስንፍና ሳይሆን በስራ የተጠመዱ በመሆናቸው ይህ ጥያቄ ከአንደበታቸው አይጠጣም፤

<u>ሰሪው የበለጠ ያውቃል</u>

ሁለተኛ፡- አንዳንዶቹ ሐዲሱ ግን ነው። አላህ ሰብር እውቀቱን ጻፊ እንዳለ በግልጽ ይናገራል። ታዲያ እንውን ሰው ዘንድ እርሱ ራሱ ፖርት እያለ እኛኑ መልሶ ለምን ይቀጣናል" የሉ። ይህን ነጥብ ለማብራራት እንደ ምሳሌ ልጥቀስ። እንበልና አን። አባት ሦስት ልጆች እሎት። ለእያንዳንዳቸው ፓውንድ ገንዘብ ሰጣቸው። የሰጠኋችሁን ገንዘብ ላሻችሁ ተግባር አውሉት። የፈለጋችሁትን ነገር ተገዙበት ዘንድ ውሎ ነጻነት ሰጥቻችኋለሁ። ሲልም አዘዛቸው። ልጆቹ ያሰቡትን ሊገዙ ወጡ። አባትም ወረቀት አወጣ እና ሦስቱ ልጆቹ በገንዘቡ ምን ሊርጉ እንደሚችሉ ያለውን ግምት ፃፈ። አንደኛው እጅ ገንዘቡን በአላህ መንቲ እንደሚያውለው፤ ሁለተኛው ስስታም በመሆኑ በሳ ቤስቲን እንደማያወጣ፤ ሦስተኛው አላህን በሚያስቆጣ ተግባር እንደሚያውለው ያለውን ግምት ከወረቀት ላይ አሰፈረ። ሦስቱም ልጆች ላይ ተመለሱ፥ ገንዘቦቻቸውን ምን እንዳደረገበትም አው። የአባት ግምት

ትክክል ሆነ። ሱብሐነላህ። አባታቸው ልጆቹን በደንብ ያውቃል፣ ይህም ሆኖ፡- «ይህን ስሩ ያን ስሩ» በማለት አላስገደዳቸውም። የፈጠረን አላህ ብእርን እንድትጽፍ ሲያዛት የሚያውቀውን አሰፈረ እንጅ እያስገደደን አይደለም። ያሻንን እንድንሰራ : ነጻነት ተሰጥቶናል። ሁሉም ነገር በለውሃል መህፉዝ ላይ ተጽፏል። ግና ከመካከላችን እዚያ ላይ የተጻፈውን የሚያውቅ አለን? ስለዚህም እኛ በስራና በታዛዥነት ዓለም ውስጥ ነን። ያሻህን መርጠህ የመስራት ነጻነት ተችሮሐል። ሁለት መንገዶችም ተዘርግተዋል። አንደኛው ወደ አላህ' ሌላኛው ወደ ሰይጣን ያደርሳሉ።

ሦስተኛ፡- ከላይ የሰፈሩት ሁለቱ ምላሾች የማያረኩት እና በጥርጣሬ የሚዋልል፣ ሦስተኛ ምላሽም የሚሻ ሰው አለ። ለእንዲህ ዓይነት ሰዎች አንድ ጥያቄ አቀርብላቸዋለሁ፡

“አምላካችን አላህ በዳይ ነው ወይስ ፍትሃዊ?»

መልሳቸው በእርግጥም ፈጣን እንደሆነ አስባለሁ። አምላካችን አላህ ፍትሃዊ እንጅ በዳይ አይደለም። እንደሚሉም እርግጠኛ ነኝ። ይህ ከሆነ ይህን ሁሉ ጥርጣሬና አለመረጋጋት ምን አመጣው? አላህ ፍትሃዊ መሆኑን እያወቅክ ለምን ትታወካለህ?

ይህ ጥያቄ ብቻውን ለጥያቄያቸው በቂ ምላሽ ነው። ከዚህ በኋላ፡- «የሰው ልጅ ተግባራት ተገዶ የሚፈጽማቸው፣ ሐላፊነትም የማይወሰድባቸው ናቸው ያለ አላህን በበዳይነት እየወነጀለ ነው።

<u>ዓላማችን</u>

ወደ ሐዲሱ እንመለስና አላህ ለብእር ጻፍ አለው። ብእርም እስከ እለተ ቂያማ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ጻፈ። ይህ መልእክት «ሱብሐነከ! አንተ ካሳወቅከን ውጭ ሌላ የምናውቀው ነገር የለም። የሚል ስሜት አላጫረብህምን?

አላህ ከቀልቦች ውስጥ ያሉ ነገሮችን ሁሉ ያውቃል። ሁሉንም ነገር አዋቂ ነው። አላህ ዘወትር እንደሚያይህ ተሰምቶሐል? እያንዳንዷ

እንቅስቃሴህ በአላህ እይታ ስር መሆኗ አልታሰበህምን? ይህ ከሆነ እንዴት ሐራም ነገሮች ለማየት ትደፍራለህ? አላህ እንደሚያይህ አላወቅክምን? ሐጢአት ስትፈጽም ሰዎች እንዳያዩህ ትፈራለህ። አላህ ቢያይህ ግን አትፈራም። የአላህን ማየት ከሰዎች አሳንሰህ አየህውን? አላህ እንዲህ ብሏል፡

أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِي السَّمَوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ مَا يَكُونُ مِن نَجْوَى ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ رابِعُهُمْ وَلَا خَمْسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمْ وَلَا أَدْنَى مِن ذَٰلِكَ وَلَا أَكْثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمْ أَيْنَ مَا كَانُوا ثم يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوا يَوْمَ الْقِيَٰمَةِ إِنَّ اللَّهَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمُ)

አላህ በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉትን የሚያውቅ መሆኑን ኢታይምን በሦስት ሰዎች መካከል የሚደረግ ሚስጥራዊ ውይይት ሹክሹክታ የለም እርሱ አራተኛ ቢሆን እንጂ በአምስት ሰዎች መካከለም የለም እርሱ ስድስተኛ ቢሆን እንጂ። ከዚህ ያነሰ ወይም የበዛ ቁጥር ባላቸው ሰዎች መካከልም አይኖርም የትም ቢሆኑ እርሱ ከነርሱ ጋር ያለ ቢሆን እንጅ : ከዚያም በትንሳኤ ዕለት ይሠሩት የነበረውን ይነግራቸዋል አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ ነው›› (አል ሙጂደላህ)

የሰው ልጅ ሆይ፣ ምን ነካህ? አምላክ እንዳለህ ረሳህን? የምርመራ ቀን መኖሩን ዘነጋህን?

<u>እንቅልፍ ማጣት ይብቃ</u>

ብእሩ እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የሚሆነውን ነገር ጽፏል። ከተጻፉት ነገሮች መሐል ሲሳይ አንዱ ነው። አይደለም እንዴ? የእያንዳንዳችን ሪዝቅ ተጽፏል። ታዲያ ሪዝቅ እንዳያመልጠን መስጋትንና እንቅልፍ ማጣትን ምን አመጣው? ሁሉም የወደፊቱን ሕይወትና ዘመን ይፈራል፡ ፡ ሪዝቅ ለማግኘት የሚያበቁ ሰበቦችን እስካደረስክ ድረስ ፍርሃት ለምን? እስከጣርክና እስከሰራህ ድረስ ስጋት ለምን?

ወዳጅቼ ሆይ፣ ሪዝቅ : በለውሃል መሕፉዝ _ ላይ _ በእርግጥ ተጽፏል። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ እውነት ተናግረዋል።

‹‹በአላህ በትክክል ብትመኩ ኖሮ አሞራን እንደሚመግበው እናንተንም ይመግባችሁ ነበር። አሞራ በባዶ ሆዱ ይወጣል። ሆዱን ሞልቶም ይመለሳል።››16

በአላህ ትክክለኛ መመካት ሁለት እርምጃዎችን ይሻል።

አንደኛ፡- ሲሳይ (ሪዝቅ) ከለውሃል መህፉዝ ላይ ተጽፏል ብሎ በእርግጥ ማመን።

ሁለተኛ፡- ይህን የተጻፈ ሪዝቅ ለማግኘት የሚያስችሉ ሰበቦችን እና ጥረቶችን ሁሉ ማድረስ።

<u>መመካት በተግባር ሲገለጽ</u>

የአላህ መልእክተኛ ለአንድ ትንሽ ልጅ (ለኢብን አባስ) የሰጡት ተከታዩ ትምህርት በሁላችንም ልቦና ውስጥ ለዝንተ ዓለም ሊጻፍ የሚገባው ቁም ነገር ይዟል። እንዲህ ብለውታል፡-

ሰዎች አንተን በአንዳች ነገር ለመጥቀም ቢሰበሰቡ አላህ ከጻፈልህ ነገር ውጭ በሌላ በምንም ሊጠቅመህ እንደማይችሉ እወቅ። ሰዎች ሁሉ አንተን ለመጉዳት ቢሰበሰቡ አላህ ከጻፈልህ ነገር ውጭ በሌላ በምንም ሊጎዱህ እንደማይችሉ እወቅ። ብእሮች ተነስተዋል። ገጾቹም ደርቀዋል።*17

በአላህ ላይ ያለን እምነት በዚህ አኳኋን ሊጸና ይገባል። እምነታችን እንዲህ ጥልቅ፣ በአላህ መመካታችን እንዲህ ጠንካራና እውነተኛ ሊሆን ይገባል። ሪዝቅ ያመልጠኛል የሚል ስጋት መሠረት አልባ መሆኑን ማወቅ ያሻል። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ሲሳያችሁን እንዳከፋፈላችሁ ሁሉ ባህሪያችሁንም አከፋፍሏችኋል።*18

*16ቲርሚዚና ቢን ማጃህ
*17ቲርሚዚና ሐኪም
*18አህመድና ሐኪም

የሁላችንም ሲሳይ (ሪዝቅ) ተጽፏል። የየድርሻችንም ተከፋፍሏል። ታዲያ ለእንጀራ ብለን ለምን እርስ በርስ እንጋደላለን? አንች መልካም እናት ሆይ፣ ‹‹የሴት ልጅቼ ጋብቻ ዘገዬ፣ እድሚያቸው ገፋ እያልሽ መጨነቅሽ ለምን? የልጆችሽ ባል ስም ከአላህ ዘንድ ተጽፏል። ብእሩ እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የሚሆነውን ሁሉ ከትቧል።

እናንተ ሰዎች ሆይ፣ ሴቶችም ወንዶችም በአላህ በትክክል ተመኩ። ደካሞች ናችሁና ወደርሱ ተጠጉ። በራሳችሁ ብቻ ከተማመናችሁ ሰፊዋ ምድር ትጠብባችኋለች። በራሱ ብቻ የሚመካ የጭንቀት አውራ ይበላዋል።

<u>ይህን ተጠንቀቁ</u>

ከላይ እንደገለጽነው መጀመሪያ የተፈጠረው የአምላክ ዓርሽ ነው። ከዚያም ብእሩ፣ ቀጥሎ ለውሃልመህፉዝ ተፈጠረ። የጀመርነውን ከማጠናቀቃችን በፊት አንድ ነገር ማከል ጥሩ መስሎ ታይቶናል። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሰይጣን ከናንተ መሐል ወደ አንደኛችሁ ይመጣና ሰማይን ማን ፈጠረው? ይለዋል። አላህ በማለት . ይመልሳል። ምድርንስ ማን ፈጠራት? ይለዋል። አላህ በማለት ይመልሳል። አንተንስ ማን ፈጠረህ? ይለዋል። አላህ ሲል ይመልሳል። አላህንስ ማን ፈጠረው? በማለት ይጠይቀዋል። ከናንተ አንዳችሁ ይህ ሐሳብ በልቦናው ውስጥ ካደረበት (ይህ ጥያቄ ከመጣበት)፡- በአላህ እና በመልእክተኛው አመንኩ ይበል። ጥያቄው ከሰይጣን የመነጨ ነው።*19

እንዲህም ብለዋል፡-

‹‹ስለ አላህ ፍጡራን ተመራመሩ። ስለ አላህ ማንነት ግን አትመራመሩ። ከአቅማችሁ በላይ ነውና።*20

እንዲህም ብለዋል፡-

*19አህመድ
*20ሉዩጢ

“ሰዎች ሁሉንም ነገሮች ይጠይቋችኋል። እነዚህ የአላህ ፡ ፍጡራን ናቸው! አላህንስ ማን ፈጠረው? የሚል ጥያቄ ሳይቀር ያቀርቡላችኋል። ይህ ጥያቄ አቀረበላችሁ አላህ ከሁሉም ነገር በፊት ነበር። ሁሉንም ነገር ፈጥሯል፤ ከሁሉም ነገር በኋላም ይቀራል፣ የሚል መልስ ስጡ።*21

እዚህ ላይ አንዳንድ ሰዎች ብሽቦታ ያጋጥማቸዋል። አእምሯችንን ማሰራት አንችልምን? ሲሉ ይጠይቃሉ። በእርግጥ አላህ አእምሮን እናስብበት ዘንድ ሰጥቶናል። እውቀት ፍለጋን በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ግዴታ አድርጓል። ስለዚህም አእምሮ ስለ ሁሉም ነገር እንዲያስብ ይፈለጋል። ግና አላህን በተመለከተ ከአእምሮ ወሰን በላይ በመሆኑ ስለርሱ መመራመር አይችልም። እናም፡- «እርሱን የሚመስል የለም, ከማለት ውጭ ሌላ ምርጫ የለውም። አእምሯችን ጎደሎና አቅሙ ውስን ነው። ጎደሎ የሆነ ነገር ምሉእ እና ፍጹም የሆነውን አካል ምንነት መረዳት ይችላልን?

<u>አንዳች ሐሳብ አወከኝ</u>

ኢብን አባስን ተከታዩ ክስተት አጋጠማቸው። አንድ ሰው መጣና፡- «ኢብን አባስ ሆይ፣ ከልቦናዬ ውስጥ አንዳች ሐሳብ አወከኝ።» አላቸው። «እርሱ ምንድን ነው?» ሲሉ ጠየቁት። «በአላህ እምላለሁ፣ መናገር አልፈልግም።» አላቸው። ኢብን አባስም፡-«ጥርጣሬ ነውን?» ሲሉ ጠየቁት። «አዎ፣ ግን እንዴት አወቁ?» አላቸው። ከአላህ ጋር በሚደረግ መልካም ግንኙነት ጅማሬ ላይ ይህ ዓይነቱ ነገር እንደሚከሰት አውቃለሁ። ይህ ነገር ሲያጋጥምህ፡- የመጀመሪያውም የመጨረሻውም፣ ግልጽም ስውርም እርሱ ነው። ከአላህ ሌላ አምላክ የለም። እርሱን የሚመስልም የለም በል»አሉት።

ይህ ዓይነቱ መጠራጠር የሚያጋጥመውን ሰው እምነተ ደካማ፣ ወንጀለኛ ወይም ዝንጉ አድርጎ የማሰብ ችግር በአንዳንዶቻችን ዘንድ ሊስተዋል ይችላል። የኢብን አባስ ማብራሪያ ግልጽ ነው። «ከአላህ ጋር በሚደረግ

*21ሱዩጢ

መልካም ግንኙነት ጅማሬ ላይ ይህ እንደሚከሰት አውቃለሁ።» ማለታቸውን እናስተውል። ሶላት፣ ዚክር፣ ዱዓና በጎ ስራ በጀመረ ሁሉ ላይ ይህ ሊከሰት ይችላል። እንደርሳቸው ገለጻ። አላህን የመታዘዝ ጎዳና ከጀመርኩ ሰይጣን በዚህ መልኩ አይወሰውሰኝም ብለህ ታስባለህን? ይህም ባይሆን ሌላ መንገድ አይጣልህም በዋዛ እንደማይተውህ አትጠራጠር። በየቀኑ በአዳዲስ መልክ አላህን እንድትወነጅል መጣሩ አይቀሬ ነው። ከአላህ ጋር መልካም ግንኙነት የጀመረ ሁሉ እንዲህ ዓይነት ወስዋሶች ሊያጋጥሙት እንደሚችሉ መረዳት ይበጃል።

<u>በእውነት ላይ ነህ</u>

ይህ ወስዋስ ያገኘው ሰው በሐቅ ላይ፣ ያላገኘው ደግሞ በስህተት ላይ ተደርጎ እንዳይታሰብ ስለተሰጋ ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ወደድኩ። በእርግጥ አላህ ከእንዲህ አይነት ወስዋስ የሚያድነው ሰው አለ። ስለዚህም ያልተወሰወሰ ሁሉ በስህተት ላይ ነው የሚለው እሳቤ ትክክል አይደለም።

ግና ሰይጣን በኢባዳዎች ላይም በመምጣት ጥረቱን ይቀጥላል። ዓላማው በጎ ስራን እንድንጠላ ማድረግ አይደል? በውዱእ ላይ የሚከሰትን ወስዋስ በብዛት እናስተውላለን። አንዳንድ ሰዎች ሰይጣን ስለሚያውካቸው ደጋግመው ውዱእ በማድረግ ተግባር ይጠመዳሉ።

ሰይጣን አንዳንድ ወጣቶችን፦ ‹‹ወደ አላህ ለመቃረብ፣ ዲነኛ ለመሆን ብቁ አይደላችሁም›› በማለት ተስፋ እያስቆረጠ ከአላህ ሊያርቃቸው ሲጥር ይስተዋላል። እድሜ ልኩን ሲጠቀምበት የኖረ የማሳሳቻ ስልት ነው። ከዓላማው ለመድረስ ሁሉንም ዓይነት ስልቶች በስራ ላይ ያውላል፡ ፡ እንዲሳካለት አንተ አጋዥ ትሆነዋለህን?

<u>የጤንነት ምልክት</u>

አላህ ከዚህ ወስዋስ ያዳነው ሰው በስህተት ውስጥ ነኝ ብሎ ማሰብ የለበትም። ይልቁንም አላህን ለዚህ ጸጋው ያመሰግነው። ብዙዎቹ

ሐይማኖተኞች ግን እንዲህ ዓይነት ወስዋስ ያጋጥማቸዋል። ይህ ወስዋስ ሰውየው ወደ አላህ የመቃረቡ ምልክት መሆኑን ማስተዋል ተገቢ ነው። ሰይጣን ሁሉንም አይነት መሳሪያዎች ተጠቅሞ ማሰፍሰፉንና ጥቃቱን ለመመከት እንዲዘጋጁ ወጣቶቹን አነሳሳለሁ። የሰይጣን ስልትና መሳሪያ ከኢማን ትጥቅ አንጻር ኢምንት እና ደካማ ነው።

<u>መድሐኒትህ በእጅህ</u>

በመሆኑም ሰይጣን ስለወሰወሰህ ራስህን መጥፎ አድርገህ አታስብ። ሰይጣን ሊወስውስህ ሲመጣም ነቢዩና ኢብን አባስ ያስተማሩህን ዱዓ ግልጹም ማለትም፡- «በአላህ እና በመልእክተኛው አመንኩ በል። ከአላህ ሌላ አምላክ የለም»ብል። «የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ስውሩም እርሱ ነው» በል። «ከተረገመው ሰይጣን በአላህ እጠበቃለሁ . በል።

አላህን ስታወሳ ሰይጣን ጥሎህ ይፈረጥጣል። ለዚህ በሽታ መድሐኒት መጠቆም እንሻለን። ይህውም፡- አንደኛ፡- አንተ ምንም ነገር አለመሆንህን እወቅ- (You are nothing)

ሁለተኛ፡- ከላይ የተማርከውን ዱዓ አድርግ። አላህንም አውሳ። ሦስተኛ፡- ሶደቃ አውጣ (ምጽዋት ስጥ)፣ ይህ አሪፍ ሐሳብ ነው። ይህን ሐሳብ አብራራልህ ዘንድ ፍቀድልኝ፡

<u>አሪፍ ሐሳብ</u>

ሰይጣን መወስወስ ሲጀምርህ መጠነኛ ሶደቃ ለምሳሌ 10፣ 25፣ 50 ሳንቲም ስጥ። ብዙ ሶደቃ ለማውጣት አታስብ። ምክንያቱም አቅምህ አይፈቅድልህም። ግና ወስዋስ ባጋጠመህ ቁጥር ወዲያውኑ መጽውት። ለምሳሌ በቀን 10 ጊዜ ወስዋስ ቢያጋጥምህና በእያንዳንዱ ወስዋስ 10 ሳንቲም ብትመጸውት በቀን አንድ ብር / ሶደቃ : አወጣህ ማለት ነው። ሰይጣን በድርጊትህ ግራ ይጋባል። በወሰወሰህ ቁጥር አንተ መልካም ስራ መስራትህ ያበሳጨዋል። ላንተ የደግ ስራ በር መክፈቱ ይቆጨዋል።

መወስወሱ እንደማያዋጣው ይገነዘባል። ይህም ሆኖ ተስፋ አይቆርጥም። ይህ ሰው ከአንድ ወር በላይ አይታገስም በማለት መወስወሱን ይቀጥላል፡ : አንተ ግን በአቋምህ ከጸናህ ታሸንፈዋለህ። እየቆየ ሲሄድ ተስፋው ይሟሽሻል። በጦርነቱ ቅስሙ ተሰብሮ ይመለሳል። በእርግጥ ሌላ መንገድ ፈልጎ ሊያጠቃህ መሞከሩ አይቀሬ ነው።

ሰይጣንን ጦርነት ገጥሞ ማሸነፍ እጅግ ከፍተኛ የድል አድራጊነት ስሜት ይፈጥራል። ዑመር ቢን አልኸጧብ አላህ ይዘንላቸውና ሰይጣንን ድል አድርገውታል።

<u>ማድረግ ይችላል</u>

የነብያትን ሕይወት በአዲስ እይታ ለመቃኘት ስናስብ ዓላማችን ታሪክን መተረክ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ርዕስ ወደተጨባጭ ሕይወታችን በማውረድ ትምህርት ለመቅሰም መሆኑን አብራርተናል፡ : የአላህ ዓርሽ፣ ብእሩና ለውሃል መህፉዝ ከተፈጠሩ በኋላ ምን ሆነ? ሰማይና ምድር ታነጹ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

إن رَبَّكُمُ اللَّهُ الَّذِى خَلَقَ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ اسْتَوَى عَلَى الْعَرْشِ

«ጌታችሁ አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት የፈጠረ ነው። ከዚያም ራሱን ከዙፋኑ ላይ አደላደለ፡» (አል አእራፍ 54)

በሌላ የቁርአን አንቀጽ የሰማያትንና የምድርን አፈጣጠር እንዲህ ሲል ያብራራል፡-

قُلْ أَئِنَّكُمْ لَتَكْفُرُونَ بِالَّذِى خَلَقَ الْأَرْضَ فِي يَوْمَيْنِ وَتَجْعَلُونَ لَهُ أَندَاداً ذَلِكَ رَبُّ الْعَالَمِينَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَاسِيَ مِن فَوْقِهَا وَبَرَكَ فِيهَا وَقَدَّرَ فِيهَا أَقْوَاتَهَا فِي أَرْبَعَةِ أَيَّامٍ سَوَاءَ لِلسَّايِلِينَ ثمَّ اسْتَوَى إلى السَّمَاءِ وَهِيَ دُخَانٌ فَقَالَ لَهَا وَالأَرْضِ ائْتِيَا طَوْعًا أَوْ كَرْهَا قَالَتَا أَتَيْنَا طَابِينَ فَقَضَهُنَّ سَبْعَ سَمَوَاتٍ فِي يَوْمَيْنِ وَأَوْحَى فِي كُلِّ سَمَاءٍ أَمْرَهَا وَزَيَّنَا السَّمَاءَ الدُّنْيَا بِمَصَبِيحَ وَحِفْظاً ذَلِكَ تَقْدِيرُ الْعَزِيزِ الْعَلِيمِ ـفصلت: ٩)

“ምድርን በሁለት ቀናት በፈጠራት (አምላክ) ትክዳላችሁን? ለርሱም ባላንጣዎች ታደርጋላችሁን? እርሱ የዓለማት ጌታ ነው” በላቸው ከበላይዋ የረጉ ጋራዎችን ተከለ። በረከትም አደረገባት በአራት ቀናትም ውስጥ ሲሳይዋን ወሰነ። (ይህ አፈጣጠሯን) ለሚጠይቁ ሁሉ ፍፁም ትክክለኛ የሆነ (መረጃ) ነው። ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ ጭስ ነበረች እርሷንና መሬትንም ወዳችሁም ሆነ ሳትወዱ ነ አላቸው ወደ (እና ታዛዦች ሆነን) መጣን” አለ። በሁለቱ ቀናት ውስጥም ሰባት ሰማያት አድርጐ አነጻቸው ለሁሉም ሰማያትም የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች አደረገ (አሟላ የቅርቢቱንም ዓለም ሰማይ በመብራቶች አስጌጥናት (ከሰይጣናት) መጠበቅንም (ለገስናት) ይህ አሸናፊና ዐዋቂ የሆነው አምላክ ውሳኔ ነው›› (ፉሲለት 9-12)

አላህ ሰማያትን እና ምድርን በቅጽበት መፍጠር ይችላል። ሁን ቢላቸው ወዲያውኑ ይሆናሉ። ግና በስድስት ቀናት በመፍጠር አንድ ትልቅ ጥበብ ሊያስተምረን ከጀለ።

<u>አስተውል!</u>

ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት በመፍጠር የሂደታዊ ለውጥን ጽነስ ሐሳብ ሊያስተምረን ከጀለ። በዚህች ዓለም ውስጥ እያንዳንዱ ነገር ቀስ በቀስ እና በሂደት እንደሚከናወን ነገረን። ስለዚህም አንዳች ችግር ያጋጠመው ሰው ቅጽበታዊ መፍትሄ መጠበቅ የለበትም። ቀስበቀስ እና በሃደት ችግሩን ለመፍታት መታገስ ይበረታል።

እንደዚሁም ለሰዎች ዳእዋ ማድረግ የፈለገ ይታገስ። ሰዎች በቅጽበት ቅኑን ጎዳና አይዙም። ትእግስት ያሻል። ረዥም ትንፋሽ ያስፈልጋል።

ይህ መልእክት እጅግ ከባድና ጠቃሚ ነው። አንዳንዶቻችን ይህን ባለመገንዘብ ታዳኙን እንስሳ ለመግደል እንደሚያራውጥ ድብ ሰዎችን ያራውጣል። ወደ ቅን ጎዳና ሊመራቸው ይከጅልና ያስበረግጋቸዋል። ይበልጥ

<u>አላህን ተዳፈሩ</u>

ከሰማያትና ከምድር አፈጣጠር ጋር በተያያዘ አይሁዶች እጅግ አደገኛ አስተሳሰብ አላቸው። በእርግጥ በብዙ ጉዳዮች ላይ ያላቸው አስተሳሰብ

እጅግ መጥፎ ነው። እንዲህ ይላሉ፦ “አምላክ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠረ። ድካም ስለተሰማውም በሰባተኛው ቀን አረፈ። ይህም ቀን ቅዳሜ ነበር።»

ላኢላሐ ኢለላህ!

አላህም ለዚህ ቅጥፈታቸው የሚከተለውን ምላሽ ይሰጣል፦ وَلَقَدْ خَلَقْنَا السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ وَمَا مَسَّنَا مِن لُّغُوبٍ

ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያሉትንም (ፍጡራን) በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠርን። (ይህን ስናደርግ) ድካም አልተሰማንም። ቃፍ 38)

እናንተ አይሁዶች ሆይ፣ ምን ዓይነት ፍጡራን ናችሁ? በአላህ ላይ እንዴት እንዲህ ዓይነት ነገር ትናገራላች ሁ?

ማረፍ የድካም ምልክት ነው። አላህ ይደክመዋልን?

ለዚህ አባባል መድሐኒቱ መታገስ ነው። በእርግጥ ትእግስት ለችግሮች ሁሉ መፍትሄ፣ ሊለወጡ ለሚችሉ ነገሮች ሁሉ ፈውስ ነው።

<u>ትከጅያለሽን?</u>

አላህ በመጀመሪያ ዓርሽን ፣ ቀጥሎ ብእርን፣ ቀጥሎ ለውሐል መህፉዝን ፈጠረ። ከዚያም ሰማያትንና ምድርን አስገኘ። ሁለቱን ባረካቸው። በምድር ላይ ለሕያውያን ቀለብ የሚሆኑ ነገሮችን አስቀመጠ። እዚህ ላይ አንድ ቁም ነገር ማስታወስ እንከጅላለን። አላህ ከፍጥረታት ጅማሬ ጋር እጅግ ድንቅ የሆነ እሴት አበጀ። እርሱም የስነ ምግባር እሴት ነው። ይህም የሆነው አደምን ከመፍጠሩ በፊት ነው። ከዚህ እውነታ ጋር በንጹህ ነፍስ፣ በበሳል አእምሮ፣ በመለኮታዊ ድባብ ውስጥ ሆነን ጥቂት ቆይታ እናድርግ። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹አላህ ፍጡራንን ፈጥሮ ሲያጠናቅቅ ዝምድና ቆመችና፡- ይህ ከመቆረጥ ባንተ የምጠበቅበት ቦታ ነው፣ አለች። አላህም፡- አዎ፣ የቀጠለሽን እንድቀጥል፣ የቆረጠሽንም እንድቆርጥ ትከጅያለሽን? አላት። አም አለች። ይህው ሆኖልሻል አላት።*22

እድሉን ተጠቀምና ከዚህ ሐዲስ ጋር የፈጠርከውን መስተጋብር ፍሪያማ አድርገው። ስሜትህ ፈጥኖ ይነሳ። ፈጥነህም ተግብረው። ወደ ዘመዶችህ ሁሉ ሂድና ጠይቃቸው። ዝምድናን ቀጣይ ሁን።

ዝምድና በፍጥረታት መጀመሪያ ላይ ያቀረበችው ጥሪ ይህ ነበር። ከዓለም ፍጻሜ በኋላ የሚሆነውንም ተመልከት። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- ሲራጥ ይተከላል። ዝምድናና አደራ ይወጡና በሲራጡ ሁለት ጎኖች ይቆማሉ። እያንዳንዱ ሰው ባለፈ ቁጥር፡- አላህ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ቀን የሰጠንን መብት ስጠን በማለት ይጠይቃሉ።*23

ዱንያ እጅግ ርካሽ ነገር ናት። ቤተሰብ ሊፋጅባት የምትገባ አይደለችም፡ ለውርስ ገንዘብ ስትል ከወንድምህ ጋር ትቆራረጣለህን? በአንዳች ችግር ሰበብ ከእህትሽ ጋር ትጣያለሽን? መልስህን እሻለሁ፣ መልስሽን እሻለሁ።

አንች ዱንያ ሆይ፣ ሰዎች ትክክለኛ ዋጋሽን ቢያውቁ ኖሮ ካንች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያስተካክሉ ነበር።

<u>በሩ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?</u>

ቲርሚዚና ቢን ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ አንድ ሶሐባ እንዲህ ሲል አውግቷል፡-
በስተምእራብ በኩል ስላለ አንድ በር ነቢዩ ነገሩን። ስፋቱ ጋላቢን ሰባ አመት ያስኬዳል። አላህ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ ፈጥሮታል። እስካሁንም ድረስ እንደተከፈተ ነው። በሩ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?›› በማለት ነቢዩ ጠየቁን። _ አላህና መልእክተኛው

*22ቡኻሪና ሙስሊም
*23ሙስሊም

ያውቃሉ›› አልናቸው፡፡ ‹‹የተውበት በር ነው፡፡ ከሰባ ሺህ ዓመታት ርቀት ላይ ተከፍቶ ይጠባበቃል›› አሉን፡፡

ከዚህ በኋላ አደም ተፈጠሩ፡፡ በእርግጥ ይህ በር ለሰው ልጅ ታላቅ ብስራት ነው፡፡ የተውባ በር ምንጊዜም ክፍት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ብስራት በኋላ፡- ‹‹አላህ ተውባዬን ይቀበለው ይሆን?›› በማለት የሚጠይቅ ይኖር ይሆን?

ዝምድናን መቀጠልን ያስታወሰክ ይመስለኛል፡፡ አሁን ደግሞ ተውባን አስታውስ፡፡ እጅህን ወደላይ ዘርጋና ከልብ የመነጨ ለቅሶ እያለቀስክ፣ እንባህን እያፈሰስክ፣ የደረቀውን የተውባ አፈር አርጥበው፡፡

<u>እድሉን ተጠቀም</u>
የተውባ መስፈርቶች- ሁላችንም እንደምናውቀው ሦስት ናቸው፡-

አንደኛ፡- መጸጸት
ሁለተኛ፡- ወንጀሉን መተው
ሦስተኛ፡- ወደ ወንጀሉ ላለመመለስ መወሰን፡፡

እነሆ፣ ሁላችንም ወንጀሎቻችንን ከፊት ለፊታችን እናቅርብ፡፡ አንድ በአንድ እያስታወስንም እነዚህን ሦስት መስፈርቶች በስራ ላይ በማዋል እንቶብት፡፡ ይህን ያደረገ እድለኛ ነው፡፡ ስለተሳካልህ እንኳን ደስ ያለህ፡፡ ሰይጣንን በማሸነፍህ እንኳን ደስ ያለህ፡፡ በአላህ በመመካትህ እንኳን ደስ ያለህ፡፡ የመልካም ቀልብ ባለቤት ሁሉ እንኳን ደስ ያለህ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-
‹‹አላህ ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት መጽሐፍ ጻፈ፡፡ ከውስጥ ሁለት አናቅጽን አሰፈረ፡፡ በነዚህ አናቅጽ የአል በቀራህን ምእራፍ ቋጨ፡፡ ከአንድ ቤት ውስጥ ለሦስት ተከታይ ሌሊቶች ውስጥ ከተነበቡ ሰይጣን ያን ቤት አይቀርበውም፡፡*24

*24አህመድና ዳሪሚ

እነዚህ አናቅጽ የአልበቀራህ ምእራፍ | መቋጫዎች ናቸው። እንዲህ ይነበባሉ፡-

دامَنَ الرَّسُولُ مَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ كُلّ مَا مَنَ بِاللَّهِ وَمَليكيه. وكه. وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ، وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ العيد لا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا لَهَا مَا كَسَبَتْ وَعَلَيْهَا مَا اكْتَسَبَتْ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَا إِن نَّسِينَا أَوْ أَخْطَأْنَا رَبَّنَا وَلَا تَحْمِلْ عَلَيْنَا إِصْرًا كَمَا حَمَلْتَهُ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِنَا رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلْنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِ وَاعْفُ عَنَّا وَاغْفِرْ لَنَا وَارْحَمْنَا أَنتَ مَوْلَنَا فانصُرْنَا عَلَى الْقَوْمِ الْكَافِرِينَ

«መልዕክተኛው (ሙሐመድ ሶ.ዐ.ወ) ከአላህ ወደርሱ በተወረደለት መልዕክት አመነ አማኞችም እንዲሁ አመነ ሁሉም በአላህ፤ በመላእክት በመጻሕፍትና በመልዕክተኞች በመካከላቸው ምንም ልዩነት አናደርግም ከፊሎቹን አምነን በከፊሎቹ አናስተባብልም ያሉ ሲሆን አመነ። ጥሪህን ተቀብለናል፣ ለትዕዛዝህ አደረናል። ምሕረትህን እንሻለን። ጌታችን ሆይ መመለሻም ወደ አንተ ነው አለ አላህ አንድን ሰው ከችሎታው በላይ አያስገድደውም። በሠራው መልካም ሥራ ልክ ይመነዳል። በፈፀመው ጥፋት መጠን ይቀጣል። ጌታችን ሆይ! በመርሳታችን ሰበብ ወይም በስህተት ለምንፈጽመው ጥፋት አትቅጣን ጌታችን ሆይ ከባድ ሸክምን ከኛ በፊት የነበሩ ሕዝቦች ላይ እንደ ጉክ በእኛም ላይ አትጫንብን። ጌታችን ሆይ! የማንችለውን አታሸክመን። ይቅር በለን። ምሕረትህንም ለግሰን። እዘንልንም። አንተ ረዳታችን (ደጋፊያችን) ነህና በከሓዲያን ሕዝቦች ላይም ድልን አጐናጽፈን » (አል በቀራህ 285-286)

ብዙ ሰዎች -በተለይም እንስቶች- በጋኔን የመጠቃት ነገር ያሳስባቸዋል። ይህ ሐዲስ ከዚህ ስጋት ይገላግለናል። እነዚህ የቁርአን አንቀጾች የተቀሩበትን ቤት ሰይጣን እንደማይቀርበው ነቢዩ ነግረውናል። ስለዚህም ወደ ጠንቋይና አዋቂ መሄድ ይቅር። መስጋትም አይገባም። መፍትሄው በጃችሁ፣ መድሐኒቱ በደጃችሁ ነውና።

እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የተቀደሰች

አደም ከመፈጠራቸው በፊት የተከሰቱ ነገሮችን መቃኘታችንን ቀጥለናል። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል።

«አላህ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ መካን የተቀደሰች ከተማ አድርጓታል። እስከ እለተ ቂያማ ድረስም የተቀደሰች ሆና ትኖራለች።*25

እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ሰላም እንደምትሆን ጽኑ እምነት አለን። የመልእክተኛው ተወዳጅ ከተማ የሆንሽው መካ ልናይሽ፣ ልንጎበኝሽ እንናፍቃለን። እንጓጓለን። በእርግጥም ቅዱስ፣ በእርግጥም የተጠበቅሽ፣ የሰው ልጆች ፈርጥ የሆኑት ነብይ ከበላይሽ የተራመዱብሽ ከተማ ነሽ።

<u>ለኪዛራ የሆነ ሰው ብቻ ነው</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ መዶ ረህመቶችን ፈጠረ። እንዲን ወደ ምድር አወረዳት፡ ፡ ፍጡራን የሚተዛዘኑት በርሷ ነው። በእለተ ቂያማ ይህችን አንዷን ከዘጠና ዘጠኙ ጋር ይጨምራታል። ከዚያም ሁሉንም ለፍጡራኑ ይዘረጋቸዋል። ያኔ የሚከሰረው ለኪዛራ ተገቢ የሆነ ሰው ብቻ ነው።*26

በአንዷ ረህመት ብቻ የሰው ልጆች ባጠቃላይ መጠቀማቸው፣ እርሷን መሠረት አድርገው መተዛዘናቸው የዚህችን እዝነቱን ስፋት ያመለክታል። አላህ ሆይ፣ አዛኞችን ነህና እዘንልን። ልትቀጣን ብትችልም አትቅጣን። ጌታችን ሆይ፣ እዝነትህን። ጌታችን ሆይ፣ መልካም ውሳኔህን።

<u>ዘልዓለማዊ መልእክት</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ፍጡራንን በፈጠረ ጊዜ መጽሐፍ ጻፈ። ከዓርሽ በላይ ከርሱ ዘንድ ይገኛል። ከርሱ ላይ፡- እዝነቴ ቁጣዬን ቀድማል የሚል መልእክት ተጽፎበታል።»

*25ኢብን ማጃህና አህመድ
*26ሙስሊምና አህመድ

በሌላ ዘገባም፡- ‹‹እዝነቱ ቁጣዬን አሸንፏል።›› ማለቱን ተናግረዋል።*27

ይህ ዘልዓለማዊ መልእክት እጅግ የተላቀና የተከበረ ከሆነ ስፍራ ተገር ተቀምጧል። ስለዚህም አላህ ከኛ ጋር ባለው ግንኙነት መሠረታዊ ባህሪው እዝነት ነው። የቁጣው ምክንያት የኛ ድርጊት እና ባህሪ ነው። ወንድሜ ሆይ፤ የሕይወት ራእይና ዓላማህን እንደገና መቅረጽ፣ ቅደም ተከተሉን ዳግም ማደራጀት ይኖርብሐል፡ የፍጥረታት አጀማመር ጥልቅ መልእክትና ግዙፍ አላማ ይዟል። ይህንኑ ላንተ ለማድረስ የበኩሌን ጥረት አድርጊያለሁ። ተሳክቶልኝ ይሆን?

<u>ግንኙነትህን ፈትሽ</u>

ከአደም መፈጠር በፊት እውን የሆነ ክስተቶችን በመቃኘት ላይ መሆናችንን ያስታውሷል። አንኳር ነጥቦችን አንስተናል፡ የመጀመሪያ ዝምድናንና እርሷን የመጣስን አደጋ አየን። ከዚያም ተውበትንና የተከፈተ _ በሩን፣ ከሰይጣን የሚጠብቁ _ ሁለት _ አንቀጾችን፣ መካንና ቅድስናዋን፣ በመጨረሻም የአላህን ራህመት ስፋት ቃኘን።

ቀጥሎ አንዲት ነጥብ በማንሳት ቅኝታችንን እንቋጫለን። ይህም ነጥብ ብርሃናዊ እና ረቂቅ መንፈስ የሆነትን መላእክትን የሚመለከት ነው። ስለነርሱ ማውጋት ለቀልብ ተወዳጅ ነገር ነው። ሐሴትን ይረጫል። በመላእክት ማመን የእምነታችን አካል መሆነ ይታወቃል። ስለነርሱ ከማውጋቴ በፊት አንድ ጥያቄ ላቅርብ። መላኢኮችን እንወዳቸዋለን? በመካከላችን ግንኙነት አለን? በየትኛው መልክ? ለእነዚህና ለሌሎች ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ከነቢዩ ሐዲስ ጋር ጥቂት ቆይታ እናደርጋለን። እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹መላኢኮች ከብርሃን፣ ጅኖች ከእሳት፣ ከተገለጸላችሁ ቁስ (ከአፈር) ተፈጠሩ።*28 አደም ደግሞ ለናንተ

*27ቡኻሪና ሙስሊም
*28ሙስሊም እና አህመድ

መላእክት ብርሃናዊ _ ፍጡራን መሆናቸውን እናውቃለን። በዚህም እናምናለን። ግና እንዴት ዓይነት ይሆኑ? እያልን በ አእምሯችንን እናማስንም። መላእክት ከአደም በፊት መፈጠራቸውንም እናውቃለን። ተከታዩ የአላህ ቃል ይህንኑ ያመለክታል፡-

وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَئِكَةِ إِنِّي جَاعِلٌ فِي الْأَرْضِ خَلِيفَةً قَالُوا أَتَجْعَلُ فِيهَا مَن يُفْسِدُ فِيهَا وَيَسْفِكُ الدِّمَاءَ وَنَحْنُ نُسَبِّحُ بِحَمْدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَ قَالَ إِنِّي أَعْلَمُ مَا لَا

ሙሐመድ ሆይ ጌታህ ለመላእክት እኔ በምድር ላይ ወኪል (ኸሊፋህ) ለመፍጠር አቅጃለሁ ባላቸው ጊዜ የሆነውን አሰታውስ፣ ለሕዝቦችህም ተርክላቸው) (አንተን በመወንጀል) ጥፋት የሚፈፅምን፥ ደሞችን (በግፍ) የሚያፈስን (ፍጡር) ከርሷ (ከምድር ላይ ትፈጥራለህን? እኛ አንተን ከማመስገን ጋር ከጉድለት የምናጠራህ፥ የምናወድስህም ሆነን እያለ አለት እናንተ የማታውቁትን አውቃለሁ አላቸው።» (አል በቀራህ 30)

የመላአክት ቅርጽ ምን አይነት ይሆን? ባህሪያቸውስ? አስበህ ታውቃለህ? ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«ጅብሪልን በትክክለኛ ተፈጥሮው _ አየሁት። ስድስት መቶ ክንፎች አሉት። እያንዳንዱ ክንፍ አድማሱን ይሞላል። ወደሰማይ አንድ አቅጣጫ ባየሁ ቁጥር ሞልቶት አገኘዋለሁ።»

ይህን ግዙፍ ፍጡር በምናብህ _ ለማሰብ ሞክር። ራስህን፣ ደካማ ማንነትህን ተመልከት። ምን ያህል ደካማ ፍጡሮች እንደሆንን አየህ? ይህም ሆኖ ግን በአላህ ላይ ስንኮራ፣ ስናምጽበት፣ ወንጀል ስንሰራ ይገርማል።

ዓላማዬ አእምሮህን በመረጃ ማጨቅ ሳይሆን መረጃዎችን ወደ ተግባር መለወጥ ትችል ዘንድ መርዳት ነው። የለበሰውን አቧራ የሚያራግፍለት ሰው ወደሚሻው ቀልብህም መድረስ እከጅላለሁ። እውነተኛ ዓላማዬ ወደ አላህ አንድ እርምጃ መሄድ እንድንችል፣ ከዚያም ሌሎች እርምጃዎችን

እንዲቀጥል መርዳት ነው። ይህ ካልሆነ ልፋቱ ከንቱ ሆኗል። ቀልብ ወደ አላህ መቅረብ ካልቻለ ይህ ጽሑፌ አይፈይዳችሁም።

<u>መተናነስ ያሻናል</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦
‹‹የዓርሽ ተሸካሚ ከሆኑት የአላህ መላኢኮች መካከል አንዱን እንዳወጋ ተፈቀደልኝ ከጆሮው ልም ጀምሮ እስከ ትከሻው ያለው ርቀት ሰባት መቶ ዓመታት ያስኬዳል።*29

ሱብሐነላህ፤ ምን ያህል ደካሞች ነን። አላህ እንዲህ ብሏል፦

انتم أشد خلقا أن السماء تنها) رَفَعَ سَنكَهَا مَونَهَا وَأَعْطَشَ لَيْلَهَا وَأَخرج منها

‹‹እናንተ አጋሪዎች ሆይ ለመፍጠር ይበልጥ አስቸጋሪ የትኛው ነው? እናንተ ወይስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት፡ ጣሪያዋን አጓነ አስተካከላትም። ሌሊቱን ጨለማ፡ ቀኑን ግልጽ አደረገ።›› ‹‹አል ናዚአት 27-29)

የዚህን መላኢካ ግዝፈት አስተውል። ከአላህ ፍጡራን መካከል አንዱ ነው። አንተም እንደዚሁ። ይህን ያህል ግዙፍ ፍጡር ሆኖ አላህን ይታዘዛል። ለርሱ ይተናነሳል። አንተስ እንደርሱ ነህ ወይስ ባህሪህ ከዚህ ይለያል?
መላእክት ክንፍ እንዳላቸው አላህ እንዲህ በማለት ገልጿል፡

الْحَمْدُ لِلَّهِ فَاطِرِ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ جَاعِلِ الْمَلَكَةِ رُسُلًا أُولَ أَجْنِحَةٍ مَنْقَ وَثُلَثَ وَرُبَعَ
فِي الْخَلْقِ مَا يَشَاءُ إِنَّ اللَّهَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ خاطر ١ يَزِيدُ في) .
ምስጋና ለአላህ ይሁን፡ ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ መላእክትንም ሁለት ሁለት ሦስት ሦስት ወይም አራት አራት ክንፎች ያሏቸው መልዕክተኞች አድራጊ ለሆነው (አምላክ) በፍጡራኑም ውስጥ የሻውን ይጨምራል። እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነውና።›› (ፋጢር ١)

*29አቡ ዳውድ

በምድርም ሆነ በሰማይ የታላቁ ወገኖችን የሚያመለከተን ግሩም አዳ ተላልፏል። ጅብሪል ከበይ ዘንም መጣና እናንተ ዘንደ ብሄር ከመታ የተሳተፉትን እንዴት ታዩአቸዋላችህ ሲል ጠየቃቸው። ከመካከላችን ምርጦች እነርሱ ናቸው። አሎ። ሳኛ መላእኮችም በበይር ዘመን የተሳተፉትን የምናዬው እንደዚሁ ነው›› አላቸው።

<u>ኢባዳቸው ከኛ ኢባዳ አንጻር</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል።
“ሰማይ ልትወድቅ ቀረበች። እንዲያ መሆን ይገባታል። ምክንያቱም የአንዲት ጣት ማረፊያ የምታክል ቦታ የለባትም የቆመ፤ ሩኩእ ወሃም ሱጁድ ያደረጉ መላእክት ያሉበት ቢሆን እንጅ። ቂያማ ጋር “አምላካችን ሆይ፣ ክብር አላመለክንህም፣ይላሉ።*30 ላንተ ይሁን። በተገበያ ሁኔታ

ያ አላህ፣ እኛስ ምን እንበል? ተከታዩን የአላህ ቃል አላነበብን ይሆን

(إن بنا بذهِكُمْ وَبَأْتِ بِخَلْقٍ جَدِيدٍ لا

“ቢሻ እናንተን አጥፍቶ አዲስ ፍጠር ይተካል።›› (ፋጢር 16)

አላህን በማምለካችን ተጠቃሚዎች እኛ እንጅ እርሱ አይደለም፡ መላኢኮች እንዲህ አይነት ዓቢዶች ከመሆናቸው ጋር አላህ ለአያም ክብር እሰገዳቸው። ከአላህ ዘንድም ያለህን ክብር አየህን?

ይህም ሆኖ መላእክት ለኛ ዱዓ ያደርጋሉ። ምህረት ይለምንልናል። በሁለት ወገኖች መካከል ያለ ግንኙነት። አንደኛው ወገን መላኢኮች ሲሆነ ግንኙነቱ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አሟልተዋል። ሁለተኛዎቹ ወገኖች እኛ የሰው ልጆች ስንሆን ሐላፊነታችንን አልተወጣንም።

30*አህመድ

የአደም አፈጣጠር

መሠረታዊ ዓላማ

የአደምን አፈጣጠር በማስመልከት የማስተላልፈው መልእክት አላማ ለአላህ መተናነስንና መዋደቅን እንድንማር፣ ምን ያህል ደካሞች፣ ወራዶችና ከጃዮች መሆናችንን እንድንረዳ ማድረግ ነው።

በአደም መፈጠርና ለአላህ በመተናነስ ባህሪ መካከል ጥብቅ ትስስር እናገኛለን። እኛ ብልሐትም ሐይልም የሌለን ደካማዎች፣ ካለመኖር ወደ መኖር የመጣን ኢምንቶች መሆናችንን በጥልቀት ስንረዳ የመተናነስ ስሜት ይሰርጸናል።

የአጀንዳችን አስኳል ይህ ነው። ምን አልባትም ከላይ የጠቀስኩት የመተናነስ ስሜት ያልተሰማው ሰው ይኖራል። ግና እንደሚሰማው እተማመናለሁ። በቅርቡ

የአደም አፈጣጠር እርከኖች

በቁርአን ውስጥ አላህ አደምን ከአፈር መፍጠሩን እናነባለን፡-

(إِنَّ مَثَلَ عِيسَى عِندَ اللَّهِ كَمَثَلِ ءَادَمَ خَلَقَهُ مِن تُرَابٍ ثُمَّ قَالَ لَهُ كُن فَيَكُونُ

«ከአላህ ዘንድ ዒሳ እንደ አደም አምሳያ ነው። (አላህ አደምን) ከአፈር ፈጠረው ሁን አለው ሆነ። »(አሊ ዒምራን 59)

በሌላ የቁርአን አንቀጽ ደግሞ ከጭቃ መፈጠሩ ተጠቅሷል፡

إِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي خَٰلِقٌۢ بَشَرا من طين (ص ٧١

“ጌታህ ለመላክእት:- “እኔ የሰውን ልጅ ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ” ባለጊዜ (የሆነውን አስታውስ)» (ሷድ 71) በሌላ አንቀጽም ከሚጣበቅ ጭቃ መፈጠሩ ተመልክቷል፡

(النتينِهِمْ أَهُمْ أَشَدُّ خَلْقًا أَم مَنْ خَلَقْنَا إِنَّا خَلَقْنَهُم مِن طِين لاري

ሙሐመድ ሆይ! ሞቶ መነሳትን የሚያስተባብሉትን) ጠይቃቸው። ለመፍጠር ይበልጥ አስቸጋሪ እነርሱ ናቸው ወይስ (ሌሎች) ፍጡራኖቻችን? ከሚያጣብቅ ጭቃ ፈጠርናቸው (አልሷፋት ፲፩) በሌላ አንቀጽም ከሚቅለጨለጭና ከሚገማ ጭቃ መፈጠሩ ተብራርቷል፡-

(وَلَقَدْ خَلَقْنَا الإنسَنَ مِن صَلْصَلٍ مِّنْ حَمَإٍ مَسْنُونِ

MA የሰውን ልጅም ከሚቅጨለጨል እርጥብ ሸክላ ጠረን ካለው ጥቁር ጭቃ ፈጠርነው።›› (አል ሂጅር 26)

በሌላ አንቀጽም ከደረቅ ጭቃ መፈጠሩ ተነግሯል፡-

نَ مِن صَلْصَلٍ كَالْفَخَارِ خَلَقَ الْإِنسَنَ مِن

የሰውን ልጅ እንደሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠረው።››

(አል ረህማን 14)

ሱብሐነላህ! ብዥታን ይፈጥራል። አደም የተፈጠረው ከየትኛው ቁስ ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ ግልጽ ነው። አደም የተፈጠረው ከላይ ከተዘረዘሩ ቁሶች ሁሉ ነው። አንቀጾቹ አደም ሲፈጠር ያለፈባቸውን እርከኖች ይገልጻሉ። አደም ሲፈጠር በርካታ እርከኖችን አልፏል። እያንዳንዱ እርከን ወደ ቀጣዩ እያሸጋገረ በመጨረሻም አደም የተሟላ ፍጡር ሆኗል።

<u>ከርሷ ፈጠርናችሁ</u>

የአደም አፈጣጠር እርከኖች ስድስት ሲሆኑ ሁሉንም በአላህ እገዛና ፈቃድ እንመለከታቸዋለን።

ገለጻ ከመጀመራችን በፊት አንድ ነገር ማስታወስ እንሻለን። እያንዳንዱ እርከን የሚያስተላልፈው የራሱ መልእክት አለው። አላህ ይህን መልእክት እና ሚስጥር እንድትገነዘቡ ይሻል።

የመጀመሪያው እርከን አፈር ነው። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህ አደምን ከምድር በቆነጠራቸው አፈሮች ፈጠረው። ጅብሪልን፡ ከሁሉም የምድር አይነቶች አፈር ቆንጥረህ አምጣ፣ ሲል አዘዘው። የአደም ልጆች አፈሩ በተቆነጠረባቸው መሬቶች ልክ ሆኑ፡»

የአደም ልጆች በአካላዊ ገጽታና ባህሪ የተለያዩት ከምድር : የተለያዩ አፈሮች ስለተሰሩ ነው። እናም ነጭ፣ ቀይ፣ ጥቁር። እንዲሁም ልስልስ፣ ቆዛሚ፣ ጥሩ፣ መጥፎ በመሆን በገጽታና በባህሪ የተለያዩትም ለዚሁ ነው።

ይህ እርከን የመተናነስን በር እንዳንረግጥ፣ በዘር እንዳንበላለጥ የሚያደርገን የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ከአፈር መፈጠራችን የታወቀ ሆኖ እያለ ኩራት ለምን?

<u>የባህሪ መመሳሰል</u>

የአደም ልጅ ሆይ፣ ጅምርህ አፈር ነበር። ከአፈር ብዙ ባህሪዎችን ወርሰሐል። የቆዳ ቀለምህ ልክ እንደ አፈር ቀይ፣ ጥቁር ወይም ሌላ ነው። የአፈርን ባህሪም ወርሰሐል። ከፊል ሰዎች የመልካም እና የለም አፈር ባህሪ አላቸው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች አላህን በአንድ ሚባዳ ወይም መልካም ንግግር እንዳወቁት ወዲያውኑ ከርሱ ጋር በቀላሉ ይተሳሰራሉ። ከልቦናቸው ያረፈውን የእምነት ችግኝ ልክ እንደ ለም አፈር ተቀብለው በመንከባከብ ያፋፋሉ። የመጥፎ መሬት ባህሪ ያላቸው ሰዎችም አሉ። የቱን ያህል ቢመከሩና ቢዘከሩ ወደ በጎ አይመለሱም። በእሾህ እንደተሞላ መሬት አስቸጋሪ፣ ለሌሎች በጎ የማይወድ፣ ቀልቡ ደረቅ፣ በምቀኝነትና በጥላቻ የተሞላ ሰውም ታገኛለህ። እንደ ገርና ሜዳማ መሬት ባህሪው ገር፤ ከሰዎች ጋር በቀላሉ የሚግባባ፣ ምክርን የሚቀበል፣ ተግሳጽ በቀላሉ የሚሰርጸው ሰውም ታገኛለህ።

ሁላችንም ቆም ብለን ስለራሳችን እናስብ። ራሳችንን እንወቅ። የትኛው የአፈር አይነት ባህሪ እንዳለብን፣ ባህሪያችን እንዴት እንደሆነ፣ እንወቅ። ነውሩ መሳሳት ሳይሆን ከስህተት አለመማር መሆኑን እንገንዘብ።

<u>አስገራሚ ነገር</u>

ቂምርህ አፈር ነው። አፈርን እንዲናገር፣ እንዲቀሰቀስ ያስቻለ አምላክ ክብሩ ይስፋ። የሰውን ልጅ ከአፈር ፈጥሮ አዳዲስ ነገሮችን የሚፈጥር፣ ምድርን የሚለውጥ፣ ያደረገው አምላክ ክብሩ ይስፋ። ሱብሐነላህ!

መነሻህ አፈር እንደሆነ ሲታወስህ ደካማነትህ አይሰማህምን? ይህም ሆኖ አምላክህን ለመሐጥየት እንዴት ደፈርክ? ልትኮራ እንዴት ደፈርክ? ለአላህ አለመስገድህ ኩራት መስሎ አልታየህምን? እህቴ ሆይ፣ አንች የምድር አፈር ሆይ፣ «ሂጃብ ስለማላምንበት ማድረግ አልችልም› የሚለውን ቃል ከአንደበትሽ ለማውጣት እንዴት ደፈርሽ?› አላህ እንዲህ ብሏል፡-

قبل الإنسنُ مَا أَكْفَرَهُ مِنْ أَيِّ شَيْءٍ خَلَقَهُ فَقَدْرَهُ ثُمَّ السَّبِيلَ يَتَرَهُ

የሰው ልጅ ተረገመ፤ ለክህደት መዳረጉ እጅግ የሚደንቅ ነው (አላህ) ከምንድን ነው የፈጠረው? ከፈትወት ጠብታ ፈጠረው፤ መጠነውም። ከዚያም (ጐዳናውን) ገርና ቀላል አደረገለት። ከዚያም ለሞት አበቃው፣ እንዲቀበር አደረገውም። በሚፈልግ ጊዜም (ከሞት ይቀሰቅሰዋል።» (ዓበስ 17-22)

አህ! ሁኔታው ይገርማል። ምንም አቅም እንደሌለህ፣ የምንም ነገር ባለቤት እንዳልሆንክ እንዴት ተዘነጋህ።

አንተ የምድር አፈር ሆይ፣ ተናነስ። የአንተ መነሻ የሆነው አፈር ራሱን ዝቅ አድርጎ እግሮች እንደሚረግጡት በመፍቀዱ አላህ ክብርን ለገሰው። ግንባሮች ይሰግዱለት ዘንድ ተገቢ ሆነ። እናም ተናነስ። አሁንም ተናነስ። ትሁት ሁን። አፈር እንጅ ሌላ አይደለህምና።

አፈር ወደ ወርቅነት ተቀየረ

ነቢዩ (ሰዐወ) አኢሻን እንዲህ ብለዋታል፡-

«አኢሻ ሆይ፣ ብፈልግ ኖሮ የወርቅ ጋራዎች አጅበውኝ በተጓዝኩ ነበር።» «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እንዴት?» በማለት ጠየቀቻቸው። እንዲህ አሏት፡-

«ከሰማይ መላኢካ መጣልኝ። መሐከሉ እንደ ካእባ ዓይነት ነው። የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ አላህ ሰላምታ አቅርቦልሐል። መላኢካ ነብይ ወይም ባሪያ ነብይ ትሆን ዘንድ አስመርጦሐል።» አለኝ። ጅብሪልን ተመለከትኩ። ራስህን አስተናንስ» የሚል ምልክት አሳየኝ። ነብይ ባሪያ መሆኑን መረጥኩ። » (ጦበራኒና አቡ የእላእ)

አላህ ሆይ፣ በተላቀ እጃቸው አጠጣን። የሚቆርጥልንን ጣፋጭ መጠጥ። አሚን ጥምን ለዘልዓለም

ረሃብ ጠንቶባቸው ከሆዳቸው ላይ ድንጋይ የሚያስሩት የአላህ መልእክተኛ፣ አላህ በለገሰህ ሲሳይ እና እድል መደሰትን እንዲሁም መተናነስን ያስተምሩሐል። «ሙሐመድ ሆይ፣ ራስህን አስተናንስ

አንተ የምድር አፈር ሆይ፣ ራስህን ዝቅ ባደረግክ ቁጥር ፣ ከአምላክህ ልቅና አኳያ መተናነስ በተሰማህ ቁጥር በስብእናህ፣ በባህሪህ፣ ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት ወርቅ ትሆናለህ። እጹብ ድንቅ ትሰኛለህ።

አንተ የምድር አፈር ሆይ፣ አፈር በሆንክ ቁጥር ወርቅ እየሆንክ ትሄዳለህ። ለብልህ ምልክት ብቻ ይበቃዋል።

የሰያሜው ምክንያት

አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ማለቱን ነቢዩ ነግረውናል፡

ለኔ እንዲህ የተናነሰልኝ (የእጃቸውን ሆድ ወደ መሬት ዝቅ አድርገው)፣ እንዲህ ከፍ አደርገዋለሁ፡ ፡ (የእጃቸውን ሆድ ወደ ላይ አንስተው)።»

መተናነስ፣ አፈር መሆን እንደ ወርቅ ለመወደድ እና ለመከበር ያበቃል። ቀጥሎ ወደ ስያሜው እናምራ። አደም ለምን በዚህ ስያሜ ተጠሩ? ከምድር ቆዳ (አደም)፣ ከአፈር የተገኙ በመሆናቸው ነው። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

ሁላችሁም የተገኛችሁት ከአደም ነው። አደም የተገኘውም ከአፈር ነው፡ ፡» (ረቢእ)

የአደምን አፈጣጠር የመጀመሪያ እርከን ቃኝተናል።ከዚህ እርከን ያገኘነውን ጠቃሚ ትምህርት ወደ ተግባር እንለውጠው። ሶላትን በወቅቱ መስገድ ባህሪያችን ይሁን። «አላሁ አክበር» የሚለውን የአዛን ድምጽ በሰማን ቁጥር ምላሻችን ፈጣን ይሁን። መነሻችንን አውቀናል። ከዛሬ በኋላ ላንኮራ ቃል ገብተናል።

<u>የንጽህና ተምሳሌት</u>

ወደ ሁለተኛው እርከን እንሸጋገር። እርሱም ጭቃ ነው። ከአፈሩ ላይ ውሃ ሲታከልበት ጭቃ ሆነ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

إِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي خَٰلِقُۢ بَشَرًا مِن طِينٍ مصر : ٢١٠

«ጌታህ ለመላክእት- እኔ የሰውን ልጅ ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ። ባለጊዜ የሆነውን አስታውስ)።» (ሷድ 71)

እዚህ ላይ ትኩረት የሚሻ ነጥብ አንስተናል። አላህ ውሃን ለምን መረጠ፡

ከአፈሩ ጋር ሌላ ነገር- ለምሳሌ ብረት- ለምን አልቀላቀለም?
ይህ የሆነው ለሁለት ምክንያቶች እንደሆነ አስባለሁ። አንደኛ፡- መተናነስንና ትህትናን ማስተማር

ሁለተኛ፡- እጅግ ጠቃሚ መልእክት ያለው ጉዳይ ነው። ይህውም የውሃ አንዱ ጠቀሜታ ንጽህና መሆኑን እናውቃለን። ምድርን በተመለከተም ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

ምድር ለኔ መስገጃ ቦታ፤ አፈራም ንጹህ ተደረገልኝ። (ሙስሊም) ውሃ በማይኖር ጊዜ በአፈር ተየመም እንደምናደርግ ይታወቃል። የዚህ ሚስጥሩ ውሃም አፈርም የንጽህና ግልጋሎት የሚሰጡ መሆናቸው ነው፡

የሰው ልጅ ሆይ፣ መሠረትህ ንጹህ ነገር ነው። አላህ ንጹህ ከሆነ ቁሶች አዋቅሮሐል። ስለዚህም ይህን ንጽህና እንዳታቆሽሽው ተጠንቀቅ። አላህን በሚያስቆጣ ነገር ውስጥ በመሳተፍ ለምሳሌ ኢ-ሞራላዊ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን በመከታተል ንጹህ ማንነትህን እንዳታረክሰው ተጠንቀቅ።

<u>የእስልምና ጸጋ</u>

ጸጋ የሰው ልጅ መነሻው ንጹህ ነው የሚለውን ይህን የእስልምና እይታ ከምእራቡ አለም ምልከታ ጋር ስናነጻጽረው የእስልምና ይገለጽልናል። አንድ ዓለም አቀፋዊ ሐሳብ አፍላቂ (Thinkers) የሰውን ልጅ በተመለከተ እንዲህ ብሏል፡-

«የሰው ልጅ ማለት በሕይወት ቆሻሻ ውስጥ የሚኖር እርኩስና ወራዳ ተባይ ነው።»

ኢስላም ደግሞ የሰው ልጅ ወራዳ ሳይሆን የተከበረ፣ ቆሻሻ ሳይሆን ንጹህ ፍጡር ነው ይለናል። ከሁለት ንጹህ ነገሮችን ከአፈርና ከውሃ- መፈጠሩን ይነግረናል። ለእያንዳንዱ ወጣት ተከታዩን ጥሪ አስተላልፋለሁ፡-

ወጣቶች ሆይ፣ እባካችሁን ንጹህ ተፈጥሯችሁን በድርጊታችሁ አታቆሽሹት። ዝሙት የሚሰራ ራሱን እያቆሸሸ ነው። ከንጹህ የውሃ ገንዳ ውስጥ ዓይነ ምድር በመጣል እንደሚያበላሸው ማለት ነው።

ስለዚህም ለንጽህናችሁ ክብደትና ግምት ስጡ። ጠብቁትም። ከሙስሊም የሚጠበቀው ይህ ነው። እንዲህ ባላቃችሁና የላቀ ደረጃችሁን

ባሳወቃችሁ ሃይማኖታችሁም ኩሩ። አላህንም ሙስሊም ስላደረጋችሁ አመስግኑት። ከናንተ ውጭ ያሉ ሰዎች ራሳቸውን እንዴት እንደሚያዩ አስተውሉ፦ «ቆሻሻ ተባይ» አድርገው ራሳቸውን ይመለከታሉ።

<u>የሚያጣብቅ ጭቃ</u>

የአደም አፈጣጠር ሦስተኛ እርከን ይከተላል። ይህውም ጭቃው በአንድ ይሰበሰባል። እርስ በርስ ይጠባበቃል። ጭቃ እንዲህ ሲሆን ወደፈለጉት ቅርጽ ለመቀየር ይገራል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

إِنَّا خَلَقْنَٰهُم مِّن طِينٍ لَّازِبٍ) الصافات: ١٩ ከሚያጣብቅ ጭቃ ፈጠርናቸው» (አል ሷፋት ፲፩)

እዚህ ላይ እጅግ ጠቃሚ ትምህርት እንቀስማለን። ጭቃው እርስ በርሱ የተያያዘ፣ የተጣበቀ ጠንካራ እንጅ እየተቆራረሰ የሚወድቅ ልፍስፍስ አይደለም። ይህ እውነታ ተከታዩን መልእክት በአንደምታ ያስተላልፋል፡አንተ ሰው ሆይ፣ ጥንካሬና ጽናት የስሪትህ አካል ናቸው።

ስለዚህም ጽኑ መንፈስ፣ ጠንካራ ወኔ ያለው ፍጡር ሁን። አላህን በመታዘዝ ይህን አቅምህን አሳይ።

ወንድሜ ሆይ፣ መሠረታዊ ዓላማችንን አትዘንጋ። መተናነስን፣ ትህትናን። በአላህ እምላለሁ፣ የአላህ እገዛ የሚያሻህ ደካማ ፍጡር ነህ። መጀመሪያ አፈር ነበርክ። ከዚያም ጭቃ ሆንክ። ሌሎች እርከኖችን አልፈህ አንደበት ያለው ፍጡር ለመሆን በቃህ።

ለዚህ ደረጃ መብቃትህ ትልቅ ጸጋ አይደለምን? ይህ አይሰማህምን? ጸጋስ ጭቃ የነበርክበትን እርከን አስታውስ። መናገር፣ መንቀሳቀስ ፣ መተንፈስ የማትችልበትን የሕይወት ዑደት ለማሰብ ሞክር። ገና በመፈጠር ሂደት ላይ የነበርክበትን፣ ካለመኖር ዓለም ውስጥ የሆንክበትን።

ከአምላክህ ዘንድ ያለህ ዋጋ

ከዚያም አራተኛው እርከን ይከተላል። አላህ በተከበሩ እጆቹ ያበጀህና የሚቅለጨለጭ ሽክላ ዓይነት ይሆናል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

( ) قَالَ ينابيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسْجُدَ لِمَا خَلَقْتُ بِيَدَى أَسْتَكْبَرْتَ أَمْ كُنتَ مِنَ الْعَالِينَ

«(አላህም)- “ዲያብሎስ ሆይ! በእጄ ለፈጠርኩት ፍጡር ላለመስገድ ምክንያት የሆነህ ምንድን ነው (አሁን) ኮራህን ወይስ ቀድሞውኑም ከትዕቢተኞቹ ነበርክ? (አለው) (ሷድ 75)

የሰው ልጅ ሆይ፣ ከአምላክህ ዘንድ ያለህን ክብር አስተውል። በተላቁ እጆቹ በመፍጠር ልቅናን አጎናጸፈህ። ይህን ሁሉ አድርጎልህ እያለ ትእዛዙን ትጥሳለህ? ታምጽበታለህን?በዚህ ክብርህ ሳቢያ ከአላህ ዘንድ ውድ ዋጋ አለህ። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- (ዘ

«ሦስት ነገሮችን አላህ በእጁ ፈጥሯቸዋል። ከነዚህ ውጭ በእጁ የፈጠረው ሌላ ነገር የለም። እነርሱም አደም፣ ጀነቱል አድናንና ለሙሳ የጻፈላቸው ሰሌዳዎች ናቸው።»

ሌሎችን ፍጡራን ግን «ሁን» በሚለው ቃሉ ነው ያስገኛቸው።

አላህ ለሰው ልጅ የለገሰው ይህ ልቅና አንዳች ስሜት አያጭርብህምን? መልስልኝ እንጅ። ምነው በዝምታ ተሸበብክ? ወይስ በተመስጦ በማሰብ ላይ ነህ? እንዲያ ከሆነ ጥሩ ጅምር ነው። ከአላህ ዘንድ ያለን ደረጃ ይህ ሆኖ እያለ ከወንጀል ቆሻሻ ውስጥ በመዘፈቅ ለምን ራሳችንን እናዋርዳለን?

አምላኬ ሆይ! ወዳንተ ቶበትኩ

አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

«የአደም ልጅ ሆይ፣ በእጄ ፈጠርኩህ። በጸጋዬም አደግክ። ይህም ሆኖ ትእዛዜን ትቃረናለህ። ሐጢአት ትፈጽማለህ። ወደኔ ከተመለስክ ይቅር እልሐለሁ። እንደኔ አይነት የት ታገኛለህ? እኔ መሐሪና አዛኝ ነኝ።»

_አምላኬ ሆይ፥ እኔ ራሴን በጣም በድያለሁ። ካንተ ሌላ ወንጀልን የሚምር የለምና አምላኬ ሆይ፣ ምህረትህን ፡ አምላኬ ሆይ፥ እዝነትህን።

ወንጀሌ በዝቷል። መከራዬ ጠንቷል። መላም ጠፍቶብኛል። ስለዚህም አምላኬ ሆይ፣ ተቀበለኝ። ማረኝ። እዘንልኝ፡

<u>የሚገማ ጭቃ</u>

በአምስተኛው እርከን የሚቅጨለጨል ሸክላ የሆነው አካል እስኪደርቅ እና ጠረኑ እስኪቀየር ድረስ ተቀመጠ። ቀለሙም ተቀይሮ ጥቁር ሆነ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَلَقَدْ خَلَقْنَا الإِنسَنَ مِن صَلْصَلٍ مِنْ حَما مَسْنُونِ) الحجر: ٢٦ የሰውን ልጅም ከሚቅጨለጨል እርጥብ ሸክላ ጠረን ካለው ጥቁር ጭቃ ፈጠርነው።›› (አል ሂጅር 26)
እስኪደርቅ ድረስ ተቀመጠ።›› የሚለውን ሐረግ አስተውል። ደካማነትህን ተመልከት።
ባለፉት እርከኖችም ይህ የደካማነት ስሜት ተሰምቶሐልን?

<u>በእርግጥም ደካማ ነህ</u>

በስድስተኛው እርከን ወደ ሸክላነት ተቀየረ። ሩህ(ነፍስ) የሚባለውን ነገር ለማስተናገድም ዝግጁ ሆነ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

حمن
خَلَفَ الإِنسَانَ مِن صَلْصَلٍ كَالْفَخَارِ)

የሰውን ልጅ እንደሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠረው

ባልረህማን 14)

አብሊስ በዚህ ሕይወት አልባ ፍጡር ዙሪያ ይዞር እንደነበር ተነግሯል። ይህም እርከን ለሰው ልጅ ተከታዩን አዋጅ ያስተላልፋል፤

የአደም ልጅ ሆይ! ጅምርህ አፈር እና ውሃ የሆነ ምንም የማድረግ አቅም የሌለህ ደካማ ፍጡር ነህ አፈሩን የሚያስብ፣ የሚኖር፤ የሚቀሰቀስ የሚመራመር፣ አዳዲስ

ነገሮችን የሚፈጥር ድንቅ ፍጡር ያደረገው የአላህ ችሎታ ነው።)

እዚህ እርከን ላይ አደም ነፍስ አልባ በድን ሆነው ቆመዋል። በዚህ

ሁኔታ ውስጥ ለአርባ ዓመታት ተተወ። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- ይት

‹‹አደም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለ40 ዓመታት ተተወ። ይህ የሆነው ደካማነቱን ለማሳየት ነው። ቅርጻዊ ማንነቱ በኋላም ነፍስ አልባ፣ እንቅስቃሴ አልባ ነበር፡

<u>ደካማ ጎኑን አውቆታል</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

አላህ አደምን በጀነት ውስጥ ቅርጻቸውን ካበጀ በኋላ እርሱ እስከፈቀደው ጊዜ ድረስ ባሉበት ሁኔታ ተዋቸው። ኢብሊስም ዙሪያውን እየዞረ አያቸው። ባዶ ሆነው ባገኛቸው ጊዜ ስጋዊ ስሜቱን ለመቆጣጠር የሚከብደው ፍጡር መሆናቸውን ተረዳ።

ይህን ሐዲስ ሙስሊም ዘግበውታል። ስጋዊ ስሜቱን ማሸነፍ የማይችል ፍጡር›› የሚለውን ገለጻ ልብ ይሏል። ሰይጣን የሰውን ልጅ በዚህ በኩል በቀላሉ ሊያጠቃው ይችላል ማለት ነው። ሰይጣን ይህን ፍጡር እንዴት እንዳጠናው አያችሁን? ጥቃቱን የሚሰነዝረው በግብር ይውጣ ሳይሆን በተጠና መልኩ ነው።

እነሆ ኢብሊስ ደካማ ጎንህን አውቋል። አላህ ግን ነገሩን እንደዚሁ አልተወውም። ስር ነቀል መፍትሄ አበጅቶለታል፡ የሰይጣንን ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ መሣሪያ ለሰው ልጅ ለግሶታል። እንዲህ ብሏል።

(إِنَّ عِبَادِى لَيْسَ لَكَ عَلَيْهِمْ سُلْطَانُ إِلَّا مَنِ العَكَ مِنَ المارِينَ

በባሮቼ ላይ (ቅንጣት) ሥልጣን የለህም ራሳቸውን ለጥመት የዳረጉትና የተከተለሁ ሲቀሩ - (አል ሂጅር 42)

ብቸኛው መፍትሄ ይህ ነው። የአላህ ባሪያ መሆን። የርሱን ጥላ ከለላነት መሻት፣ ወደርሱ መጠጋት፣ በርሱ መጠበቅና መታገዝ፤ መዳንን ከርሱ ዘንድ መሻት። የሰው ልጅ ሆይ፥ አእምሮህን በፍጥነት አሰራና ስድስቱን እርከኖች ካስታወስክ በኋላ ለሚከተለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሞክር፡-

هل أتى على الإنسان حين من الدهر لم يكن شَيْئًا مذكورا - ሳይኖረው የሰው ልጅ የሚታወስ ሳይሆን ሕልውና ሳይኖረው ረዥም ዘመን ተቆጥሯል ። (አል ኢንሳን 1)

<u>ቀልብህን ሰብስብ</u>

ይህን እርከን በዓይነ ሕሊናህ ለማየት ሞክር። አደም ሕይወት አልባና ባዶ ሆነው ጀነት ውስጥ ተጥለዋል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትልቅ ነገር ይከሰታል። አስገራሚ ተአምር እውን ይሆናል። ስለዚህ ትንፋሽህን ሰብስብና የሚሆነውን በጥሞና ተከታተል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(فإذا سويته ونفخت فيه من روحي فَقَعُوا الله سعدين

(ውብ አድርጌ) በቀረጽኩትና ከመንፈሴም በነፋሁበት ጊዜ ለርሱ ስገዱ። (አል ሃጀር 29)

አካሉ ከመሬት ንጹህ ቁሶች -ከውሃና ከአፈር የተዋቀረው፣ አላህ በተላቁ እጆቹ ያበጀው አደም መለኮታዊ እስትንፋስ ተነፋበት።

የሰው ልጅ ዋጋ ይበልጥ እየናረ ክብሩ እየመጠቀ፣ ማንነቱ ይበልጥ እየደመቀ ሄደ። ደረጃህን አሁን ተረዳህን ተራ ፍጡር አይደለህም። ክሌሎች ፍጡራን ትለያለህ። የአደም ልጅ ነህና። በምድር ላይ የአላህ ወኪል የሆነው አደም፤ አላህ መላእክትን ያሰገደለት አደም። አሁንስ የላቀ ደረጃህ ተገለጸልህን

ከዚህ በላይ ክብር የለም

አላህ ለሰው ልጅ የለገሳቸውን ሦስቱን ክብሮች የሚያሳየውን አንቀጽ ደጋግመን እናንብበው፡-

فَإِذَا سَوَّيْتُهُ وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن رُّوحِي فَقَعُوا لَهُ سَجِدِينَ) الحجر

(ውብ አድርጌ) በቀረጽኩትና ከመንፈሴም በነፋሁበት ጊዜ ለርሱ ስገዱ፡ (አል ሂጅር 29)

በአንቀጹ ውስጥ የተካተቱት ክብሮች እንዳስደሰቱህ እገምታለሁ። ግልጽ ናቸው።

አንድ፡- አስተካከልኩት- ማለትም በጣም ባማረ ገጽታ ፈጠርኩት፤
ሁለት፡- ከመንፈሴ ነፋሁበት፤
ሦስተኛ፡- መላእክትን አሰገድኩለት፤

አላህ ይህን ያህል አልቆጠል። ክብርህን አምጥቆታል። ደረጃህን አጉኖታል። የሰው ልጅ ሆይ፣ አእምሮህ የት ገባ? ለድርጊቶችህ ተጠያቂ የሆነው ቀልብህስ የት ደረሰ? የአምላክ እስትንፋስ በውስጥህ መኖሩ ልዕልናን ሊያላብስህ ሲገባ መርከስ ለምን?

ከኔ ሌላ አምላክ አለህን?

ከላይ የቀረበው ማብራሪያ ስሜትህን አለመሰርሰሩ ተስፋ አያስቆርጥም። ዘግይቶም ቢሆን በጎ ነገር እንደማያመልጥህ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም አካልህም ውስጥህም ንጹህ ነውና። አሁን ቀልብህን ማናገር እፈልጋለሁ፡ እርሷ ከተስተካከለች ሌሎች የአካል ክፍሎችህ ይስተካከላሉና። መልእክቴን እነሆ፣ አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

‹እኔ የሰው ልጅ እና አጋንንት የሚገርም ዜና አለን። እኔ ፈጥሬው እርሱ ሌላ ያመልካል። እኔ ሲሳይ ሰጥቼው _ እርሱ _ ሌላን አካል ያመሰግናል። በጎ ነገሬ ወደባሮቼ ይወርዳል። የነርሱ ክፉ ነገር ወደኔ ይመጣል። እኔ ከነርሱ ምንም ነገር የማልፈልግ ሆኜ እያለ በእዝነቴ

የነርሱን ውዴታ ለማግኘት እጥራለሁ። እነርሱ ግን እኔን የሚከጅሉ ሆነው እያለ በሐጢአት ያስቆጡኛል። እኔን የሚያስታውሱ አብረውኝ ናቸው። ከኔ ጋር መሆን የፈለገ ያውሳኝ። የሚታዘዘኝን እወዳለሁ። የሚያምጹብኝ ከእዝነቴ ተስፋ እንዲቆርጡ አላደርጋቸውም። ወደኔ ከቶበቱ ወዳጃቸው ነኝ። እምቢ ካሉም ሐኪማቸው ነኝ። ከነውር ላጸዳቸው በመከራ እፈትናቸዋለሁ። በጎ ስራ ከኔ ዘንድ አስር እና ከዚያ በላይ እጥፍ ምንዳ ያስገኛል። ወንጀልን ግን ራሱን ብቻ እጽፋለሁ፣ ወይም ይቅር እላለሁ። በክብሬና በልቅናዬ እምላለሁ፣ ከወንጀል ምህረት ከጠየቁኝ እምራቸዋለሁ። ቶብቶ ወደኔ የመጣን ከሩቁ እቀበለዋለሁ። ከኔ የሸሸን ፡ ከቅርብ ሆኜ እጠራዋለሁ። የት ትሄዳለህ? ከኔ ሌላ አምላክ አለህን? እለዋለሁ።»

ይህን ሐዲስ ሰምቶ ስሜቱ የማይነሳ ምን አይነት ቀልብ ነው? ይህን መልእክት አድምጦ የማያነባ ዓይን ምን አይነት ዓይን ነው? «ከኔ ሌላ አምላክ አለህን?» የሚለው ጥያቄ አልናጠህምን? «እኔ ወዳጃቸው ነኝ» ማለቱ አልወዘወዘህምን?» «ምህረት ከለመኑኝ እምራቸዋለሁ» የሚለው ቃሉ አልነቀነቀህምን?

<u>ከኔ ለሸሹት ያለኝ ጉጉት</u>

አላህ ለዳውድ እንዲህ የሚል መልእክት አወረደላቸው፡

ከኔ የሸሹ ሰዎች ለነርሱ ያለኝን ፍቅርና ጉጉት ቢያውቁ ኖሮ በናፍቆት ተቃጥለው ወደኔ በተመለሱ ነበር። ዳውድ ሆይ፣ ከኔ ለሸሹት ያለኝ ጉጉት ይህን ያህል ከሆነ ወደኔ ለዞሩት ያለኝ ፍቅርስ ምን ያህል ይሆናል?»

ይህ ሐዲስ ያዘለው መልእክት የሚፈጥረውን ልዩ ስሜት ለመግለጽ አንደበት አቅም ያንሰዋል። ብእር ይሳነዋል። ቃላት ይልፈሰፈሳሉ። ፊደላት ክህሎት ያጣሉ።

<u>ምን ነካህ?</u>

አላህ በሐዲስል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹ባሪያዬ ሆይ፣ ካለመኖር ወደ መኖር አመጣሁህ። ጆሮ፤ አይን፣ አእምሮና ልቦናም ፈጠርኩልህ። ባሪያዬ ሆይ፤ ነውርህን እሸፍናለሁ፡ አንተ ግን አትፈራኝም። አስታውስሐለሁ፣ ትረሳኛለህ። ባሪያዬ፤ ካንተ ይሉኝታ ይይዘኛል። አንተ ግን ከኔ ይሉኝታ አይዝህም። ከነ ይበልጥ ቸር ማን ነው? በሬን አንኳኩቶ የማልከፍትለት፣ ጠይቆኝ የማልሰጠው ማን አለ? ባሪያዬ ለኔ የሚነፍገኝ እኔ እውን ንፉግ ሆኘ ነውን?›› አንተ ቀልብ ሆይ፣ ምን አገኘህ? ይህ የአምላክህ ቃል የተለየ ስሜት አላሳደረብህምን? እነኝህን ቃላት ስታነብ ሐፍረት አይሰማህም፣ ይሉኝታስ አይዝህም?

<u>ራሱን እንጅ ሌላን አይውቀስ</u>

ውስጣችሁ እንዲነካ በመጣር ላይ ነኝ። የአምላካዊ እስትንፋስ ባለቤቶች ናችሁና ሩሐችሁ ከአምላክ ፡ ቃል ፡ የመሰነቅ መብት አላት። አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ይላል፡-

‹‹ባሮቼ ሆይ፣ እኔ በደልን በራሴ ላይ _ እርም _ አድርጌያለሁ። በመካከላችሁም እርም አድርጌዋለሁ። ስለዚህም አትበዳደሉ። ባሮቼ ሆይ፣ ሁላችሁም ጠማሞች ናችሁ እኔ ያቀናሁት ሲቀር። ቀናትን ለምኑኝ አቀናችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፣ እኔ ያበላሁት ሲቀር ሁላችሁም የተራባችሁ ናችሁ። ጠይቁኝ እመግባችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፤ እኔ ያለበስኩት ሲቀር ሁላችሁም የታረዛችሁ ናችሁ። ለምኑኝ አለብሳችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፣ በቀንም በሌሊትም ትሳሳታላችሁ። እኔ ወንጀልን ሁሉ እምራለሁ። ስለዚህም ምህረት ለምነኝ እምራችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፣ እኔን መጉዳትም ሆነ መጥቀም አትችሉም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያች ሁም የመጨረሻችሁም፤ ሰዎቻችሁም ጅኖቻችሁም ___መካከላችሁ ይበልጥ እኔን የሚፈራ ሰው ፡ ያለውን አይነት ልቦና ቢኖራቸው ከንግስናዬ ፡ የሚጨምሩልኝ ነገር የለም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያችሁም የመጨረሻችሁም፣ ሰዎቻችሁም ጅኖቻችሁም ከመካከላችሁ ይበልጥ ጠማማ የሆነውን ሰው ልቦና ቢይዙ ከንግስናዬ ቅንጣት ታክል _ አያጎድሉም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያችሁም የመጨረሻችሁም ሰዎቻችሁም ጀኖቻችሁም በአንድ መስክ ላይ ቆመው

ቢለምኑኝና ለሁሉም የጠየቁትን ሁሉ ብሰጣቸው ክር ከባህር ውስጥ ቢነከር የሚያነድለውን ያህል ቢሆን እንጅ ከሐብቴ አያነድሉም። ባሮቼ ሆይ፣ ስራችሁን በጥንቃቄ እመዘግባለሁ። የስራ ዋጋችሁንም እሰጣችኋለሁ። መልካም ነገር ያገኘ አላህን ያመስግን። ከዚህ ውጭ የሆነበት ግን ራሱን እንጅ ሌላን ማንንም አይውቀስ።» (ተርጊብ 275)

ባሮቼ ሆይ፣ የሚለው ጥሪ ውስጥን ይሰረስራል። ከታላቁ አላህ ወደ ባሪያው የተላለፈ መሆኑ ደግሞ የተለየ ስሜት ይሰጣል። የተኙ ቀልቦችን የሚያነቃ ጥሪ። ለረኸም ዘመን ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ የሰጠሙ ልቦናዎች ዛቻ እንጅ አያነቃቸውም። ስለዚህም፡- ‹ ለጥፋታቸው ሁሉ ራሳቸውን እንጅ ሌላን ማንንም አይውቀሱ።»

<u>እጅግ ጠቃሚ ምክር</u>

ከአደም አፈጣጠር ጋር በተያያዘ ሌላ ጠቃሚ ነጥብ እናንሳ። አላህ እኛን የሰው ልጆችን ከሁለት ቁሶች ፈጥሮናል። ሌሎች ፍጡራን ግን የተፈጠሩት ከአንድ ቁስ ብቻ ነው። እነዚህም ሁለት ቁሶች ውጫዊ ሽፋናችን የሆነው አካላችንና ውስጣዊ እምነታችን የሚለው ሩሃችን ነው። አካል ከአፈር እንደተፈጠረ አይተናል። ሩህ ግን ከላይ የወረደ የመለኮታዊ እስትንፋስ ውጤት ነው።

የሰው ልጅ ሆይ፣ በአንድ በኩል ወደምድር የሚጎትትህ አፈራዊ ባህሪ፣ በሌላ በኩል ወደ ሰማይ የሚያነሳህ መንፈሳዊ ጉልበት እንዳለህ ተረዳ።

ሁለቱም ቁሶች የየራሳቸው ቀለብ አላቸው። የአካል ቀለብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ወሲብ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ወዘተ ሲሆን የሩህ ቀለብ ደግሞ ወደ አላህ መቃረብ ነው።

ስለዚህም እነዚህን ሁለት ቁሶች በሚዛናዊነት መቀለብ ተገቢ ነው። ይህ ሚዛናዊነት ሲዛባ በሰው ልጅ ላይ ጉዳት ያስከትላል።

እስልምናችን ሁሌም ሚዛናዊነትን ያስተምረናል። ልከኝነትን ያበረታታናል። ለአንዱ ገጽታችን አለቅጥ አናበዛም፡ትኩረት ችረን ሌላውን እንዳንዘነጋ ግሩም ስልጠና ይሰጠናል።

ለዱንያችን ዘልዓለም እንደምንኖር፣ ለአኺራችን ደግሞ አሁን እንደምንሞት አድርገን እስካልሰራን ድረስ ሕይወታችን ፈር አይዝም። የአምላክ ትክክለኛ ባሮችም አንሆንም።

<u>ጋላቢው ማን ነው?</u>

ቁርአን ውስጥ አንድ ሙሉ ምእራፍ ለአካል የመኖርን አደጋ ያብራራል። ይህን ምእራፍ ሁላችንም በቃላችን እናውቀዋለን። አልተካሱር ምእራፍ ይባላል።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

الهَىكُمُ التَّكَاثُرُ حَتَّى زُرتُمُ الْمَقَابِرَ كَلَّا سَوْفَ تَعْلَمُونَ) الا سوف تعلمون ثم كلا سوف الترون الجَحِيم تعلمون لا لو تَعْلَمُونَ علم اليقين

عِلْمَ ثُمَّ لَتُسْلُنَ يَوْمَيذٍ عَنِ النَّعِيب عين اليقين

በዚህች ዓለም ፀጋዎች ብዛት መፎካከር (አላህን ከማምለክና ለመው ዓለም ሕይወት ከመዘጋጀት) አዘናጋችሁ መቃብሮችን እስክትጐበኙ (ለሕልፊት እስክትበቁ) ድረስ (የዚህችን ዓለም ፀጋዎች ፍለጋ ትማስናላችሁ) (ከዚህ አድራጐታችሁ ታቀቡ (ለዚህች ዓለም ፀጋዎች ከተገቢው በላይ ትኩረት በመስጠት የፈፀማችሁትን ስህተት ውጤት ወደፊት ታውቃላችሁ (ከአድራጐታችሁ ታቀቡ (የጥፋታችሁን ውጤት ወደፊት ታውቃላችሁ ታቀቡ በመጭው ዓለም የሚጠብቃችሁን አስከፊ ቅጣት በእርግጠኝነት ብታውቁ ኖሮ (በዚህች ዓለም ፀጋዎች ብዛት በመፎካከር አላህን ከማምለክና ለመጭው ሕይወት ከመዘጋጀት ባልተዘናጋችሁ ነበር። ገሃነምን በእርግጥ ታያላችሁ አዎ በዓይኖቻችሁ ታይዋታላችሁ የዚያን ቀን (በዚህች ዓለም) ስለተሰጧችሁ ፀጋዎች ሁለ ትጠየቃላችሁ። (አል ተካሰር 1-8)

ከምእራፉ ጋር ጥቂት ቆይታ እናድርግ። በገንዘብ ብዛት መፎካከር፣ በአካል ቀለብ መፎካከር ነው። ከዚሁ ላይ የተከለከለው ብዙ ሐብት ማግኘት ሳይሆን ይህ ፉክክር ያስከተለው ጥፋት ነው። እርሱም ቀብርን እስኪነኙ ወይም እስኪሞቱ ድረስ ለዚሁ ዓላማ መኖር፤ ከአምላክ መዘናጋት ነው። ምእራፉ ለአካሉ ብቻ የሚኖርን፣ በመንፈሱና በአካሉ መካከል ሚዛናዊነትን ያልጠበቀን ክፉኛ ይወቅሳል። መሠረታዊና አብዩ

ተግባር መንፈስን ማጥራት ነበር። ይህ ሲሆን አካልም ይረካል፣ ይጠግባል።

እንበልና አንድ ሰው ሊዘይርህ መጣ። አመጣጡ በፈረስ ነው። አንተም ተቀበልከው። እርሱን ወደ ፈረሶች ጋጥ አስገባህና ፈረሱን ግን እየጎተትክ ወደሳሎንህ ወሰድከው። ይህ ትክክለኛ ድርጊት ነውን? ሩህን ትቶ ለአካል ማተኮር ከዚህ ድርጊት በምን ይለያል?

አካልን የምትጋልበው ሩህ አይደለችምን?

ለልጆቻችሁ አስተምሩ

የአደምን አፈጣጠር መቃኘታችንን እንቀጥል። ሩህ ወደ አደም አካል የገባችው በራሱ በኩል ነበር። በዚህ ጊዜ አደም አስነጠሰ። መላኢኮችም ለአላህ ምስጋና ይገባው በል» አሉት። ‹አላህ የተመሰገነ ይሁን» አለ። አላህም፡- «አምላክህ አዝኖልሐል» አለው። አደም የሰማው የመጀመሪያው ቃል ይህ ነበር። «አምላክህ አዝኖልሐል። ሐዲሱን ቲርሚዚ ዘግበውታል።

የአላህ እዝነት አካብቦናል። ርህራሄው ለኛ በጣም ቅርብ ነው። ግና እኛ ራሳችን ከርሱ እንርቃለን።

ወዳጆቼ ሆይ፣ ከናንተ መካከል አንዱ ሲያስነጥስ «አልሐምዱ ሊላህ ይበል። ይህን ቃሉን የሰማውም «የርሐሙከላህ» (አላህ ይዘልንህ) በማለት ይመልስ። _ አስነጣሹም፡- «አላህ ቅኑን ጎዳና ይምራህ። ውሎህንም ያሳምርልህ።» ይበለው፡ ነቢዩ (ሰዐወ)፡- ‹ሙስሊም በሙስሊም ላይ ያሉት መብቶች ስድስት ናቸው።» በማለት ከዘረዘሩት ውስጥ ይህ መብት ተካቷል።

ይህንን ስርዓት ለልጆቻችሁ፣ ለወዳጅ ዘመዶቻችሁ፣ ለምታውቁት ሁሉ አስተምሩ።

የቀናት ሁሉ አውራ

አደም የተፈጠረው መቼ ቀን እንደሆነ ታውቃለህን? ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡

‹‹ጸሐይ ከወጣችባቸው ቀናት ሁሉ ይበልጥ መልካሙ የጁሙዓ ቀን ነው። በርሱ ውስጥ አደም ተፈጠሩ። በርሱ ውስጥ ወደ ምድር ወረዱ። በርሱ ውስጥ ሞቱ። ቂየማ የምትቆመውም ጁሙዓ ቀን ነው። (ሙስሊም)

ጁሙዓ ቀን ከአላህ ዘንድ ያለው ልቅና ይህን ይመስላል። የጁሙዓ ቀን ሱንናዎችን ትጠብቃላችሁን? ትተገብራቸዋለህን?

ውድ ወዳጄ ሆይ፣ መተግበር ከፈለግክ ከዚህ በታች በዝርዝር አስቀምጨልሐለሁ፡-

1) መታጠብ
2) ሽቶ መቀባት
3) በነቢዩ ላይ ሶለዋት ማድረግ
4) አልከህፍ ምእራፍን መቅራት
5) ማልዶ ወደ ጁሙዓ ሶላት መሄድ
6) ጥሩ ልብስ መልበስ
7) ጥርስን መፋቅ

ሙስሊም በዘገቡት ሌላ ሐዲስ ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የአደም የመፈጠር ሂደት የተጠናቀቀው ጁሙዓ ቀን በዓስርና በሌሊት መካከል ባለች የመጨረሻ ሰአት ነው።››

ይህችን ጊዜ በተመለከተ ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡

‹‹ጁሙዓ ቀን አንዲት ሰአት አለች። ሙስሊም የአላህ ባሪያ ይህችን ጊዜ አግኝቶ አላህን አንዳች ጉዳይ ከጠየቀው አላህ ይሰጠዋል።›› (ሙስሊም)

ይህች ሰአት አደም የተፈጠረባት እንደሆነች ከዓሊሞች ከፊሎቹ ተናግረዋል።

ሊታወስ የሚገባው

የኢብን መስዑድ _ አባባልም ሊዘከር ይገባል። ይህውም አንድ ቀን የጁሙዓ ሶላት ለመስገድ ወደ መስጊድ ገቡ። ከሌሎቹ ሰዎች ቀድመው ከመስጊድ መገኘት ልምዳቸው ነበር። የዚያን ቀን ግን ሁለት ሰዎች ቀድመዋቸው በማግኘታቸው እጅግ አዘኑ። ታፋቸውን እየመቱም «ኢብን መስዑድ ሆይ፣ እንዴት ሦስተኛ ሰው ትሆናለህ» በማለት በጣም ተቆጩ። በመጨረሻም፡- «ሦስተኛ ሆኖ የገባ ሰው ከአላህ ብዙ የራቀ አይደለም» ሲሉ ራሳቸውን አጽናኑ።

ከራሳችን ይበልጥ ያውቀናል
ነቢዩ የአደምን ገጽታ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህ አደምን በያዘው ገጽታ ፈጠረው። እርዝመቱ በሰማይ ውስጥ ስልሳ ክንድ ነበር። ጀነት የሚገባ ሁሉ የአደምን ገጽታ ይይዛል። ቁመቱም ስልሳ ክንድ ይሆናል። ከርሱ በኋላ የሰዎች ቁመት እያነሰ ሄዷል።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

ያ አላህ፣ ስልሳ ክንድ በጣም ረዥም ነው። ቁመታችን ለምን እያነሰ እንደሄደ ታውቃለህ? አላህ ስላዘነልን ከአካል ሸክም ገላገለን። እውቀታችን በጨመረ፣ አእምሯችን ባደገና በበለጸገ ቁጥር አካላችን መጠኑ እያነሰ ይሄዳል። ይህም _ ወሰን እንዳናልፍ እና እንዳንኮራ ያደርገናል። አላህ እኛን ከራሳችን ይበልጥ ያውቀናል።

አእምሮን ለመታደግ

ወደ ሐዲሱ እንመለስ። አላህ አደምን በያዘው ገጽታ እንደፈጠረው ተመልክቷል። በየትኛው ገጽታ? ወደ ምድር ሲወርድ በያዘው ገጽታ ማለት ነው። በምድርም በጀነትም ተመሳሳይ ቅርጽና ገጽታ ነበረው።

ሱብሐነላህ! በአሁኑ ዘመን የሰው ልጅ መነሻ ዝንጅሮ ነው የሚለውን አባባል ስንሰማ የዚህን ሐዲስ ክብደትና ዋጋ እንረዳለን። ለዳርዊናዊያን

ጥሩ ምላሽ ነው። ነቢዩ እውነት ብለዋል፡- «ከልብወለዳቸው አይናገሩም። በወህይ የተገለጸላቸውን ቢሆን እንጅ።»

ከዚያም አላህ አደምን፡- «ሃድና ለነዚያ መላኢኮች ሰላምታ አቅርብላቸው ፡ እነርሱ ላንተ የሚያቀርቡትን ሰላምታም አድምጥ። ያንተም ካንተ በኋላ የሚመጡ ዝርያዎችህም ሰላምታ ይህ ይሆናል።» አለው።

አደም ወደ መላኢኮች ሄደ። «አሰላሙ አለይኩም» በማለት ሰላምታ አቀረበላቸው። «ወዓለይኩሙ በማለትም መለሱለት። ሰላም ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ

የጀነት ሰዎች ቁንቋ አረብኛ መሆኑን ይህ ሐዲስ ያስተምረናል። አደም የተናገሩት የመጀመሪያው ቃልም _ ሰላምታ _ ነበር። ይህ ከሐዲሱ የምንማረው ትልቁ ቁም ነገር ነው። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«እስካላመናችሁ ድረስ ጀነት አትገቡም። እስካልተዋደዳችሁ ድረስም አታምኑም። ብትሰሩት የምትዋደዱበትን ነገር ላመላክታችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አብዙ።» (ሙስሊም፣ ቲርሚዚና ቢን ማጃህ)

ሰላምታ ስታቀርብ ፊትህን አታጨፍግግ። ሰላምታህ በፈገግታ የታጀበ ይሁን። ልክ እንደ ነቢዩ። ንግግርህም ተግባርህም ሰላም ይሁን።

<u>የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ስሪት</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህ አደምን በፈጠረ ጊዜ ጀርባውን አበሰው። ከጀርባው እስከ እለተ ቂያማ የሚፈጥራቸው ዝሪያዎች ሁሉ ወደቁ።» (ቲርሚዚ) የዘር ፈሳሽ ከጀርባ አጥንት እንደሚወጣ ይህ ሐዲስ ይጠቁማል። አላህም

እንዲህ ብሏል፡-

وَإِذْ أَخَذَ رَبُّكَ مِنْ بَنِي عَادَمَ مِن ظُهُورِهِمْ ذُرِّيَّتَهُمْ وَأَشْهَدَهُمْ عَلَى أَنفُسِهِمْ أَلَسْتُ بِرَبِّكُمْ قَالُوا بَلَى شَهدنا أن تَقُولُوا يَوْمَ الْقِيَمَةِ إِنَّا كُنَّا عَنْ هَذَا غَفِلِينَ (الأعراف :

ጌታህ ከአደም ልጆች ከጀርባዎቻቸው ዝርያዎቻቸውን ያወጣና ጌታችሁ አይደለሁምን? በማለት በራሳቸው ላይ ባስመሰከራቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ) አዎ (ጌታትን መሆንህን) መስካሪዎች ነን አሉ። በዕለተ ትንሳኤ፥ ይህንን (ቃልኪዳን) ፈጽሞ አናስታውስም" እንዳትሉ» (አል አዕራፍ 172)

በአላህ በሚያምን፣ በእለተ ቂያማ ከርሱ ፊት ቀርቦ ለመጠየቅ እየተዘጋጀ በሚገኝ እያንዳንዱ ሙስሊም ስሪት ውስጥ ያለ ተፈጥሮ። በቂያማ ቀን የሚሰጥ ምስክርነት። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

እያንዳንዱ ልጅ ተፈጥሯዊ ሐይማኖት ይዞ ይወለዳል። ከዚያ በኋላ ወላጆቹ ክርስትያን፣ አይሁድ ወይም መጁስ ያደርጉታል።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

ውድ ወንድሜ ሆይ፣ ተፈጥሮህ ንጹህ ነው። ታዲያ ለምን ታቆሽሸዋለህ? ለምን አላህን ትወነጅላለህ? እባክህን ተፈጥሯዊ ባህሪህን አትበርዝ። ስሪትህን አትበክል።

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«በእለተ ቂያማ እሳት ለተወሰነለት ሰው፡- «በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ ቢኖሩህና ራስህን ከእሳት ለማዳን እነርሱን እንድትሰዋ ብትጠየቅ ትለዋለህን? የሚል ጥያቄ ይቀርብለታል። አዎ፣ ሲል ይመልሳል። አላህም፡- «ከዚህ በጣም ያነሰ ነገር ነበር የተጠየቅከው። ከአደም ጀርባ ላይ እያለህ በእኔ ምንንም ነገር እንዳታጋራ ቃል አስገብቼህ ነበር ይለዋል።»

ይህ ከአላህ የተሰጠን ሐላፊነት፣ አደራ፣ እማኝነት ነው። የአደም አፈጣጠር ይህን ይመስላል። የአደምን አፈጣጠር ያወሳንበትን ዋነኛ ዓላማ ታስታውሳለህን?

አደምና ሐዋእ

ኢብሊስ ከመላኢኮች ነበር

አምላካችን አላህ ለአደም ትልቅ ደረጃ ሰጠው። እርሱም በእጁ ጠረጠ መላኢኮችን አሰገደለት። አምላክ በእጁ ለፈጠረው ክቡር ፍጡር ሰገነ ኢብሊስ ግን አልሰገደም። በትእዛዙ ላይ ለማመጣ የፈረ። የዚያን ድፍረቱን መንስኤ ከማየታችን በፊት አንድ ጥያቄ እንመልስ። አለ፡ ከመላኢኮች ነበርን አላህ እንዲህ ብሏል፡

وَلَا قُلْنَا الْمَلَكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَى وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ

ሙሐመድ ሆይ ለመላእክት ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ የሆነውን አስታውስ ለሕዝቦችህም ተርክላቸው። ሁለም ሰገዱ፡ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር። (እርሱ ግን) እምቢ አለ ኮራም (በዚህ እምቢተኝነቱ ሰበብ) ከከሓዲያን ተፈረጀ፡›› (አል በቀራህ

ይህ አንቀጽ ኢብሊስ የመላኢኮች አካል እንደሆነ ያስመስለዋል። ግና የነርሱ አካል እንዳልሆነ ዑለሞች በአንድ ድምጽ አጽድቀዋል። ኢብሊስ ከጅኖች ነው። በምድር ላይ ይኖሩ ነበር። ምድርን በከሏት። አላህም መላኢኮችን በመላክ አስወገዳቸው። ከመካከላቸው አላህን ይታዘዝና ያመልክ የነበረውን ኢብሊስን ብቻ ወደ ሰማይ ወሰዱት። በሰማይ ውስጥ እያንዳንዱን ቦታ ኢብሊስ ሱጁድ እንዳደረገባት ይነገራል።

ግና የኢብሊስ ነፍስ አንድ ከባድ ነውር ነበረባት። አላህ ይህን ነውር ያውቀዋል። መላኢኮች ግን ከነውር የጸዱ ናቸው። ኢብሊስ የመላኢኮች አካል እንዳልሆነ ለማመልከት ጠንካራው መረጃ የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ነው፡-

وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَٰٓئِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ كَانَ مِنَ الْجِنِ فَفَسَقَ من أمي

رة الكهف ٥٠

ለመላእክት ለአደም ስገዱ ባልን ጊዜ የሆነውንም አስታውስ። 5) ሰገዱ፡ ዲያቢሎስ ሲቀር። እርሱ ከኣጋንንት ነበረ። በጌታው እዛዝ አመፀ (አል ከህፍ 50)

አመጽ የመላኢኮች ባህሪ አይደለም። አላህ አደምን በሁን ቃሉ በቅጽበት መፍጠር ይችል ነበር። ግና በእጁ ፈጠራቸው። ይህ ለርሳቸው ልቅና ሲል የተደረገ ነው። ኢብሊስ ይህን ክብራቸውን በአመጽ ለማጉደፍ ቶሎ አልተሳካለትም። ይህም በመሆኑ የሰውን ልጅ ክብር የሚያረክስ ምንም ዓይነት ፍጡር የለም። የሰው ልጅ ራሱ ሲቀር። እርሱ ግን አምላኩን በማሐጥየት ራሱን ያዋርዳል። ኢብሊስ በአመጹ ከአላህ እዝነት ለባረርና ለመረገም አደጋ እንደተዳረገው።

<u>ለምን ታዘዘ?</u>

አላህ ለአደም እንዲሰግዱ ያዘዘው መላእክትን እንጅ ጅኖችን አይደለም። ታዲያ ኢብሊስ ባልታዘዘው ነገር ለምን ይቀጣል?

ነገሩ እንዲህ ነው። በእርግጥ ኢብሊስ የጅኖች አካል ነው። ግና ከኢኮች ጋር ይኖር ስለነበር ትእዛዙ እርሱንም የሚመለከት ሆነ። ይህም በመሆኑ አላህ ለምን እንዳልሰገደ ላቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ፡- ‹‹ስላላዘዝከኝ›› የሚል ሳይሆን ሌላ ነው። ተከታዩን አንቀጽ እንመልከት፡-

قَالَ كَابْلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسْجُدَ لِمَا خَلَقْتُ بِيَدَى اسْتَكْبَرْتَ أَمْ كُنتَ مِنَ الْعَالِينَ قَالَ
أنا خَيْرٌ مِنَهُ خَلَقْتَنَى مِن نَّارٍ وَخَلَقْتَهُ مِن طِينٍ

አላህም - ዲያብሎስ ሆይ! በእጇ ለፈጠርኩት ፍጡር ላለመስገድ ምክንያት የሆነህ ምንድን ነው! (አሁን) ኮራህ ወይስ ቀድሞውኑም ከትዕቢተኞቹ ነበርክ? አለው። እኔ ከርሱ የተሻልኩ ነኝ እኔን የፈጠርከኝ ከእሳት ሲሆን፡ እርሱን ግን የፈጠርከው ከጭቃ ነው። እለ= (ሷድ 75-76)

በሌላ የቁርአን አንቀጽም አላህ እንዲህ ማለቱ ይህን ሐሳብ ይበልጥ ያጎላዋል፡-

(٥ قَالَ مَا مَنَعَكَ أَلَّا تَسْجُدَ إِذْ أَمَرْتُكَ قَالَ أَنَا خَيْرٌ مِنْهُ خَلَقْتَنِى مِن نَّارٍ وَخَلَقْتَهُ مِن طِينٍ
الإعراف

«(አላህም) ባዘዝኩህ ጊዜ እንዳትሰግድ የከለከለህ ምንድን ነው ሲል ጠየቀው እኔ ከርሱ የተሻልኩ ነኝ እኔን የፈጠርከኝ ከእሳት ሲኾን፣ እርሱን ግን የፈጠርከው ከጭቃ ነው አለ (አል አዕራፍ 12)

የመላኢኮችን ባህሪ አስተውል። ለአላህ ፍጹም ታዛዥነት። ማመንታት እና ማሰብ ወይም መዘግየት የለም። ትእዛዙን ወዲያውኑ ፈጸሙ። ጊዜ ሳይወስዱ ስገዱ፣ ተቃውሞ ወይም ጥያቄም አላነሱም።

የአላህን ትእዛዝ ያለ ማመንታት ከፈጸምክ ከአላህ ዘንድ ከመላኢኮችም በላይ ክብር ይቸርሐል። በነርሱ ላይ አላህ ይመጻደቅብሐል። እነርሱ ከዝንጋታና ከሐጢአት የጸዱ ብጹአን ፍጡሮች ሆነው እያለ።

ዝንጋታን እና ሐጢአትን፣ እንዲሁም ከሰይጣን ጋር የሚያስተሳስርህን ነገር ሁሉ ተጠንቀቅ። ድንገት ከጥፋት ላይ ከወደቅክ እንኳ በርሷ ላይ አትዘውትር። ከአላህ ጋር የሚያስተሳስርህ ማንነት አለህ። እርሱም በውስጥህ የሚገኘው አምላካዊ እስትንፋስ ነው። የሕልውናህ ሚስጥርም እርሱ ነው።

<u>ኢብሊስ ወይስ ሰይጣን</u>

ይህን የመጀመሪያ ወንጀለኛ ቁርአን አንዳንድ ጊዜ ኢብሊስ፣ ሌላ ጊዜ ስይጣን በማለት ይጠራዋል። ሁለቱም ስሞች የርሱ ናቸውን? ትርጉማቸውስ ምንድን ነው?

ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት ስሙ ኢብሊስ ነበር። ሰይጣን የሚለው ቃል ዓረብኛ ሲሆን ስርዎ ቃሉ «ሸጠነ»፣ ትርጉሙም ራቀ ማለት ነው። ኢብሊስ በአምላክ ትእዛዝ ላይ በማመጽ ከታዛዥነት ራቀ። ከተውባ ራቀ። ከአላህ ይቅርታ ራቀ። ከጀነትም ራቀ። ከበጎ ነገሮች ሁሉ በጣም በመራቁ

ሸይጣን ተባለ። ስለዚህም ስሙ ኢልቢስ ሲሆን፥ ባህሪው ደግሞ ሸይጣን ነው።

ከሰዎች መሀልም በወንጀሉ ሳቢያ ዓሲ (ወንጀለኛ)፥ ፋሲቅ (አመጸኛ) ጃሂድ (አስተባባይ) ፥ ካፊር (ከሀዲ) ተብሎ እንደ ጥፋቱ መጠንና ባህሪ የሚጠራ አለ። በመሆኑም አላህን ከመታዘዝ ብትርቅ እንኳ ከተውባ አትራቅ።

እኩይ ሰዎች ቢቀርቡህም እንኳ ከበጎ ሰዎች ጋር አትቆራረጥ። ሰይጣን በሴራው ቢያካብብህም ከአላህ ዘንድ የሆነ ጠባቂ አብሮህ ምንጊዜም አለ። የርሱ በር ሌት ከቀን ላንተ ክፍት ነው። ከቅጣቱ ይልቅ ምህረቱ ወዳንተ ይፈጥናል። አላህ ከምንም በላይ ላንተ ቅርብ ነው። ስለዚህም ወዳጅህንና አምላክህን አጥብቀህ ያዝ።

ልዩነታቸው ምንድን ነው?

ግልፅ ሊሆንልን የሚገባው ሌላው ነገር ሁሉም ሸይጧን የጅን አካል ሲሆን ሁሉም ጅን ግን የሸይጣን አካል አይደለም። ማለት የፈለግኩትን ለማብራራት አመጸኛና ከሐዲ የሆነ ጅን ሁሉ ሸይጧን ተብሎ ይጠራል። ሸይጣን የሚባሉት ከጅኖች መሐል ወንጀለኞች ናቸው። አላህን የሚታዘዙ አማኝ ጅኖች ግን በዚህ ስም አይጠሩም።

ሦስት አደገኛ ፊደላት

የኢልቢስ ልቦና ውስጥ የነበረውና ከአላህ እዝነት እንዲባረር ምክንያት የሆነው ነውር በሦስት የንረብኛ ፊደላት ይገለጻል -አነ እኔነት ይፋ ቃል መጠን አናሳ ናት። የተሸከመችው መልእክት ግን ከቢድ ነው። እነ አደገኛ የቀልብ በሽታ የሆነው ኩራት። ኢብሊስ በዚህ በሽታ ተስፉ ስም እንዲሰግድ ሲታዘዝ በራስ መኮፈስና ኩራት የተጠበቀበት መልስ ሰጠ።

(قَالَ مَا متعبة إِلَّا تَسْجُدَ إِذ أَرى قَالَ أَنا خيرية على من نَّارٍ وعته من باري

(አላህም ባዘዝኩህ ጊዜ እንዳትሰግድ የከለከለህ ምንድን ነው? ሲል ጠየቀው “እኔ ክር የተሻልኩ ነኝ እኔን የፈጠርከኝ ከእሳት ሲኾን እርሱን ግን የፈጠርከው ከጭቃ ነው” አለ (አል አዕራፍ 12) አላህ እንዲህ ብሏል፡-

قَالَ يَا بَلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسْجُدَ لِمَا خَلَقْتُ يَدَى اسْتَكْبَرتَ أَمْ كُنتَ مِنَ المالِينَ) قَالَ أنا خَيْرٌ مِنْهُ خَلَقْتَنَى مِن نَّارٍ وَخَلَقْتَهُ مِن طين (ص ٧٥٠ ـ ١٩٨٦٧٦٩

አላህም ዲያብሎስ ሆይ በእጄ ለፈጠርኩት ፍጡር ላለመስገድ ምክምያት የሆንህ ምንድን ነው (አሁን) ኮራህ ወይስ ቀድሞውኑም ኩትቢተኞቹ ነበርክ አለው) (ሷድ 75-76)

በዚህ ባህሪው በምድር ላይ ከታዩ ሁለት እኩይ ፍጡራን መካከል አንዱ ሆነ። እነዚህ ፍጡራን ኢብሊስና ፊርዓውን ናቸው። ኢብሊስ ‹‹እኔ ከርሱ እሻላለሁ አለ። ፊርዓውን ደግሞ፡- እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ› አለ። አስተውል የጥፋት መንስኤ ‹በኔነት›› ይወጠናል። ይህ ስሜት እያደገ በሄደ መጠን የሰው ልጅ ሰይጣናዊ ባህሪም አብሮ ያድጋል።

እናም በሕይወት ውስጥ ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት የሰይጣንን ስሜት ተጠንቀቅ። አንዳንዶች ‹‹እኔ በሂጃብ አላምንም››፣ ሌሎች፡- የሚዘይሩኝን እንጅ አልዘይርም ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ›› ይላሉ። ወዘተ እንዲህ ዓይነት ስሜቶች ሰይጣናዊ ናቸው። የማን አህሎኝነት አድራጎቶች ያጠፋሉ፡ ወደ አላህ የሚደረግ ጉዞ ነፍስያህን ተቃርነህ ትእቢቷን ረግጠህ በምትራመዳት አንዲት እርምጃ ይጀመራል።

<u>አደገኛ በሽታ</u>

የሰው ልጅ ራሱን ከፍ አድርጎ ማየቱ ይገርማል። ምንም ነገር የሌለው ሆኖ እያለ ይህ የኢብሊስ ታሪክና ያጋጠመው መከራ ለሁላችንም ሕይወት ብርሃን የሚሆን እጅግ ጠቃሚ ትምህርት ይዟል። ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች ያስተውሉ፡

የመጀመሪያው ሐጢአት ኩራት ነው። ኢምንት ታክል ኩራት አለብህን ይህን ጥያቄ ፈጽሞ አትዘንጋ፤ ምክንያቱም የኩራት ፍጻሜ የከፋ ነውና።

ባለቤቱን ከጀነት ማቀቡ ብቻ በቂ ጥፋት ነው። በቁርአን ውስጥ ኩራትና ኩራተኞች በተወሱ ቁጥር ጀሐነም አብሯቸው ይወሳል። በመጀመሪያው ኩራተኛ ላይ አላህ ያስተላለፈውን ውሳኔ አስተውል፡-

(قال فأفقط مِنها فَمَا يَكُونُ لَكَ أَن تَتَكَبَّرَ فِيهَا فَأَخْرُجُ إِنَّكَ مِنَ الصَّغِرِينَ

ከርሷ (ከገነት) ውረድ፣ ከውስጧ ሆነህ ልትኮራ አይገባም ውጣ አንተ ከወራዶች ነህና አለው። (አል አዕራፍ 13)

የክፋቱ ውጤት ከጀነት እና ከአላህ እዝነት መባረር ነው። ጀነት ለትእቢተኞች ተስማሚ ቦታ አይደለችም። በሐቅ / ላይ የተኮፈሰ፣ የአምላኩን ትእዛዝ እምቢ ያለ ሁሉ ቅጣቱ ውርደት ነው። ነቢዩ ትእቢተኞችን ሁሉ እንዲህ ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡

«ከልቦናው ውስጥ ቅንጣት ታክል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም» (ሙስሊም እና ቲርሚዚ)

አላህ እንዲህ ማለቱንም ነግረውናል፡-

«ኩራት ኩታዬ ነው። ክብርም ሽርጤ ነው። ከነዚህ ከሁለቱ አንዱን የተቀናቀነኝን ጀሃነም ውስጥ እከተዋለሁ።» (ቢን ማጃህ)

የሌላን ሰው ንብረት ያለ አግባብ መውሰድ ትልቅ ወንጀል መሆኑ ይታወቃል። የኩራት ሸማ ያንተ አይደለም። መስጠትም መንፈግም የሚችለው፣ የሕይወትም የሞትም ፈጣሪ፣ የክብርና ሐያልነት ባለቤት የሆነው አምላክ ሐብት እንጅ። የርሱን ልብስ መቀናቀንህ ምን ያህል ግዙፍ ወንጀል እንደሆነ ይታይሐል? ይህ መዳፈር በሰይጣን ላይ መስራ አምጥቶበታል። አለመኩራት ችሮታ ሳይሆን ግዴታ ነው። ለአላህ ሐቅ እውቅና መስጠት ነው። አላህ በእዝነቱ ይህን ግዴታህን መወጣትህን፣ ለርሱ ሐብት እውቅና መስጠትህን ወደ መላኢካ ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ኢባዳ አደረገልህ። ማንነትህን አውቀሐል። በዱንያም በአኼራም የትርፍ ዋስትና አግኝተሐል።

የዚህ በሽታ አምስት ገጽታዎች

ኩራት እጅግ አስከፊ በሽታ በመሆኑ ሁላችንም ራሳችንን በመፈተሽ የበሽታው ምልክት እንዳለብን እና እንደሌለብን ማጣራት ይኖርብናል። አውቀንም ይሁን ሳናውቅ በበሽታ እንዳይዘን መጠንቀቅ ይኖርብናል። የሚያስከትለው ቅጣት እጅግ አሳማሚ ነውና። ይህውም በዚህች ዓለም ውስጥ ውርደት በመጭው ዓለም ደግሞ ጀሃነም ነው። ነገሩን ቀለል ለማድረግ አምስት የኩራት ዓይነቶችን እዘረዝርልሐለሁ። በእያንዳንዱ ራስህን መዝን። መንገድህን ወደሚያመላክትህ ውጤት ላይ ትደርሳለህ፡-

አንደኛ፡- ሰዎችን መበደልና መናቅ

ሰዎችን አሳንሶ ማየትና ማናናቅ፣ እነርሱን መበደልንና ራሳቸውን መዳፈርን ቀላል ያደርገዋል።

*ሴቶች ከቤት ሰራተኛቸው ጋር ይህን ይፈጽማሉ።

*አሰሪዎች ከተቀጣሪዎቻቸው ጋር ይፈጽሙታል።

*ወጣቶች በትምህርት ተቋማት ውስጥ በእውቀት ከነርሱ ባነሱት ላይ ይፈጽሙታል።

*ሐብታም በማሕበራዊ ቦታው ከርሱ ዝቅ ባለው ወይም ድሃና ደካማ በሆኑት ላይ ይፈጽመዋል።

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«ኩራተኞች በእለተ ቂያማ ከውርደታቸው የተነሳ ቅንጣት አክለው ይቀሰቀሳሉ። ሰዎችም በእግሮቻቸው ይድጧቸዋል።» (ቲርሚዚ)

ሁለተኛ- በአረማመድ መኮፈስ

ሰውየው በውበቱ፣ በተጎናጸፈው ልብ ኩራት ይሰማናል ይህን ስሜቱ በአረማመድ ያንጸባርቃል። የሰዎችን እይታ ለመሳብና እንዲያደንቁት፣ ከራሳቸው ከፍ አድርገው እንዲያዩት ለማድረግ እየተጀነነ ይራመዳል።

*እንስት በውበቷና በአልባሳቷ ትኮፈሳለች።

⁕ወንዱም በአለባበሱና _ በአካላዊ እሱነቱ ኩራት ይሰማዋል።

⁕ይህም ማለት መጥፎና ቆሻሻ አልባትም እንበልና ማለት አይደለም።
ነቢዩ፡- «አላህ ውብ ነው። ውበትንም ይወዳል» በማለት ተናግረዋል።
(ሙስሊም፣ ቲርሚዚና አህመድ)

እጅግ የተዋቡ አልባሳትን መልበስ ትችላለህ። ግና ሳትኮራ። ቡኻሪ ባሰፈሩት ዘገባ ነቢዩ ሙሐመድ እንዲህ ብለዋል፡-

አንድ ሰው በራሱ ተደንቆ እየተንጠባረረ እና እየኮራ በመጓዝ ላይ እንዳለ አላህ ምድርን ገለበጠበት። እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ወደ ታች ማሽቆልቆሉን ይቀጥላል።»

<u>ሦስተኛ፡- ሐቅን አለመቀበል</u>

ምክርን አለመስማት ፣ እውነት ግልጽ አለመመለስ የኩራት አንዱ ገጽታ ነው። ከሆነልህ በኋላ ወደርሱ

✓ ቤተሰቦችህ ከመጥፎ ጓደኛ እንድትርቅ ሲመክሩህ፣
✓ ባልንጀራህ ሶላት እንድትሰግድ ሲመክርህ፣
✓ ባለቤትህ አላህን ትፈራ ዘንድ ስትመክርህ፣
✓ ጓደኛሽ ሂጃብ ታደርጊ ዘንድ ስትመክርሽ፣

ምክራቸውን ውድቅ ማድረግ ትልቅ ወንጀል ነው። እውነት መሆኑን ባውቅም በእገሌ በኩል ስለመጣ አልቀበለውም» ማለት ትልቅ ጥፋት ነው። ሐቅ ከሁላችንም ይልቃል። _ አላህ _ እንዲህ ዓይነት ሰዎችን በተመለከተ ሲናገሩ እንዲህ ብሏል፡-

(وإذا قيلَ لَهُ اتَّقِ اللهَ أَخَذَتْهُ الْعِزَّةُ بالإثم فَبُهُ جَهَم وَلَبِئسَ الْمِهَادُ)
البقرة: ٢٠٦

“አላህን ፍራ” በተባለ ጊዜ ትዕቢቱ ለበለጠ የኃጢአት ተማ ያነሳሳዋል። ገሃነም በቂው ናት። (ገሃነም) እጅግ አስከፊ ማረፊያ ናት. (አል በቀራህ 206)

<u>አራተኛ፡- ሰዎች እንዲተናነሱልህ መፈለግ</u>

ሰዎች ባዩህ ቁጥር ከኋላህ እንዲከተሉህ፣ ስትመጣ ከተቀመጡበት እንዲነሱልህ፣ እንዲሸቆጠቆጡልህ የምትከጅል ከሆነ፤ ይህን ሳያርጉ ሲቀሩ ከጠላሃቸው አንዱ የኩራት አይነት ነግሶብሐል።

አንዳንድ ሰዎች የባለቤታቸውን እንባው ማየት ይወዳሉ፡ ተሸቆጥቁጣ አንገቷን እንድትደፋ ይፈልጋሉ።፡ ሁሌም

ሰዎች እንዲፈሩት፣ ሲመጣ እንዲያሞግሱት፤ ሲጣራ አቤት ወዴት እንዲሉት፤ ትእዛዙን ሰጥ ለጥ ብለው እንደፈጽሙለት ይሻል። ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«ሰዎች እንዲቆሙለት የከጀለ ሰው እሳት ውስጥ ያዘጋጅ።» (አቡ ዳውድ) - መቀመጫውን

<u>አምስተኛ፡- ሶላትንና ዱዓን መተው</u>

ከመካከላችን ከአምላኩ የሚብቃቃ ሰው አለን? የት ይሄዳል? ሁለ ነገሬን እራሴ እፈጽማለሁ። አምላክ አያሻኝም የሚል አለን? እንዲህ የሚል ይኖራል ብዬ አልገምትም። ይህም በመሆኑ ሶላትንና ዱዓን መተው የኩራት አንዱ ገጽታ ሆኗል።

ሲሰግድ ልብሱ እንዳይቆሸሽ ወይም እንዳይጨማደድ፣ ግንባሩም አቧራ እንዳይነካ ፈርቶ ሶላት የተወ፤

በቂ እውቀት ስላለኝ ዱዓ አያስፈልገኝም የሚል ሰው ከኩራት ማእድ የድርሻውን ዘግኗል።

ሶላት ባንተና በአላህ መካከል ተመራጭ የግንኙነት መስመር ነው። ዱዓ ደግሞ ጉዳይህን ለአላህ የምትነግርበት ሚባዳ ነው።

وَقَالَ رَبُّكُمُ ادْعُونِي أَسْتَجِبْ لَكُ إِنَّ الَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِي سَيَدْخُلُون
جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ

«ጌታችሁ ጥሩኝ ለጥሪያችሁ ምላሽ እሰጣለሁ እነዚያ እኔን ከማምለክ የኩራት ገሃነም ውስጥ የተዋረዱ ሆነው በእርግጥ ይገባል: ብሏል። (ጋፊር 6O)

ምን አልባትም ኢባዳ ጥቂት በፈርዶች ብቻ የተወሰነ ሊሆን ይችላል። ግና ለአላህ መተናነስህ እና መዋደቅህ ከብዙ ዓቢዶች በላይ እንድትሆን ያደርግሐል። ኢብሊስ ከአደም እንደሚበልጥ በማሰቡ አላህ ትክክለኛ ደረጃውን አሳወቀው። ውርደትንም አከናነበው።

ትክክለኛ ማንነትህን እንድትዘነጋ ያደረገህ ነገር ሁሉ ቀልብን የሚያቆሽሽ ቅዥት ብቻ ነው። አላህ ጥሩ ነው። ጥሩን እንጅ አይቀበልም። ጀነትም መልካም ናት። መልካምን እንጅ አትቀበልም።

<u>የኩራት ውጤት</u>

ኩራት ኢብሊስን በቂልነት እንዲከድ አደረገው። ከጭቃና ከእሳት እሳት ይበልጣል ብሎ እንዲያስብ አደረገው። ኩራቱ ዓእምሮውን ሰወረው። ናቸውን ሰወረው።

አላህን መታዘዝህ ከየትኛውም ነገር በላይ ነው። መላኢኮች ገቡ። የተፈጠሩት ብርሃን ነውና። ኢብሊስ ግን ከጭቃና የፈጠርከውን ፍጡር አልሰግድም» አለ። በእርሱ እይታ እሳት ከጭቃ የጠነከረና የበላይ ነው። የበላይ ለበታቹ እንዴት ይሰግዳል? በእርግጥ ይህ ለኩራት በሽታው ምክንያት ያደረገው አስተሳሰቡ ቂልነት ነው። አንዳንድ ሰዎች እውነት ከነርሱ ዘንድ ይመስላቸዋል። እውነታው እነርሱ ከያዙት እሳቤ ተቃራኒ ቢሆንም።

ሁነኛ መረጃ

እሳት ባህሪው ማቃጠልና ማውደም ሲሆን፣ ጭቃ ግን ተግባሩ በጎ ነገርና ማፋፋት ነው። አላህ እንዲህ ይላል።

و لقد خلقنا الإنسكن في أحسن تقويم - التين :

«የሰውን ልጅ እጅግ ውብና ማራኪ በሆነ አቋም ፈጠርነው» (አልቲን 4)

ስለዚህም በእርግጥ የኢብሊስ ሐሳብ ትክክል ነው። ጥፋቱ አምላኩን አለመታዘዙ _ ነው» ብለህ እንዳታስብ። ምክንያቱም የርሱ ስህተት የጌታውን ትእዛዝ ያለመፈጸም ወንጀል ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ ግድፈትም ጭምር ነውና። ጭቃ ባህሪው የጋና የጸና ነው። እሳት ደግሞ ባህሪው ግለትና መንቀዥቀዥ ነው። ጠቀሜታ ቢኖረውም ሁላችን የምንፈራው ክፉ ባህሪ አለው። አደጋና ውድመት ሊያስከትል ይችላል። ጭቃ ግን በጎ ነገር እንጅ ሌላ የለበትም። ኢብሊስ በኩራት በመታወሩ ሳቢያ ሁለቱን ነገሮች በአግባቡ ማነጻጸር አልቻለም።

የሰው ልጅ ያለ አስተውሎት የሚጓዝበት የትእቢት መንገድ የት የሚያደርስ ይመስለዋል? ለሌሎች እውቅናና ክብር ሳይሰጥ፣ ማእረግ ካላቸው በማእረግ ስማቸው ለመጥራት ተጠይፎ፣ የዓሊምን ደረጃ፣ የአዋቂዎችን ልቅና ሳያውቅ፣ ሐቅን እየመለሰ እና ሰዎችን እየናቀ የሚጓዝበት ይህ የቅሌት ጎዳና ወደ የት የሚወስደው ይመስለዋል? ወደ ጀሃነም አይደለምን?

የተሳሳተ እይታ

አንዳንድ ሰዎች የአላህን ትእዛዝ በተመለከተ የራሳቸው አስተያየት (Comment) እንዳላቸው ያስባሉ። ሰይጣንም ይህን እይታቸውን አሳምሮና አበጃጅቶ ትክክል አስመስሎ ያሳያቸዋል። በመጨረሻ ግን በዚህ እይታቸው ጦስ ጀሃነም ይቀቀላሉ።

ከፊሎቹ እንዲህ ብለው ያስባሉ «ለተቃራኒ ፆታዎች እንደ ልብ እንዳይንቀሳቀሱ መከልከል ስነልቦናዊ ስብራትን ይፈጥራል አንዱ ሌላኛውን የማወቅና የመሞከር

ስሜታቸውም በጣም እንዲፈላለጉ ያደርጋቸዋል። የተረጋጋ ስነልቦና እንዲኖራቸው እና በፆታዊ ጉዳይ እንዳይጠመዱ ለማደረግ እንደ ልብ እንዲቀላቀሉ መተው የተሻለ ነው።»

በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ የኢብሊስ አሻራ አለበት። ምእራቡ አለም እነሱ እንደሚሉት አድርጓል። ውጤቱ ግን ካሰቡት የተለየ ነው። የወሲብ ስሜቱ ይበልጥ ተቀጣጠለ። ዝሙት ተስፋፋ። ብልግና ተንሰራፋ። የተማሩ። ከተፈጥሯዊው የወሲብ መንደ ኤፈር ወን ኣመላ ጌታ ላለ ተሸጋገረ።

ይህም በመሆኑ ኢስላም የሁለቱን ጌታዎች ግንኙነት በጋብቻ በጎዳ ስር ብቻ እንዲደረግ ደንግጓል። ከዚህ ውጭ ሁለቱ ጎታዎች ማስፋት አይኖራቸውም። ይህም ሲሆን ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ ንብ ሕይወት መኖር ያስችላል። የእንስታም ክብር ይጠበቃል።

አንድን የአላህ ትእዛዝ መጣስ የሰውን ልን ሕይወት መላ የቀርም። ደካማ አእምሮህን ተጠቅመህ ከአላህ ሐይማኖት ወስጥ ሃላህን መቀበልና ያሻህን ውድቅ ማድረግ እንቃምትችል ማሰብህ ሁለቱን ዓለማት ያጠፋ ብሐል። ለጀሃምም ይዳርግሐል። ሁለ ነገርህን ለህ አስረክብ። ትእዛዙን ያለማመንታት የሚፈን መብን (በተመለከተ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

من عَمِلَ صَٰلِحًا مَن ذَكَرٍ أَو أَنىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ الأخل

ከሴትም ይሁን ከወንድ አማኝ ሆነው መልካም የሠሩትን ጥሩ ሕይወትን እናኖራቸዋለን። ምንዳቸውንም ከሠሯቸው መልካም ሥራዎች ይበልጥ መልካም በሆነው (መኖሪያ) እንመነዳቸዋለን -- (አል ነህል 97)

ጥልቅ ግንዛቤ

የኢማንን እውነታዎች ማወቅ ብቻ ፋይዳ የለውም። ይህን እምነት ወደተግባር መለወጡ ነው ቁም ነገሩ። ኢብሊስ በአላህ አልካደም። ሌላው ቀርቶ እንደ ፊርዓውን እኔ የበላይ ጌታችሁ ነኝ _ ለማለት እንኳ አልደፈረም። ፈጣሪው አላህ መሆኑን ያውቃል። ለዚህም ነው እንዲህ ያለው።

(قَالَ مَا مَنَعَكَ أَلَّا تَسْجُدَ إِذ أَمَرْتُكَ قَالَ أَنَا خَيْرٌ مِنْهُ خَلَقْتَنِي مِن نَّارٍ وَخَلَقْتَهُ مِن يلين

(አላህም ባዘዝኩህ ጊዜ እንዳትሰግድ የከለከለህ ምንድን ነው? ሲል ጠየቀው እኔ ከርሱ የተሻልኩ ነኝ። እኔን የፈጠርከኝ ከእሳት ሲኾን እርሱን ግን የፈጠርከው ከጭቃ ነው አለ። (አል አዕራፍ 12) በአላህ ክብር ምሏል፡-

((قَالَ فَريكَ لَأُغْوِنَهُمْ أَجْمَعِينَ

«ዲያቢሎስም እንዲህ አለ “በአሸናፊነትህ እምላለሁ። ሁሉንም መንገድ አስታቸዋለሁ›› (ሷድ 82)

ቂያማ የሚባል ቀን እንዳለም ያምናል፡-

(قَالَ أَنظِرْنِي إِلَى يَوْمِ يُبْعَثُونَ

«(ዲያቢሎስም)- እስከሚቀሰቀሰበት ቀን ድረስ አቆየኝ ሲል ጠየቀ (አል አዕራፍ 14)

የአምላኩን ትእዛዝ በጣሰ ጊዜ እምነቱ ጠቀመውን? በፍጹም አልጠቀመውም።

«በአላህ እምላለሁ። ከሌሎች እላለሁ የሚል ሰው ያጋጥመሐል። ትሰግዳለህን?› በማለት ስትጠይቀው ግን «እውነቱን ለመናገር አልሰግድም። ግና አላህ ፈጣሪና መጋቢ መሆኑን አውቃለሁ›› ይላል።

ኢማን ማለት ምንድን ነው? በቀልብ ውስጥ የሰረጸና በስራ የተረጋገጠ አይደለምን? እምነት ከስራ ሊነጠል ፈጽሞ አይችልም። ቁርአን ሁለቱን ምንጊዜም አስተሳስሮ ነው የሚያመጣቸው።

(الَّذِينَ ءَامَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ طُوبَى لَهُمْ وَحُسْنُ مَئَابٍ

እነዚያ ያመኑትና መልካም የሠሩት ስኬትና ድሎት ይጠብቃቸዋል። መልካም መመለሻም (ተዘጋጅቶላቸዋል) (ላቸውም) (አል ረዕድ 29)

የመፍጠር ባለቤት የሆነው አምላክ የማዘዝም ባለቤት ነው። በፈጣሪነቱ ማመን ትእዛዙን መፈጸምን ግድ ያደርጋል። አላህ እንዲህ ብሏል።

الامر (أَلَا لَهُ الْخَلْقُ وَالأَمر تَبَارَكَ اللهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ አዋጅ መፍጠርም ማዘዝም የርሱ ሥልጣንና መብት ነው የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ (ክብር ላቀ (አል አዕራፍ 54)

(وَكَانَ أَمْرُ اللَّهِ مَفْعُولًا

«የአላህ ትእዛዝ ምንጊዜም ተፈጻሚ መሆን አለበት።» (አል አህዛብ 36)

የሐይማኖታችን መጠሪያ ስም ኢስላም ሲሆን፣ በዚህ ሐይማኖት የሚያምን ሁሉ ደግሞ ‹ሙስሊም› ይባላል። ኢስላም አላህን ያለ ተቃውሞ መታዘዝ ሲሆን ሙስሊም ለአላህ እጅ የሰጠ፣ ትእዛዙን እስከቻለ ድረስ ያለ ተቃውሞና ቅሬታ የሚፈጽም ማለት ነው።

ምን አልባትም ከአንድ ወንጀል ላይ -ሐራም መሆኑን እያወቅክ ልትወድቅ ትችላለህ። ግና ከርሱ መቶበትን ትመኛለህ። ስህተትን ማወቅና ከርሱ ለመጽዳት መሞት መልካም ጅማሬ ነው። ከወንጀል ላይ የጸና፤ እንደሚፈቀድለት ያመነ፣ አልተወውም በማለት የተኮፈሰ ግን ኢብሊስን ከአላህ እዝነት ካራቀው ችግር ውስጥ እርሱም ወድቋል።

አስፈላጊ አዋጅ

ኢብሊስ ለአደም ባለመስገድ ጥፋት ብቻ አልተወሰነም። ከዚህም አልፎ በርሱ ላይ ጦርነት አውጇል። ለዚህ ጦርነትም ዓላማ አስቀምጧል። ስትራቴጂ ነድፏል። ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቷል። ስለዚህም ግል ጠላታችን ነው። እነሆ፣ አላህ እንዳዘዘን ጠላት አድርገን እንያዘው:

ف إِنَّ الشَّيْطَنَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَاتَّخِذُوهُ عَدُوا إِنَّمَا يَدْعُوا حِزْبَهُ لِيَكُونُوا مِنْ أَصْعَبِ الشعير (ج)

«ሰይጣን በእርግጥም ጠላታችሁ ነው። ስለሆነም ጠላት አድርጋችሁ ያዙት። ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ሰዎች እንዲሆነ ነው. (ፋጢር 6)

ለዚህም ቃል እንግባ። ኢብሊስ እኛን ገደል ለመክተት ለራሱ ቃል ገብቷል። እንዲህ ብሏል።

قَالَ أَنظرت إِلَى يَوْمِ يُبْعَثُونَ قَالَ إِنَّكَ مِنَ الْمُنظَرِينَ) قَالَ فَبِمَا أَغْوَيْتَنِي لَأَقْعُدَةٌ هُمْ مرطك الْمُسْتَقِيمَ ثُمَّ لَهُم مِن بين أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَنِهِمْ وَمَن شَمَالِهِمْ وَلَا تَجِدُ

أكثر هم شكرين

«ዲያቢሎስም)- እስከሚቀሰቀሰበት ቀን ድረስ አቆየኝ ሲል ጠየቀ (አላህም) - አንተ (እስከተወሰነ ወቅት ድረስ) ከሚቆዩት ተደርገሃል አለው።

መንገድ እንድስት ስላደረግከኝ ከቀና ጐዳና መካከል እቀመጥባቸዋለሁ አለ ከዚያም ከፊት ለፊታቸውም፡ ከበስተኋላቸውም፡ ከበስተቀኞቸውም ከበስተግራቸውም እመጣባቸዋለሁ። አብዛኛዎቹንም (ለፀጋዎችህ) ምስጋና አድራሾች ሆነው አታገኛቸውም። (አል አዕራፍ 14-17)

ከኢብሊስ ጥቃት የምንድነው የአላህን ቃል ኪዳን ስንይዝ፣ ወደርሱ ስንመለስ ብቻ ነው።ቁርአን የኢብሊስን የአመጽ ባህሪ፣ በኛ ላይ ጦርነት ማወጁንና ዝርዝር እቅዱን አብራርቶልናል። ስለዚህም የጠላታችን ሐሳብና ዓላማ ግልጽ ነው።

ሴራው የአደባባይ ሚስጥር ነው። እኛም በጦርነቱ የሚሸነፍ ሰው ሽንፈቱ ለርሱ ተገቢው አይደለምን?

አላህ ለኛ ሲል ኢብሊስን ጠላት አድርጓል። ከእዝነቱ አባሮታል። ረግሞታል። በተላቁ እጆቹ ፈጥሮ ሩህ ካስገባብን በኋላም የኢብሊስን ጠላትነት ነግሮናል። ይህን ሁሉ ያደረገልንን አምላካችንን ትተን ከጠላታችን ከኢብሊስ ጋር፣ ጀሃነም ያስገባን ዘንድ የእርቅ ስምምነት እንፈራረማለን?

<u>የትእቢተኛ ቅጣት</u>

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

() قَالَ فَأَهْبِطَ مِنْهَا فَمَا يَكُونُ لَكَ أَن تَتَكَبَّرَ فِيهَا فَأَخْرُجْ إِنَّكَ مِنَ الصَّٰغِرِينَ

ከርሷ (ከገነት) ውረድ ከውስጧ ሆነህ ልትኮራ አይገባም። ውጣ። አንተ ከወራዶች ነህና አለው (አል አዕራፍ 13)

መዋረድ የኩራት ተቃራኒ ነው። አንቀጹ ለትእቢተኞች ሁሉ በዱንያ እንደሚዋረዱ፣ በመጭው ዓለምም እግሮች እንደሚረግጧቸው ማስጠንቀቂያ አዝሏል።

ሰዎች በእግራቸው ከሚረግጡት የበለጠ ወራዳ አለን? ይህን የሚያደርጉት የአንዲት ቀዬ ወይም ከተማ ሰዎች አይደሉም። በእለተ ቂያማ ለፍርድ በተሰበሰቡት ሁሉ እንጅ። ከነርሱ እግር ስር ለመቀስቀስ ግድ ይበረታል። እንዲህ ዓይነቱ ውርደት ለራሱ የሚል አለን?

<u>ወሰን የለሽ ጥላቻ</u>

ኢብሊስ ለአደም ያለው ጥላቻ ይህ ወሰን የሚባል አይደለም። ከአላህ የጠየቀ የጠላትነት ዘመን ይህን የጀመረ ጥላቻ በጉልህ ያነሳሳዋል።

አደም ሕይወት ወይም ከራሳቸው በኋላ እስከሚመጣው ትውልድ ድረስ ብቻ መቆየትን አልነበረም የጠየቀው። «እስከ እለተ ቂያማ፣ እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ።» ሲል የሰውን ልጅ ለማጥቃት

ረዥም እድሜ ጠይቋል። በእያንዳንዱ ትውልድ፣ በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ ጥላቻ የምቀኝነት ስሜቱን ማራገፍ ይፈልጋል።

ጥላቻና ምቀኝነት ለምን አይነት ጥፋት እንደሚዲን አህን ረፍት ይነሳል። አእምሮን ይቆጣጠራል። ጊዜን በበቀል ይሞላ። እተ ቀያች በኋላ ሌላ ዱንያዊ ሕይወት ቢኖር ኖሮ ፡ ኢብሊስ እስከዚያ ድረ ለመቆየት ይጠይቅ ነበር።

በእርግጥም ኩራት የጥፋቶች ሁሉ መሠረት ነው። ሕሊናን ያውራ ባለቤቱንም በጥላቻ ይሞላል። የእንቅስቃሴዎቹ ሁሉ ዓላማ ሱል እንዲሆን ይዳርጋል። ከጀሃነም ውጭ መድሐኒት የለውም።

<u>የተስፋ ድልብ</u>

ኢብሊስ በአላህ ትእዛዝ ላይ በማመጹ እርግማን ወረደበት። አላህ እዝነትም ተባረረ። ረዥም እድሜ ያኖረው ዘንድም አላህን ለመነ አላህም እንዲህ አለው፡-

«(አላህም)- አንተ (እስከተወሰነ ወቅት ድረስ ከሚቆዩት ተደርገል: አለው። (አል አዕራፍ 15)

እጅግ አስከፊ ፍጡር ቢሆንም ዱዓውን ተቀበለው። የርሱን ዱ የተቀበለው አላህ፣ አላህ ወደርሱ የሚመለስን አማኝ ዱዓ አይቀበልምን? አንድ ታቢዒ እንዲህ ብለዋል፡-

«ነውርህ እና እኩይ ድርጊትህ አያዘናጋህ። አላህ ከሁሉም የከፋ ፍ የሆነውን የኢብሊስን ዱዓ እንኳ ተቀብሏል።»

ስለሆነም በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብትሆን ከአላህ እዝነትና ይቅርታ ተስፋ አትቁረጥ። ከክህደት ውጭ ከእዝነቱ የሚያስወጣህ ወንጀል የሉ አላህን እጅግ በሚወደው ነገር ታዘህዋል። እርሱም ኢማን ነው። እጅግ የሚጠላውን ወንጀል፤ ማለትም ክህደትን ባለመቅረብም ታዘህዋል።

በነዚህ በሁለቱ መካከል ሆነህ የምትፈጽመውን ግድፈት ይምርህ ዘንድ ለምነው።

ኢብሊስ በሁሉም አቅጣጫ፣ በፊት በኋላ፣ በቀኝ በግራ እንደሚመጣ ሲናገር፡- «በላይ በኩል እመጣባቸዋለሁ» አላለም። ባንተ እና በአምላክህ መካከል ግርዶ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። ስለዚህም ጉዳይህን ወደ አላህ አንሳ። አስተማማኝ አቅጣጫና መንገድ ከላይ በኩል ያለው ብቻ ነው። ጅማራህ - አላህን መታዘዝ፣ በመካከላቸው ወንጀል ቦታ የለውም። ፍጻሜህም አፈር እስከሆነ ድረስ

<u>ኢብን አባስ እውነት ብለዋል</u>

ኢብሊስ የሰውን ልጅ የማጥመም እቅዱን ሲነድፍ እንዲህ ብሏል፡-

(قَالَ فَبِمَا أَغْوَيْتَنِي لَأَقْعُدَنَّ لَهُمْ صِرَاطَكَ الْمُسْتَقِيمَ

መንገድ እንድስት ስላደረግከኝ ከቀና ጐዳና መካከል እቀመጥባቸዋለሁ " አለ፤ (አል አዕራፍ 16)

እዚህ ላይ እጅግ አደገኛ የሆነ ሃሳብ ከኢብሊስ አንደበት ፈልቋል። እርሱም ከአላህ ጋር ስርዓት ማጣት የተንጸባረቀበት ነው። «አምላኬ ሆይ፣ ያጠመምከኝ አንተ ነህ።» ሲል አላህን ወንጅሎታል።

አንዳንድ ሰዎች ይህን የኢብሊስ እኩይ ሐሳብ ይጋራሉ፡-

→አላህ ቢሻ እሰግዳለሁ፣ ሂጅብም አደርጋለሁ፣ ይላሉ።

→ ሌሎቹ ደግሞ፡- «ጥሩ ሰው መሆን እፈልግ ነበር። ግና አላህ በጎ አልሻልኝም። ከንቱ አደረገኝ።» ይላሉ።

ይህ የኢብሊስ አስተሳሰብ ነው። አላህ በባሮቹ ላይ ወንጀልን ጽፎ እንዲሰሩት ያስገደዳቸው ያስመስላል። ይህም በመሆኑ አላህ የኢደምንና የኢብሊስን ታሪክ በአል አዕራፍ ምእራፍ ውስጥ ከዘከረ በኋላ እንዲህ ይላል፡-

وَإِذَا فَعَلُوا فَتَحِشَةً قَالُوا وَجَدْنَا عَلَيْهَا وَابَاءَنَا وَاللَّهُ أَمَرَنَا بِهَا قُلْ إِنَّ اللَّهَ لَا يَأْمُرُ اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ قُلْ أَمَرَ رَبِّي بِالْقِسْطِ وَأَقِيمُوا بِالْفَحْشَاءِ أَتَقُولُونَ عَلَى

(وُجُوهَكُمْ عِندَ كُلِّ مَسْجِدٍ وَادْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينُ كَمَا بَدَأَكُمْ تَعُودُونَ

فَرِيقًا هَدَى وَفَرِيقًا حَقَّ عَلَيْهِمُ الضَّلَالَةُ إِنَّهُمُ اتَّخَذُوا الشَّيْطِينَ أَوْلِيَاءَ مِن دُونِ اللَّهِ وَتَحْسَبُونَ أَنَّهُم مُهْتَدُونَ

«(አጋሪዎች ፀያፍ ተግባርን በፈፀሙ ጊዜ አባቶቻችን ይህንኑ ሲፈጽሙት አግኝተናል። አላህም ይህን እንድንፈጽም አዞናል።" ይላሉ አላህ በፀያፍ ድርጊት አያዝም: በአላህ ላይ የማታወቁትን ነገር ትናገራላችሁን? በላቸው: ጌታዬ ያዘዘው ፍትህን እንድታሰፍኑ ነው: በማንኛውም ቦታና ጊዜ ስትፀልዩ ፊታችሁን (ወደርሱ) እንደ ታዞሩ ነው በፍፁም ቅንነትና ታማኝነት አምልኩት። "መጀመሪያ እርሱ እንደፈጠራችሁ (በመጨረሻም ወደ ርሱ ትመለሳላችሁና።" በላቸው ከፊሉን ወደ ቅኑ ጐዳና መራ ከፊሎችም መንገድ እንዲስቱ ተወሰነባቸው ምክንያቱም እነርሱ ከአላህ ሌላ ሰይጣናትን ወዳጆቻቸው አድርገዋልና ቅኑን ጐዳናም እንደያዙ ያስባለ » (አል አዕራፍ 28-30)

ኢብሊስ እንዲህ ሲል ዝቷል፡

“ወደ መስጊድ ከሚሄድ፣ ሂጃብ ከምታደርግ፣ ዝምድናን ከሚቀጥል፣ በኒያው እንኳ ቢሆን በጎ ለመስራት ከሚጥር ሰው መንገድ ላይ እቀመጣለሁ። ደግ እንዳይሰሩም እንቅፋት እሆናቸዋለሁ።።»

የቡና ቤት (ባር) ሰዎችማ ግድ አይሰጡትም። እነርሱው ራሳቸው እርሱ የሚፈልገውን እያደረጉ ከድካም ገላግለውታል። አብደላህ ቢን አባስ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

አንድ ሰው ከኔ ዘንድ መጣና አይሁዶች የሰይጣን ውስወሳ እንደማያጋጥማቸው ይናገራሉ» አለኝ። «እውነት ብለሐል፡ ሰይጣን ከፈረሰ ቤት ውስጥ ጉዳይ የለው።» አልኩት።

ሰይጣን ሾተል የመዘዘው አላህን በሚታዘዙ ሰዎች ላይ ነው። ሰውየው መቀናቱ በጨመረ ቁጥር የሰይጣን ጦርነትም የዚያኑ ያህል ይበረታል።

የጦርነቱ ባህሪ ይህን ይመስላል።በጽናት ትፋለማለህ ወይስ ትልፈሰፈሳለህ?

ይህም በመሆኑ ሙስሊም ከሰይጣን ፊት የትግል አርማ ሊያነሳ ይገባል። መፈክሩም አላህን መታዘዝ እና ከወንጀል መቶበት ይሁን።

በመልካም ኒያና ስራ፣ በበጎ ነገር ላይ በመጽናት አላህን ይታዘዛል። ወንጀልን በመተውና ከርሷ በመቶበትም ይታገላል። የሰይጣን ሴራ ደካማ ነው። ይህም ሆኖ ግን እግርህ ከጀነት _ ምድር _ እስኪያርፍ ድረስ አይተውህም።

<u>ጥንቃቄ</u>

ሰይጣን የሰውን ልጅ የሚያጠቃባቸውን አራት አቅጣጫዎች እንዲህ ሲል አመላክቷል፡-

ثم لا يَنهُم مِّنْ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَنِهِمْ وَعَن شَمَائِلِهِمْ وَلَا تَجِدُ أَكْثَرَهُمْ شَكِرِينَ

ከዚያም ከፊት ለፊታቸውም ከበስተኋላቸውም ከበስተቀኛቸውም ከበስተግራቸውም እመጣባቸዋለሁ አብዛኛዎቹንም (ለፀጋዎችህ) ምስጋና አድራሾች ሆነው አታገኛቸውም" (አል አዕራፍ 17)

ሁለት አቅጣጫዎችን ግን አላወሳም። ምክንያቱም በነርሱ በኩል ማጥቃት አይችልምና። እነርሱም ላይና ታች ናቸው። ከዚያም፡- «ብዙዎቹን አመስጋኞች ሆነው አታገኛቸውም» ሲል ደመደመ።

አስተውል። ቁርአን የሰይጣንን ስልት እና መግቢያ መንገድ፣ እንዲሁም የበለጠ አመስጋኝ የምትሆንበትን ብልሐት አመላከተ። የሰይጣንን ይሁንታና ስልት -ትጠነቀቀው ዘንድ - ምንድን ነው?

⇒አምላክህን ያስረሳሐል፡ ጸጋዎቹንም እርሱን ማመስገንን ትዘነጋ ዘንድ ያስረሳሐል። በአራቱም አቅጣጫዎች የሚያከናውነው ተግባር ይህ ነው።

⇒ጥቃቱን ለመመለስ፣ ሴራውን ለማክሸፍ ልትከተለው የሚገባህን ስልት ደግሞ ልጠቁምህ፡-

⇒ ዘወትር አላህ የለገሰህን ጸጋ አስታውስ። ጸጋን ማስታወስ ቀልብን ያለዝባል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(فَاذْكُرُوا وَالَاءَ اللَّهِ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ

“ትድኑ ዘንድ የአላህን ፀጋዎች አስታውሱ (አል አዕራፍ: 69) ይህም የጸጋውን ባለቤት የመውደድን ስሜት ከልቦና ላይ ይፈጥራል፡

⇒ ሁሌም ለሁለቱ አቅጣጫዎች ትኩረት ስጥ። እነሱም የሱጁድና የዱዓ አቅጣጫ ናቸው። እነርሱ የአላህ እዝነት ማረፊያዎች በመሆናቸው ኢብሊስ በነርሱ በኩል ወዳንተ ለመቅረብ አይደፍርም።

ግልጽ ኪዛራ

ተከታዩን የአላህ ቃል አብረን በጥሞና እናንብበው። በአንቀጾቹ ውስጥ የሰፈረውን እናነጻጽረው፡ የኢብሊስ አባባል ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር

إِن يَدْعُونَ مِن دُونِهِ إِلَّا إِنَٰثًا وَإِن يَدْعُونَ إِلَّا شَيْطَٰنًا مَّرِيدًا لَعَنَهُ اللَّهُ وَقَالَ لَأَتَّخِذَنَّ مِنْ عِبَادِكَ نَصِيبًا مَفْرُوضًا (٣) وَلَأُضِلَّنَّهُمْ وَلَأُمَنِّيَنَّهُمْ وَلَآمُرَنَّهُمْ فَلَيُبَتِّكُنَّ وَاذَانَ الْأَنْعَمِ وَلَآمُرَنَهُمْ فَلَيُغَيِّرُنَ خَلْقَ اللَّهِ وَمَن يَتَّخِذِ الشَّيْطَانَ وَلِيًّا مِن دُونِ اللَّهِ فَقَدْ خَسِرَ خُسْرَانًا مُّبِينا)

«(አጋሪዎች) ከርሱ (ከአላህ) ውጭ እንስቶች (ጣዖታትን) እንጅ አያመልኩም:: አመፀኛውን ሰይጣንን እንጅ አይገዙም። (ሰይጣንን) አላህ ረግሞታል። እርሱም “ከባሮችህ የተወሰነን ድርሻ በእርግጥ እይዛለሁ : ብሏል። “በእርግጥ አጠማቸዋለሁም። (ከንቱ) ምኞቶችም አስመኛቸዋለሁም የእንስሳትን ጆሮዎች እንዲተለትሉም አዛቸዋለሁ የአላህን ዲን (በክህደትና በኃጢአት) ይለውጡ ዘንድም አዛቸዋለሁ

(ብሏልም)። ሰይጣንን ከአላህ ውጭ ረዳቱ አድርጐ የያዘ ሰው ግልጽ የሆነን ኪሣራ ከሰረ።›› (አል ኒሣእ 117-119) የኢብሊስ ጥላቻ መጨመሩን አስተዋልክን? እንዲህ ይላል፡-

⇒ በማይጨበጥ ምኞት አጠፋቸዋለሁ። በተለያየ ስልት ከዝሙት ውስጥ እንዲዘፈቁ አደርጋለሁ። ለምሳሌ _ አንዲት ወጣት ከአንድ ወጣት ጋር በፍቅር› እንዲተሳሰሩ፣ ግንኙነትም እንዲጀምሩ አደርጋለሁ። ልጅት ግንኙነታቸው ለፍሬ እንደሚበቃ በማሰብ በባዶ ምኞት ትሞላለች። ወንዱ ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እርሷን ትቶ ሌላ ሴት ያገባል። እርሷም ሁሉንም ነገር ታጣለች።

⇒ ወደ ጥመትና ወደ ትልቅ ወንጀል _ ውስጥም _ እጥላቸዋለሁ። ወላጆቹን የሚታዘዝን ወጣት በሌላ መንገድ እመጣበታለሁ። ለምሳሌ ትምህርቱን እንዳያጠና እጎተጉተዋለሁ። ‹‹ጎበዝ ስለሆንክ ፈተና ሲደርስ ታጠናለህ። ከአሁኑ ለምን ራስህን ታደክማለህ›› ስል አግባባዋለሁ። እርሱም ጥናት ያቆማል። በፈተናም ይወድቃል። ወላጆቹም በውድቀቱ እሳት እንዲለበለቡ አደርጋለሁ።

አንተ ወጣት ሆይ፣ ለወላጆችህ የስኬትን ደስታ ለምን ትነፍጋቸዋለህ? ይህስ መብታቸውን መጣስ አይደለምን? ልጆች ለወላጆቻቸው ኡፍ የምትል ቃል እንኳ እንዳይናገሩ ከልክሏል። ይህ ቃል ቢያንስ ያበሳጫቸዋል። ቃሉ በአንደበት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ሊገለጽ ይችላል። ጥናትን መተው ከዚህ ቃል ቢበዛ እንጅ አያንስም። ከወላጅ ፊት ላይ ከመትፋት አይተናነስም። ወላጆችህ ይህ ድርጊት ባንተ ሊፈጸምባቸው ይገባልን?

ወጣቷ እህቴ ሆይ፣ ኢብሊስ እንዲህ ይልሻል፡-

«ሂጃብ መልበስ ግዴታ ቢሆንም በኋላ ይደርሳል። አሁን የደስታሽ ቀን ስለሆነ አያስፈልግሽም። በሰርግሽ ቀን ውበትሽን ሰዎች ቢያዩት እና ቢያደንቁት ክፋት የለውም። ሂጃብ ከጋብቻ በኋላ ትለብሻለሽ።›››

ሰይጣን ይህን ይላል። የሰርጓን ቀንም እንደልቡ ይጫወትባታል። እንዳሻው ይዘልባታል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(إِنَّ اللَّهَ لَا يُصْلِحُ عَمَلَ الْمُفْسِدِينَ

«አላህ የበካዮችን ምግባር መልካም አያደርግምና።" አለ። (ዩኑስ 81)

ሰይጣን እንዲህ ሲልም ዝቷል፡-

«የአላህን ፍጥረታት እንዲለውጡ አደርጋቸዋለሁ። ወጣቶቹ ወንዶች ከፊል ራሳቸውን ተላጭተው ከፊሉን እንዲተው፣ ከጆሮና ከአፍንጫቸው ሎቲ እንዲያንጠለጥሉ አደርጋቸዋለሁ። በሁሉም መስክ እና መንገድ እዋጋቸዋለሁ። በስነ-ምግባር፣ በስራ፣ በቤተሰብ መስኮች እፋለማቸዋለሁ፡

አላህ ለዚህ የሰይጣን ዛቻ የሰጠው መልስ የጠላትነቱን አስከፊነት ያሳይሐል። እንዲህ ብሏል፡-

وَلَأُضِلَّنَّهُمْ وَلَأُمَنِّيَنَّهُمْ وَلَآمُرَنَّهُمْ فَلَيُبَتِّكُنَّ عَاذَانَ الْأَنْعَمِ وَلَآمُرَنَّهُمْ فَلَيغَيرنَ خَلْقَ اللهِ وَمَن يَتَّخِذِ الشَّيْطَنَ وَلِيًّا مِّن دُونِ اللَّهِ فَقَدْ خَسِرَ خُسْرَانًا مُبِينًا يَعِدُهُمْ وَيُمَنِيهِمْ وَمَا يَعِدُهُمُ الشَّيْطَانُ إِلَّا غُرُورًا)
النساء ١١٩ - ١٣١ أُولَئِكَ مَا وَلَهُمْ جَهَنَّمُ وَلَا يَجِدُونَ عَنْهَا يَحِيصًا

በእርግጥ አጠማቸዋለሁም (ከንቱ) ምኞቶችም አስመኛቸዋለሁም : የእንስሳትን ጆሮዎች እንዲተለትሉም አዛቸዋለሁ የአላህን ዲን (በክህደትና በኃጢአት) ይለውጡ ዘንድም አዛቸዋለሁ" ብሏልም። ሰይጣንን ከአላህ ውጭ ረዳቱ አድርጐ የያዘ ሰው ግልጽ የሆነን ኪሣራ ከሰረ (ተፈጻሚነት የሌለው ተስፋ ቃል ይሰጣቸዋል : ከንቱ ምኞቶችንም ያስመኛቸዋል ሰይጣን ከንቱ ቃልን እንጅ አይገባላቸውም። እነኝህ መኖሪያቸው ገሃነም ናት። ከርሷ ማምለጫን አያገኙም።›› (አል ኒሣእ 119-121)

<u>ተሳካለትን?</u>

የሰይጣን የጦርነት ስልቶች በበርካታ የቁርአን ምእራፎች ውስጥ ተመልክተዋል። በእርግጥ የአንዱ ምእራፍ ድምጸት ከሌላው ይለያል። ሁሉም ግን የሰውን ልጅ ሙሉ ለሙሉ ሊያጠፉ የሚችልን የሰይጣን

ክፋት በመግለጽ ላይ ይስማማሉ። በአል _ ኢስራእ ምእራፍ ውስጥ የሰፈረውን መልእክት አስተውል፡-

قَالَ أَرَءَيْتَكَ هَذَا الَّذِي كَرَّمْتَ عَلَىَ لَئِنْ أَخَرْتَنِ إِلَى يَوْمِ الْقِيَمَةِ لَأَحْتَنِكَنَّ ذُرِّيَّتَهُ إِلَّا قَلِيلا) الإسراء: ይህን ከኔ ያላቅከውን (ደካማ ፍጡር) አየህን? እስከ ዕለተ ትንሳኤ ካቆየኸኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ሙሉ በሙሉ አጠማቸዋለሁ። (አለም)፡ (አል ኢስራእ 62)

ጥላቻውን አጠማቸዋለሁ እና ስርዓት አልበኝነቱን ተመልከት። የሚለውን ገለጻ ተመልከት። «በእርግጥ ለአህተኒከነሁም» የሚለው የዓረብኛው አገላለጽ በአጽንኦትና በመሐላ የተጠናከረ ነው። የቃሉ መሠረት ‹ሐነኩ ሲሆን፣ ትርጉሙም ‹‹ልጓም›› ማለት ነው። ከአፋቸው ውስጥ ልጓም አስገብቼ እጎትታቸዋለሁ›› ማለቱ ነው።

አንዳንዶቻችን ቁርአን አንቀራም። ቁርአንን ብናነሳው ለመቅራት

ይከብደናል። አላህ ቁርአንን ገር አድርጎታል። ግና በአፋችን ውስጥ ያለው የሰይጣን ልጓም ከቁርአን ይስበናል። ሰይጣን፡- ‹‹ጥቂቶች ብቻ እንጅ የሚያመልጠኝ የለም›› ሲል ዝቷል፡ ዛቻው ተሳካለትን አንተን ማሸነፍ ሆኖለታልን? አላህ እንዲህ ብሏል፡-

قَالَ اذْهَبْ فَمَن تَبِعَكَ مِنْهُمْ فَإِنَّ جَهَنَّمَ جَزَاؤُكُمْ جَزَاء مَوْفُورًا وَاسْتَفْزِزْ مَنِ اسْتَطَعْتَ مِنْهُم بِصَوْتِكَ وَأَجلِبْ عَلَيْهِم بِحَمْلِكَ وَرَجِلِك وَشَارِكَهُمْ فِي الْأَمْوَالِ وَالْأَوْلَدِ وَعِدُهُمْ وَمَا يَعِدُهُمُ الشَّيْطَانُ إِلَّا غُرُورًا) و الاسترالية ٦٣ ـ ٦٠ ‹‹አላህም-ሂድ ከነርሱ የተከተለህ ገሃነም ቅጣታችሁ ይሆናል ተገቢ የሆነ ቅጣት" አለው። ከነርሱ ውስጥ የቻልከውን በድምጽህ አታልል በፈረሰኛና እግረኛ ሠራዊትህም ዝመትባቸው ገንዘባቸውንም ልጆቻቸውንም ተጋራቸው፡፡ ቃልም ግባላቸው። (አለውም) ሰይጣን የሚገባላቸው ቃልኪዳን ማታለል እንጅ ሌላ አይደለም›› (አል ኢስራእ 63-64)

«ሂድ» ማለቱ ጥያቄውን መቀበሉን አያመለክትም። ቁጣንና ማዋረድን እንጅ። የሰይጣንን ወዳጅነት የወደደ፣ ከአፉ ልጓም እንዲያደርግበት የፈቀደ ሁሉ ቅጣቱ ጀሃነም ይሆናል፡ የጦርነቱን ባህሪ ተረዳህንን ኢብሊስ በእግረኛ እና በፈረሰኛ ሰራዊቱ፣ እንዲሁም ሸህዋ ቀስቃሽ በሆነ ድምጹ ጦርነቱን ይጀምራል።

⇒የወሲብ ስሜት የሚያቀጣጥሉ ድምጾችን ያመጣል። ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ከቤተሰብ ተደብቀው ስለ ወሲብ ያወጋሉ። በእርግጥ የሚያወጉት በራሳቸው አንደበት አይደለም። በሰይጣን እንጅ።

⇒የሐራም ገንዘብ እና በርሱ የመሳተፍ ድምጽ፣ ለማይጠቅም ወይም ለሚጎዳ ነገር የማዋል ድምጽ፣ ገንዘብን

⇒ቤተሰብ አላህን ያለመታዘዛቸው ድምጽ፣ ይህ ሲሆን ሰይጣን በልጅ አስተዳደግ ይጋራቸዋል። ልጆች ሰይጣናዊ በሆነ መልኩ ያድጋሉ።

⇒ለሶላት የሚደረግን አዛን የሚሸፍን ድምጽ። እነዚህና ሌሎችም የሰይጣን ድምጾች ናቸው። ከኛ ዘንድ ይህ ሴራው በሙሉ ወይም በከፊል ተሳክቶለታልን? አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(وَلَقَدْ صَدَّقَ عَلَيْهِمْ إِبْلِيسُ ظَنَّهُ فَاتَّبَعُوهُ إِلَّا فَرِيقًا مِنَ الْمُؤْمِنِينَ

«ሰይጣንም ምኞቱን አረጋገጠባቸው። እነርሱም ተከተሉት ጥቂት አማኞች ሲቀሩ።» (ሰበእ 20)

<u>ምክንያቱ አንተ ነህ</u>

ጎበዝ፣ ለዚህ ጦርነት እንንቃ። ኢብሊስ አያት ቅድመ አያቶቻችንን ሲያከስር ኖሯል። የመጀመሪያውን አባታችንን አደምን ከጀነት አስወጥቷል። ጎበዝ ንቃ። ያንተ ሰራዊት እና ጉልበት ከኢብሊስ ጉልበት ይበልጣል። መሳሪያህን ዘንግተህ፣ ትጥቅህንና ስንቅህን ረስተህ ወደ ጦር ሜዳ መግባት ትሻለህን? ይህን ካደረግክ እንዲያሸንፍህ መንገዱን

ያመቻቸህለት፣ እንዲረታህ በሩን የከፈትክለት አንተ ነህ። አላህ እንዲህ ብሏል፡

((أَفَتَتَّخِذُونَهُ، وَذُرِّيَّتَهُ أَوْلِيَاءَ مِن دُونِي وَهُمْ لَكُمْ عَدُوٌّ بِئْسَ لِلظَّالِمِينَ بَدَلًا
الكهف

«እርሱንና ዝርያዎቹን (ግልጽ) ጠላቶቻችሁ ሆነው እያለ፣ ከኔ ሌላ አጋር አድርጋችሁ ትይዟቸዋላችሁን? ለበዳዮች የሚሰጠው ልዋጭ የከፋ ነው።» (አል ከህፍ 50)

ከአላህ በመራቅ ራስህን የበደልከው አንተው ራስህ ነህ። አላህን ስትታዘዝ ታሸንፋለህ። አላህ ካንተ ጋር ከሆነ የሰውና የአጋንንት ሰይጣናት ምን ሊያደርጉህ ይችላሉ?

አካልህ አላህን ከታዘዘ መለኮታዊ ሰራዊትህ ይሆናሉ። አይንንና ምላስን ከሐራም መጠበቅ፣ ዘወትር ውዱእ ማድረግ፣ ጆሮን ከነገር ማሳበቅ መጠበቅ፣ እነዚህን አካሎችህን የአንተ ያደርጋቸዋል። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ኢብሊስ ባንተ ላይ ስልጣን አልተሰጠውም። የወንጀልን ጥሩነት ተከራክሮ ሊያሳምንህ፣ እንድትሰራውም ሊያስገድድህ አቅም የለውም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(إِنَّ عِبَادِى لَيْسَ لَكَ عَلَيْهِمْ سُلْطَنٌ إِلَّا مَنِ اتَّبَعَكَ مِنَ الْغَاوِينَ

“በባሮቼ ላይ (ቅንጣት) ሥልጣን የለህም። ራሳቸውን ለጥመት የዳረጉትና የተከተለህ ሲቀሩ።” (አል ሂጅር 42)

ማድረግ የሚችለው መወስወስ ብቻ ነው።አላህን በመታዘዝና በተውባ ውስጥ እስካለህ ድረስ አንተን ከመወስወስ አይሰለችም። ትልልቅ ወንጀሎችን እንድትሰራ ይጋብዝሐል። ካልተሳካለት ትንንሽ ወንጀሎችን አቅልሎ ያሳይሐል። ከሐላል ነገሮች አብዝተህ ከኢባዳ እንድትዘናጋ ሊያደርግህ ይሞክራል። ይህም ሲሆን መስጊድ ውስጥ ሶላት ለመስገድ ጊዜ ታጣለህ። በሂደትም በስራ ቦታህ ወይም በቤትህ ውስጥ ለሶላት ጊዜ

እንዳታገኝ ያደርግሐል። በመጨረሻም ሶላት እንድትተው ያደርግሐል። እርሱን ከተውክ ሌሎች የዲን ተግባራትን ለመተው ይቀልሐል። ይህን ካልቻለ ሌሎችን እንድትጠላና እንድትርቅ ያደርግሐል። ጥላቻዊንን ይላጫል። ሰይጣን የፈለገውን ውጤትም ያገኛል።

በዚህ ካልቻለ በወሲብና በሸህዋ ይመጣብሐል። መጥፎ ጓደኞችን ያሰማራብሐል። ጦርነቱን መቼም ቢሆን አያቆምም። የጥፋት አርማውን አያወርድም። የምቀኝነት ሾተሉን አይመልስም። አላህ እንዲህ ብሏል፦ ወደ አፎቱ መቼም ቢሆን

(وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُّبِين

«የሰይጣንን ፈለግ አትከተሉ ግልጽ ጠላታችሁ ነውና።» (አል በቀራህ 168)

ይህም ሆኖ ግን አላህን እስከታዘዝክና እርሱ አብሮህ እስከሆነ ድረስ ድል ያንተ ነው። ወንጀል ላይ በምትወድቅ ጊዜ ወዲያውኑ እስከተጸጸትክ ድረስ ድሉ ያንተ ነው። የመዳኛ ቃላት የሆኑትን ኢስቲግፋርንና ተውባን በእጅህ ይዘህ እንዴት ትጠፋለህ። አባትህ አደም የዳነው በነዚህ ነው።

<u>የሐዋ አፈጣጠር</u>

ኢብሊስ ከጀነት ተባረረ። ከውስጧም ብቻውን ይኖር ጀመር። ብቸኝነትም ተሰማው። ተኝቶ እያለም ከጎን አጥንቱ አላህ ሐዋእን ፈልቅቆ አወጣለት። ሲነቃ ከጎጉ አገኛት። «ማን ነሽ?» ሲልም ጠየቃት። «እንስት ነኝ» አለችው። «ስምሽስ» ሲላት «ሐዋእ» ስትል መለሰች። «ለምን ተፈጠርሽ?» ሲላት «ወደኔ እንድትረጋ፣ በኔ እንድትረካ» አለች፦

ለምን «ኢምረአህ» (እንስት) ስትል መለሰች? ቃሉ የተፈለቀቀው ‹መርእ› (ወንድ) ከሚለው ቃል ነው። እርሷም የተፈለቀቀችው ከወንድ ሲሆን፣ ተባእት በውስጧ የሚገኝ የእርሷ አካል ነው።

⇒ ለምን ሐዋእ ተብላ ተጠራች? ሐዋእ፡ (ሕያው) ማለት ሲሆን፣ በዚህ ስም የተጠራችው ሕያው ከሆነ ነገር ማለትም ከወንድ አጥንት ስለተፈጠረች ነው።

⇒ ለምን ተኝቶ እያለ ተፈጠረች? ኢማም ቁርጡቢ እንዳሉት በአፈጣጠሯ ሕመም እንዳይሰማውና ይህን ሕመሙን ባስታወሰ ቁጥር ለርሷ ያለው መልካም ስሜት እንዳይደፈርስ ሲባል ነው። እናም ቀልቡ ምንጊዜም በፍቅሯና ለእርሷ በማዘን እንደተሞላ ይኖራል፡ እንስት በምታረግዝበትና በምትወልድበት ጊዜ እጥፍ ድርብ ሕመም ይሰማታል።

حَمَلَتْهُ أُمُّهُ وَهْنًا عَلَى وَهْنٍ) لقمان: ١٤

እናቱ ከድካም ላይ ድካምን እያስተናገደች አረገዘችው" (አልነው)። (ሉቅማን 14) ይህም ሆኖ ግን ለልጆቿ ያላት ፍቅር በቃላት ሊገለጽ አይችልም።

ምክንያቱም ከእንስት ስሜት ውስጥ እንዲህ አይነት ስሜት (Emotion) በጣም ያየለና የበዛ ስለሆነ ነው።

መርጋት ወይም መርካት ትርጉሙ ምንድን ነው?በርሷ አማካይነት ውስጣዊ ሰላምን ማግኘ ማለት ነው። ወንድ ያለ ሴት ይዋልላል። እርጋታ ያጣል። እርካታ ይነፈጋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَمِنْ ءَايَتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَجًا لِتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم

مَوَدَّةً وَرَحْمَةُ إِنَّ فِي ذَلِكَ لَآيات لقوم يتفكرُونَ) الروم

«ከራሳችሁም የሆነችን ተጣማሪ ትረኩባት ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና መተዛዘንን ማድረጉ ከተአምራቱ ነው በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሰዎች ተአምራት አለ። (አል ሩም 21)

አንች ሙስሊም እንስት ሆይ፣ የአላህ ተአምር ነሽ። ይህን ተገንዝበሽ ታውቂያለሽን? የፍቅር፣ የእዝነትና የውስጣዊ ሰላም ሙዳይ ነሽ። ይህን

ሚናሽን ለመጫወት ዝግጁ ነሽን? አላህ አደምንና ሐዋእን በአንድ ላይ መፍጠር ይችል ነበር። ግና የብቸኝነትን ስሜት ያውቅ ዘንድ ለተወሰነ ጊዜ ብቻውን ተወው። በእርግጥም ጀነት ውስጥ ሆኖ ይህ ስሜት ተሰማው። ሐዋእ ስትፈጠር ተወገደለት። ወንድ ልጅ ከእንስት ሰላምንና እርካታን ካጣጣመ በኋላ የእርሷን መፈጠር ጥበብ አይዘነጋም። የጀነት ድሎት እንኳ እርሷን በማጣት የሚፈጠረውን የብቸኝነት ስሜት ሊያጠፋ፣ ክፍተቱን ሊሞላ አልቻለም። ሐዋእ ግን የብቸኝነቱን ጨለማ ገፈፈች። የእርጋታና የእርካታ ብርሃን ፈነጠቀች። ተጋቢዎች ይህ ጥልቅ መልእክት ሰርጿቸዋልን?

ከመብት በፊት ግዴታ

እንስት ከቤቷ ልትወጣ ስታስብ ብቻ ራሷን እያበጃጀች በቤት ውስጥ ግን ንጽህናዋ ሳያሳስባት፣ ለአለባበሷ ሳትጨነቅ በባሏ ፊት እንዳሻት መሆኗ ተገቢ ነገር አይደለም። ሙስሊም እንስት በቤቷ ውስጥ ሰላም እንዲነግስ በመጣር፣ ልጆቿን በመንከባከብና የቤቷን ድባብ ለባሏ ስክነት በማዘጋጀት ራሷን ለእርሱ መርጊያና መርኪያ ማድረግ ትችላለች። ወደ ቤት ሲመጣ በፈገግታ አስተናግድው። አለባበስሽም ያማረ ይሁን፡ ሚናሽን ምንጊዜም አስታውሺ። የርሱ መርጊያና መርኪያ መሆንሽ ይታሰብሽ። ባልሽ በቤት ውስጥ ጋዜጣ ይዞ መቀመጡ፣ ከቴሌቭዥን ስር ማፍጠጡ ወይም ውጭ ከጓደኞቹ ጋር መሆኑ ሊያበሳጭሽ ይችላል። በእርግጥ ጥቂት ጊዜ እንዲሰጥሽ ትፈልጊያለሽ። ይህ መብትሽ ነው። ግና መብትሽን ከመጠየቅሽ በፊት ግዴታሽን ተወጥተሻልን?

ሙስሊም ሚስት የእመት ኹዲጃን ባህሪ ብትማር እንዴት መልካም ነበር። ለመልእክተኛው ጥሩ ሚስት፣ እውነተኛ መርጊያና መርኪያ ነበሩ። በሞቱ ጊዜ ጅብሪል ከሰማይ ወርዷል። ለነቢዩም እንዲህ ብሏቸዋል፡-

«ለኸዲጃ ሰላምታ አቅርብልኝ። ከጅነት መስክ ላይ ጩኸትም ችግርም የሌለበት ሕንጻ እንደሚታነጽልሽም አላህ ብስራት ነግሮሻል በልልኝ።»31 በእርግጥ ኸዲጃ ለዚህ ክብር ተገቢ ናቸው። የመልካም ሚስት ተምሳሌት ነበሩ። የሰው ልጅ ሕይወት : የምትረጋበት ሕግ መብትና ግዴታ በሚባሉት ሁለት ቃላት የተዋቀረ ነው። የሰው ልጅ መብቱን ብቻ በመጠየቅ ሕይወቱን በዚህ ሕግ ግማሽ አካል ላይ ሲያዋቅር መረጋጋት ያጣል። ስክነትን ይነፈጋል።

ስለሆነም ተጋቢዎች መብታቸውን ከመጠየቃቸው በፊት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

<u>የአካልህ ክፋይ</u>

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

بمالها الناس القوا ربكم الذى علم من نفس و وخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا قضاء والقوا الله الذي تساءلون بهِ، والأرحام إن الله كان عليكم رضا) الساعة ال

እናንተ ሰዎች ሆይ ያን ከአንዲት ነፍስ የፈጠራችሁን ክርሷም ተጣማሪዋን የፈጠረውንና ከነኝህ ከሁለቱ በርካታ ወንዶችንና ሴቶችን ያበዛውን ጌታችሁን ፍሩ። ያን በርሱ (የጋራ መብቶቻችሁን የምትጠያየቁበትን አላህ ፍሩ፡ ዝምድናንም ከመቁረጥ ተጠንቀቁ)

አላህ እናንተን ዘወትር ተጠባባቂ ነውና፡» (አል ኒሣእ ፣) ሐዋእ ከአደም አካል ተፈጠረች። ከርሱ ውጭ ራሷን ችላ መፈጠር ትችል ነበር። ይህ የሆነው ወንድ የአካሉ ክፋይ መሆኗን በማጤን እንዲያዝንላት፣ እንዳይበድላት፣ እንዳይጨክንባት ለማስታወስ ነው። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«ሴቶች የወንዶች አጋር ናቸው።»32

የነቢዩ የመጨረሻ ነዛዜ እንዲህ የሚል ነበር፡-

*31ሙስሊም
*32አል ዓጅላኒ- ከጅፉል ኸፋእ

«ለሴቶች መልካም ትሆኑ ዘንድ አደራ እላችኋለሁ።»33

ሴቶችን ነጻ ለማውጣት በሚል አላማ የተቋቋሙ ተቋማት ያነሱት ችግር፡- «ከአንድ ነፍስ የተፈጠረች ሆናለች» በሚለው ቁርአናዊ መልእክት ይፈታል። ሴት ልጅ የአካልህ ክፉይ ሆና እያለ እንዴት ትጨክንባታለህ? እንዴትስ ትኮራባታለህ?

ማስታወሻ

አደም ከአፈር ተፈጠረ። ሐዋእ ደግሞ ልብን ከከበባት የጎን አጥንት ተፈጠረች። ይህ እውነታ ሁለቱ ወገኖች በሕይወት የሚኖራቸውን የሙያ ክፍፍልና ሚና አመላካች ነው። ውስጥ

ወንድ ከአፈር እንደመፈጠሩ የስራ ሐላፊነቱ ከአፈር ጋር የተያያዘ ነው። እናም ገበሬ፣ እደ ጥበብ ሰራተኛ፣ ነጋዴ ወይም ተዋጊ ነው።

ሴት ልጅ ከሰው አካል፣ ከጎን አጥንት የተፈጠረች እንደመሆኗ የስራ ሐላፊነቷ ከሰዎች ጋር የተያያዘ ነው። እናም ከባሏ ጋር እንደ ሚስት፣ ከልጆቿ ጋር እንደ እናት ትልቅ ሚና ይኖራታል። ይህ ሐላፊነት ከፍተኛ የፍቅር፣ የማዘንና የመራራት ስሜት ይፈልጋል። ስስ ስሜትን ይሻል። እናም ቀልቧ በዚህ የተሞላ ነው።

ሁሉንም ፍጡራን በተለያየ ባህሪ ፈጥሮ ሁሉንም በሚበጃቸው ሚና ያስማራቸው ጥበበኛ አምላክ ክብሩ ይስፋ። ሱብሐነላህ።

አስደሳች መልእክት

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«አደራችሁን፣ ለሴቶች በጎ ሁኑ። ከታጠፈ የጎን አጥንት የተፈጠሩ ናቸውና። ከጎን አጥንት መካከል ይበልጥ የታጠፈው የላይኛው ነው። ቀጥ ልታደርገው ብትሞክር ትሰብረዋለህ። ከተውከው ደግሞ የታጠፈ እንደሆነ ይኖራል። ለሴቶች በጎ ሁኑ፣ አደራ።»34

*33ቢን ማጃህ
*34ቡኻሪና ሙስሊም

ሐዋእ የተፈጠረችው ከአደም የግራ ጎን አጥንት ነው። ይህ አጥንት ደግሞ የታጠፈ ነው። መታጠፉ ልብን ከጉዳት ለመከላከል ሚናው አስፈላጊ ነው።

በሐዲሱ የተጠቀሰው የእንስት ተፈጥሮ ስነ ምግባሯን ሳይሆን ለተፈጠረችለት ሚና አስፈላጊ የሆነውን በስሜት (Emotion) የመሞላት ባህሪዋን ያመለክታል። ይህ ባህሪ በባልዋና በልጆቿ ሕይወት ውስጥ ለምትጫወተው ሚና አስፈላጊ ነው። ስለዚህም ወንዶች ይህን ተፈጥሮዋን በሐይል _ ለማረቅና ስሜት አልባ ለማድረግ ከመሞከር ይታቀቡ። ይህ ከሆነ እርካታና እርጋታ የሚያገኙበትን የማንነቷን አብይ ክፍል እንድታጣ ያደርጓታል።

ይህ መታጠፍ ተፈጥሯዊ ባህሪ መሆኑንና እንስት ቤቷን በፍቅር እንድትመራ፣ የባሏንና የልጆቿን ቀልብ እንድትጠብቅ የሚረዳት መሆኑን ወንዶች መረዳታቸው ግድ ነው። ለዚህም ነው የአላህ መልእክተኛ በሐዲሱ መግቢያ ላይ ወንዶች ለሴቶች በጎ እንዲውሉ አደራ ያሉት። መልእክታቸውን የቋጨትም በዚሁ ኑዛዜ ነው። እንስትን ከነተፈጥሯዊ ባህሪዋ እንዲወዳት፣ ስሪቷን | ለማረቅ በመታገል እና አግባብ ባልሆነ ድርጊት እንዳይሰብራት ለማሳሰብ ነው ይህን አደራ ደጋግመው የሰጡት።

አንዳንድ ወንዶች ከእንስቶቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ሸካራ እና ሐይል የተቀላቀለበት የጭካኔ በመሆኑ ከቀልቧ ውስጥ ለነርሱ ያላትን ስሜት ይገድሉታል።

አንዳንድ እንስቶችም ማንም ሳያስገድዳቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሸካራ ያደርጋሉ። የሴት ወንድ እንደሆነች፣ በቤቷ ውስጥ ውሳኔ ወሳኝ እንደሆነች፣ ባሏ ምንም ማለት እንዳልሆነ አገር ያውቅላት ዘንድ በመሻት ይህን ታደርጋለች። ቀስ በቀስ እንስታዊ ተፈጥሮዋ ይሟሸሻል። የእዝነት ሳይሆን የጭካኔ ምንጭ ትሆናለች።

እህቴ ሆይ፣ በዚህ ዓይነት ባህሪ ቤትሽን እንዳታበላሽ አደራ። የተፈጥሮሽ አካል የሆነውን በስሜት (Emotion) የመሞላት (የመታጠፍ) ባህሪ ተንከባከቢው። የስክነት፣ የፍቅርና የርህራሄ ምንጭ ነውና።

የእንስት ትልቁ ጸጋ ከአእምሯዊ ክሕሎቷ ይልቅ ስሜቷ ያየለ መሆኑ እንደሆነ ታውቃለህን?

አእምሯዊ ክህሎቷ አይሎ ስሜቷ (Emotion) አናሳ ቢሆን ኖሮ ከቤት ውስጥ ከወንድ ጋር እየኖርክ እንደሆነ ይሰማህ ነበር። በፍቅርና በርህራሄ ከምታውድህ እንስት ጋር ሳይሆን ከባልንጀራህ ጋር የኖርክ ያህል ይሰማህ ነበር። ስለዚህም የአላህ መልእክተኛ እንደነገሩህ ይህን ተፈጥሮዋን በጸጋ ተቀበለው። በዚህ ሁኔታዋም ተጠቀምባት።

<u>አሻፈረኝ አለች</u>

ኢማም ቁርጡቢ ከሐዋእ አፈጣጠር ጋር የተገናኘ አንድ ታሪክ አውስተዋል። ይህውም መላእክት አደምን፡- «ትወዳታለህን?» ሲሉ ጠየቁት፡ «አዎ» አላቸው። «አንችስ ትወጅዋለሽን?» ሲሉ ሐዋእን ጠየቋት። «አልወደውም» አለች።

ቁርጡቢ እንዲህ አሉ፡-

«እርሱ ለርሷ ያለውን ፍቅር በብዙ እጥፍ በሚያስከነዳ መውደድ ከልቦናዋ ውስጥ ቢኖርም ለመግለጽ አለመፈለጓን ያስተውሏል። እንስት ለባሏ ያላትን ፍቅር በትክክል መግለጽ የምትሻ ቢሆን ኖሮ ሐዋእ ባደረገችው ነበር።»

ምን አልባትም ቁርጡቢ ተመሳሳይ ሁኔታ አጋጥሟቸው ይሆናል። ምን አልባትም ፍቅሯን ከመላኢኮች ፊት ለመግለጽ ይሉኝታ ይዟት ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ዝምታዋ የልቧን ሐሳብ ከአንደበቷ ይበልጥ የሚገልጽበት ሁኔታ ይስተዋላል። ያም ሆነ ይህ የእንስት ፍቅር ለሁሉም የቤተሰቡ አባት ተማር ይተርፋል። ትንሽ ትልቁ፣ ሴት ወንዱ ከእዝነቷ ይቋደሳል። ፍቅሯን ይታደላል።

<u>ጀነት ውስጥ ነን</u>

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَٰٓئِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَى فَقُلْنَا تَٰعَادَمُ إِنَّ هَٰذَا عَدُوٌّ لَّكَ وَلِزَوْجِكَ فَلَا تُخْرِ
حَنَّا مِنَ الْجَنَّةِ فَتَشْقَى إِنَّ لَكَ أَلَّا تَجُوعَ فِيهَا وَلَا

(تعرى (وَأَنَّكَ لَا تَظْمُوا فِيهَا وَلَا تَضْحَى)

«ለመላእክትም - ለአደም ስገዱ" ባልን ጊዜ የሆነውን አስታውስ) ኢብሊስ (ዲያቢሎስ) ሲቀር (ሁሉም) ሰገዱ። "አደም ሆይ! ይህ ለአንተም ለባለቤትህም በእርግጥ ጠላት ነው: ከገነት አያስወጣችሁ እንግልት ይደርስባችኋልና።" አልን ከውስጧም ረሃብም ሆነ እርዛት እንዳያገኝህ (በቂ መስተንግዶ ተዘጋጅቶልሃል) ጥማትም የፀሐይ ጨረርም አያገኝህም" (አልነውም) (ጧሃ 116-119)

ሰይጣን ከኛ ጋር የሚያደርገው ጦርነት ፍጻሜ ከሚያገኝበት ጀነት ውስጥ ነን። ዱንያን በእንግልት ካሳለፍክ በኋላ አሁን ወደዋናው አገርህ መልሶሐል። ወደ ጀነት። ወደ እውነተኛ መኖሪያ። ወደ መጀመሪያው ቀየህ።

ጀነት ውስጥ ሁሉም ነገር በቀላሉ ይገኛል። ፍራፍሬዎች፣ መጠጦች ወዘተ መታረዝና ረሃብ የለም። ጥማት የለም። ሐሩርና ቁር የለም። ድሎት ብቻ።

በጀነት ውስጥ ሁላችንም የምንዘነጋው አንድ ጸጋ አለ። አለመታረዝ። ወንዶችም ሆነ ሴቶች ወደ ጀነት ሲገቡ አላህ ስለሚያለብሳቸው ከውስጧ አይራቆቱም። የሰው ልጅ መራቆትን ያወቀው የአላህን ትእዛዝ የጣሰ ጊዜ ነው። የሰው ልጅ ስልጣኔ ከአላህ በራቀ ቁጥር የመራቆት ባህል እየጨመረና እየተስፋፋ ይሄዳል።

አላህ አደምን ጀነት ውስጥ እንዲኖሩ ፈቅዷል። ግና ብቻቸውን አልተዋቸውም። ባለቤታቸው ሐዋእ አብራቸው እንድትሆን አደረገ። ሁላችንም ከባለቤቶቻችን ጋር ጀነት መግባት እንሻለን። ስለዚህም በጀነት ውስጥ የአደምን የብቸኝነት ጨለማ ለገፈፈችለት እንስት ልዩ ትኩረት ልንሰጥ ይገባል።

አንዳንድ ወንዶች «ጀነት ስገባ ባለቤቴ አብራኝ እንድትሆን አልፈልግም። በዱንያ ውስጥ ከርሷ ጋር የሆንኩት አንሶኝ» ሲል ይደመጣል። አባባሉ

በመካከላቸው ያለው ፍቅር ዱንያ ከማለቋ በፊት ተንጠፍጥፎ ማለቁን ያረዳል። ይህ እንዳይሰማህ ተጠንቀቅ። አላህን የሚታዘዙ ተጋቢዎችን ቤት አላህ በዱንያም በጀነትም ውስጥ በፍቅር ያደምቀዋል።

በባልና ሚስት መካከል ያለውን ፍቅር እና መተዛዘን አላህን ከመውደድና ከመታዘዝ ይበልጥ የሚያድሰው ነገር የለም። የዓሊይን አንድ ገጠመኝ ላጫውትህ። ባለቤታቸው እመት ፋጡማ በመፋቂያ ስትፍቅ ዓሊ ተመለከቱና ይቀልዷት ጀመር። መፋቂያውን ከእጇ ወሰዱና እንዲህ አሏት፡-

መፋቂያ ደስ ይበልህ
የባለቤቴን አካል ተዳፈርክ
እኔን ሳትፈራ ከንፈር ጥርሶቿን ዳበስክ
ሌላ ሰው ይህን ቢያደርግ አልምረውም።
እገድለዋለሁ አልተወውም።
ከቁጣዬ ያመለጥክ
አንተ ብቻ ነህ የተጠበቅክ።

እጮኛ የምትሰማውን ቁልምጫ ሚስት የማትሰማው ለምንድን ነው? ሐላል ተናግረን ሚስትን ከማስፈንደቅ ለምን ሰይጣን አንደበታችንን ይለጉመዋል? ሚስትህ ጣፋጭ መልእክት ካንተ ከምትሰማ መንጋጋህ ወልቆ ቢወድቅ የሚቀልህ ለምንድን ነው? ጎበዝ፣ በርታ እንበልና የሰይጣንን ድምጽ ዝም እናሰኝ። በጎጇችን ውስጥ የፍቅር ድባብ ለማስፈንም ከባለቤቶቻችን ጋር እንተባበር።

ከዛፏ ላይ ችክ ማለት ለምን?

የሰይጣንን የተለመደ ብልሐት ልንገራችሁ። ሰውየው ሐላልን እንዲጠላ ያደርገዋል። ሐራምን ደግሞ አስውቦና ከሸኖ ያቀርብለታል። በምግብም፤ በመጠጥም፣ በአልባሳትም፣ በወሲብም ሐራም እንዲያጓጓው ያደርጋል።

አደም ዘንግተው የተከለከለችውን አንዲት ዛፍ በሉ። _ ወዲያውም ወደጌታቸው በተውበት ተመለሱ። ታሪኩ እዚህ ላይ ተቋጨ። አንተ ግን በየቀኑ ብዙ ሺህ የተከለከለ ዛፎችን ትመገባለህ። ሰይጣን ሺዎች የሐራም ዛፎችን አስውቦ ያሳየናል። ሐላልን እንድንጠላም ያደርገናል። እንዲህ ይለናል፡-

«ጭማቂ አትጠጣ። ዊስኪ ቢራ ይሻልሐል።»
‹‹ሚስትህን አታጫውት። የስራ ባልደረባህ ይበልጥ ቆንጆ ናት።››

የስራ ባልደረባው በውበት ከሚስቱ ያነሰች ልትሆን ትችላለች። ግና የሰይጣን ድምጽ ከሐራም ላይ መሰማቱ፣ ከሐላል ላይ ደግሞ አንደበት መዘጋቱ ይህችን ይበለጥ ውብ አድርጎ ያሳየዋል። ባሏን ለማስደሰት ደፋ ቀና የምትል መልካም ሚስት መኖሯ አላህን ልታመሰግንበት የሚገባ ትልቅ ጸጋ መሆኑን አታውቅምን? ተከታዩን የኢብሊስን ምኞት ልታሳካ ትሻለህን?

ثُمَّ لاتينهم مِنْ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَانِهِمْ وَعَن شَمَائِلِهِمْ وَلَا تَجِدُ أَكْثَرَهُمْ شَاكِرِينَ
الاعراف

«ከዚያም ከፊት ለፊታቸውም ከበስተኋላቸውም ከበስተቀኞቸውም፡ ከበስተግራቸውም እመጣባቸዋለሁ አብዛኞዎቹንም (ለፀጋዎችህ) ምስጋና አድራሾች ሆነው አታገኛቸውም» (አል አዕራፍ 17)

አንድ ጊዜ ከራስህ ጋር ተፋለምና ከሐራም ታቀብ። ከዚህ በኋላ ከአሁን ቀደም ያላገኘህውን ለዛ ከልቦናህ ውስጥ ታጣጥማለህ። አሁንም ራስህን ታገልና ሚስትህን ማጫወትን ለአንደበትህ አለማምደው። ያኔ ልዩ ደስታ ይሰማሐል። ሚስትህን የማጫወት፣ የማዝናናት፣ የማስደሰት ሱስ ይይዝሐል። ይህ ሲሆን፡-

⇨ ወደርሱ በመመለስህ አላህ ይደሰታል።

⇨ መላኢኮችም ይደሰታሉ።

⇨ክብርህ ይጠበቃል። የሰው ልጅ የሚራቆተው በሐጢአት ብቻ ነው።

ሙስሊም እህቴ ሆይ፣ በትክክለኛ ጋብቻ ካልሆነ በቀር ራስሽን ለሌላ ወንድ አሳልፈሽ አትስጭ። አምላክ ጠብቆሻል። ክብርና ደረጃም ለግሶሻል፡ ፡ ስለዚህም ራስሽን ጠብቂ። አላፊ አግዳሚው እንዲዳብስሽና እንዲስምሽ በመፍቀድ ክብርሽን አታርክሺ።

<u>በምልክት ብቻ</u>

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

فَوَسْوَسَ إِلَيْهِ الشَّيْطَانُ قَالَ يَتَنَادَمُ هَلْ أَدُلُّكَ عَلَى شَجَرَةِ الْخُلْدِ وَمُلْكٍ لَا يَبْلَى

«ግና ሰይጣን ጐተጉተው አደም ሆይ ዝንተዓለም መኖርና የማይወገድ ሥልጣን ማግኘት የምታስችልህን ዛፍ ላመላክትህን? አለው (ጧሃ 120)

እውን ዛፏ ዘልዓለም የመኖር ዛፍ ናትን? በፍጹም አይደለችም። ግና ሰይጣን አደምን ለማማለል እና እንዲመገባት ለማድረግ ሲል በዚህ ስያሜ ጠራት። የመጥፎ ነገሮችን ስያሜ ሰይጣን ዛሬም ይለውጣል። ለምሳሌ፡-

⇨አስካሪ መጠጥን መንፈሳዊ መጠጥ ሲል ይጠራዋል።
⇨ገላን ማራቆትን ዘመናዊነት ይለዋል።
⇨አምላክ የለሽነትን ነጻነትና ጥበብ ሲል ይሰይመዋል።
⇨ዝሙትን ፍቅር ይለዋል።

ቃላትን በማሸሞንሞንና የነገሮችን ትክክለኛ ስያሜ በመለወጥ የሚደረግ ጦርነት እጅግ ብርቱ ነው።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(وَقَاسَهُما إني لكما لَمِنَ النَّصِمِينَ

“እኔ ለናንተ (በጐን) መካሪያችሁ ነኝ ሲል ማለላቸው።(አል አዕራፍ: 21)

ሁለተኛው የኢብሊስ ወንጀል ይህ ነው። የሐሰት መሐላ። አደም በኢብሊስ የመጀመሪያ ጉትጎታ ዛፏን አልበሉም። ይልቁንም ኢብሊስን ተቋቁመውታል። እርሱም እርሳቸውን ለማሳመን በሐሰት ለመማል ተገዷል።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

فَدَلَّٰهُمَا بِغُرُورٍ

«በማታለልም አዋረዳቸው።።» (አል አዕራፍ 22)

አላህ አደምን ዛፏን እንዳይቀርበ ከልክሏቸው ነበር። ኢብሊስም« ዛፏን ሳትመገብ ከስሯ ተቀምጠህ በጥላዋ ተጠለል።» ሲል አግባባቸው። አደምና ሐዋእ ተፈጥሯቸው ንጹህ ከመሆኑ የተነሳ በአላህ በሐሰት የሚምል ፍጡር ይኖራል ብለው ፈጽሞ አልገመቱም። በመጨረሻ አደምና ሐዋእ ዛፏን ቀመሱ። አላህም ተቆጣ። የሆነውም ሆነ።

ለኛ ግን ሰይጣን መማል አላስፈለገውም። ሳይምል ይጫወትብናል። ወደ ወንጀል ማመላከት ብቻ በቂው ነውና። የታዘዝነውንም ሳናዛንፍ እንፈጽማለን።

⇨መጠጥ ጠጡ ማለት አያስፈልገውም። ከእገሌ ጋር ተቀምጠህ ተጫወት፣ ተዝናና ማለት በቂው ነው። ከዚያ በኋላ መጠጡን እኛው እንገባበታለን።

⇨ከጓደኞቼ ጋር ሽርሽር (Picnic) እሄዳለሁ። በወንጀል ግን አልጋራቸውም»ትላለህ። አላህ አደምን ዛፏን እንዳይቀርብ መከልከሉ አልታወሰህምን?

⇨አደምና ሐዋእ ዛፏን አንድ ጊዜ በመቅመሳቸው ብቻ : አላህ ተቆጣባቸው፡ ከወንጀል ላይ ወንጀል እያነባበረ በሚፈጽም ሰው ላይስ ቁጣው ምን ያህል ይሆናል? ግና በሩ ክፍት ነው። ያንተን መመለስ ይጠባበቃል።

ከዚያም ለአደምና ሐዋእ ውስጥን የሚቆጠቁጥ ጥያቄ ቀረበላቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَنَادَتْهُمَا رَبهُمَا أَلَمْ أَنهَكَمَا عَن تِلكُمَا الشَّجَرَةِ وَأَقل لكما إِنَّ الشَّيْطَانَ لَكُمَا عَدُوٌّ مُّبِينٌ

«ጌታቸውም ይህችን ዛፍ እንዳትነኩ አልከለከልኳችሁም ሰይጣንም ግልጽ ጠላታችሁ መሆኑን አልነገርኳችሁም ነበር?" ሲል ተጣራ (አል አዕራፍ 22)

ለአንተ ተመሳሳይ ጥያቄ ሲያቀርብልህ መልስህ ምን ሊሆን ነው? እገሌ ሆይ፣ ይህን ይህን እንዳታደርግ አልከለከልኩህም ነበርን? በማለት ሲጠይቅህ ምን ልትመልስ ነው? አላህ በእለተ ቂያማ ባሪያውን እንዲህ ሲል እንደሚያናግር ተዘግቧል፡

«ባሪያዬ ሆይ፣ ከኔ ጋር መገናኘትን አቅልለህ ተመለከትከው። ለሰዎች ስትዋብ ከኔ ዘንድ ቆሸሸህ ትቀርባለህን? እኔ ካንተ ዘንድ እንዲህ የረከሰ ዋጋ ነው ያለኝን? በዓይኖችህ ሐራም ስታይ እኔ እመለከትህ እንደነበር ዘነጋህ? ከንፈሮችህ ሐራም ሲናገሩ እኔ እመለከትህ _ አልነበረምን? ምንድን ነው ከኔ ያታለለህ? የስራ መዝገብህን አንብብ።»

ወንድሜ ሆይ፣ የስራ መዝገብህን በምታነብ ጊዜ በወንጀሎች ጠልሽቶ ስታየው ምን ይሰማህ ይሆን? ያ ቀን መምጣቱን ትጠራጠራለህን? «አልጠራጠርም» እንደምትል አውቃለሁ። እውነት ብለሐል። በዚያ ቀን መኖር ታምናለህን? «አዎ» እንደምትል አውቃለሁ። እውነት ብለሐል፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

الصافات: ١٤
(وَقِفُوهُمْ إِنَّهُم مَّسْئُولُونَ

«አቁሟቸውም እነርሱ ተጠያቂዎች ናቸውና» (የሚል ትእዛዝ ለመላእክት ይተላለፋል) (አል ሷፋት 24)

ከሞት እንደሚቀሰቀስ ያወቀ ከአላህ ፊት እንደሚቆምም ያውቃል። ከአላህ ፊት እንደሚቆም ያወቀ እንደሚጠየቅ ማወቅ አለበት። እንደሚጠየቅ ያወቀ መልሱን ከአሁኑ ማዘጋጀት አለበት።

እድሜ ጨመረ

ወንጀልም ተከመረ

በተለምዶ እንዲህ ይባላል

ወጣት ቢያጠፋም ግድ የለ ይቶብታል ይመለሳል።

ብዙ ቀርቶ አንዲት ወንጀል

ይችላልን ቅጣቷን መቀበል?

አካል የሰራውን አይቷል

ሊመሰክርበትም ተዘጋጅቷል።

ወደ ምድር መውረድ

የሰይጣን የጠላትነት ቃል ኪዳን

ሰይጣን እኛን መጥላት በልቦናው ውስጥ እንደሰረጸው እኛም የርሱን ጠላትነት በልቦናችን ውስጥ ማስረጽ እንሻለን። ውስጥህ ጠላትነቱን በማይፋቅ ሁኔታ ይመዘግብ ዘንድ የጠላትነት ቃል ኪዳኑን ማወቅ ይገባሐል። እንዲህ ማለቱን ቁርአን መዝግቦ አስተላልፎልናል፦

قَالَ أَرَءَيْتَكَ هَذَا الَّذِى كَرَّمْتَ عَلَىَّ لَئِنْ أَخَّرْتَنِ إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَـٰمَةِ لَأَحْتَنِكَنَّ ذُرِّيَّتَهُۥٓ إِلَّا قَلِيلًا قَالَ أَذْهَبْ فَمَن تَبِعَكَ مِنْهُمْ فَإِنَّ جَهَنَّمَ جَزَآؤُكُمْ جَزَآءً مَّوْفُورًا وَاسْتَفْزِزْ مَنِ اسْتَطَعْتَ مِنْهُم بِصَوْتِكَ وَأَجْلِبْ عَلَيْهِم بِخَيْلِكَ وَرَجِلِكَ وَشَارِكْهُمْ فِي الْأَمْوَالِ وَالْأَوْلَادِ وَعِدْهُمْ وَمَا يَعِدُهُمُ الشَّيْطَانُ إِلَّا غُرُورًا)

«ይህን ከኔ ያላቅከውን (ደካማ ፍጡር) አየህን? እስከ ዕለተ ትንሳኤ ካቆየኸኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ሙሉ በሙሉ አጠማቸዋለሁ እለም (አላህም) “ሂድ ከነርሱ የተከተለህ፤ ገሃነም ቅጣታችሁ ይሆናል። ተገቢ የሆነ ቅጣት አለው ከነርሱ ውስጥ የቻልከውን በድምጽህ አታልል በፈረሰኛና እግረኛ ሠራዊትህም ዝመትባቸው ገንዘባቸውንም ልጆቻቸውንም ተጋራቸው። ቃልም ግባላቸው። (አለውም። ሰይጣን የሚገባላቸው ቃልኪዳን ማታለል እንጅ ሌላ አይደለም» (አል ኢስራእ 62-64)

በአል ኒሣእ ምእራፍ ውስጥ የሚከተለው መልእክት ሰፍሯል፦

لَعَنَهُ اللهُ وَقَالَ لَأَتَّخِذَنَ مِنْ عِبَادِكَ نَصِيبًا مَعْرُوضًا وَلَأُضِلَّنَّهُمْ وَلَأُمَنِّيَنَّهُمْ وَلَآمُرَنَّهُمْ فَلَيُبَتِّكُنَّ وَاذَانَ الْأَنْعَامِ وَلَآمُرَنَّهُمْ فَلَيُغَيِّرُنَ خَلْقَ اللَّهِ وَمَن يَتَّخِذِ الشَّيْطَنَ وَلِيًّا مِن دُونِ اللَّهِ فَقَدْ خَسِرَ خُسْرَانًا مُّبِينًا يَعِدُهُمْ وَيُمَنِّيهِمْ وَمَا يَعِدُهُمُ الشَّيْطَانُ إِلَّا غُرُورًا)

«አላህ ረግሞታል። እርሱም ከባሮችህ የተወሰነን ድርሻ በእርግጥ እይዛለሁ ብሏል። “በእርግጥ አጠማቸዋለሁም። (ከንቱ) ምኞቶችም አስመኛቸዋለሁም የእንስሳትን ጆሮዎች እንዲተለትሉም አዛቸዋለሁ።

የአላህን ዲን በክህደትና በኃጢአት) ይለውጡ ዘንድም አዛቸዋለሁ። ብሏልም። ሰይጣንን ከአላህ ውጭ ረዳቱ አድርጐ የያዘ ሰው ግልጽ የሆነን ኪሣራ ከሰረውኃ (አል ኒሣእ 118-120)

((مَّ لَا يَنَّهُم مِنْ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَنِهِمْ وَعَن شَمَالِهِمْ وَلَا تَجِدُ أَكْثَرَهُمْ شَكِرِينَ

«መንገድ እንድስት ስላደረግከኝ ከቀና ጐዳና መካከል እቀመጥባቸዋለሁ አለ ከዚያም ከፊት ለፊታቸውም ከበስተኋላቸውም ከበስተቀኛቸውም ከበስተግራቸውም እመጣባቸዋለሁ አብዛኛዎቹንም (ለፀጋዎችህ) ምስጋና አድራሾች ሆነው አታገኛቸውም" (አል አዕራፍ 16-17)

ጠላትነቱን አየህ? ላንተ ያዘጋጀልህን ሰራዊት ተመለከትክ? እግረኞች፣ ፈረሰኞች፣ አሳሳች ድምጾች አንተን ለማጥመም አሰፍስፈዋል። ሊያጠቁህ ተሰልፈዋል። አንተስ ለርሱ ጥላቻ ውስጥህ ምን ያህል ተዘጋጅቷል? ጥቃቱን ለመከላከል ምን ያህል ተሰናድቷል?

<u>ይህን ጠላት ለመመለስ የሚያስችሉ ስልቶች</u>

ከሰይጣን ጋር በምታደርገው ጦርነት ደካማ አይደለህም። በርካታ ስልቶችና መሣሪያዎች ካጠገብህ አሉ። ሁሉም በአንድ ተደምረው ቀርቶ እያንዳንዳቸው ሰይጣንን ለመስበር በቂ ጉልበት አላቸው። አበይቶቹን ከዚህ በታች ዘርዝሬልሐለሁ።

1) <u>ኢስቲዓዛ (በአላህ መጠበቅ)</u>፡- ኢስቲዓዛን አብዛ። በአላህ ከተረገመው ሰይጣን ዘወትር ተጠበቅ።

2) <u>አላህን ማስታወስ (ዚክር)</u>፡- አላህን ምንጊዜም አስታውስ። ሰይጣን ብቅ እልም የሚል ጠላት ነው። ማለትም ስትዘናጋ ይቀርብሐል። አላህን ስታስታውስ ደግሞ ይርቅሐል። ሙአዊዘተይን የተባሉ የቁርአን ምእራፎችን ማንበብ ሰይጣንን ያባርራል። አያተል ኩርሲ የቀራ አላህ በዚያ ሌሊት ከሰይጣን ተንኮል ይጠብቀዋል። ከአንድ ቤት ውስጥ አልበቀራህ ሱራ ከተቀራ ለሦስት ቀናት ሰይጣን ያን ቤት አይቀርበውም።

ኢብሊስ አንተን ለመዋጋት ቢዘጋጅም አንተም እርሱን የምታሸንፍበት እና የምታባርርበት መሣሪያ አለህ። ጦርና ጋሻህ ከጥቃቱ ይጠብቅሐል። ከመጠበቅም አልፎ ያቃጥለዋል። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል:

«በቀን መቶ ጊዜ፡- ላኢላሐ ኢለላህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ አላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፣ ያለ ቀኑን ሙሉ ከሰይጣን ጠባቂ ይሆንለታል።»35

ይህን ዚክር ካልከ ቀኑን ሙሉ ሰይጣን አይቀርብህም። ምሽት ላይ ካልከው ሌሊቱን ሁሉ ከሰይጣን ትጠበቃለህ። እናም ሰይጣን ቢቀርብህ እንኳ አያጠቃህም።

እንዲህ ዓይነት ምክሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ስንሰማቸው ስሜት ይሰጡናል። ልንተገብራቸውም አንድ ሁለት ጊዜ እንሞክራለን። ከዚያ በኋላ ግን መተግበርን ስለምንዘነጋ ምንም ዓይነት ተጽእኖ አይኖራቸውም። ስለ ዚክር እንሰማለን፣ ግን ዚክር አናደርግም። ስለ ወላጅ ሐቅ እንሰማለን። ግን ሐቃቸውን አንጠብቅም። ይህ ባህሪያችን እስከመቼ ይቀጥላል?

3) **<u>ውዱእ</u>**፡ ሰይጣን የተፈጠረው ከእሳት ነው። እሳትን ደግሞ ውሃ እንጅ አያጠፋውም።
4) **<u>እይታን መቆጣጠር</u>**፡- ሐራም እይታ የሰይጣን ፍላጻ ነው። እይታን መቆጣጠር ይህን ፍላጻ ይሰብረዋል። ጥቃቱን ያከሽፈዋል። ዒላማውን ያስተዋል። ቀልብን እንዳይጎዳውም ይከላከላል። እምነትህም ፍላጻው ሊያዳክመው ከቃጣው በኋላ እንደገና ይበረታል።
5) **<u>መጥፎ ጓደኛን መተው</u>**፡- የዲን ሰዎችን ተጎዳኝ። ምክንያቱም ሰይጣን የሰውን ልጅ የሚያጠቃ ተኩላ ነው። ተኩላ የሚበላው ከመንጋው የተነጠለችን ፍየል ነው።

*35ቡኻሪ፣ ሙስሊምና ቲርሚዚ

6) **<u>ሶላት፡-</u>** ሙስሊም በሚሰግድ ጊዜ ሰይጣን እያለቀሰ እና እንዲህ እያለ ይሸሻል፡«እርሱ እንዲሰግድ በታዘዘው መሠረት በመስገዱ ጀነት ገባ። እኔ ግን ታዝዥ ባለመስገዴ እሳት እገባለሁ።»

7) **<u>ተውባ፡-</u>** ኢብሊስ በአላህ ክብር ምሎ በሕይወት እስካለን ድረስ ሊያጠምመን ዝቷል። አላህም፡- «በክብሬ እምላለሁ! ምህረት እስከጠየቁኝ ድረስ እምራቸዋለሁ» ብሏል።

ያወቅከውን ተግብር። ሰይጣን አንተን እንዲያጠቃህ አታግዘው። መሣሪያህን ጥለህ ልጓምህን ለርሱ አታስረክብ። ይህ ራስህን በግልጽ መበደል ነው። የበዳዮች እጣ ፈንታ ምን ይከፋ! በዱንያም በአኼራም የደስታ ምንጭ የሆነውን የአምላኩን ተገንነት ትቶ በዚህችም ሆነ በእለተ ቂያማ ለመከራ እና ለጀሀነም ወደሚዳርገው ሰይጣን ጉያ የሚወሸቅ ምን ዓይነት ሰው ነው። አእምሮ የሌለው እንስሳ እንኳ ወደ ገደል ልትወረውረው ስትሞክር፣ አንተን እሺ ብሎ ገደል መግባት ጥፋት መሆኑን ደመ ነፍሱ ስለሚነግረው ይቃወምሐል። ታዲያ አንተ ምን ነካህ? አእምሮ እና የማሰብ ክሕሎት ተሰጥቶህ እያለ ጠላትህን መታዘዝህ ለምን? ወደ ጀሃነም ሲጎትትህ አሜን ብለህ ትጎተታለህን? አላህ በእለተ ቂያማ የእሳትን ሰዎች እንዲህ ብሏቸዋል፡

((وَلَقَدْ أَضَلَّ مِنكُم جِبِلًّا كَثِيراً أَفَلَمْ تَكُونُوا تَعْقِلُونَ

ግና (ሰይጣን) ከመካከላችሁ ብዙዎቹን መንገድ እንዲስቱ አደረገ። አስተዋዮች አልነበራችሁምን?" (ያሲን 62)

አእምሮ የለህምን?

<u>ጉርሻ</u>

አንድ ወጣት ደወለልኝና በቁርአን ውስጥ ኢብሊስ የሚለው ቃል ፲ ጊዜ መወሳቱን እና በአላህ መጠበቅም እንደዚሁ ፲ ጊዜ እንደተወሳ አስልቶ መረዳቱን ነገረኝ። እርሱ ያለው ነገር ትክክል መሆኑን እኔም አስልቼ

አረጋገጥኩ። ቁም ነገሩ ወዳላቀህና ላንተ ሲል ሰይጣንን ወዳባረረውና ወደረገመው አምላክ መጠጋትህ ነው። አላህ ከጎንህ በተሰለፈበት ጦርነት ውስጥ ሰይጣን ባንተ ላይ ምን አቅም ይኖረዋል?

<u>አስታውስ</u>

የአደምን፣ የሐዋእንና የኢብሊስን ወይም የትኛውንም ታሪክ ስታስታውስ ለተጨባጭ ሕይወትህ ትምህርት ለመቅሰም መሆኑን አትዘንጋ። ስለሆነም ፋይዳ በሌላቸው አጀንዳዎች ጊዜህን አታባክን፡ ተከታዩን መርህ በቃል ልናጠናው ልናደርገውም ይገባል። ይገባል። የሕይወታችን ቋሚ መመሪያ ምክንያቱም የአስተሳሰብ መንገዳችንን ያስተካክልልናል። የቱን ትተን ከየት ላይ ማተኮር እንዳለብን ጥሩ ሚዛን ይሆነናል። መርሁን እነሆ፡-

وكل مسألة لا ينبنى عليها عمل فا الخوض فيها من التكلف الذي نهينا عنه

«ተግባር የማይታነጽበትን የትኛውንም አጀንዳ መፈትፈት በሸሪዓ የተከለከልነው ጸጉር ስንጠቃ ነው።

አንዳንዶቹ ቅንጣት ሊያሳስብ የማይገባው አጀንዳ ያሳስባቸዋል። ተግባር የማይታነጽበት ጉዳይ አእምሯቸውን ይጠምደዋል። ከርእሳችን ጋር የተያያዘ ዋቢ እናቅርብ።

ለምሳሌ፡-

⇒ አደም የተመገባት ዛፍ ምን አይነት ናት የበለስ ወይስ የወይን ዛፍ? ዛፏ የትኛዋም ብትሆን በታሪኩ ላይ የምትጨምረው ነገር ስለሌለ ይህ ሊያስጨንቅህ አይገባም።

⇒ አደም የተቀመጠባት ጀነት _ ዘልዓለማዊዋ ናት ወይስ ሌላ? ብዙሐን ዓሊሞች ዘልዓለማዊዋ ገነት ናት ቢሉም አጀንዳው ጊዜን ከማባከን በቀር ፋይዳ የለውም።

⇒ሰይጣን ወደ ጀነት እንዴት ገባ? አላህ በሚያውቀው አካኋን ገብቷል። በዚህ ረገድ መፈትፈት አይፈይደንም። ከላይ

የተቀመጠውን መርህ እንደማንረሳ ተስፋ አደርጋለሁ ብዙ ነገሮችን ያቃልልናል።

ተጠያቂው ማን ነው?

አላህ አደምንና ሓዋን ጀነት ውስጥ አስቀመጣቸው ሰይጣንም አላህ በሚያውቀው ስልት ወሰወሳቸው ዛፏንም ተመገቡ ለዚህ ወንጀል ተጠያቂው ማን ነው?

የጥንት ሐይማኖቶች በሙሉ ለዚህ ወንጀል ተጠያቂ ሓዋ እንዲሆናች አስተምረዋል። አደምን ያሳሳቶች እርሷ መሆኗን ሰብከዋል። ሴቶች በሚያደርገው ጥበቃ የሚመመጻደቀው የምእራብ ዓለም ስለጣ እንኳ ለዚህ አስተሳሰብ ጽድቅ ይቸራል። ኢስላም ብቻ ከላም በመለየት ሐጥእን ከደሙ ንጹህ አድርጓታል። የዚህን ጥፋት ሸክም ለርሷ ብቻ አላሸከመም። ሁለቱም ጥፋቱን እንደሚጋሩ አስተምረዋል። ተከታዩን የአላህ ቃል አብረን እናንብብ፡-

وب ادم السكن أَنتَ وَزَوْجُكَ الْجَنَّةَ فَكُلَا مِنْ حَيْثُ مِنْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَذِهِ الشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ الظَّالِمِينَ لا فَوَسْوَسَ لَهُمَا الشَّيْطَانُ لِيُبْدِعَ هَمَا مَا وُرِى عَنْهُمَا مِن سَوْءَ أَيْهِمَا وَقَالَ مَا تَهَنكُما رَبِّكُمَا عَنْ هَذِهِ الشَّجَرَةِ إِلَّا أَن تَكُونَا مَلَكَيْنِ أَوْ تَكُونَا مِنَ الخَلِدِينَ (وَقَاسَمَهُمَا إِنِّي لَكُمَا لَمِنَ التموين مَدَلَهُمَا بِغُرُورٍ فَلَمَّا ذَاقَا الشَّجَرَةَ بَدَتْ لَهُمَا سَوْءَ بُهُمَا وَطَفِقَا يَحْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ المَةِ وَنَادَتْهُمَا رَبِّمَا أَلَا أَنكُمَا عَن تِلكُمَا الشَّجَرَةِ وَأَقُل لكما إِنَّ الشَّيْطَنَ لكا عدُو مين) قَالَا رَبَّنَا ظَلَمْنَا أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ نَا وَتَرْحَمْنَا لَتَكُونَنَّ مِنَ الْخَسِرِينَ

“አደም ሆይ! አንተና ሚስትህ ገነት ውስጥ ተቀመጡ። የከጀላችሁትንም ተመገቡ። ግና ይህችን ዛፍ አትቅረቡ ከበዳዮች ትሆናላችሁና። ሰይጣንም ጐተጐታቸው ሀፍረተ ገላቸውን ሊያጋልጣቸው ጌታችሁ ይህችን ዛፍ እንዳትመገቡ የከለከላችሁ መላእክት እንዳትሆኑ ወይም ዝንተ ዓለም ከሚኖሩት መሆን እንዳትችሉ ነው አላቸው። እኔ ለናንተ (በጐን) መካሪያችሁ ነኝ።” ሲል ማለላቸው። በመሐላው አታለለ። ለውድቀት ዳረጋቸው። ዛፏን በቀመሱ ጊዜ ነውራቸው

ተገለፀላቸው። በላያቸው ላይም የገነትን ቅጠል ይደርቱ ጀመር። ጌታቸውም “ይህችን ዛፍ እንዳትነኩ አልከለከልኳችሁም ሰይጣንም ግልጽ ጠላታችሁ መሆኑን አልነገርኳችሁም ነበር?” ሲል “ጌታችን ሆይ! ራሳችንን በድለናል። ካልማርከንና ተጣራ ካላዘንክልን ከከሣሪዎች እንሆናለን።" በማለት ጌታቸውን) ተማፀነ (አል አዕራፍ: 19 23)

በአንቀጹ እንደተገለጸው ሁለቱም ሐላፊነት ተሸክመዋል። ሰይጣን ሁለቱንም ወስውሷል። ሁለቱም ዛፏን ተመግበዋል። ሁለቱም አላህን ይቅርታ ጠይቀዋል። አላህ በሌላ ቦታ እንዲህ ብሏል፦

فَوَسْوَسَ إِلَيْهِ الشَّيْطَنُ قَالَ يَتَنَادَمُ هَلْ أَدُلُّكَ عَلَى شَجَرَةِ الْخُلْدِ وَمُلْكِ لَا يَبْلَى

«ግና ሰይጣን ጐተጐተው። አደም ሆይ! ዝንተዓለም መኖርና የማይወገድ ሥልጣን ማግኘት የምታስችልህን ዛፍ ላመላክትህን? አለው (ጣሃ 120)

ስለዚህ ሐዋእ ከደሙ ንጹህ ናት። ግና ወንጀሉን ተጋርታለች። የአደም ተጠያቂነት ይልቃል። ስለሆነም በዚህ አንቀጽ ዋነኛው ተወቃሽ እርሱ ሆኗል።

አባወራ የሐራም ገንዘብ ካጋበሰ በኋላ፦ «ሚስቴ ገፋፍታኝ ነው» ቢል አግባብ አይደለም። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

«በሐራም ምግብ የበቀለ ስጋ ሁሉ ለእሳት ተገቢ ነው።”35

ሚስት እርሱን በመገፋፋት የወንጀሉ ተጋሪ ልትሆን የምትችልበት አጋጣሚ ቢኖርም ዋነኛው ተጠያቂ ግን እርሱ ነው። ስለዚህም ሚስት ባሏን ብዙ ነገር እንዲገዛ በመጠየቅ የርሷን ፍላጎት ለማሟላት ሲል ሐራም ውስጥ እንዲዘፈቅ መጫን የለባትም።

*35ጦበራኒ

ይህችን ስህተት አርም

አንዳንድ ስህተቶች ከሌላ ባህል ወደኛ አስተሳሰብ ሰርገው ገብተዋል። ኢስላም ከነዚህ ስህተቶች የጠራ ነው። አንዳንድ ተከታዮች ግን ሲናገሯቸው ይደመጣሉ። እነርሱም፡-

⇒በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚከሰት ጥፋት ዋነኛ ተጠያቂዋ ሴት ናት። እንስት የየትኛውም ክፋት (በላእ) ሰበብ ናት።

⇒እንስት አእምሮዋም ዲኗም ጎደሎ ነው። ይህ ስህተት የመነጨው በዚህ ረገድ የተነገረውን ሐዲስ በወጉ ካለመረዳት ነው።

⇒ ለነዚህ ስህተቶች አሁን መልስ እውነታዎች ጋር አስተዋውቅሐለሁ። አልሰጥም። ግና ከአንዳንድ

⇒ከአላህ መልእክተኛ በኋላ ለአላህ መጀመሪያ የሰገደችው እንስት ናት፡ ፡ እርሷም ኸዲጃ መሆኗን ዑለሞች በአንድ ድምጽ አጽድቀዋል።

⇒ ነቢዩ አሊሻን በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፡- «የሐይማኖታችሁን ግማሽ ከዚህች ሴት ያዙ።»

⇒ እንስት በተፈጥሮዋ አእምሮዋም ዲኗም ጎደሎ ቢሆን ኖሮ ግማሽ ሐይማኖትን ከርሷ መማር ተገቢ አይሆንም ነበር።

⇒ አላህ በቁርአን ውስጥ እንስቶችን በተምሳሌትነት አቅርቧል። የፊርዓውን ሚስትና የኢምራን ልጅ መርየም በናሙናነት መጠቀሳቸው ይታወቃል። ይህ መልእክት ቢገባን እጅግ መልካም ነበር። ያኔ እኛ በሴቶች ላይ ያለን እምነት፣ ሴቶችም በራሳቸው ላይ ያላቸው እምነት ይመለሳል። ሕብረተሰቡ የሚስተካከለው ሴቷ ስትስተካከል መሆኑን እርግጠኞች እንሆናለን። ምክንያቱም ወንድ የሚውለው ከቤት ውጭ ነው። እርሷ ግን ልጆችን አላህን በመታዘዝ መሠረት ላይ ታንጻለች። መልካም ትውልድ ትቀርጻለች። ይህን ካላደረገች ሕብረተሰቡ እጅግ ጠቃሚ ጉልበት አባክኗል።

ከከንቱ ስሜት የገጠመ ግንዛቤ

አንዳንድ ወንዶች የእንስትን አእምሮና ሐይማኖት ጎዶሎነት እያወሱ እርሷን ማናናቅ፣ እይታዋን ማጣጣል ደስ ይላቸዋል። የዚህ ድርጊታቸው ሰበብ ከንቱ ስሜት ሊሆን ይችላል።

በሐዲስ የተጠቀሰው የእንስት የአእምሮና የዲን ጎድለት የመጠን እንጅ የጥራት ጉድለትን አያመለክትም። ትክክለኛ ትርጉሙ ይህ ነው። እንስት በወር አበባ ጊዜ ሶላትም ጾምም ታቆማለች። ዒባዳዋ በቁጥር ይጎድላል። የምታገኘው አጅር ግን አይጎድልም። ሴቶች በዒባዳ ብዛት ሳይሆን በዲን ጥልቀት፣ በአማን ጥንካሬና ድምቀት ከወንዶች ሊበልጡ ይችላሉ። የዲን ጉድለት ትርጉሙ ይህ ነው።

አእምሮዋን የሚመለከተው ጉድለት ደግሞ ስሜት እንደሚያይልባት ለመግለጽ ነው። ይህ የሆነውም ከባሏና ከልጆቿ ጋር ያላት ሕይወት የሰመረ ይሆን ዘንድ አላህ ያኖረው ጥበብ እውን እንዲሆን ለማስቻል ነው።

<u>ወሳኝ ስለሆነች ከርሷ ላይ አተኮረ</u>

አላህ አደምን ጀነት ውስጥ አስቀመጠው። ከውስጧ እንደማይራብ፣ እንደማይታረዝ እና እንደማይጠማ፣ ብርድና ሐሩርም እንደማያገኘው ነገረው። ዛፏን መመገብ ከነዚህ አራት ጸጋዎች እንደሚከለከለው ኢብሊስ ተረዳ። ግና በአንዷ ላይ ብቻ የበለጠ አተኮረ።

(قال أهيطوا بعضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ وَلَكُمْ في الأَرْضِ مُسْتَقَرٌّ وَمَتَعٌ إلى حين

ከፊላችሁ የከፊሉ ጠላት ሆናችሁ (ወደ መኖሪያ ሥፍራችሁ ውረዱ ምድር ላይ ጊዜያዊ ማሪፊያና ለመኖር የሚያስፈልጓችሁ ነገሮች ተዘጋ ጅተውላችኋል አላቸው (አል አዕራፍ 20)

ሰይጣን ሕብረተሰቡን በዝሙት ባህር ውስጥ ለማስጠም፣ ብልግና እንዲስፋፋ ለማድረግ በሐፍረተ ገላ መገለጥ ላይ አተኮረ። መጀመሪያ

ሰይጣን ሕብረተሰቡን በዝሙት ባህር ውስጥ ለማስጠም፣ ብልግና እንዲስፋፋ ለማድረግ በሐፍረተ ገላ መገለጥ ላይ አተኮረ። መጀመሪያ ገላን አራቆተ። ከዚያም ሐራም እይታን አስከተለ። ይህም የወንጀሉ ሁሉ ጅማሬ ሆነ።ሙስሊም እህቴ ሆይ፣ የሃጃብን ጠቀሜታ አሁን ተረዳሽን?

ከስድስቱ አምስቱ

በአደም እና በኢብሊስ ታሪክ ውስጥ መታረዝ (መራቆት) የሚለውን ሐሳብ የተወሳባቸውን የቁርአን አናቅጽ ብንቆጥር ከስድስት አንቀጾች ውስጥ በአምስቱ መወሳቱን እንገነዘባለን።። ይህ እውነታ የአጀንዳውን ክብደት አያመለክትምን? ለምሳሌ አል አዕራፍ 22 ላይ አላህ «ተራቡ» አላለም። ይልቁንም እንዲህ ነው ያለው፡

فَدَلَّىٰهُمَا بِغُرُورٍ فَلَمَّا ذَاقَا الشَّجَرَةَ بَدَتْ لَهُمَا سَوْءَ تُهُمَا وَطَفِقَا يَخْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ

በመሐላው አታለለ ለውድቀት ዳረጋቸው ዛፏን በቀመሱ ጊዜ ነውራቸው ተገለፀላቸው: በላያቸው ላይም የገነትን ቅጠል ይደርቱ ጀመር ጌታቸውም "ይህችን ዛፍ እንዳትነኩ አልከለከልኳችሁም ሰይጣንም ግልጽ ጠላታችሁ መሆኑን አልነገርኳችሁም ነበር? ሲል ተጣራ። (አል አዕራፍ 22)

አንቀጽ 26 ላይ እንዲህ ብሏል፡-

ينبَنِي ءَادَمَ قَدْ أَنزَلْنَا عَلَيْكُمْ لِبَاسًا يُوَرِى سَوْءَاتِكُمْ وَرِيشًا وَلِبَاسُ التَّقْوَى ذَلِكَ خَيْرٌ ذَلِكَ

مِنْ عَايَتِ اللَّهِ لَعَلَّهُمْ يَذَّكَّرُونَ)

የአደም ልጆች ሆይ ሐፍረተ ገላችሁን የሚሸፍን፡ ጌጥም የሚሆናችሁ ልብስ አውርደንላችኋል። ግና የመልካም ምግባር ልብስ ከሁሉም የተሻለ ነው እነኝህ የአላህ ተአምራት ናቸው ይገሰፁ ዘንድ (ገለፀላቸው)»» (አል አዕራፍ 26)

አንቀጽ 20 ላይ እንዲህ ተጽፏል፡-

فَوَسْوَسَ لَهُمَا الشَّيْطَانُ لِيُبْدِى لَهُمَا مَا وُرِى عَنْهُمَا مِن سَوْءَ يْهِمَا وَقَالَ مَا نَهَنكُمَا رَبِّكُمَا عَنْ هَذِهِ الشَّجَرَةِ إِلَّا أَن تَكُونَا مَلَكَيْنِ أَوْ تَكُونَا مِنَ الخَلِدِينَ (الأعراف: ٢٠

«ሰይጣንም ጉተታቸው ሐፍረተ ገላቸውን ሊያጋልጣቸው ጌታችሁ ይህችን ዛፍ እንዳትመገቡ የከለከላችሁ መላእክት እንዳትሆኑ ወይም ዝንተ ዓለም ከሚኖሩት መሆን እንዳትችሉ ነው አላቸው (አል አዕራፍ 20)

ቁርአን በእያንዳንዱ ታሪክ መቋጫ ላይ ከታሪኩ የሚቀሰሙ ትምህርቶችን ይዘክራል። እነዚህን ትምህርቶች በደንብ ብናውቃቸው፣ በወጉ ብንረዳቸው፣ በግልብ እይታ ብቻ ባንብቃቃ መልካም ነበር። እስኪ ተከታዩን አንቀጽ እንይ፡-

يبي ءَادَمَ قَدْ أَنزَلْنَا عَلَيْكُمْ لاَسًا يُوَرى سَوْءَ نِكُمْ وَرِينَنا وَلبَاسُ التَّقْوَى ذَلِكَ خَيْرٌ ذَلِكَ عراف: ٢ مِنْ ءَايَاتِ اللَّهِ لَعَلَّهُمْ يَذَّكَّرُونَ

«የአደም ልጆች ሆይ ሐፍረተ ገላችሁን የሚሸፍን፣ ጌጥም የሚሆናችሁ ልብስ አወርደንላችኋል። ግና የመልካም ምግባር ልብስ ከሁሉም የተሻለ ነው። እነኝህ የአላህ ተአምራት ናቸው ይገሰፁ ዘንድ (ገለፀላቸው። (አል አዕራፍ 26)

የሰው ልጆች ሆይ፤ ውስጣችሁንም ሆነ ላያችሁን ከማራቆት ተጠንቀቁ ማለት ነው። ይህን ትምህርት አስተዋልክን!? ገላን በጨርቅ መሸፈን፣ ውስጥን ደግሞ አላህን በመገዛትና በመፍራት መሸፈን

<u>ኋላ ከመቆጨት</u>

አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡- «ሂጃብ ለብሰው ባህሪያቸው የከፋ፣ እየሰገዱ ከወንጀል ላይ የሚወድቁ፣ ለስሙ ብቻ ሲሉ ሐጅ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ» የሚል አስተያየት ይሰነዝራሉ።

አካልንም ቀልብንም መሸፈን እንሻለን። ሁለቱም ተፈላጊዎች ናቸው። አንዳንድ ሰዎች በሚፈጽሙት ስህተት ሳቢያ እነዚህን በጎ ነገሮች ችላ ልንል አይገባም። ይህ ለራሳችንም ሆነ ለሕብረተሰቡ ደህንነት ትልቅ ዋስትና ነው። አላህ ኢብሊስን በተመለከተ እንዲህ ይላል፡-

: يَبَنِى ءَادَمَ لَا يَفْتِنَنَّكُمُ الشَّيْطَنُ كَمَا أَخْرَجَ أَبَوَيْكُم مِّنَ الْجَنَّةِ يَنزِعُ عَنْهُمَا لِبَاسَهُمَا لِيرِيَهُمَا سَوْءَتِهِمَا الأعراف: ٢٧

«የአደም ልጆች ሆይ! ሰይጣን ወላጆቻችሁን ነውራቸው ይገለጥ ዘንድ ልብሶቻችውን በመግፈፍ- ከገነት እንዳስወጣ እናንተንም አይፈትናችሁ።» (አል አዕራፍ 27)

«መግፈፍ» የሚለውን ቃል አስተውል። የታገላቸው ለዚህ ነው። ልብሳቸውን ሊገፍ፣ ሊያራቁታቸው፣ ሐፍረተ ገላቸውን ሊያሳይ ዓላማው እርቃንነትን ማስፋፋት ነው።

⇨ ሴቶቻችን አካላቸውን የሚያሳዩ ስስ ልብሶች ሲለብሱ፣

⇨ከአካላቸው ጋር የተጣበቁ የወሲብ ስሜት ቀስቃሽ አልባሳትን ሲለብሱ፣

⇨ እምብርታቸውን፣ ጡታቸውንና ሌላ የሰውነት ክፍላቸውን የሚያሳዩ ልብሶችን ሲለብሱ ደንታ ሳይሰጠን በዝምታ እናያቸዋለን።

ይህን ተከትሎ ችግሮች ሲፈጠሩ ግን ቤተሰብ ያለቅሳል። ልጅት ትቆጫለች። ወንጀለኛው ወጣት. ግን ምንም ዓይነት ሐላፊነት አይወስድም። ሰይጣን በመጭው ዓለም ለተከታዮቹ እንዲህ በማለት እንደሚሸሸው፡-

(فَلَا تَلُومُونِي وَلُومُوا أَنفُسَكُم

«እኔን አትውቀሱኝ ራሳችሁን ውቀሱ" (ኢብራሂም 22)

በእርግጥም የምታስከፋ

የሐፍረተ ገላ መገለጥ በአረብኛው ሰውአህ መሰኘቱን አስተዋልከንን ሳኡ አስከፊ፣ የማይገባ ማለት ነው። ሐፍረተ ገላን ማየት እና ማራቆት ያሚሸሻል። በእርግጥም ያስከፋል። ተገቢ አይደለም። ይሉኝታንና የክብር ስሜትን ይገድላል። የእንስትነትንና የተባእትነትንም ባህሪ መተማመንን ያጠፋል። ዝሙትን በማስፋፋት ያከፋል።

ሐፍረተ ገላን ለማየት ሲል ኢንተርኔት ለመክፈት ከመካከላችን አለን? ይህ እይታ ተፈጥሮን ይበክላል። ከጊዜ በኋላ ይህ ሰው ዓለምን፣ በኢንተርኔት እንደሚያየው የተራቆተች አድርጎ ያስብና ይሳሳታል። የሚፈቅድ:

አላህ አንድን ነገር የሚከለክለው ለራሱ ለሰው ልጅ ጥቅም ሲል ነው። ታዲያ እኛ ምን እያደረግን ነው?

በእርግጥ ተሳክቶለታል፣ ግን...

ሰይጣን የአደምንና የሐዋእን ልብስ በመግፈፍ እና ሐፍረተ ገላቸውን በማጋለጥ ላይ አተኮረ። ተሳካለትም። በሁሉም ትውልዶች ላይም ተመሳሳይ የመግፈፍ ስራ አከናውኗል። ሐፍረተ ገላዎችን አጋልጧል። እንስቶችን እርቃን አስቀርቷል። በጃሂልያ ዘመን የዓረብ ትውልድ ላይ የፈጸመው የመግፈፍ ስራ ለአብነት ይጠቀሳል። ሴቶችና ወንዶች እርቃናቸውን ሆነው ካእባን ይጎበኙ ነበር።

ይህም በመሆኑ ነቢዩ መካን እንደተቆጣጠሩ ያሰሙት የመጀመሪያ አዋጅ ካእባን እርቃን ሆኖ መጎብኘት ክልክል መሆኑን መግለጽ ነበር።

ኢብሊስ ዓረቦችን ያታለለው ወንጀል በሰራችሁበት ልብስ ጠዋፍ አታድርጉ፣ አምላክ አይቀርባችሁም ማለት ነበር። በባህላቸው ሐያእ ያላቸው ሰዎች የሆኑም አምላክ ጠዋፋቸውን እንዲቀበላቸው ሲሉ እርቃናቸውን ሆኑ።

በዚህ ባለንበት የስልጣኔ ዘመንም ሰይጣን እንስቶችን በተመሳሳይ ስልት ያሳስታል፡ ባይሆን ስሙን ቀይሮ፡ «የግለሰብ ነጻነት፣ ዘመናዊነት፣

ስልጣኔ» ብሎታል። ሰይጣን እንደየ አካባቢውና ዘመነ የማሳሳቻ ስልቱን ይቀያይራል።

ሰይጣን በከፊሎች ላይ ዓላማው ቢሳካለትም እርሱን አሸንፈው፣ ቅስሙን ሰብረው በምድር ላይ ለሰው ልጆች የአላህ መረጃዎች፣ የአልረህማንን አርማ ተሸካሚዎች የሆነ እንስቶችን እናገኛለን። ሰይጣንን ለማሸነፍ የተጠቀሙባቸውን ስልቶች ከአሁን ቀደም መዘርዘራችን ይታወሳል። ሰይጣን እንዳሸነፋት አውቋል። እነርሱን መርታት እንዳልሆነለት ተረድቷል። ይህንንም እንዲህ በማለት ተናዟል፡

قَالَ فَبِعِزَّتِكَ لَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ الْمُخْلَصِينَ

(ዲያቢሎስም) እንዲህ አለ በአሸናፊነትህ እምላለሁ ሁሉንም መንገድ አስታቸዋለሁ ከመካከላቸው የተመረጡና ታማኝ አገልጋዮችህ ሲቀሩ። (ሷድ 82-83)

የአደም ኃጢአት ውጤት

የአደም አንዲት ጥፋት በርካታ ችግሮችን አስከተለችበት። ሁላችንም እነዚህን የጥፋት ውጤቶች በወጉ ማወቅ አለብን። ከወንጀል ላይ ስንወድቅ እንድናስታውሳቸው፡-

1) የሐፍረተ ገላ መገለጥና መዋረድ፣

2) ከጀነት መውጣት፣ የአላህን ጉርብትና ማጣት፣ ወደ ምድር መውረድ

3) ወደ ምድር ሲወርዱ ከሐዋእ ጋር መነጣጠል፣

4) «ወንጀል ፈጻሚ» በሚለው መጥፎ ባህሪ መገለጽ፣

وَعَصَى عَادَمُ رَبَّهُ، فَعَوَى) طه

አደም (በዚህ አካኋን) የጌታውን ትእዛዝ ጣሰ ስህተት ላይ ወደቀም።» (ጧሃ 121)

5) ብርቱ ወቀሳ፡-

وَنَادَتْهُمَا رَبُّهُمَا أَلَمْ أَنْهَكُمَا عَن تِلْكُمَا الشَّجَرَةِ وَأَقل لكما إِنَّ الشَّيْطَانَ لَكُمَا عَدُوٌّ مُّبِينٌ الأعراف: ٢

“ጌታቸውም “ይህችን ዛፍ እንዳትነኩ አልከለከልኳችሁም ሰይጣንም ግልጽ ጠላታችሁ መሆኑን አልነገርኳችሁም ነበር? ሲል ተጣራ። (አል አእራፍ 22)

እስረኛ ማለት ቀልቡ ከአላህ የታሰረ ነው። ምርኮኛ ከንቱ ስሜቱ የማረከው ነው፤ የአላህን ጉርብትና ካገኙ በኋላ ከመባረር፣ የጀነትን ድሎት ከተለገሱ በኋላ ከመንገላታት የበለጠ አስቸጋሪ ነገር አለን የወንጀል መጥፎ ውጤት ይህ ብቻ ቢሆን እንኳ ለመጠንቀቅ በቂ ምክንያት ነው።

አቃልለህ አትመልከት

ይህ ሁሉ የሆነው አደም የተከለከሉትን ዛፍ በመቅመሳቸው ብቻ ነው። ጉዳዩ ያለው ከወንጀሉ አናሳነት አይደለም። ትእዛዙን ከጣስከው አምላክ ትልቅነት እንጅ። ዘንግተህ እቀባውን ስትዳፈር ባንተና በርሱ መካከል ግርዶ ታበጃለህ። ስለዚህም ይህን ግርዶ በተውበት አስወግደው። ወንጀልን አቃልለህ አትመልከት። በአንዲት ጥፋት ይህ ሁሉ መከራ አደም ከደረሰባቸው ብዙ ወንጀሎችን የምንሰራው እኛስ? ከአላህ ምህረት ተስፋ እያስቆረጥኩህ አይደለም። ወንጀልን አቃልለህ መመልከትን እያስጠነቀቅኩህ እንጅ።

ሐጢአተኛ ሁሉ ይጠንቀቅ

ሐጢአት ብዙ ችግሮችን ያደርሳል። በርካታ መከራዎችን ያስከትላል። ጥቂቶቹን ቀጥሎ እናቀርባለን፡-

♦የአላህ ቁጣ፡- አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡- ‹እኔ አላህ ነኝ። ከኔ ሌላ አምላክ የለም። ሲታዘዙኝ እደሰታለሁ። ስደሰት እባርካለሁ። በረከቴም ፍጻሜ የለውም። ትእዛዜ ሲጣስ እቆጣለሁ። ስቆጣ እራገማለሁ። እርግማኔም እስከ ሰባት ቤት (እስከ ልጅ ልጅ) ይደርሳል።› (አህመድ)

♦ሙእሚኖች ይጠሉሃል፡- ሐሰነል በስሪ እንዲህ ብለዋል፡- «ከናንተ አንዳችሁ የሙእሚኖች ቀልብ ሳያውቀው እንዳይረግሙት ይጠንቀቅ፡ ፡ ወንጀል በሚሰራ ጊዜ አላህ በሙእሚኖች ልቦና ውስጥ የርሱን ጥላቻ ያስቀምጣል።»

♦እውቀትን መነፈግ፡- ኢማም ሻፊዒ እንዲህ ብለዋል፡- የማስታወስ ችሎታዬ መቀነሱን መላ እንዲሹ ጠየቅኳቸው

♦የሂፍዝ ተሰጥኦዬ መኮሰሱን ሳልደብቅ ለወኪእ ነገርኳቸው ነገሩኝ መሆኑን እውቀት ችሮታ ለሐጢያተኞች የማይበረከት ስጦታ

♦ሪዝቅ መነፈግ፡- ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- ሰውየው በሚፈጽመው ወንጀል ሳቢያ ሪዝቅ ይከለከላል። (አህመድ)

♦ከአላህ ጋር መቆራረጥ፡- ከወንጀልህ ብዛት የተነሳ እጅህን ወደላይ አንስተህ ዱዓ ልታደርግ ይከብድሐል።

♦ከሰዎች ጋር መራራቅ፡- የወንጀልህን ፋና ከሰዎች ላይ ታየዋለህ። ካንተ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሲበላሽ ትመለከታለህ።

<u>ፊት ገጽታ መጨለም</u>:-ኢብን አባስ እንዲህ ብለዋል፡- ወንጀል ፊትን ያጠቁራል። ቀልብን ያጨልማል፤ አካልን ያደክማል። ሪዝቅን ያጠብባል። ከሰዎች ዘንድም ተጠይነትን ያስከትላል።

<u>ሽይር ስራ መነፈግ</u>፡- ወንጀል ወንጀልን ያስከትላል። ሽይር ስራ ቦታ ያጣል። ሰውየው ከአላህ ዘንድ ስለተናቀ ወነጀለው። አላህ ባይንቀው ኖሮ ከወንጀል ይጠብቀው ነበር።

وَمَن يُهِنِ اللَّهُ فَمَا لَهُ مِن تُكْرِمی

«አላህ ያዋረደውን የሚያልቀው የለም (አል ሐጅ 18)

❋በቀልብ ውስጥ ውርደትን ያሰርጻል

❋ጸጋን ያስወግዳል

አንደበትን ይቆልፋል። ይህም የሚሆነው መናገር እጅግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ነው። ወንጀለኛ ሊሞት በሚያጣጥር ጊዜ ሸሐዳ መናገር ያቅተዋል። በሐጢአቱ ክምር ምክንያት አንደበቱ ይዘጋል። አንድ ወጣት የነገረኝን ላጫውታችሁ: በአውሮኘላን በመጓዝ ላይ እያለ አንድ ያማረ ሰው ከአጠገቡ ተቀምጧል። በእጁ ሻንጣ ይዟል። አውሮኘላኑ እየበረረ ባለበት የሞት መላእክ መጣበት። ወጣቱ ሸሃዳ ሊያስብለው ሞከረ። እርሱ ግን አልሆነለትም። ሻንጣውን አጥብቆ ይዞ ማለት አልችልም ሲል ይናገራል። ለሸሃዳ ግን አንደበቱ ይተሳሰራል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

فَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسْلِمُونَ) البقرة: ١٣٢

ለአላህ ፈቃድ ያደራችሁ ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ እስከ ሕልፍተ ሕይወታችሁ በኢስላም እንደ ፀናችሁ ኑሩ) * (አል በቀራህ 132) ስንሞት በእስልምና የመሞት ዋስትና እናገኝ ዘንድ በእስልምና እንኑር።

«አንተን ብቻ እናመልካለን። አንተን ብቻም እገዛ እንጠይቃለን።» (አልፋቲሐ 5)

⇒ ወንጀልን ለመቋቋም የመጀመሪያው ነገር ሐጢአትን የመከላከል አቅም ይሰጠን ዘንድ አላህን መለመን፣ እገዛውን መማጸን ነው።

⇒ነፍስን መታገል

⇒ሰይጣንን ምንጊዜም በንቃት መጠበቅ

⇒ከመጥፎ ጓደኞች መራቅ

⇒አላህን አብዝቶ ማወደስ፣ ዚክር ማብዛት

⇒ቁርአን መቅራት

⇒መስጊድ ውስጥ መስገድ

⇒የኢልም ማእዶችን መታደምና የዳእዋ ካሴቶችን መስማት

ለተውበት ያበቃቸው ሁኔታ

አደምና ሐዋእ ጥፋት ከፈጸሙ በኋላ በሐፍረት ተውጠው ጀነት ውስጥ ይጓዙ ጀመር።
አላህም - ሐኪም እንደዘገቡት- እንዲህ አላቸው :-

«አደም ሆይ፣ ከኔ ሸሽት ነውን?› እርሱም :- ጌታዬ ሆይ፣ አይደለም። ሐፍረት ይዞኝ፣ ይሉኝታ ተሰምቶኝ ነው» አለ።

አላህ የማይወደውን ስራ በምንሰራ ጊዜ ከርሱ ሐፍረት ይሰማናልን? ይሉኝታ ይይዘናልን? ኢብንል ቀይም እንዲህ ብለዋል፡-

በወንጀል መደሰትህ ከአላህ ዘንድ ከወንጀሉ የባሰ አስከፊ ነው። ወንጀል እየሰራህ መሳቅህ ከአላህ ዘንድ ከወንጀሉ የበለጠ ከባድ ጥፋት ነው። ምክንያቱም ለአላህ ይሉኝታ አጥተሐል። እርሱን ማፈርን ትተሐል። አንድ ወንጀል ስላመለጠህ ማዘንህ ከአላህ ዘንድ ከወንጀሉ የከፋ ወንጀል ነው። ወንጀል እየሰራህ ወንጀሉን ለመደበቅ መሞከርህም ከአላህ ዘንድ ከወንጀሉ የበለጠ ሐጢአት ነው። ምክንያቱም እርሱ እያየህ መሆኑን ታውቃለህና።»

አደም ከአላህ ‹ሐያእ ያዛቸው። ስላጠፉ ሐፍረት ተሰማቸው። ተውባ ለማድረግ ፈለጉ። ምን አደረጉ? እንዲህ አሉ፦

“አምላኬ ሆይ፣ በእጅህ አልፈጠርከኝምን?”

“አዎ ፈጥሬሐለሁ።”

“አምላኬ ሆይ፣ ጀነት ውስጥ ባነጠስኩ ጊዜ፦ “አምላክህ ይዘንልህ ያልከኝ አንተ አልነበርክምን?”

“አዎ፤ እኔ ነኝ”

“አምላኬ ሆይ፣ እዝነትህ ከቁጣህ የቀደመች አይደለችምን?”

“አዎ”

“አምላኬ ሆይ፣ ከቶበትኩ ወደጀነት ትመልሰኛለህን?”

“አዎ፤ እምልስሐለሁ”

“አምላኬ ሆይ፣ እንዲህ ከሆነስ ወዳንተ በተውባ ተመልሻለሁ።” (ሐኪም እንደዘገቡት)

አደም እንዴት ተውባ እንደሚያደርጉ አላወቁም። እኛ ግን እንዴት መቶበት እንዳለብን እናውቃለን። አደም የመጀመሪያው ሰው ከስለነበሩ እውቀት አልነበራቸውም።

النقرة: ٣٧
فَتَلَقَّى ءَادَمُ مِن رَبِّهِ كَلِمَةٍ فَتَابَ عَلَيْهِ إِنَّهُ هُوَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ)

“አደም ከጌታው ጥቂት (የፀሎት) ቃላትን ተማረ፤ (በርሷ ተማፀነውም (አላህ) ንስሐውን ተቀበለው እርሱ (አላህ) ንስሐን ተቀባይ አዛኝ (አምላክ) ነው›› (አል በቀራህ 37) እንዲህ እንዲሉ አላህ አስተማራቸው፦

((قالا ربَّنَا ظَلَمْنَا أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ لَنَا وَتَرْحَمْنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ الْخَسِرِينَ
الاعراف ٢٣

አደም ከጌታው ጥቂት (የፀሎት) ቃላትን ተማረ፡ (በርሷ ተማፀነውም (አላህ) ንስሐውን ተቀበለው። እርሱ (አላህ) ንስሐን ተቀባይ, አዛኝ (አምላክ) ነው።።» (አል በቀራህ 37)

እንዲህ እንዲሉ አላህ አስተማራቸው፡-

((قَالَا رَبَّنَا ظَلَمْنَا أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ لَنَا وَتَرْحَمْنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ الْخَسِرِينَ

الأعراف: ٢٣

ጌታችን ሆይ! ራሳችንን በድለናል። ካልማርከንና ካላዘንክልን ክክሣሪዎች እንሆናለን።" በማለት (ጌታቸውን) ተማፀነ።።» (አል አዕራፍ 23)

«ይህን ካልክ እምርሐለሁ» አላቸው። አደም የተባሉትን አደረጉ። አላህም ንስሐቸውን ተቀበለ።

የኛ ነገር ይገርማል። አላህን እያወቅነው አንወደውም። በእዝነቱ እና በበረከቱ የኛን ውዴታ ለማግኘት እየጣረ፣ እኛ ወደ ሌላ እንሄዳለን። ሳይጠይቁት የሚሰጥን አምላክ ትተን እንሸሻለን። የወንጀልን አስከፊ ውጤት ከጠላን ለምን ተውበት አናደርግም? ለምን አሁኑኑ ወደርሱ አንመለስም? የሰው ልጅ በባህሪው ይሳሳታል። አላህም በባህሪው ይምራል። ተውበትን ማዘግየት ከመወንጀል የበለጠ አስከፊ መከራ ነው።

<u>ወደ ተግባር</u>

አሁኑኑ መቶበት እንችላለን? አዎ፣ እንችላለን። ለዓመታት የቆየንበትን ወንጀል አሁን እንተው። የወላጆችን መብት ከመጋፋት፣ አስካሪ መጠጥ ከመጠጣት፣ ከአደንዛዥ እጽ፤ ከዚና አሁኑኑ ተገላግለን ወደ አላህ መመለስ እንችላለን? ባለፈው ጥፋታችን ከተቆጨንና ዳግም ላለማጥፋት ከወሰንን ይህ ይቻላል። በዚህ አቅጣጫ ከእውነተኛ ውሳኔ ላይ በደረስንበት፣ ከልብ በቶበትንበት ቅጽበት አላህ ይምረናል።

ተስቶን ወደ ወንጀል ከተመለስንስ? ተውባችንን በድጋሜ ይቀበለናልን አዎ፣ ደጋግመን ብናጠፋም ይቀበለናል። ከተውባ የሚጋርድ ምንም ነገር የለም።

በጎ ስራ የማትሰግድ እና ሂጅብ የማትለብስ እንስት ተውባ ብታደርግ አላህ ይቀበላታልን? አዎ፣ ይቀበላታል። ወንጀሏንም ወደ ይለውጠዋል። አንድ በደዊን ከመልእክተኛው ዘንድ መጣና ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ወንጀል ብሰራ ምን ይሆናል?› ሲል ጠየቃቸው። ‹ይጻፋል› አሉት። ‹ስቶበትስ?› አላቸው። ይታበሳል› አሉት። ‹ተመልሼ ወንጀል ከሰራሁስ? አላቸው። ይጻፋል› አሉት። ከቶበትኩስ?› አላቸው ‹ይታበሳል› አሉት። ‹‹እንደገና ከሰራሁስ?› አላቸው። ይጻፋል አሉት። ‹ከቶበትኩስ?› አላቸው። ‹ይታበሳል› አሉት። ‹‹አምላካችን ለምን ያህል ጊዜ ነው ወንጀልን የሚያብሰው?›› አላቸው። እናንተ ምህረት መለመን እስካልሰለቻችሁ ድረስ እርሱ ከመማር አይሰለችም።›› አሉት።

ይቅርታ እና ምህረት ከመጠየቅ የሚሰለች ከመካከላችን ይኖር ይሆን? የጌታውን ይቅርታ ከወንጀለኛ ይበልጥ ተስፋ የሚያደርግ ማን አለኝ ሰፊዋ ምድር ስትጠብበት ወደማን ይሸሻል? በወንጀሉ ምክንያት ሰዎች ከጠሉት ማን ይቀበለዋል? አለኝታው፣ ምህረቱ ከሁሉም ነገር የሰፋው አላህ ብቻ ነው፡

ጣፋጭ መልእክት

አደም አምላካቸውን ምህረት በለመኑ ጊዜ ማራቸው፡ መረጣቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

فَأَكَلَا مِنْهَا فَبَدَتْ هَمَا سَوْءَ تُهُمَا وَطَفِقَا يَخْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ الْجَنَّةِ وَعَصَى

(عَادَمُ رَبَّهُ، فَعَوَى (٢) ثُمَّ اجْتَبَهُ رَبُّهُ، فَتَابَ عَلَيْهِ وَهَدَى

«ከርሷም በሎ፡ ሐፍረተ ገላቸውም ተገለፀላቸው፡ በላያቸው ላይም የገነት ቅጠል ይለጥፉ ጀመር። አደም (በዚህ አካኋን የጌታውን ትእዛዝ ጣሰ ስህተት ላይ ወደቀም ከዚያም ጌታው መረጠው ንስሐውንም ተቀበለው፡፡ መቀናትንም ለገሰው (ጧሃ 121-122)

አደም ስለ ጥፋታቸው ብዙ አልቅሰዋል።።ምህረት ጠይቀውም ተምረዋል። ይህም ሆኖ ግን በእለተ ቂያማ ይህችን ጥፋታቸውን አስታውሰው ይጸጸታሉ። አላህን ይፈራሉ። በይሉኝታ ይዋጣሉ።። ይህውም ሰዎች በእለተ ቂያማ ‹ያለንበትን ሁኔታ አታይምን? ከጌታችን ዘንድ እማልደን በማለት ሊጠይቋቸው የሚሰጡት መልስ ይገርማል፡ የራሴ ጉዳይ ያሳስበኛል። የተከለከለችውን ዛፍ የመመገብ ጥፋት ፈጽሚያለሁ።።› ይላሉ።።

አደም የፈጸሚትን አንዲት ጥፋት ሁሌም ማስታወሳቸው ይገርማል። የወንጀል ክምር ተሸክሞ ምንም መስሎ የማይታየው ስንት ሰው አለ? አርጌ መከና ያለችው ሰው በአካሏ ላይ የሚደርስ መፋፋቅና ጉዳት ምንም መስሎ አይታየውም። ምክንያቱም ወትሮውንም አካሏ የተጎሳቆለ ነውና። አዲስ መከና ሲይዝ ግን ጥቂት ጭረት ታመዋለች። ኢምንት ጉዳት ትሰማዋለች።።

ከአላህ ጋር የተገናኙት ነፍስም እንደዚሁ ናት። ቆሻሻ ሲነካት ባለቤቷ መታጠስ አይችልም። በተውባ ወይም በጥሩ ሐጅ ወዲያውኑ ያጸዳታል።

ወደ አላህ ተመለስ

ኢብንል ቀይም እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

አላህ ለአደም እንዲህ የሚለው ይመስላል፡- ‹አደም ሆይ፥ በወንጀል የፈተንኩህ ችሎታዬ ባንተ ላይ እንዲሳለጽ ስለፈለግኩ ነው። ባትወንጅሉ ኖሮ እናንተን አጥፍቼ ወንጀል ሰርተው ምህረት የሚለምኑኝንና የምምራቸውን ሌሎች ፍጡራን አመጣ ነበር።።አደም ሆይ፥ ከወንጀልህ በፊት ከኔ ዘንድ ልከ እንድ ንጉስ ወደ ሌላ ንጉስ በሚገባበት ሁኔታ ትገባ ነበር። አሁን ግን ባረያ ወደ ንጉስ በሚገባበት አኳኋን ትገባለህ፡ ለሁላችንም ይህ ተመራጭ ነው። እንተን እና ልጆችህን ከሐጢአት ከጠበቅኩ ተውበትን ተቀባይና አዛኝ እንደመሆኔ፥ ይቅርባይነቴን፥ አዘኑቴን፥ ተውበት ተቀባይነቴ በማን ላይ ልነልጽ፥ ለማን ልቸር ነው? አደም ሆይ፥ ከጀነት ስላስወጣሁህ አትዘን። ጀነትን ለአንተ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳትም። ግና የትግልና የጥፋት አገር ወደሆነችው ምድር

ውረድ። የተቅዋ ችግኝም ትከልባት። ወደኔ መግባት አትፈልግ ሲናፍቅህ አቀበልሐለሁ። የጀነትን በር እከፍትልሐለሁ። ወደነበርንበት ቦታ እመልስሐለሁ። ጎረቤቴም አደርግሐለሁ። ለኔ የሚያስተናንስህ ወንጀል፣ ከሚያመ�ዴድቅህ በጎ ስራ የተሻለ ነው።

ለይዩልኝ ከሚሰሩ ሰዎች ውዳሴ ይልቅ የወንጀለኞችን ለቅሶ እወዳለሁ።

ተውባ የእላህ ተገዥነት አስኳል ነው። በርሱ ቀልብህ ለእላህ ይሰበራል ይተናነሳል። ከእላህ ሌላ መጠጊያ እንደሌለው፣ የምህረት ባለቤትም እርሱ ብቻ እንደሆነ ይረዳል። እላህ ለተጸጸተ ወንጀለኛ ባሪያው እንዲህ ይላል፡-

የእያም ልጅ ሆይ፣ ከለመንከኝ እና ተስፋ ከጣልከብኝ ጥፋትህን ሁሉ እምርልሐለሁ። ይህን ማድረግ አይገድኝም። የእያም ልጅ ሆይ፣ ወንጀልህ እስከሰማይ ድረስ በደርስና ምህረት ብትለምነኝ ጥግ እምርሐለሁ። ይህን ማድረግ አይገድኝም። የእያም ልጅ ሆይ፣ ምድርን የሚያክል ወንጀል ይዘህ ብትገናኘኝ በኔ ላይ ምንም ነገር እስክላጋራህ ድረስ ምድርን የሚያክል ምህረት ይኸ አጠብቅሐለሁ።›› (ቲርሚዚ)

ታዲያ ለምን ወደርሱ ፊታችንን አናዞርም? ከርሱ የተሻለ አዛኝና ቸር አካል አገኘን? በፍጹም! ዑለሞች እንደሚሉት፡-

«የቀልብን መሰበርና መዋረድ ያስከተሉት ወንጀል በኩራት ካስከፈሰች በጎ ስራ ትሻላለች።»

የዓለማት ጌታ ወደርሱ ይጠራሐል። እንደምትመለስም ተስፋ አድርጓል። ብዙ ምንዳ ከርሱ ዘንድ አለ። ምህረት፣ ፍቅር አለ። ሐጢኣትን ወደበጎ ስራ ይለውጣል። ከሌሎች ዘንድ የዚህን ሽርፍራፊ እንኳ ታገኛለህን?

ልዩነታቸው

ኢብሊስም አደምም ጌታቸውን ወንጅለዋል። አላህ የአደምን ተውባ ተቀበሎ ኡብሊስን ምህረት የሄጋው ለምንድን ነው?

⇨ ኢብሊስ ከወንጀሉ ላይ ዘወተረ። ተውባም አላደረገም። ስለዚህም በወንጀል ላይ ከሚጸነት፥ ለተውባ ደንታ ቢስ ከሆኑት እንዳትሆን ተጠንቀቅ።

⇨ አደም ተጸጸተና ቶበተ። ኢብሊስ ግን በትእቢቱ ጸና። የሁለቱ ልዩነት ይህ ነው። ተውባ።

⇨ የኢብሊስ ወንጀል የቀልብ ወንጀል ነው። ሰበቡም የኩራት በሽታ ነው። እስክ አለተ ቂያማ ድረስ አድሚው ረዝሞ የአደምን ዘሮች ለማጥመም እስከመወሰን ይህ በሽታ አድርሶታል።

የአደም ወንጀል ግን የአካል ወንጀል ነው። የሰውን ልጅ አንድ የአካል ክፍል ሊያገኝ የሚችል በሽታ ነው። የቀልብ ወንጀሎች ከአካል ወንጀሎች ይበልጥ ያጠፋሉ።የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፦

«ከቀልቡ ውስጥ ቅንጣት ታክል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም።» (ሙስሊም፣ አቡ ዳውድና ቲርሚዚ)

በመሆኑም ጥላቻንና ምቀኝነትን፣ እንዲሁም ሌሎች የቀልብ በሽታዎችን ተጠንቀቅ። ጸንያንም አሺራንም ያበላሻሉና።

በወንጀሉ የተጸጸተው፣ አምላክን ምህረት የጠየቀው፦ ጌታዬ ሆይ፣ ተውባ ማድረግ እፈልጋለሁና እንዲት እንደምዶበት አስተምረኝ። ተውባዬንም ተቀበለኝ።» ያለው የአላህ ባሪያ (አደም)፣ በወንጀሉ ላይ

ከጸናውና በጥፋቱ ከተኩራራው፣ አላህን በሚታዘዝ ሁሉ ላይም የጥላቻ ሾተል ከመዘዘው እኩይ ጋር እንዴት ይስተካከላሉ? ዒባዳንና ባለቤቱን መናቅ በወንጀል ላይ ከዘወተሩ ሰዎች በቀር ሁሉም ሰዎች መህረት ያገኛሉ። አንድ ሰው ከአላህ መልእክተኛ ዘንዴ በግራ እጁ ተመ «በቀኝህ ተመገብ» አሉት። ‹አልችልም› አላቸው። አትቻል ሲሉ ረገሙት። ሽባ ሆነ። (ዳሪማ እና አህመድ)

ቁጣዩን መልእክት ተረዳ

አደም ወደ ምድር ወረዱ። በርሳቸውና በሏብሊስ መካከል ጠላትነት ታወጀ። አደም ከጀነት የወረዱበትን ሁኔታ በዓይነ ሕሊናህ ለማሰብ ሞክረ። ምን ተሰምቷቸው ይሆን?

አስተውል፤ እያንዳንዱ ሙስሊም በጀነት ውስጥ ደረጃ አለው። የተለያየ ደረጃ።

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

የጀነት ውስጥ በሁለት ደረጃዎች መካከል ያለው ልዩነት በሰማይና። በምድርር መካከል ያለውን ርቀት ያህላል።» (አቡ ሸይባህ)

አንድ ደረጃ ከሌሎች ዝቅ በማለትህ ሊደርስብህ የሚችለውን ቁጭት አስበው። እንዲህ እያልክ በቁጭት መቃጠልህ ይታሰብህ፡-

⇒ በዚህ ቀን የሱብሂን ሶላት ሰግጀ በነበር።
⇒ ይህች ወንጀል ባትኖር ኖሮ ደረጃዬ ይጨምር ነበር።
⇒ ቁርአን ቀርቼ ቢሆን ኖሮ ወደ ላይ አዘልቅ፣ በጣም እመነጠቅ ነበር።

ቁርአን ስንቀራ በእያንዳንዱ ፊደል (ሐርፍ) 10 ሐሰና (ምንዳ) እናገኛለን። የተከታዩን ቃል ምንዳ እናስላ፡-

بسم الله الرحمن الرحيم

በዚህ ቃል ውስጥ 19 ሐርፎች ይገኛሉ። 190 ሐሰና (ምንዳ) አለህ ማለት ነው።
አንድ ጁዝእ 70 ሺህ ያክል ፊደላት አሉት። 700 ሺ

ምንዳ ማለት ነው። ከእንድ ሰአት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል ምንዳ መሰብሰብ ድንቅ ነገር አይደል

አሁን እንተ በዳንያ ውስጥ ነህ። እድሉ ተመችቶልሐል። ስለዚህም ተጠቀምበት። ቀጠሮ አታብዛ፤ አሁኑኑ ተመለስ። አሁኑኑ ጀምር። ሞት ከመምጣቱ፥ እድሉ ከመነሳቱ በፊት። የጀነት ሰዎች ጀነት ውስጥ ከሚያዩት ልቅና የተነሳ አላህን ሳይዝጡት ያሳለፋት እያንዳንዱ ቅጽበት በቁጭት ታንገበግባቸዋለች።

ወደ ምድር ወረደ

ብዙሐን ዑለሞች እንደሚሉት አደም በሕንድ አካባቢ ወረደ። ሐዋእ ደግሞ ጅዳ አካባቢ, ወረደች። ሁለቱ ሲፈላለጉ ከቆዩ በኋላ ዓረፋ ተራራ ላይ ተገናኙና። ተዋወቁ

የቃሏ ይዘት

አደምና ሐዋእ በሂደት የመሳሳብ ስሜትን አዳበሩ። ጀነት ውስጥ ይህ ስሜታቸው አልነበረም። ሃዋእ በእያንዳንዱ እርግዝና ሴትና ወንድ ልጆችን መውለድ ጀመረች። ምድር በግብርናና በእደ ጥበብ መልማታቷ ተወጠነ። አደም አምላኪ ብቻ አልነበሩም። ምድርን በማልማትም ስኬታማ ነበሩ። ሁሉም ሐይማኖተኛ ልከ እንደርሳቸው ሊሆን ይገባዋል። ሙስሊም ሐገሮች በእድገትና ብልጽግና ጓላ ቀር እንዲሆኑ እንዴት ወደድን? ከሦስተኛው ዓለም እንዲመደቡ እንዴት ፈቀድን?

አደም ተግባራቸውን በሚገባ አውቀዋል። አላህ በምድር ላይ ወኪል (ኸሊፋ) ላደርግ ነኝ ሲል የጣለበቸውን ሐላፊነት በወጉ ተረድተዋል።

አንተም በምድር ላይ የአላህ ወኪል ነህ። የዚህን ቃል መልእክት አጢነህው ታውቃለህ? «ዓለምን መቀየር እችላለሁን?» በማለት ትጠይቅ ይሆናል። አዎ፥ ትችላለህ። የሕይወት አላማህም ይህ ነው። አላህ ግዴታ ያደረገብህ መልክም ስራ እንጅ ውጤት አይደለም። አምላክህ ኸሊፋ አድርጎሃልና ራስህን ዝቅ አድርገህ አትመልከት።

አቅሷ መጅመሪያና መጨረሻ

አደም ወደ ምድር በሚወርድ ጊዜ ስፋታን ተመለከተና፡- በምድር ላይ ከኔ ጋር ሆኖ አንተን የሚያወድስ ሌላ አካል አለን? በማለት አላህን ጠየቀው። ‹አደም ሆይ፥ ከልጅህ የኢባዳ አጋር ይኖርሐል። በምድር ላይም የምመለክበቸው መስጊዶች ይኖሯችኻል።› አለው። እርሱ የሚመለክበት ቤት ይገነቡ ዘንድም አደምን አዘዘው። አደም «በይተል ሐራም» (የመካን የተቀደሰ መስጊድ) ገነቡ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(إِنَّ أَوَّلَ بَيْتٍ وُضِعَ لِلنَّاسِ لَلَّذِي بِبَكَّةَ مُبَارَكًا وَهُدًى لِلْعَالَمِينَ)

«ለሰው ልጅ የተቀመጠው የመጀመሪያው (የአምልኮ) ቤት ያ በበካ የሚገኘው ነው የተባረከና ለዓለማትም መመሪያ (የሚፈልቅበት እንዲሆን ተደረገ።» (አል ዒምራን 96)

የአሁኗ መካ በካህ» በሚል ስያሜ የተጠራችው ከውስጢ አልቃሾች (ለአላህ የሚያለቅሱ ሰዎች) ስለሚበዙ ነው። (በካኣ ትርጉሙ· ማልቀስ ማለት ነው።)

ከዚያም አላህ ሰዎችን ወደ ተቀደሰው የሐረም መስጊድ ሐጅ እንዲያደርጉ አዘዘ።አደምንም መስጊዱል አቅሷን እንዲያንጹ አዘዘቸው።

አደም ወደ ምድር ሲወርዱ ያስጨነቃቸውን ነገር አየህን? በመጀመሪያየ ያሳሰባቸው ኢባዳ ነበር። የአላህ ዚክር እና ውዳሴ (ተስቢህ) ነበር። በዚህ የኢባዳ ተግባር የሚጋራቸውን ጠየቁ። እኛንስ የሚያሳስበን ነገር ምንድን ነው?

ለአደም ኢባዳ በጣም የሚያሳስባቸው ጉዳይ ቢሆንም ምድርን ከማኑጽ ግን አላዘናጋቸውም። ኽሊፋነታቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል። ምድራዊ ሕይወትን አደራጅተዋል። በአላህ የተመረጡ ኑቢይ ነበሩ።

ሶሐቦች ነቢዩን፡- «በሁሉቱ መስጊዶች መካከል ያለው የእድሜ ልዩነት ምን ያህል ነው? በማለት ጠየቁ። ነቢያም ፡- አርባ አመታት ሲሉ መለሱ። አባታችን አደም ሁሉቱን መስጊዶች በአርባ አመታት ልዩነት

ገንብተዋል። አላህ፣ የመጨረሻው ነብይ ለሆኑት ለነብያችን ሁሉቱን መስጊዶች በአንድ አንቀጽ አጣምሮ አውርዶላቸዋል፦

سُبْحَانَ الَّذِي أَسْرَى بِعَبْدِهِ، لَيْلًا مِنَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ إِلَى الْمَسْجِدِ الْأَقْصَا الَّذِي بَرَكْنَا حَوْلَهُ لِنُرِيَهُ مِنْ آيَاتِنَا إِنَّهُ هُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ ( ) الإسراء :

«ከብር ለዚያ ባሪያውን (ሙሐመድን) ከተከበረው (የሐረም) መስጊድ ወደዚያ ዙርያውን ወደባረክነው ሩቁ (የአል-አቅሷ) መስጊድ በሌሊት ለወሰደው (አምላክ) ይሁን። ተአምራታችንን ልናሳየው ይሆን አደረግን)። እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚም ተመልካችም ነው› (አል ኢስራ ነ)

የአላህን የተቀደሰ ቤት ለማየት ናፍቀሐልን? አቅሷን ከአይሁዶች ቁጥጥር ነጻ ለማውጣ አስበህ ታውቃለህን? አየተፈጸመበት ያለው ጥፋት ያማሐል? ስቃዩስ ይቆጭሐል? ዋይታው ይለማሐልን? ለእነዚህ ሁለት የተቀደሱ መስጊዶች የምንሰጠው ዋጋ ምን ያህል ነው?

ذَلِكَ وَمَن يُعَظِّمْ شَعَائِرَ اللَّهِ فَإِنَّهَا مِن تَقْوَى الْقُلُوبِ) الحج: ٣٢ ››

ይህ (የአላህ ሃይማኖታዊ ድንጋጌ ነው። ሃይማኖታዊ ትእዛዛትን ያከበረ ይህች (ድርጊቱ) አላህን ከምትፈራ ልቦና (የመነጨች) ናት።› (አል ሐጅ 32)

ከእባትህ ተማር

ኢብሊስ አደምን ወደ ምድር ከወረዱ በኋላ ዳግም ሊያሳስታቸው አልቻለም፡ ሙአሚን በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ሁለት ጊዜ አይገባምና። እኛ በየቀኑ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ 20ና 30 ጊዜ መግቢታችን ምን ነክቶን ነው?

ኢብሊስ አደምን ሊያሳስታቸው እንደማይችል እርግጠኛ ሆነ። እናም እርሳቸውን ትቶ በልጆቻቸው ላይ ለማተኮር ወሰነ። አባካችሁ ጅማንትን ከአባታችን ከአደም እንማር።

የጅነት ናፍቆት

ኢብን ሂባን እንደዘገቡት አደም 940 ዓመታት በምድር ላይ ኖሩ። ብዙ ልጆችንም አፈሩ። 21 ያህል መጽሐፍት ወረደላቸው። በአድሚያቸው መጨረሻ ላይ ልጆቻቸውን ሰበሰቡና ዛሩም የሆነ መልእክት አስተላለፉ። እንዲህ ማለታቸው ተጽፏል፡

«ልጆቼ ሆይ፣ የጅነትን ፍራፍሬዎች ናፍቂያለሁ።»

እኛስ ከዳንያ ስቃይ ለመገላገል ጀነትን ናፍቀን እናውቃለን? ነፍስህ የእረፍትና የድሎት አገር ወደሆነው ጀነት በናፍቆት ተጉዛ ታውቃለችን አደም በምድር ላይ 10 ክፍለ ዘመናት ያህል በኖሩም ጀነትን ሊረሱ አልቻሉም። ሰይጣንን ከልብ ብንጠላ ኖሮ ነፍሳችን ወደ ጀነት በሐሳብ በከነፈች ነበር።

ከዚያም መላኢኮች መጡ። ሞትም መጣ። ጁመዓ ቀን ነፍሳቸውን አወጧቸው። መላኢኮች አጠቧቸው፣ ገነዟቸው፣ ቀብሯቸውም። ከዚያም እንዲህ አሉ፡-

የአደም ልጆች ሆይ፣ ይህ ከእደመ በኋላ የምትከተሉት ሱንና (ሙታንን የመሸኘት ስርዓት) ነው።»

በዛጀዎች ውስጥ ፍቅር ያለው ለዚህ ነው

አደም ሞቱ። ሐዋኢ ምን እንዳደረጉት ታውቃለህን? ለአንድ ዓመት ያህል አምርራ አለቀሰች። በጣም አዘነች። ለአደም ልዩ ፍቅር ነበራት። አዎ፣ ይህ ወሰንህ የማይለል ፍቅር።

የኛ ሁኔታ ያሳዝናል። ይህች ዓለም እንዴት አበላሸችን? እንዴት በከለቸን? ዳንያ ተቆጣጠረችንና በየቢታችን የሰው ፍቅር ቀለለ። የንዋይ ፍቅር አየለ። ዶጋማ የአላህ ባሮችን ሁኔታ ግን አስተውሉ።

ዑመር ቢን አልኸጧብ የአሊ ቢን አቢ ጧሊብ ልጅ የሆኑትውን ኡም ኩልሱምን ሲያገቡ በጣም ወደዷት። አርዕያም እንደዚሁ በፍቅር ከነፉችላቸው። ፍቅራቸው በአኗኗር ብቻ ላይሆን በአሚሚትም

አልቻሉም። የሰከና ምንጭ፣ የሐሴት ማእከል ሊሆኑ አልቻሉም። እናም የጻፍውን አገኙ። ወንዶችም የአላህ መልእክተኛ፦ ለሴቶች አደራ በጎ ሁኑ።›› በማለት ያስተላለፉትን ኑዛዜ ችላ አሉ።

ግና አሁንም እድል አላቸሁ። አሁኑኑ ተጠቀሙበት። ከሁላታችሁ ማን ይጅምር? የፍቅርን እርካብ ማን ቀድሞ ይርገጥ? እንተ መቅደም እንደፈለግክ አውቃለሁ። በል፣ ተበራታ። ፍቅርህን አሁኑኑ አድስ። ፍጠን፣ እርካታ፣ እርጋታ፣ ሰከናና ረፍት ታገኛለህ። በመጭው ዓለም ደግሞ ጀነትን ትወርሳለህ። ለዚህ ዝግጁ ነህ?

በየትኛው ጎናቸው ነህ

ነቢዩ በሚእራጅ ሌሊት አንድ ሰው አዩ። ወደቀኙ ሲዞር ብዙ ሰዎች ያይና ይስቃል። ወደ ግራው ሲዞር ደግሞ ብዙ ሰዎች ያይና ያስቅሳል። «ጅብረል ሆይ፣ ይህ ሰው ማን ነው?» በማለት ጠየቁ። «አባትህ አደም ነው። ወደ ቀኙ ሲዞር አላህን የተገዙና ጀነት የተወሰነላቸው ልጆቹን አይቶ ይስቃል። በስተግራው በኩል ደግሞ አላህን የወንጀሉና አሳት የተወሰነባቸውን ልጆቹን ያይና ያስቅሳል።› አላቸው።

ሓጢኣተኞች ከአባታቸው ታሪክ ትምህርት አልቀሰሙምና አስለቀሱት። የኢብሊስ ግምት በነርሱ ተረጋገጠ። ዓላማው ተሳካ። ጠላትነቱን ረስተው ተከተሉት።አባተቸውን ከሚያስለቅሱ ሰዎች መሆን ትሻለህ? ወይስ ሰይጣንን በጠላትነት በመያዝ አባታቸውን ካሳቁት መሆን ትሻለህ? ምርጫህን ከአሁኑ አስተካክል። የጀነት ሰዎችን ለመሳራቢት የሚያስፈልገው መስፈርት በጎ ሰዎችን መውደድ፣ ሰይጣንን፣ ሴራውን እና አሳሳች ድምጹን መጥላት ብቻ ነው።

አላሁ አክበር !

በጉሻ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፦
«አላህ በአለተ ቂያማ፦ አደም ሆይ፣ አሳት የሚገቡ ሰዎችን አውጣ፣ ይላቸዋል።አምላኬ ሆይ፣ ቁጥራቸው ስንት ነው? ይሉታል። ከ1000 ሰዎች መሐል 999 ወደ አሳት ፣ ደግሞ ወደ ጀነት ይሄዳሉ ይላቸዋል።»

ሶሐቦች ይህን ሐዲስ ሲሰሙ አለቀሱ። ‹ለምን ታለቅሳላችሁ?› ሲሉ ነቢዩ ጠየቋቸው። የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ የኛ መሄጃ ወደየትኛው ነው?› በማለት ጠየቁ። 999 ሰዎች ከየእጁጅና ከመእጁጅ እንዲሁም ከቀደምት ሕዝቦች ሲሆኑ ነ ደግሞ ከናንተ ነው። የጀነት ሰዎች ሩብ እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ› አሉ። ሶሐቦች _ በጣም ተደሰቱ። መስጊዱ አስኪንቀጠቀጥ ድረስ ‹አላሁ አክበር› የሚል ድምጽ አሰሙ። ነቢዩ ደስታቸውን ሲያዩ፡- የጀነት ሰዎች ሲሶ እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ› አሉ። አሁንም ተከቢራ ተሰማ። «የጀነት ሰዎች ግማሽ እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ።› ሲሉ አከሉ። በዚህ ጊዜ፡- አላሁ አክበር! አላሁ አክበር! በሚል

ድምጽ መስጊዱ ተናጠ።

የአላህን እዝነት ስፋት አስተዋልከን? የፈለገ ሰው ይህን እዝነት ያገኛል። ይህን ችሮታ ይታደላል። ስለዚህም ሰይጣንን ከልብ በመጥላት፣ አላህን በመታዘዝና በተውባ ፈልገው። ነቢዩን በመውደድ ፈልገው። ሰውየው ከሚወደው አካል ጋር ይቀሰቀሳል።

ከሁሉም ያላቀህን፣ እዝነተ ሰፊ አምላክህን ከያዝክ ሰይጣን ምንም ሊያደርግህ አይችልም። መንገድህን አውቃሐል። በል ተነስ፣ ለተግባር ተንቀሳቀስ።

የአደም ልጆች ታሪክ

በቁጥር አትሸንገል

ከ20 ዓመታት በፊት የከተማችን ነዋሪዎች ስንት ነበሩ? ለምሳሌ ግብጽ ውስጥ ከ20ዎቹ ሚሊዮን የበለጠ አልነበረም። 100 ዓመታት ወደ ኋላ ብንመለስ ቁጥራቸው ስንት ይሆናል? 10ከፍለ ዘመናት ወደ ኋላ ብንሄድስ? ወደ አደም ዘመን ስንመለስ ሁሉቱ ልጆቻቸው የሰው ልጆችን ሲሰ ይመጥኑ ነበር። ምን ይህል ከፍለ ዘመናት ወደነርሱ ይመልሱናል?

ዳንያ እድሜዋ በጣም አጭር ነው። ረዣዥም ከፍለ ዘመናትም አጭር ናቸው። ቁርአን ወደዚያ ዘመን እንዲህ ሲል ይመልሰናል፡-

(وَاتْلُ عَلَيْهِمْ نَبَأَ ابْنَيْ ءَادَمَ بِالْحَقِّ ٢٧ المائدة)

የሁለቱን የአደም ልጆች እውነተኛ ታሪክም ተርከላቸው " (አል ማኢዳህ 27)

በመሓከል ያለውን የጊዜ ርቀት ችላ ብሎ ከስተቱ አሁን የተፈጸመ ያህል ይተርከልናል። ነቢዩ ይህን አንቀጽ ለሶሐቦቻቸው ከ1400 ዓመታት በፊት አንበበውላቸዋል። እኛም እያነበብነው ነው። ነገም ከነገ በኋላም አላህ ምድርን እስኪወርስ ድረስ አንቀጹ ይነበባል። የቅርብ ጊዜ ታሪክ ይመስላል። እጅግ በርካታ ከፍለ ዘመናት በጣት በሚቆጠሩ ቃላት ተጽፈው ቀርበዋል፡

(وَاتْلُ عَلَيْهِمْ نَبَأَ ابْنَيْ ءَادَمَ بِالْحَقِّ)

የሁለቱን የአደም ልጆች እውነተኛ ታሪክም ተርከላቸው:: (አልማኢዳህ 27)

ስለዚህም ዳንያ የሙስሊም ዓይነተኛ ግብ ልትሆን አትችልም። ለአላህ ብለህ፤ በርሷ አትታለል። መጠኑን ያለ አግባብ አግዝፈህ አትመልከት። በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች እስኪ ተመልከት። ከ100 ዓመታት በፊት

ከመከላቸው አንዱ እንኳ በሕይወት ነበርን፡ ከ100 ዓመታት በኋላ የሚኖር አለን የምድር ገጽታ በፍጥነት ይቀየራል። ዱንያ ለአቪራ በጣም ቅርብ ናት። ገጣሚው እንዲህ ሲል እውነትን ተናግሯል፡-

ቀናት በፍጥነት ዓዱ
ፋታ አይሰጡን ነጎዱ
እኛን አዝለው እኛን ይዘው
በእኛ ላይ ተረማምደው

ታሪኩ

ይህን ታሪክ የሚቃኙ የቁርአን አንቀጾችን ከማቅረባችን በፊት እኛው ባጭሩ እንዳስሰው፡

ሐዋእ በእያንዳንዱ እርግዝና ሴትና ወንድ የሆኑ መንታ ልጆችን ይወልዱ ነበር። የኔው ሕግ ወንዱ መንትያ እህቱን እንዳያገባ ይከለክላል። ስለዚህም የሌላ ወንድሙን መንትያ እህት ያገባ ነበር። በዚህ መልኩ የሰው ልጅ ይባዛል። የዘሩ ቀጣይነት ይረጋገጣል። ቃቢል መንትያ እህቱን ማግባት ፈለገ። ከአቤል እህት ይበልጥ ቆንጆ ስለበረች። አደም ሁለቱን ልጆቹን ለአላህ ቁርባን እንዲያቀርቡ አዘዘ። ቁርባኑ በአሳት ተበልቶለት ተቀባይነት ያገኘ የሚፈልጋትን መርጦ እንደሚያገባ ቃል ገባላቸው።፡

ቃቢል ገበሬ ስለነበር ጥሩ ያልሆነ አህል ለቁርባን አቀረበ። አቤል ደግሞ ፍየል ጠባቂ ነበርና ከፍየሎቹ መሐል መልክሙን መርጦ ቁርባን አቀረበ። አሳቷ ወረጅቾና የቃቢልን ትታ የአቤልን ቁርባን በላች፡ ቃቢል በዚህ ተበሳጨ። ወንድሙን ለመግደልም ወሰነ። በዚህ ሐሳቡ ጸንቶም ገደለው።

የአላህን ትእዛዝ በመጣስ ላይ መጽናት ገደል ይከትታል። ፈጸጸትና ለኪሣራ ይዳርጋል። በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ጥቂት ቀናት ቆይቶ ሊሆን ይችላል። በመጨረሻ በጎው

ይህ ወንጀል እንዲከሰት ምክንያት የሆነው ምንድን ነው? ቃቢል ወንድሙን በመግደሉ ነገሩ ፍጻሜ ያገኛልን? በፍጹም። ከታሪኩ የሚቀሰመውን ትምህርት እንምዘዘው። በመጀመሪያ የወንጀሉን ምክንያት እንይ፡-

አንዳንድ ሰዎች ሰበቢ እንስት እንደሆኑች ይናገራሉ። ግና እንስት በስብእናዋ በዚህ ወንጀል ተጠያቂ አይደለችም። ሰበቡ በርሷ የመፈተን እባዜ ነው። ለወንድ ልጅ ከባዱ ፈተና በእንስት በኩል የሚመጣው ነው። : ለእንስትም ከባዱ ፈተና የተባለት ፈተና ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

زُيِّنَ لِلنَّاسِ حُبُّ الشَّهَوَاتِ مِنَ النِّسَاءِ وَالبَنِينَ وَالْقَنَاطِيرِ الْمُقَنطَرَةِ مِنَ الذَّهَبِ وَالْفِضَّةِ وَالْخَيْلِ الْمُسَوَّمَةِ وَالْأَنْعَامِ وَالْحَرْثِ ذَٰلِكَ مَتَاعُ الْحَيَوةِ الدُّنْيَا وَاللَّهُ عِندَهُ حُسْنُ الْمَآبِ) قُلْ أَؤُنَبِّئُكُم بِخَيْرٍ مِن ذَٰلِكُمْ لِلَّذِينَ اتَّقَوْا عِندَ رَبِّهِمْ جَنَّاتٌ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ خَالِدِينَ فِيهَا وَأَزْوَجٌ مُطَهَّرَةٌ وَرِضْوَانٌ مِنَ اللَّهِ وَاللَّهُ بَصِيرٌ بِالْعِبَادِ (1) ››

ቶችና ልጆች የተከማቹ የወርቅና የብር ሃብቶች የተሰማሩ ፈረሶች፣ ግመሎች፣ ከብቶችና ፍየሎች አዝመራም ከሰዎች ዘንድ የተወደዱ ናቸው እነኝህ የዚህች ዓለም ፀጋዎች ናቸው አላህ ከርሱ ዘንድ መልካም መመለሻ አለው። በላቸው - ከነኝህ የዚህች ዓለም ፀጋዎች የተሻለ ነገር ልንገራችሁ? ለክቢያ አላህን ለሚፈሩ ወገኖች ከሥሮቿ ወንዞች የሚፈሱባቸውና ከውስጣቸው ንጹሐን እንስት ጓደኞች ያሏቸው ጎኑቶች ከጌታቸው ዘንድ ተዘጋጅቶላቸዋል። ከዚሁ ጋር የአላህን እርካታ ይጐናፀፋሉ። አላህ ባሮቹን ዐዋቂ ነው» (አሊ ዒምራን 14- 15)

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«ከኔ ሕልፈት በኋላ ለወንድ ልጅ ከሴት የበለጠ ፈተና አልተውኩም።» (ቡኻሪ)

ከላይ የሰፈረው አንቀጽ እንዳወሳው ከወንድ ልጅ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ከሆነ ስጋዊ ፍላጎቶች መካከል የመጀመሪያውና ዋነኛው እንስት ናት።

ሐዲሱ ደግሞ ከፈተናዎች ሁሉ ከባዱ እንስት መሆኗን ያወሳል። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

«ዱንያ ጣፋጭ ነገር ናት። አላህ የምትሰሩትን ለማየት በርሷ ውስጥ ወኪል አድርጓችኋል። ዱንያን ተጠንቀቁ። ሴትንም ተጠንቀቁ። የበኒ እስራኤል የመጀመሪያ ፈተና ሴት ነበረች።» (ሙስሊም)

ወጣቶች ሆይ፣ እንስት የወንድን ሐሳብ የምትበትን፣ ድህነቱን ከአይኖቹ መከከል የምታደርግ ከባድ ፈተና እንደምታደርስም ጥርጥር የለውም። ናት። ወደማያምር ፍጻሜ

«የእደምን ልጆች ዘና ተርክላቸው።»

ተገቢውን ትምህርት አገኘን?

ትኩረት የተቸሩ ሁለት ነጥቦች

ኢብሊስ እደምንና ሐዋእን ከጅነት ለማስወጣት በተከተለው ስልት ሐፍረተገላቸውን ከመግለጥ እና ከማራቆት ላይ ማተኮሩ ይታወሳል፣ አላህ እንዲህ ብሏል፦

فَوَسْوَسَ لَهُمَا الشَّيْطَانُ لِيُبْدِيَ هُمَا مَا وُرِيَ عَنْهُمَا مِن سَوْءَاتِهِمَا) الأعراف: ٢٠

«ሰይጣንም ጐተጐታቸው ዕፍረተ ገላቸውን ሊያጋልጣቸው:: ጌታችሁ ይህችን ዛፍ እንዳትመገቡ የከለከላችሁ መላእክት እንዳትሆኑ ወይም ዘንተ ዓለም ከሚኖሩት መሆን እንዳትችሉ ነው:: አላቸው። (አል አዕራፍ 20)

በመቀጠልም ከሌላ ፈተና ላይ አተኮረ። እርሱም የእንስት ፈተና ነው። ይህም በመሆኑ ወጣቱ የእንስት ፎቶ በማየት፣ የነርሱን የተራቆተ ገላ በማነፍነፍ ይጠመዳል። ይህ ሲሆን በሁሉቱም ዳታዎች ላይ ውድቀት ይከተላል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

ግንኙ ዓለም ከሚኖሩት መሆን እንዳትችሉ ነው::" አላቸው» (አል አዕራፍ 20)

በመቀጠልም ከሌላ ፈተና ላይ አተኮረ:: እርሱም የእንስት ፈተና ነው:: ይህም በመሆኑ ወጣቱ የእንስት ፎቶ በማየት፥ የነርሱን የተራቆተ ገላ በማነፍነፍ ይጠመዳል:: ይህ ሲሆን በሁለቱም ጾታዎች ላይ ውድቀት ይከተላል:: አላህ እንዲህ ብሏል፦

الْفَقْرَ وَيَأْمُرُكُم بِالْفَحْشَاءِ وَاللَّهُ يَعِدُكُم مَّغْفِرَةً مِّنْهُ وَفَضْلاً وَاللَّهُ وَاسِعٌ عَلِيمٌ) البقرة: الشَّيْطَانُ يَعِدُكُمُ ٢٦٨)

«ሰይጣን (ገንዘባችሁን ለዘካ ብትለግሱ ድህነት እንደሚያገኛችሁ በመግለጽ ያስፈራራችኋል። በመጥፎ ነገሮች ያዛችኋልም:: በእንጻፋ አላህ ከርሱ የሆነን ምሕረትና ትሩፋት ቃል ይገባላችኋል። አላህ ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነው» (አል በቀራህ 268)

ወጣት ወንድሜ ሆይ፥ የቱን ትመርጣለህ? ከሰይጣን ጋር በመኝዳኘት ይህችን ዓለም በድህነት፥ አቪራህንም ደግሞ በብልግና (ፋህሻ) ማጣትን ወይስ ወደ አላህ ተመልሰህ ዱንያንም አቪራንም በምህረቱና በችሮታው ማትረፍን?

አምላኩን ችላ ያለ ወዮለት:: ድርጊቱ ያሳዝናል:: ጥፋቱ ያሳዝናል:: ኪሣራው ያሳዝናል:: ሚስኪን!

የአያም ልጆች ታሪክ፡- «ጊዘሙ ከማለፉ በፊት» በማለት በከፍተኛ ድምጽ ያስጠነቅቃል:: ሐራምና ሹብሐ ሽሕዋዎች የሚያስከትሉትን አደጋ የሚገልጽ ዘልዓለማዊ መልእክትም ይዟል::

<u>የእንስት ፈተና መገለጫዎች</u>

<u>አንደኛ፡- ፍላጻውን ተጠንቀቅ።</u>

ነቢዩ በሐዲሰል ቁድስ እንደገለጹት አላህ እንዲህ ብሏል፡- «አይታ ከኢብሊስ ፍላጻዎች መካከል አንዱ ነው።» (ሐኪም)

አዎ፣ ቀልብን የሚመታ፣ አማንን የሚያላሽቅ ፍላጻ ነው። ፍላጻ ምን እንደሚያደርግ ታውቃለህ? ያቁስላል። ለሞት አደጋ ከሚዳርግ ቦታ ላይ ሊወጋ ይችላል። የተመረዘ ከሆነ ደግሞ ገዳይነቱ ጥርጥር የለውም።

ወጣቱ አላህን ለመገዛት ወስኖ ከቤቱ ይወጣል። ከቆይታ በኋላ ግን ቀልቡ ይቀየራል። ለምን? አይታውን በየአቅጣጫው ያለ ገደብ ለቆታላ! እናም ሸህዋ በረታበት። የማየገኘውን ነገር አይቷልና ውስጡ በስቃይ ተቀጣ። ሰይጣን አላገጠበት። በሕጻን ልጅ አማር እንዳለች ኳስ ተጫወተበት።

ሁለተኛ፦ መግናኛ ብዙሐንስ?

የብልግና ድረ ገጾችን ማየትም ተመሳሳይ ውጤት ያስከትላል። ተጽእኖው ፈጣን ነው። ወደ ቀልብ በብርሃን ፍጥነት ይደርሳል። ውጉም በጣም ይጎዳል። የብልግና ቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ማየትም እንደዚሁ። አንዳንድ ሰዎች ቀኑን ሙሉ ብልግና ሲያዩ ይውላሉ። ይህ ፈተና ቃቢልን የአላህን ሕግ እንዲጥስ፣ በመጨረሻም የወንድሙን ደም እንዲያፈስ ገፋፍቶታል። ይህን ዓይነቱን አይታ ለመቋቋም ሙከራ ያደረግንበት ጊዜ አለን? እንስት አላያም፣ የብልግና ድረ ገጾችና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን አላይም በማለት ወስነህ፣ ተግባሩንም ሞክረህው ታውቃለህን?

ወጣቶች ሆይ፣ እስኪ ዛሬውኑ እንሞክረው። ትልቅ የጀግንነት መለያ ነው።

ሦስተኛ፦ ቴሌፎን?

በወጣት ተቃራኒ ጾታዎች መካከል የሚደረግ የስልክ ውይይትም እንደዚሁ ነው። ልጅት በስልክ የምታወራውን አባቷ ቢሰማ በሐፍረት ትሸማቀቃለች። ወንድም ድርጊቱን አባቱ ቢያውቅበት የሚገባበት ያጣ ነበር። ግና ማንም እንደማይሰማቸው ስለሚያውቁ ለጆሮ የሚከብድ ወሬ ያወራሉ። አላህ እንደሚያያቸውና እንደሚሰማቸው ዘነጉን?

አራተኛ፡- እርቃን አለባበስ

ሂጃብ ያላደረጉች፣ ግና ሳይናፋርና አደበኛ፣ አለባበሷም ስርዓት ያለው እንስት ልታገኝ ትችላለህ። ይህች ከጊዜ በኋላ ሙሉ ሂጃብ ትለብሳለች። በጣም አደገኛዋ ግን የሰውነቷን ቅርጽ አንድ በአንድ የሚያሳዩና የሚያስቀጥር ልብስ የምትለብሰው እንስት ናት። እርቃን ከሆነች እንስት አትለይም። ወይም ደግሞ የአካሏን የተወሰነ ክፍል አራቁታ ሌላው የሸፈነች እንስት ታጋጥምሐለች። ነቢዩ እነዚህን በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፡-

«ከተከታዮቼ ውስጥ ጀነት የማይገቡ፣ ሽታዋን እንኳ የማያገኙ እንስቶች አልሉ፡ ሽታዋ ከአምስት መቶ አመታት ርቀት ላይ የሚያውድ ቢሆንም እንኳ።»

የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እነዚህ እንስቶች እነማን ናቸው? የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው። እንዲህ የሚል መልስ ሰጡ፡-

«ለብሰው ግን እርቃናቸውን የሆኑ፣ ተሳስተው የሚያሳስቱ፣ ራሳቸውን እንደ ግመል ሻኛ የቆለለ እንስቶች ናቸው።» (ሙስሊም)

አምስተኛ፡- የሚያጋጥም ግድፈት

ለጋብቻ የተጫጨ ወጣቶች አላህን እንዲፈሩ እመክራቸዋለሁ። አላህ ጋብቻቸውን ይባርክላቸው ዘንድ ይህን ያድርጉ። ምክንያቱም በአጮኛነት ዘመን በርካታ ወንጀሎች ይፈጸማሉ። በአጮኛሞች መካከል በተከሰተ የሐራም ድርጊት ምክንያት ጋብቻቸው የቀረ ብዙ ወጣቶችን እናገኛለን። የጋብቻ ሕይወቱን ቀጣይ ማድረግ የፈለገ ከጅምሩ ላይ አላህን ይፍራ። የአጮኛነት ዘመንን ግድፈት ይጠንቀቅ። አንድን ነገር ጊዜው ከመድረሱ በፊት ለማግኘት የሞከረ፣ እርሱን በማጣት ይቀጣል።

ስድስተኛ፡- የቁያማ ምልክት

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«ሌሊት በሕልሜ ሁለት (መላእክት) መጡ፦ «እንሂድ። አሉኝም። አብሪያቸው ሄድኩ። ጨዝት ወዳለው ምድኛ ወሰዳኝ። ወደ ውስጡ ተመለከትን። እርቃናቸውን የሆኑ ሴቶችና ወንዶች አየን። ነበልባል ከስር በኩል እየተነሳ ይገርፋቸዋል። እነዚህ እነማን ናቸው? በማለት ስጠይቅ ዝሙተኞች ናቸው ተባልኩ።» (ኢማም አህመድ)

ዝሙት መስፋፋቱ ከባድ ፈተና ነው። የቂያማ ምልክትም ነው። ቅጣቱም ብርቱ ነው። ስለሆነም ከዚህ ወንጀል ላይ ላለመውደቅ ቁርጥ ውሳኔ አድርግ። ኢብሊስ እንዳየሳንፍህ በርታ። ከወንጀሉ ላይ የወደቀ ሰውም ይቶቢት። በጎ ስራም ያብዛ።

አንድ ሰው ከነቢዩ ዘንድ መጣና፦ «ባእድ እንስት ሳምኩ።» አላቸው። ፊታቸውን አዞሩበት። ወዲያውም ተከታዩ የቁርአን አንቀጽ ወረደ፦

وَأَقِمِ الصَّلوةَ طَرَفَيِ النَّهَارِ وَزُلَفًا مِنَ الَّيْلِ إِنَّ الحَسَنَتِ يُذْهِبْنَ السَّيِّئَتِ ذَلِكَ ذِكْرَى

«ሶላትንም በቀን ጫፎች ከሌሊቱም በተወሰነ ክፍል ደንቡን አሟልተህ ስገድ መልክም ሥራዎች ኃጢአቶችን ያብሳሉና። ይህ (መልዕክት) ለአስተዋሾች ማስታወሻ ነው።» (ሁድ ፲፬)

<u>ሰባተኛ፦ በነቢዩ ዘመን የተከሰተ</u>

አርቃን የሰበሱ እንስቶች ፈተና፣ መንገድ ላይ ለእንስት ምልከታ መጋለጥ። በነቢዩ ዘመን የተከሰተ አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ። አንድ ልብከ ለመስለምና ከነቢዩ ጋር ቃል ኪዳን (በይዓ) ለመጋባት ወደርሳቸው ይመጣል። ከመካከላቸው አንድ ወጣት አለ። መንገድ ላይ እንስት ያይና ይጎትታታል። ልብኩ ከነቢዩ ዘንድ ደረሰ። አንድ በአንድ እጃቸውን እየየዙ ቃል ተጋቡ። የወጣቱ ተራ ሲደርስ፦ እንስት ጎታች አይደለህምን?› አሉት። ዝም አለ። ካንተ ጋር ቃል አልጋባም› አሉት። ‹በአላህ እምላለሁ፥ ዳግም ይህን ተግባር አልፈጽምም› አላቸው። እጃቸውን ዘረጉለትና ቃል ተጋቡ። (ሐኪም)

እየያዙ ቃል ተጋቡ። የወጣቱ ተራ ሲደርስ፦ እንስት ጎታች አይደለህምን? አሉት። ዝም አለ። ካንተ ጋር ቃል አልጋባም» አሉት። በአላህ እምላለሁ፥ ዳግም ይህን ተግባር አልፈጽምም» አላቸው፥ እጃቸውን ዘረጉለትና ቃል ተጋቡ። (ሐኪም)

ወጣቶች ሆይ፥ ይህ ልጅ የነቢዩን ቁጣና ከርሱ መሸሻቸውን በጣም ፈራ። ተውባ ለማድረግም ከልቡ ወሰነ። በእለተ ቂያማ የነቢዩ መቆጣትና ከርሱ መሸሽ የማያስበው ሰው ከመከከላችን እንዳይኖር እሰጋለሁ።

<u>ሰምንተኛ፦ እንዴት ትቀበያለሽ</u>

ሴት ልጅ ባእድ ወንድ እንዳቀርባትና ያሻውን ሐራም እንዲሰራባት መፍቀዷ ወይም ደግሞ አካሏን አይኖች እንዳሻቸው እንዲሰበኙት ማድረጓ የፈተና አንድ ገጽታ ነው። ሐያእ የት ደረሰ? አንድ ቀን አማም አህመድ በመንገድ በመጓዝ ላይ አያሉ ነፋሱ የአንዲትን እንስት ቀሚስ ገለጸው። ተረከዟና ከፊል ባቷ ተጋለጠ። አማሙ ፊታቸውን በልብሳቸው ሸፈኑና፦ «ይህ የፈተና ዘመን ነው። አሉ። እኔህ ሰው በኛ ዘመን ከመከከላችን በርኖ ኖሮ ምን ይሉ ነበር!

<u>ዘጠነኛ፦ የባል (ሚስት) መባለግ</u>

አንድ ሰው ከነቢዩ ዘንድ መጣና «ዩአላህ መልእክተኛ ሆይ፥ ከአላህ ዘንድ ትልቁ ወንጀል ምንድን ነው?› ሲል ጠየቃቸው። «አላህ የፈጠረህ ሆኖ እያለ ለርሱ ተጋሪ ማድረግህ» አሉት። «ከዚህ ቀጥሎስ?» አላቸው። «ልጅህን ከእንተ ጋር አብሮ እንዳይመገብ በመስጋት መግደልህ» አሉት። «ከዚህ ቀጥሎስ?» አላቸው። «ከጎረቤትህ ሚስት ጋር ዝሙት መፈጸምህ» አሉት። (ቡኻሪና ሙስሊም)

የባልና የሚስት መባለግ ከባድ ፈተና ነው። ሰይጣን ከቃቤል ዘመን እንስቶ ምን ያህል እንደተጫወተብን ያሳያል።

<u>መፍትሄ ልስጣችሁ</u>

<u>አንደኛ፦ አይታን መቆጣጠር</u>

ወጣቶች ሆይ፥ ዐይንን መስበር፥ አይታን መቆጣጠር የሚድ ነው። አላገባሁም የሚለው ምክንያት አይሰራም። መሞከር ግድ ይላል።

አንድ ወጣት አውቃለሁ፡፡ ከቢቱ ከመውጣቱ በፊት አይታውን ለመቆጣጠርና ለይጣንን ለማሸነፍ ወሰነ፡፡ «ያሸንፈኛል ወይም አሸንፈዋለሁ።» አለ፡፡ በቀጣዩ ቀን የጥረቱን ስታስቲክሳዊ ውጤት አነኝ። 12 ጊዜ ዓይኑን ከሐራም መልሷል፡፡ 10 ጊዜ ደግሞ አልመለሰም፡ ተቀመጠና ለእያንዳንዱ ያልተፈቀደ አይታው 10 ጊዜ ኢስቲግፋር አደረገ፡፡ ከዚህ በፊት ያወሳሁትን ሐዲስል ቁድስ በድጋሚ አጠቅስላቸኋለሁ። የሐዲስንም ቀሪ ክፍል እምላላቸኋለሁ፡፡

“እይታ የኢብሊስ የተመረዘ ፍላጻ ነው። እኔን ፈርቶ እይታውን የሰበረ በእግን አለውጥለታለሁ። ለዛውንም ከቀልቡ ውስጥ ያገኛል (ዘጋቢዎቹ ከአሁን በፊት ተጠቅሰዋል)

ወጣቶች ሆይ፥ አይታን መቆጣጠርን ለሳምንት ያህል ሞክሩት። ለዛውን ከቀልባችሁ ውስጥ በእርግጥ ታገኙታላችሁ። አላህ ቃል ገብቶላችኋል።

<u>ሁለተኛ፡- በሮችን ዝጋ</u>

ቀልብ በርካታ በሮች እንዳሉት ቤት ማለት ነው። ሰውየው በሮችንም መስኮቶችንም ከፍቶ ከተዋቸው ሌባ ይገባበታል። ስለዚህም የራትና በሮችን እወቁና ዝጓቸው። ከፈተና ትድናላችሁ፡-

⇨ መጥፎ ጓደኛ ካለህ ከርሱ ጋር ያለህን ግንኙነት አቋርጥ፣
⇨መጥፎ ጓደኛ ካለችሽ ግንኙነትሽን አቋርጭ፣
⇨ ከኢንተርኔት የብልግና ገጾችን ተከልከል፣
⇨ ፈተና የሚያመጣብህን ስልክ ቁጥር ሁሉ ከቴሌፎን መዝገብህ አጥፋ።

ወጣቶች ሆይ፥ አሁኑኑ ተግባር እንጀምር። ነፍሳችን በኸይርና ለኸይር እስኪረጋ ድረስ እንሞክር። አላህ እንዲህ ሲል እውነትን ተናግሯል፡-

<u>ሦስተኛ፦ ጾም</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል።

«ወጣቶች ሆይ፥ ከመካከላችሁ የማግባት አቅም ያለው ያግባ። ያልቻለ ይጹም። እርሱ ጠባቂ ነውና።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

ወንጀል ከፈራችሁ ሰኞና ሐሙስ እንዲሁም ከየወሩ ሦስት ቀናት ጹሙ፤ ፡ ወንጀልን ለመቋቋም ከፈለጋችሁ ጾም አብዙ። የዳውድን ጾም ጹሙ። ከአላህ ዘንድ ተወዳጁ ጾም እርሱ ነው። ዳውድ አንድ ቀን ይጾሙ፥ አንድ ቀን ያፈጥሩ ነበር።

ጾም በሰው ልጅ የደም ኡደት ውስጥ የሰይጣንን ያጠበበታል። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦መዘዋወሪያ

«ሰይጣን በሰው ልጅ የደም ስር ውስጥ ይዘዋወራል።»

በሉ ጎበዝ፥ አሁኑኑ ተነሱ። የሰይጣንን መንገድ በረሃብና በጥማት እናጥብብ። ጾም ጠንካራ ጋሻ ነው።

<u>አራተኛ፦ ምንጣፍውን ማወቅ</u>

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል።

«ከርሱ ጥላ ውጭ ሌላ ጥላ በማይኖርበት ቀን አላህ ሰባት ሰዎችን ከጥላው ስር ያስጠልላቸዋል።» አሉ። ከነርሱ ውስጥ ከብርና ውበት ያላት ሴት ለዝሙት ጋብዛው «አላህን እፈራለሁ» ያላት ወንድ አንዱ መሆኑን ጠቀሱ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

⇨ ሐራም ግንኙነትን ያቋረጠ ወንድ ከዓርሽ ጥላ ስር ይሆናል፡

⇨ሐራም ግንኙነቷን ያቋረጠች ሴት ከዓርሽ ጥላ ስር ትሆናለች።

⇨አላህን በመፍራት ከሐራም እይታ ራሱን ያቀበ ከዓርሽ ጥላ ስር ይሆናል።

ይህን ምንዳ ለማግኘት የሚሻ ማን ነው? አላህ ጀነት ውስጥ፦ በሩቁ የታዘዙኝና የተገዙኝ እነማን ናቸው?" በማለት ሲጠይቅ እጅህን

አውጥተህ እንዲህ በማለት በመመላስ ልታገኘው የምትችለውን ወሰን የለሽ ደስታ በምናብህ አስብ፡-

«አምላኬ ሆይ፣ እኔ በሩቅ ታገለኸሃለሁ። ፊትና የሚያመጡ የቴሌፎን

ቁጥሮቼን ሰርጎለሁ። መገነቢን ቀድሻለሁ። አምላኬ ሆይ፣ ይህን ይህን ወንጀል ትቻለሁ።» ወጣቶች ሆይ፣ የምንዳውን ግዝፈት አስቡና ለርሱ ተገቢውን ዋጋ ከፈሉ።

<u>አምስተኛ፡- ወደ ጌታችሁ ምህረት ፍጠኑ</u>

ከእንስት ፈተና ለመጠበቅ ሌላው መንገድ ፈጥኖ መቶበት ነው። ከወንጀል የተጸጸተና ለመተው የወሰነ ወንጀል እንዳልፈጸመ ይቆጠራል። ዋናው ነገር ተውበትን አለማዘግየት ነው። እድሚያችን በእጃችን አይደለም። የአላህ እዝነት ሰፊ ነው። እጅግ በጣም ሰፊ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَرَحْمَتِي وَسِعَتْ كُلَّ شَيْءٍ فَسَأَكْتُبُهَا لِلَّذِينَ يَتَّقُونَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَوٰةَ وَالَّذِينَ هُم بِـَٔايَـٰتِنَا يُؤْمِنُونَ

«ግና እዝነቴ ሁሉንም ነገር ያካትታል። ለነዚያ ጌታቸውን ለሚፈሩትና ዘካንም ለሚሰጡት ለነዚያም በእንቀጾቻችን ለሚያምኑት አውለዋለሁ አለ። (አልአዕራፍ156)

<u>ስድስተኛ፡- ካንተ የቀደመ አለ</u>

ለፈተና በተጋለጥክ ቁጥር አንድ ወጣት አስታውስ። ወንደ ላጤ ነው። ቆንጆና ባይተዋርም ነው። በሩቅ አገር የሚኖር። አሳዳሪው በሯን ዘግታ ለዝሙት ጋበዘችው። እርሱ ግን በአላህ ተጠበቀ። የሱፍ ይባላል።

⇨"ጓደኞችህ ይህን ያደርጋሉ። ስለዚህ ከነርሱ አትለይ። አንተ ከማን ትበልጣለህ?» በማለት ሰይጣን አያታልልህ።

⇨"ጓደኛሽ አነሌን ተዋውቃ፣ በጓደኝነት ተያይዘዋል። አንችም እንደርሷ የወንድ ጓደኛ ይኑርሽ።» በማለት ሰይጣን አያታልልሽ

ወጣቶች ሆይ፣ ኢብሊስ ሊፈትናችሁ በመጣ ቁጥር ሦስት ድንጋዮች ወርውሩና አባሩት። ምታችሁ ያቃጥለዋል። ነቢያላህ ዩሱፍ በነርሱ መትተው ሰባብረውታል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَرَ‌ٰوَدَتْهُ الَّتِي هُوَ فِي بَيْتِهَا عَن نَّفْسِهِ، وَغَلَّقَتِ الْأَبْوَابَ وَقَالَتْ هَيْتَ لَكَ قَالَ معاذ اللهِ إِنَّهُ رَ‌بِّي أَحْسَنَ مَثْوَايَ إِنَّهُ لَا يُفْلِحُ الظَّالِمُونَ يوسف: ٢٣

«የሚኖርበት ቤት ባለቤትም ይገናኙት ዘንድ ፈለጎች እናም በራፎችን ሁሉ ዘጋች። አሁን ና አለችውም። በአላህ አጠበቃለሁ በእውነቱ (ባለ ቤትሽ አሳዳሪዬ ነው። መሥሪያየንም መልክም አድርጐልኛል፡ ሚስቱን ደፍሬ ልበድለው አልሻም። እነሆ፣ በዳዮች አይድኑምና፡ አለ። (ዩሱፍ 23)

<u>አንተም እንደዚሁ ሁን</u>

ኡበይድ ቢን ኡበይድ የተባለ ወጣት ነበር። አላህን በመፍራት እና በበጎ ስራ ይታወቃል። በርሱ ዘመን እጅግ በጣም የተዋበች እንስት ነበረች። ራሷን በመስታወት እየችና ይህን ውበት መቋቋም የሚችል ማን አለ፡ ስትል አሰበች። ባሏም፡- ኡበይድ ቢን ዑበይድ ይቋቋመዋል አላት። ‹እንድፈትነው ፍቀድልኝ› አለቸው። ‹ፈቀደለት› ወደርሱ ሄደችና፡- «ጥየቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ» አለችው። ፊቷንም ታሳየው ጀመር። ዓይኑን ከርሷ አሸሸ። በመጨረሻም ከርሱ ጋር መተዋወቅና ይገናኛት

ዘንድ እንደምትፈልግ በግልጽ ቋንቋ ነገረችው። «አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ፡ ፡ እርሱን በእውነት ከመለስሽልኝ የፈለግሽውን አደርግልሻለሁ።» አላት። «የፈለግከውን ጠይቅ። በእውነት እመልስልሐለሁ» አለችው። እንዲህ አላት፡-

«በዚህ ወንጀል ላይ እያለሽ የሞት መላእክት ነፍስሽን ለማውጣት ቢመጣ ትፈልጊያለሽን?»

«አልፈልግም።»

«በእለተ ቂያማ ሰዎች ሁሉ የስራ መገዘባቸውን በቀኝ እጃቸው ሲቀበሉ አንች በዚህ ወንጀልሽ ሰበብ በግራ እጅሽ መቀበል ያስደስትሻልን?» «አያስደስተኝም›

«በእለተ ቂያማ በጀሃነም ጀርባ ላይ ሲራጥ ተዘርግቶ ሰዎች እያለፉት ሲጄዱ አንች በዚህች ወንጀልሽ ሰበብ ጀሃነም ውስጥ መውደቅ ትሻለሽን?»

«አልሻም»

ከአላህ ፊት ስትቆሚ ስለዚህ ወንጀል ሲጠይቅሽ «አዎ፣ ሰርቻለሁ» ማለት ያስደስትሻልን?

«በፍጹም»

ይህ አይበቃሽምን? አላት። ‹‹ይበቃኛል። በአላህ እምላለሁ፣ ወደርሱ በተውባ ተመልሻለሁ።› አለች። ከዚህች ቀን በኋላም ጥሩ ዓቢድና መልካም ሰው ሆነች።

ይህ ጀግንነት፣ ወንጀልን የመቋቋም ታላቅነት፣ እርሱን ከሐራም በመጠበቅ ብቻ አልተወሰነም። ልትፈትነው የመጣችውን እንስት ከፉ ስሜት ሰባብሮ በጎ ጎኗ እንዲያይል አድርጓል። ከፋትን ከስሩ _ ነቅሎ በመጣል ተፈጥሯዊ ንጽህናዋን አግዝፎታል። ወደ አምላኳም መልሷታል።

ተጠያቂው ማን ነው?

ወደ ጀመርነው ታሪክ እንመለስ። ለተፈጸመው ሚድያ ተጠያቂው ማን ነው? ቃቢል ወይስ አሁቱ? ይህን ጥያቄ ያሳነው ያለ ምክንያት አይደለም። የአይሁድ አፈታሪኮች የቃቢልን አህት ተጠያቂ ስለሚያደርጉ ነው። ሐዋእን ለአደም ወንጀል፣ ወደ ምድር ለመውረዱና ከጀነት ለመውጣቱ ተጠያቂ እንዳደረጓት ማለት ነው። ይህ አስተሳሰብ በአርሜጣ ስህተት ነው። ምክንያቱም ቁርአን ለሚድያው ተጠያቂ ያደረገው ቃቢልን ብቻ ነውና።

እንስት ለወንድ መፈተን ተጠያቂ የምትሆነው መቼ ነው? ራሷን በማራቆት፣ ሂጃብ በመተው፣ ሽቶ በመቀባት፣ የወሲብ ቅላጼ ባለው አነጋገርና አረማመድ ያላሰበውን ስታሳስበው፣ ሰይጣንም እያታለለ እና እየሸነገለ የወንዶችን የወሲብ ስሜት እንድታቀጣጥል ሲጠቀምባት፣ ያኔ ለርሱ ጥፋት እርሷም የወንጀሉ ተጋሪ ትሆናለች።

አንድ ሰው በወድ ዋጋ የገዛውን ስጋ ጠረነ ተቀይሮ ለምግብነት የማይበጅ ካልሆነ በቀር በቀላሉ አውጥቶ አይወረውረውም። ሲበላሽ ግን ይጥለዋል። ሌሎች ሰዎችም አያነሱትም። ይጠሉታል። የሚቀርበው ‹አንትን› ብቻ ነው።

⇨ አላህ ጠብቆሽ እያለ ራስሽን እንዲህ ማርከስ ትሻለሽን?
⇨አላህ አልቆሽ እያለ እንዲህ መዋረድ ትከጅያለሽን?

ግንኙነቱ ምንድን ነው?

አላህ እንዲህ ብሏል።

وَاتْلُ عَلَيْهِمْ نَبَأَ ابْنَيْ ءادَمَ بِالْحَقِّ (المائدة ››

“የሁለቱን የአደም ልጆች እውነተኛ ታሪክም ተርክላቸው”(አል ማኢዳህ 27)

ይህ አንቀጽ ከርሱ በፊት የነበሩ አናቅጽ ካስተላለፉት መልእክት ጋር ትስስር እንዳለው አወቃቀሩ ያመለክታል። በአንቀጹ ውስጥ ‹ው› የሚለው መወጠኛ ፊደል ይህንን ትስስር የሚያሳይ ነው። ከርሱ በፊት የሰፈሩ አናቅጽ የተረኩት መልእክት ስለ ሙሳ ነው። እሳቸው ሕዝባቸውን ወደተቀደሰችው ምድር እንዲገባ ሲያዙና ሕዝበም ሲፈራ ይተርካሉ። በዚህ ታሪክና በአደም ልጆች ታሪክ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? አላህ ለምን በወ ፊደል አስተሳሰሮ አቀረባቸው? ግንኙነቱ እንዲህ ነው። የሙሳ ወገኖች ለመጋደል ፈሩ። ቃቢል ደግሞ ሟድያን ያለ አግባብ ተዳፈረ። ሁለቱም ማለትም ፍርሃትም ያለ አግባብ መዳፈርም ወንጀሎች መሆናቸውን አላህ መጠቆሙ ነው። አግባብ የሆነን ጀግንነት አላህ አያበረታታን ይመስላል።

እጅግ ጠቃሚ መልእክት

አላህ በዚያው ምእራፍ ውስጥ ሙሣ እንዲህ ማለታቸውን ተርኮልናል፦

قَالَ رَبِّ إِنِّي لَا أَمْلِكُ إِلَّا نَفْسِي وَأَخِي فَافْرُقْ بَيْنَنَا وَبَيْنَ الْقَوْمِ الْفَاسِقِينَ

«(ሙሳም) ጌታዬ ሆይ! ከራሴና ከወንድሜ ውጭ ማንንም ማዘዝ (ማስገደድ) አልችልም። ስለሆነም በኛና በዚህ አመፀኛ ሕዝብ መካከል ለይ" አለ።(አል ማኢዳህ25)

ሙሣ ለወንድማቸው ለሐሩን ምን ያህል ይሰስቱ እንደነበር አስተውል። ይህን እውነታ ከጥቂት አናቅጽ በኋላ ከተተረከውና ወንድሙን ‹ሕገደልሐለሁ› በማለት ከዛተው የቃቢል ባህሪ ጋር አነጻጽረው።

ወጣቶች ሆይ፤ ወንድማማችነት ከአላህ የሆነ ጸጋ ነው። ወንድም ያለው ሰው ወንድምነቱን ከሰይጣን ተንኮል ይጠብቀው። ከወንድሙ ጋር ኢስላማዊ ወንድማማችነት ያስተሳሰረው ሰው ትስስሩን ከከንቱ ስሜት ይከላከለው።
አንድነት ሐይል፣ መለያየት ደግሞ መርገምት መሆኑን ልብ ይሏል።

<u>የምቀኝነት ውጤት</u>

አላህ እንዲህ ብሏል፦

وَاتْلُ عَلَيْهِمْ نَبَأَ ابْنَيْ ءَادَمَ بِالْحَقِّ إِذْ قَرَّبَا قُرْبَانًا فَتُقُبِّلَ مِنْ أَحَدِهِمَا وَلَمْ يُتَقَبَّلْ مِنَ الْآخَرِ قَالَ لَأَقْتُلَنَّكَ قَالَ إِنَّمَا يَتَقَبَّلُ اللَّهُ مِنَ الْمُتَّقِينَ)

«የሁለቱን የአደም ልጆች እውነተኛ ታሪክም ተርክላቸው (ለአላህ) ቁርባን ባቀረቡና (አርሱም) የአንደኛውን ተቀብሎ የሌላኛውን ሳይቀበል በቀረ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ) ቁርባኑ ተቀባይነት ያላገኘው) - አገድልሃለሁ አለው ወንድምየውም አላህ የሚቀበለው እርሱን የሚፈሩትን (ሰዎች ቁርባን ነው) አለው (አል ማኢዳህ 27)

«እገድልሐለሁ» የሚለው የዛቻ ቃል በቃቤል ልቦና ውስጥ የምቀኝነት እሳት መቀጣጠሉን ያመለክታል። ወንድሙን ለመግደል ያቢቃውም ይህ ነው። ምቀኝነት በምድር ላይ የተፈጸመው የመጀመሪያው ሐጢአት ነው። ከዚህ ወንጀል በፊት የተፈጸሙ ሐጢአቶችን በቅደም ተከተል እናስቀምጥ፦

1) ኩራት
2) አደምንና ሐዋአን የተከለከለችውን ዛፍ እንዲበሉ ማነሳሳት
3) የሐሰት መሐላ
4) የእንስት ፈተና
5) ምቀኝነት

የሁሉም ሰበብ በራሱ ወይም በእንስት የተፈተነን ሰው የሚያጠቃ የቀልብ በሽታ ነው። የቀልብ ወንጀሎች ከእነዚህ ወንጀሎች የበለጠ ያጠፋሉ።

<u>ምንዳን ይበላል</u>

ምቀኝነት እና ጥላቻ በተሸከሚዎቻቸው ምልከታቸው የሚታይ በሽታዎች ናቸው።

ይህች እንስት ያችኛዋን መልክም ባል ስላላት፥ የትዳር ሕይወታ ስላማረ፥ ጋብቻዋ ስለሰመረ ትመቀኛታለች።

ይህ ያኛውን በመስሪያ ቤት እድገት ስላገኘ ይመቀኘዋል። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

«ምቀኝነትን ተጠንቀቁ። እሳት እንጨትን እንደሚበላው ሁሉ ምቀኝነትም የመልክም ስራን ምንዳ ይበላል።» (አቡ ዳውድ)

«ሁለት ነገሮች በሙስሊም ቀልብ ውስጥ በአንድ ላይ አይቀመጡም። ኢማንና ምቀኝነት።» (አቡ ዳውድ)

ምቀኝነት የበጎ ስራ ምንዳን መብላት ብቻ ሳይሆን ኢማንን ከቀልብ ያጠፋል። ሰውየውም በኢብሊስ እጅ የሚገኝ አሻንጉሊት ይሆናል።

<u>ሕክምናው</u>

አንዳንዶቻችን እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ማሕበራዊ ቀውስ ውስጥ ለማለፍ እንገደዳለን። ምክንያቱም ምቀኝነት እንደሆነ እንገምታለን። መፍትሄም እንሻለን። የምቀኝነትን ሕክምና ቀጥሎ ዘርዝረናል፦

1)ሙዐዊዘተይን"[37]መቅራት።
2)የጠዋትና የማታ ዚክሮች
3)አላህን መፍራትና ከወንጀል መታቀብ። አላህ እንዲህ ብሏል፦

وَمَا أَصَابَكَ مِن سَيِّئَةٍ فَمِن نَّفْسِكَ * النصر

«ከክፉ ነገር ያገኘህም በራስህ (ጥፋት የተከሰተ ነው። (አል ኒሣእ 79)

ወንጀልን መተው ከሒስድ ለመጠበቅ ጠቃሚ መንገድ ነው።

4)በአላህ መመካት። አላህ እንዲህ ብሏል፦

37 አል ፈቅና አል ዓስ ምሉፊኖች

وَإِن يَمْسَسْكَ اللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُ إِلَّا هُوَ وَإِن يُرِدْكَ بِخَيْرٍ فَلَا رَادَّ لِفَضْلِهِ

አላህ አንዳች ከፉ ነገር እንዲያገኝህ ቢያደርግ ከአላህ ውጭ የሚያነሳልህ ማንም የለም። መልክም ነገር ቢያቅድልህም ማንም ችሮታውን ማስቀረት አይቻለውም (ዩነስ 107)

5) ሶደቃ መስጠት። በእጅ የሚገኝን የአላህ ጸጋ ለመጠበቅ ከሶደቃ የተሻለ ዘበኛ የለም።
6) ከፉ ለሞሉብህ በጎ መሞል። አላህ እንዲህ ብሏል:-

وَلَا تَسْتَوِي الْحَسَنَةُ وَلَا السَّيِّئَةُ ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ

መልክም ሥራና ከፉ ሥራ ፈጽሞ እኩል አይደሉም። (ሰዎች ባንተ ላይ የሚያደርሱትን በደል) በዚያች መልክም በሆነችው (ምግባርህ) መልስ፡ ያን ጊዜ በአንተና በርሱ መካከል ጥል የነበረበት ሰው ልክ እንደቅርብ ወዳጅህ ይሆናል። (ፉሲለት 34)

ተቀባይነት ከርሷ ጋር የተሳሰረ ነው

አላህ የአቤልን ቁርባን በልታ የቃቤልን ተውችው። ቃቤል በወንድሙ እርሱ ባልፈጸመው ነገር - ተበሳጨ። ተመቀኘውም። በእርግጥ ጥፋቱ

የራሱ የቃቤል ነው። ምክንያቱም የአላህን ሸሪዓ አልተቀበለም። አላህን አልፈራም። ቁርባን ሲያቀርብም አልተጠነቀቀም። ለአላህ የሚያበረክተውን ስጦታ አልመረጠም። ወንድሙ አቤልም ይህን አውነታ አውስቶሊታል።

قَالَ لَأَقْتُلَنَّكَ قَالَ إِنَّمَا يَتَقَبَّلُ اللَّهُ مِنَ الْمُتَّقِينَ) المائدة: ٢٧

«(ቁርባኑ ተቀባይነት ያላገኘው) እገድልሃለሁ አለው።
(ወንድምየው-ም) - አላህ የሚቀበለው እርሱን የሚፈሩትን (ሰዎች ቁርባን ነው" አለው።» (አል ማኢዳህ 27)

ወጣቶች ሆይ፥ አላህ አቤልን እንደተቀበለው እኛንም ይቀበለን ዘንድ አላህን ልንፈራ ይገባል። ተቅዋ ምንድን ነው? ከባለቢቶቹ እንሆን ዘንድ ትርጉሙን ማወቅ ግድ ይለናል። ተቅዋ ማለት ትርጉሙ አላህ ባዘዘህ ቦታ መገኘት እና ከከለከለህ ቦታ አለመገኘት ነው።

*ከአዛን በኋላ ከሰጋጆች ሶፍ ሊያገኝህ ይገባል። ቁርአንን ዘወትር የምታነብ፣ ዝምድናን የምትቀጥል ሆነህ ሊያገኝህ ይገባል።

*ለፈተናው ተጋልጠህ እንዳያገኝህ፣ ያለ አግባብ እየጮህክ፣ የወላጆችህን መብት እየረገጥክ፣ ዝምድናን እየቆረጥክ እንዳያገኝህ።

ወጣቶች ሆይ፥ ከናንተ አንዳችሁ ነገ የተቅዋዬን መጠን መለካት አፈልጋለሁ። አላህ ወዳዘዘኝ ስፍራ እሄዳለሁ። ከከለከለኝ እርቃለሁ» በማለት ተቅዋውን መመዘን ይችላል። ማታ ላይ 80% ተቅዋ አግኝቶ ሊደሰት ይቻለዋል። አላህ የሚቀበለው እርሱን ከሚፈሩት ነው። እንዲህ ብሏል፦

(إِنَّ اللهَ يُحِبُّ الْمُتَّقِينَ

«አላህ የሚፈሩትን ይወዳልና።» (አል ተውባህ 4)

አንድ ታቢዒ ሞት በመጣቸው ጊዜ አለቀሱ። ያን ሁሉ ደግ ስራ የሰሩ ሆነው እያለ ለምን ያለቅሳሉ?» ተብለው ሲጠየቁ፦ «የማለቅሰው፦ አላህ የሚቀበለው እርሱን ከሚፈሩት ነው የሚለውን መልእክት አስታውሺ ነው።» አሉ።

አዎ፣ የስራ ተቀባይነት ከተቅዋ ጋር የተሳሰረ ነው። አላህ ጥሩ ነው። ጥሩን እንጅ አይቀበልም።

<u>እጅን ወዳንተ አልዘረጋም</u>

አቤል ለወንድሙ ሊቃቤል እንዲህ አለው፦

አንተ እኔን ለመግደል እጅህን ብትዘረጋ እኔ አንተን ለመግደል ፊጽም እጄን አልዘረጋብህም እኔ የዓለማት ጌታ አላህን እፈራለሁ (አል ማኢዳህ 28)

ኢብን አባስ እንደተናገሩት አቤል ከቃቤል የበረታ ጉልበት ነበረው። ይህ ከመሆኑ ጋር የወንድሙን ጥቃት በተመሳሳይ መልኩ ለመመለስ እንኳ አልሞከረም።

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

ለገንዘቡ ሲፋለም የሞተ ሸሂድ ነው። ለቤተሰቡ ደህንነት ሲፋለም የሞተ ሸሂድ ነው።» (ሙስሊምና አቡ ዳውድ)

የአቤል ድርቷት አሉታዊ ተደርጎ ሊወሰድ _ ይቸላልን? በፍጹም አይችልም። ምክንያቱም ነገሩ በተለየ ሁኔታና ማእቀፍ ውስጥ የሆነ ነው። ሊገድለው የፈለገው ወንድሙ ነው። _ ጠንካራ የገምድና ወንድማማችነት ያስተሳስራቸዋል። አቤል ይህን ዝምድና ከሚቆርጥ መሞትን መርጧል።

አንቀጹ ዝምድናን የመቀጠል እጅግ አስደናቂ ናሙና እያቀረበልን ነው። በርካታ ዝምድናዎች በገንዘብ ምክንያት ወይም ያለ ምክንያት ተበጥሰዋል።

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦ «ከመሐከላቸው ዝምድናን ቆራጭ ሰው ባለባቸው ሰዎች ላይ የአላህ ሀሙት አትወርድም

«መቀጠል ማለት ብድር መመለስ አይደለም። ዝምድና ቀጣይ የሚባለው

የተቆረጠችውን የሚቀጥል ነው።» (ሙስሊም) አቤል ከወንድሙ ጋር በተያያዘ ያደረገውም ይህንኑ ነው።

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

«ዝምድና በቂያማ ቀን ከሲራጥ ላይ ትንጠለጠልና፦ አምላኪ ሆይ፣ ማንም ሰው የኔን ሐቅ ሳያደርስ እንዳያልፍ አድርገው፣ ትላለች።» ዑስማን ቢን አፋን በመስሊሞች መካከል ውጊያ እንዳይኖር አጥብቀው የተከላከሉት ለዚሁ ይሆናል። ዝምድናቸውን በእርስ በርስ ጥል

እንዳይበጣጥሱት። ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ሲሉ ራሳቸውን ለመስዋእትነት አቀረቡ።

ሁለቱ ሐጢአቶች

አቡል ወንድሙን እንዲህ ሲል አስጠነቀቀው፡-

انني أريد أن تبوأ بإثمي والية فتكون من أصْحَابِ النَّارُ وَذلِكَ جَزَاؤا الظَّالِمِينَ

(ገድዬህ ለቅጣት ከምዳረግ ገድለኸኝ በእኔ ኃጠአት እኔን በመግደልህ በሚመዘንብህ ኃጢአትና) በእንተም ኃጢአት (እኔን ከመግደልህ በፊት በነበረህ ኃጢአት ሳቢያ ከእሳት ሰዎች ብትሆን እመርጣለሁ የበዳዮች የበደል) ዋጋ ይህ ነው" (አለም) (አል ማኢዳህ 29)

***እንደኛ፡- የግድያ ወንጀል**

***ሁለተኛ፡-** የአላህን ሸሪዓ ያለመቀበል ወንጀል ወጣቶች ሆይ! ከእንድ ወንጀል ላይ የወደቀ ሁለት ጥፋቶችን የፈጸመ ያህል ነው። እንደኛው ወንጀል ሐጢአቱን መፈጸሙ ሲሆን፤ ሁለተኛው የአላህን ሸሪዓ አለመቀበሉ ነው። _ ሁለተኛው ከመጀመሪያው የከፋ ጥፋት ነውና ተጠንቀቁ።

ተፈጥሯዊ ባህሪ

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

فَطَوَّعَتْ له نفسه قتل فيه فقتله، فَأَصْبَحَ مِن النيمات المالية ٢٠

"ነፍሱም ወንድሙን እንዲገድል መራችው። በመሆኑም ገደለው ከከሳሪዎች ሆነም፣ (አል ማኢዳህ 30)

«ሽለሞችለት» የሚለው አገላለጽ በጎኑ የሰው ልጅ መሠረታዊ ባህሪ እንደሆነ ያመለክታል። ይህን ባህሪ ለመለወጥ ማባበል፣ ማግባባት፣ ክፉትን ሸልሞ ማቅረብ ይጠይቃል።

ወንጀለኛ ሆኖ የሚወለድ የለም። ጠጭ፣ ዝሙተኛ ወዘተ ሆኖ የሚወለድ የለም። ሰዎች ሲወለዱ ተፈጥሯዊ የመልካምነትን ባህሪያት ይዘው ሲሆን፤ ወንጀል በኋላ ላይ እንዲለመዱት የሚደረግ ነገር ነው። ይቀበሉት ዘንድ _ አምሮ እና ተውቦ ይቀርብላቸዋል። ተሸልሞ ይጋብዙዋል።

ቃቤል ነብይ ያሳደጉት የነብይ ልጅ ቢሆንም መግደል ሆኖለታል። ሰውየው አደርጎዋለሁ ብሎ ፈጽሞ ያላሰበውን ወንጀል ከብዙ ማግባባት፣ ማባበል እና ሸልሞ ማቅረብ በኋላ ሊፈጽመው ይችላል።

አካልህ ኢብሊስን የምታሸንፍባቸው የተፈጥሮ ወታደሮችህ ናቸው፡ ነፍስን ወደ በጎ የሚመሩ አጋሮችህ ናቸው። መላኢኮች ወደ ቅን ጎዳና ይመሩሐል። በእውነት ላይ እንድትጸና ያግዙሐል። ስለዚህም ለኢብሊስ ከፍተት አትተው። እንተ ካልታዘዝከውና አካልህን ለርሱ ወታደር ካላደረግከለት አይደፍርህም። ለነፍስህ ዋጋ አትሰጥምን? ወደ ጀሃነም የሚወስዳትን ሰይጣን አግዘህ እንዴት ታጠቃታለህ?

ኢብንል ቀይም ጅማሪውን ሲያስተዋውቁ

ነፍስን ለቸይር ለመግራት እና ወንጀልን ለመቃወም ኢብንል ቀይም በአንድ ግሩም ንግግራቸው ያመለክቱትን ጉዳይ ማጤን ያስፈልጋል። ወንጀል የሚጀምረው በማሰብ ነው። ስለዚህ ከፉ ሲታሰብህ ተቋቋመው። ለምሳሌ «አዐዙቢላህ» በል። ካልተቋቋምከው የዘወትር ሐሳብ ይሆናል። ይህንም ካልተዋጋህው ወደ ጽኑ ውሳኔ ይሸጋገራል። ካልተዋጋህው ወደ ተግባር ይለወጣል። ካልተዋጋህው ልምድ ይሆናል። ከዚህ በኋላ ለመተው ይከብድሐል። ወንጀል ከተቆጣጠረህ በኋላ ለማስወገድ አሳርህን ከማየት መጀመሪያውኑ በሐሳብ ደረጃ እያለ መዋጋቱ ይቀልሐል።

ወጣቶች ሆይ፥ እነዚህን የሰይጣን እርምጃዎች ተጠንቀቁ። ካልሆነ የቃቤል እጣ ይደርስባችኋል። ቃቤል በየደረጃው ለሰይጣን እጅ እየሰጠ ቀጠለ። በመጨረሻ ወንድሙን ወደ መግደል አስከፊ እርምጃ ተሸጋገረ።

ቃቤል ወንድሙን እንዴት ገደለውን ድንጋይ እንስቶ እንደመታው ይነገራል። ተኝቶ እያለ አነቀውም ተባሏል። ቁርአን መግደሉን ብቻ ነው ያወሳው። የአዳዲሉን ሁኔታ አልተረከም።

አንዳንድ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ዝርዝር አፈጻጸማቸውን በጋዜጦች እና

ጠንካራ ትስስር ..

በመገናኛ ብዙሐን ላይ ታትበባለህ። ይህ ዝርዝር ዘገባ አንዳንድ ሰዎችን ተመሳሳይ ወንጀል በተመሳሳይ መንገድ ለመፈጸም ያነሳሳቸዋል። ቁርአን ዝርዝሩን የተወው ለዚሁ ይመስላል። ከወንጀሉ ምክንያት፣ ካስከተለው ውጤት እና ከቅጣቱ ላይ ብቻ ማተኮሩ የዚሁ ተርቢይ

ታሪኩ የሴትን ፈተና ከግድያ ጋር ያስተሳሰረው ለምንድን ነው? ምክንያቱም በመካከላቸው ጠንካራ ግኝኙነት አለ። በእንስት ሰበብ ግድያ በየቀኑ ሲፈጸም ይስተዋላል። የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት አንድ ሪፖርት እንደሚያመለክተው በ1976 ዓ.ል. በዓለማችን ላይ 25 ሚሊዮን ጽንሶች ውርጃ ተፈጽሞባቸዋል። በ1984 በተደረገው ቆጠራ አሐዙ ወደ 50 ሚሊዮን አሻቅቦ ተገኝታል። በየቀኑ ምን ያህል ሕጻናት የዚህችን አለም ብርሃን ሳያዩ በእናቶቻቸው እንደሚገደሉ አየህ? የእንስት ፈተና ከግድያ ጋር የመተሳሰሩ እንደኛው ሚስጥር ይህ ነው። በእንስት መፈተን ለዝሙት ግኝኙነት ይዳርጋል። ከግኝኙነቱ የሚፈጠሩ ጽንሶች በውርጃ ይገደላሉ።

እጅግ ጠቃሚ መልእክት

ቁርአን ቃቤልን፡- ወንድሙን ከገደለ በኋላ ከከሳሪዎች ሆነ።፡ ሲል ይገልጸዋል። የከሣሪውን መጠን አስብ። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ያለ አግባብ ከሚገደሉ ነፍሶች፥ የአይም የመጀመሪያው ልጅ የሐጢአት ተጋሪ ይሆናል።» (ቡኻሪ) እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የሚድየ ወንጀል የሚፈጽም ሁሉ ከሐጢአቱ ሊቃቡል ያሽከማል። የዘሀ ቅጣት መጠኑ ምን ያህል ነው?

ነቢዩ እንዲህ ሲሉ አስተምረውናል፡ መጥፎ መንገድ ያበጀ የርሱንም፥ እስከ እለተ ቂያማ የተከተሉትንም

ሰዎች ሁሉ ሐጢአት ይሸከማል።» (አህመድና በይሐቂ)

ስስ ልበስ በአደባባይ በመልበስ ለጓደኞቿ መጥፎ አርአያ የሆኑች እንስት፥ አስካሪ መጠጥ ካባልንጀሮቹ ፊት በመጠጣት እነርሱን የገፋፋና የርሱን መጥፎ አርአያነት እንዲከተሉ ያደረገ ወጣት፥ እነዘህ ሁሉ የተከተሏቸውን ሰዎች ሁሉ ወንጀል ይሸከማሉ።

ተውባ ወንጀልን ይብሳል። ወጣቶች ሆይ፥ ወንጀልን ለሌላ ማስተማርን በጣም ተጠንቀቁ። ሌሎችን ወንጀል ያስተማረ ከራሱ ወንጀል በላይ የነርሱንም ሐጢአት ይሸከማል። የሐጢአት ጭነቱ ይከመራል። የኪሣራውን ክብደት ተረዳችሁን

<u>የቁርአን አወቃቀር መጣጣም</u>

አላህ እንዲህ ብሏል:-

وقعت الله مرا با بحث في الأَرْض لِبريه كيف يُوَاري سَوْءَ أَخِيهِ قَالَ يَتَويلي أعجزت أَن أكون مثل هذا الغاب فَأُورِى سَوْءَةَ أَخِي فَأَصْبَحَ مِنَ السَّامِينَ © المائدة

አላህ ምድርን የሚጭር ቁራ ላኩ የወንድሙን ሬሳ እንዴት እንደሚሸሽግ ያሳየው ዘንድ: ወይኔ (ወይ ጥፋቴ እንደዚህ ቁራ መሆንና የወንድሜን በድን መሸሸግ (አፈር ማልበስ) ተሳነኝ? አለ። ከሚቆጩ ሰዎች ሆነም» (አል ማኢዳህ 31)

አላህ ቃቢልን ያስተምር ዘንድ ተራ ላከ። ቁራ ከአላህ ታዛቨር ባሮች መካከል አንዱ ነውና። እርሱም ትእዛዙን ፈጸመ፡ ግን ለምን ቁራ ተመረጠ? ከአኩይ ድርጊቱ ጸለምተኛ ቀለም ጋር እንዲጣጣም ነው። ቁራ ቀለሙ ጥቁር ነው። ቅርጹ፡ ድምጹም ሆነ ስሙ ከበራሪ አእዋፋት ሁሉ በተለየ ሁኔታ የሚያስጠላ ነው።

ቃቢል እዚህ ላይ ከዝንጋታው ይነቃል። ግና ጊዜው ካለፈ በኋላ ሆነና አልጠቀመውም።

«ሰው አህ»

ቃቢል ቁራውን ባየ ጊዜ እንዲህ አለ፡-

وقال يو بل أعجزتُ أن أكون مثل هذا الغرب فَأُوري سَوْء، أَخِي فَأَصْبَحَ مِنَ النَّدِمِينَ ٣١)

«አላህ ምድርን የሚጭር ቁራ ላከ የወንድሙን ሬሳ እንዴት እንደሚሸሽግ ያሳየው ዘንድ፡ ወይኔ (ወይ ጥፋቴ እንደዚህ ቁራ መሆንና የወንድሜን በድን መሸሸግ አፈር ማልበስ) ተሳነኝ?" አለ ከሚቆጩ ሰዎች ሆነም» (አል ማኢዳህ 31)

ሬሳውን «ሰውአህ» በሚል ቃል ነው የነለጸው። ‹ሰውአህ› ሐፍረተ ገላ ማለት እንደሆነ ከአሁን ቀደም ተነጋግረናል።
እዚህ ላይ ደግሞ «ሬሳ» የሚል ትርጉም ይዞ መጥቷል።

የቃሉ አጠቃቀም ፡ ሐፍረተ ገላ ሊሸፈን እንደሚገባው ያመለክታል። እርሱን አለመሸፈን ለበርካታ የስነ ልቦና በሽታዎችና አጥፊ ፈተናዎች ያደርጋል።

ስላቃተው ተጸጸተ

የቃቢል ድርጊት ፍጻሜው ጸጸት ሆነ። ከአንቀጹ ላይ እንደተገለጸው ከወንጀሉ ከተጸጸተ በኋላ ተውባው ለምን ተቀባይነት አላገኘም

ምክንያቱም የተጻጸተው ለአላህ ብሎ አይደለም። የተውባ ጸጻትም አልተጻጸተም። እንደቁራው መሆን የወንድሙን ሬሳ መሸሸግ ሰላታቸው እንጅ። ለምሳሌ ሰውየው ነ5ዐ ፓውንድ ከፍሎ ወደ አንድ የመብቃ ድግስ ቢሄድና ዝግጅቱ ሳይጥመው ቀርቶ ስላጠፋው ገንዘብ በጸጸት ለአላህ ብሎ አልተጻጸተም። ቢልም ጸጸቱ ለአላህ ቢሆን ኖሮ ተጠባ ይሰኝ ነበር።

ግና ለአላህ ብሎ አላደረገውምና ተውባ አልሆነለትም። ወንድሙን ገድሎ እንዲሁ ተወው። ሬሳው መግማት ሲጀምርና በተባዮች ሲወረር ቃቤል ታወከ፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ተራው መጣና የማያውቀውን ነገር አስተማረው፤ ደካማነቴን ፡ አሳየው። ስለድከመቱ ተጸጸተ፤ ወንጀሉም ዙሪያውን ከበበው።

ወጣቶች ሆይ የአላህን ትእዛዝና የሰይጣንን እርምጃ አቃልሎ መመልከትን ተጠንቀቁ። ፈተናንም ተጠንቀቁ። በሮቹንም ዝጉ። ወንጀለኛ ከቁራ አንኳ የደከመ መሆኑን አይታችኋል። ከናንተ አንዳችሁ ወንጀል ሲየገኝው ፈጥኖ ተውባ ከማድረግ የተሻለ መዳኛ የለውም። እስትንፋስ እስካለ ድረስ የተውባ በር ክፍት ነው። የአላህ እዝነትም ሰፊ ነው።

ማስታወሻ

በዚህ የመጽሐፉችን ክፍል የአደምን ታሪክ አይተናል። እጅግ ጠቃሚ - ትምህርት እንዳገኛችሁ ተስፋ እናደርጋለን። ኡስታዝ አሚር ኻሊድን እናመሰግናለን። የመጽሐፉ ክፍል ሁለት የሌሎች ነብያትን ድንቅ ታሪክ ይዘና በማራኪው የኡስታዙ ብእር ተከሽኖ በቅርቡ ከናንተ እጅ ይደርሳል።

ሒሰን ታጁ